# الشيعة والتشيع

# ሺዓ እና ሺዓነት

## በማስረጃ ሲፈተሽ

ሰይድ ሙሐመድ ሁሴን

አቡ ራኑባ ዓሊ አል-መደረንቢ

2019

www.bookshia.com
knowledge enlivens the soul

# الشيعة والتشيع

# ሺዓ እና ሺዓነት

## በማስረጃ ሲፈተሽ

ሰይድ ሙሐመድ ሁሴን
አቡ ራሩባ ዓሊ አል-መደረንቢ

2019

*የመጽሐፉ ስም፡- ሺዓ እና ሺዓነት  በማስረጃ ሲፈተሽ*

*ጸሐፊ፡- ሰይድ ሙሐመድ ሁሰይን*

*ተርጓሚ፡- አቡ ራኑባ ዓሊ አል-መደረንቢ*

*አንደኛ ዕትም፡- 1000 ኮፒ- ህዳር 2012/ November 2019*

*አዲስ አባባ- ኢትዮጵያ*

**تمت الترجمة والطباعة على نفقة العبد لله الفقير الى رحمته**

***بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ***

***الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ  الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ  مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ  إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ  صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ  غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّالِّينَ***

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡

ምስጋና ለ  ሁሉ የዓለማት ጌታ ለኾነው ለአላህ ነው፤  እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ፣  የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው፡፡ አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፡፡ የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን፡፡

መግቢያ ........................................................................ 1

1. ሺዓ-በጨረፍታ ...................................................... 12

በሺዓና ሱኒ መካከል ............................................................ 17

ሺዓ ምንድን ነው? ........................................................ 22

ሺዓዎች እነማን ናቸው? ....................................................... 23

ኢስላም በሺዓ እይታ ..................................................... 29

1. የሺዓ ዐቂዳ ............................................................ 30

2. ሸሪዓ በሺዓ እይታ ...................................................... 34

የሺዓ የሸሪዓ ምንጮች ...................................................... 36

ሑክም (አስተዳደር) በኢስላም ውስጥ ................................ 37

ኢስላማዊ ኃይል .............................................................. 38

የህዝብ የገንዘብ ምንጮች .................................................. 38

ኢስላማዊ ነጻነት ............................................................. 39

3. ኢስላማዊ ኒዛም (ሥርዓት) በሺዓ እይታ ................. 43

የሺዓ እምነት መርሆዎች/ሙዕተቀዳት ...................... 64

የሺዓ ዐቂዳዎች ..................................................................... 65

ተውሂድ ............................................................................ 65

ኑቡዋህ/ነብይነት.................................................................. 65

ነቢያት (ዐ.ሰ) ..................................................................... 66

ኢስላም ............................................................................. 66

ቁርአን ........................................................................ 71

ቂብላ ......................................................................... 73

ኢማማህ ..................................................................... 74

ኢማም መህዲ አል-ሙንተዘር (ዐ)...................................... 75

አል-ዕስማህ (እንከን-የለሽነት)............................................... 78

ነብዩ (ሶ) እና የሩቅ ሚስጥር (ገይብ) ዕውቀት ........................ 80

*ተወሊ እና ተበሪ* (አላህና ነብዩን እና የአላህን አውሊያዎች መወዳጀት እና ከአላህ ጠላቶች፣ ከነብዩና አውሊያዎች ጠላቶች መጥራትና ጠላት አድርጎ መያዝ) ............................ 80

መዓድ (ትንሳዔ)................................................................. 81

በዳእ ........................................................................... 81

ጀብር እና ተፍዊድ .............................................................. 82

ቱቂያ ........................................................................... 83

የሙትዓ ኒካህ ................................................................... 84

አፈር (ቱርባ) ላይ ሱጁድ ማድረግ ........................................ 85

ሁለት ሰላቶችን ጀምዕ አድርጎ (አጣምሮ) መስገድ ................ 87

ሸፋዓ (ምልጃ)................................................................... 89

በነብዩ(ሶ) እና በንጹሀን ቤተሰባቸው ተወሱል ማድረግ ........... 90

መሻሂዶችን (መቃብሮችን) መዘየርና በረካ መሻት (ተበሩክ) ...95

ዶሪሆችን መገንባት ............................................................ 97

የቀብር ዚያራ .................................................................. 100

ሴቶችና የቀብር ዚያራ ........................................................ 103
በበቂዕ የመቃብር ስፍራ ውስጥ መስገድ ................................ 104
በኢማም ሁሴን (ዐ) ላይ ማልቀስና ማዘን ............................ 105
ታዲያ ስድብና ማከፈርን ምን አመጣው? ............................ 109
ግዴታ የሆኑ ተግባራትና ኢስላማዊ ህግጋት ............................ 110
ኢስላማዊ ሥነ-ምግባር ........................................................ 111
አንድ ኡማ/ህዝብ ............................................................ 112
ሀገራትን ከእኩይ ተግባራት ማጽዳት....................................... 114
የኢስላም ክብርና ሉዓላዊነት መመለስ ................................... 115
ወደ ኢስላም መጣራት ........................................................ 116
ሙስሊሞችን ማነቃቃትና ማነሳሳት .................................... 117
የሺዓ ስልጣኔ ........................................................ 120
አጠቃላይ የህዝብ ብዛት (ቁጥር)........................................ 121
ሺዓና ኢስላማዊ ታሪክ ........................................................ 122
ሺዓና ኢስላማዊ ሳይንሶች (ዕውቀት)........................................ 125
የረሱሉ (ሰ) ኸሊፋዎች ........................................................ 130
የረሱሉ (ሰ) ኸሊፋዎች ........................................................ 131
የኢማሞች ታሪክ በጨረፍታ ................................................ 134
የመጀመሪያው ኢማም ........................................................ 138
*ከአሚረል ሙእሚኒን (ዐ.ሰ) ፈዷኢሎች በጥቂቱ* .................. 139

*ሐዲስ ሰድ አብዋብ (የበሮቹ መዝጊያ ሐዲስ)* ........................ 152

*ሁለተኛው ኢማም* ............................................................ 155

*ሶስተኛው ኢማም* ............................................................ 157

አራተኛው ኢማም ............................................................ 160

አምስተኛው ኢማም ............................................................ 162

*ስድስተኛው ኢማም* ............................................................ 164

*ሰባተኛው ኢማም* ............................................................ 166

*ስምንተኛው ኢማም* ............................................................ 168

*ዘጠነኛው ኢማም* ............................................................ 169

*አስረኛው ኢማም* ............................................................ 171

*አስራ አንደኛው ኢማም* ............................................................ 172

*አሥራ ሁለተኛው ዒማም* ............................................................ 173

የሺዓ ኢማሞችን አስመልክቶ የተሰጡ

የምስክር ቃሎች (እዕትራፋት) ........................................... 177

1. ኢማም አሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊ
   ቢን አቢ-ጧሊብ (ዐ) ............................................ 177
2. *ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ (ዐ)* ........................................... 181
3. *ኢማም ሁሴን ቢን ዓሊ (ዐ)* ........................................... 182
4. *ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን ዘይን አል- ዓቢዲን (ዐ)* ............ 184
5. *ኢማም ሙሀመድ አል-ባቂር (ዐ)* ................................ 185

6. ኢማም ጃዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ)........................................ 186
7. ኢማም ሙሳ አል- ካዚም (ዐ)........................................ 187
8. ኢማም ዓሊ አል-ሪዷ (ዐ) ........................................ 188
9. ኢማም ሙሐመድ አል-ጀዋድ (ዐ)................................ 189
10. ኢማም ዓሊ አል-ሓዲ (ዐ)............................................ 190
11. ኢማም ሐሰን አል- ዓስከሪ (ዐ)...................................... 191
12. ኢማም መህዲ አል-ሙንተዘር (ዐ)................................... 192
የንጹሃን ኢማሞቹ (ዐ) እና የሺዓዎቻቸው ሚና ............... 194
ሺዓ መሆን ለምን አስፈለገ? ........................................ 195
የሺዓ ማስረጃዎች ........................................................................ 196
የአሚረል ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ) ኸሊፋነት ........................... 196
የማስጠንቀቂያው (ኢንዛር) ቀን ........................................... 196
የገዲር ቀን ........................................................................ 198
ሐዲስ አል-መንዚላ (የደረጃ/ቦታ ሐዲስ) ........................... 203
ከ ነብዩ (ሶ) ዲትራ የሆኑ የተቀሩት
ኢማሞች ኸሊፋነት ............................................................ 203
የ ሰቀለይን ሐዲስ ................................................................ 205
ሐዲስ አል-ሰፊና (የመርከቡ ሐዲስ) ................................... 207
ሺዓነት በሱኒ ዑለማዎች እይታ .................................... 208

ሺዓነት እና የሱኒ ዑለማዎች ............................................. 209
ዓላማህ አል-ዘሐቢ ............................................................ 209
ሼኽ ሙሐመድ ሸልቱት ..................................................... 210
ሼክ መሐመድ አል-ገዛሊ ..................................................... 211
ዶክተር ሙስጠፋ አል-ሪፋዒ ከተናገሩት ደግሞ .................... 212
ሺዓን ለመተዋወቅ የሚረዱ መሷድሮች (ምንጮች) ....... 215
ሺዓና ሺዓነት ዙሪያ - ጥያቄና መልስ .................................. 217
ጥያቄና መልስ ..................................................................... 217

## መግቢያ

**بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ**

**በአላህ ስም እጅግ አዛኝ እና መሐሪ በሆነው**

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው፡፡ ሶላትና ሰላም በሙሐመድ እና ከማንኛዉም ጉድፍና እንከን ሁሉ በጠሩት አህለልበይት ላይ ይሁን!

**ሙስሊሞች እርስ በርሳቸው ይቀራረቡ ዘንድ ጊዜው ደርሷል፡፡ ከመለያየትና** መራራቅ የተነሳ በጫንቃቸው ላይ የተጫነውን ከባድ ቀንበርና የልዩነት ትብታብ መስበሪያውና ማብቂያው አሁን ነው፡፡ ጨቋኞች የተጠቀሙትን "የለያይተህ ግዛ" መሰሪ አካሄድ የማጋለጥና የንቃት ጊዜ አሁን ነው፡፡

ሙስሊሞች በአላህ ንዕማ (ፀጋና በረከት) ወንድማማቾች ናቸው፡፡ የተከበረው ቁርአን ወደ አንድነትና መተሳሰብ ይጣራል፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ**

**"ሙእሚኖች ወንድማማቾች ናቸው፡፡ በወንድሞቻችሁ መካከል በጎ (እርቅ) አድርጉ፡፡"**[1]

እንዲሁም በሌላ የቁርአን አያህ ፡-

**إِنَّ هَٰذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً**

**"ይህች ህዝባችሁ አንዲት ህዝብ (ኡማ) ናት፡፡"**[2]

---

[1] አል-ሑጁራት፡ 10

የሙስሊሞች 'ሰላህ' (በጎነት/መልካምነት) ወይም እርቅና ደህንነት የሚገኘው ወደ ኢስላም መስተጋብር፣ ህግጋትና መመሪያዎች በመመለስ ነው፡፡ ከምእራባውያንና እንዲሁም ከነሱ ወደ ምስራቃውያን ከፈለሰው የአኗኗር ዘይቤና ሥርዓት ሙስሊሞች ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ልምድ ቀስመዋል፤ አይተዋል፡፡ ነገር ግን ድህነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ የበታችነት፣ መፈረካከስና ኋላ ቀርነት እንጅ ምንም አላገኙበትም፡፡

ታዲያ ይህ የረዥም ጊዜ መራር ልምድ ትምህርት ለመቅሰም በቂ አይደለምን?

ሙስሊሞች ኢስላምን የሙጥኝ ብለው ይዘው በነበር ግዜ ታላቅነትን፣ ደህንነትን፣ ነጻነትንና በራስ መተማመንን ተጎናጽፈው ነበር፡፡ የተናቁና የበታች የሆኑ ሐገራት አንገታቸውን ቀና ለማድረግ ችለው ነበር፤ የኋላ ኋላ ግን ሙስሊሞች ኢስላምን ትተው ሌላ አካሄድና ህግጋትን ሲከተሉ የበታችነትና ባርነት እንጂ ያተረፉት ነገር የለም፡፡

ስለዚህ እኛ ሙስሊሞች ወደ ኢስላም ልንመለስ ይገባል፡፡ በሁሉም የህይወት መስክ የነበረንን ክብርና ታላቅነት መልሰን ማግኘት አለብን፡፡ ሙስሊሞች ለዚህ ሁሉ ችግር የተዳረጉበት ትልቁ ምክንያት ወደ ተለያዩ ፊርቃዎች (ቡድኖች) በመከፋፈላቸው፣ በመጠላላታቸውና በመራራቃቸው እንዲሁም የመተሳሰብና የአንድነት መንፈስ በማጣታቸው ነው፡፡

ሙስሊሞች ሆይ! እስቲ አሁን የመለያየትና መራራቅ ገመዶችን ለመበጣጠስ እንረባረብ!

---

[2] አል- አንቢያእ፡92

ነብዩ (ሰ) ምክራቸው እስከ ዛሬም በመካከላችን ይወሳል፡- **"በሁለት (ሰዎች) መካከል እርቅ ማስፈን (በጎ ማድረግ) ከመላው ሶላትና ጾም የተሻለ ተግባር ነው"**[3]

ከየህያ ቢን ሰኢድ በተያዘ ሐዲስ መሰረት ደግሞ ሰኢድ ቢን ሙሰየብ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ ይላል፡-

**"ከብዙ ሰላትና ጾም የበለጠ ተግባር ልንገራችሁ?"**

"አዎ!" አሉ፡-

**"በሁለት(ሰዎች) መካካል እርቅ ማስፈን"**

በሰሂህ አል-ቲርሚዝ 3/66፣ ዳር አል-ኢህያእ አል-ቱራስ አል-ዓረቢ-ቤይሩት፣ እንዲህ እናገኛለን፡- ከአቡ አል-ደርዳእ፡- ነብዩ(ሰ) እንዲህ ብለዋል፡

**"ከጾም፣ ሶላትና ሰደቃ ደረጃ የበለጠ የሆነ ነገር ልንገራችሁ?"**

"አዎ!" አሉ

**"በሁለት(ሰዎች) መካካል እርቅ ማስፈን፡፡"**

ተመሳሳይ ትርጉምና መልእክት ያላቸውን ሐዲሶች ከበርካታ ምንጮች ማግኘት ይቻላል፡፡[4]

---

[3] ቢሓር አል-አንዋር 42/256፤ ሙወጠዕ ማሊክ 2/904.

[4] ሙዕጀም አል-ከቢር 1/101፣ -አል-አደብ አል-ሙፍረድ 1/142፣ -አል-ፊርዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ 2/398፣ -ፈይድ አል-ቀዲር 3/106

በሁለት ሰዎች መካከል እርቅ ማስፈን ይህን ያህል ቦታ የሚሰጠው ከሆነ በሁለት ታላላቅ ቡድኖች መካከል እርቅና አንድነት መፍጠር ምን ያህሉን ይሆን? ያውም ሁለቱም ቡድኖች በአላህ አንድነትና በ ቂያማ ቀን (በትንሳዔ ቀን) የሚያምኑ፣ ሶላትን የሚያቋቁሙ፣ ዘካ የሚሰጡ፣ ሐጅ የሚያደርጉና የረመዳን ወርን የሚጾሙ ሁለት ታላላቅ ቡድኖች እያንዳንዱ ቡድን ቢያንስ ግማሹን  የሙስሊሞች ቁጥር የሚያቅፍና ከመቶ ሚሊዮኖች የማያንሱ የሆኑ ቡድኖች!

የቀድሞ የግብጽ መሪ አንዋር አስ-ሳዳት "ኢሐራም አል-ቃሒሪያ" በተሰኘ መጽሄት ላይ እንደተጠቀሰው፡-

"የኢስላማዊ ጉባዔ ጸሀፊ ሆኜ እያለሁ አንድ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ሙስሊሞች ግማሻቸው ሺዓ ሲሆን የቀረው ግማሽ ደግሞ ከሱኒ እንደሆነ ነው፡፡"[5]

እነሆ ዛሬም ወደ ቁርዓንና ነብዩ (ሶ) ጥሪ እንመለሳለን፡፡ ለመተዋወቅ፣ ለመቀራረብና የሙስሊሙን ኡማ ለውድቀት የዳረገውን ድርቅና ለማከተም ደጋግመን እንጠራለን፡፡ በውይይትና ጥበብ በተሞላበት ምክክር ወደ እውነታው ለመምጣት መገስገስ ያስፈልጋል፡፡

አላህም እንዲህ ይላል፡-

***ادْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ وَجَادِلْهُم بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ***

**"በጥበብና በጎ በሆነ ምክር ወደ ጌታህ መንገድ ጥሪ አድርግ፤ የበለጠ በጎ በሆነችውም ተከራከራቸው"፡፡**[6]

---

[5] አንዋር አስ-ሳዳት (1918-1981) አል-ኢህራም፡-26/12/1975፣ ገጽ 5)

[6] አል-ነኽል፡ 125

ለመተዋወቅና ለመግባባት ከሚያስችሉን መልካም አጋጣሚዎች መካከል እንደ በይቱላህ አል-ሐራም፤ የነብዩ(ሰ) የወህይ መንደርና የህጅራ ሁነቶች በላይ ምን አለ? እንደ ሐጅ ስርዓት ያሉ አጋጣሚዎች ሙስሊሙ ካለበት እንቅልፍ ለመቀስቀስ ለበለጠ ትውውቅና ከተጠናወታቸው እርስ በርሳቸው ላይ ስላላቸው መጥፎ አመለካከትና ጥርጣሬ ለመፈወስ ምንኛ መልካም እድሎች ናቸው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ፡-

***وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا***

**"በአላህ መንገድ ተያያዙ፣ አትለያዩም!"[7]**

እንዲሁም በሌላ አያህ፡-

***لِيَشْهَدُوا مَنَافِعَ لَهُم***

**"ለነሱ የሆኑ ጥቅሞችን ይታደሙ ዘንድ"[8]** (ለዱንም ሆነ ለአኺራ የሚጠቅማቸውን ነገር በመታደም ይጠቀሙ ዘንድ)

በተለይ በአሁኑ ዘመን ጽዮናዊነት ተንሰራፍቶ የተለያዩ ጠላቶች ኢስላምን ለማጥፋትና ሙስሊሞችን ለመግዛት በሚያሰፈስፉበት ወቅት ከመግባባትና መተዋወቅ ሌላ ምን የተሻለ መሣሪያ አለ? የተለያዩ የኢስላም ምሁራን ይህንን አደጋ ደጋግመው በመጥቀስ ጥንቃቄ እንዲደረግና እርምጃ እንዲወሰድ አበክረው ይመክራሉ፡፡ ይህንኑ ጉዳይ ከግብ ለማድረስ በተለያዩ ጊዜ

---

[7] ኣል-ኢምራን፡ 103

[8] አል-ሐጅ ፡ 28

ጉባዔዎችንና ኮንፈረንሶችን ሲያዘጋጁ ይስተዋላሉ፡፡ሙስሊሞችን ለማቀራረብና አለመግባባትን ለማስወገድ ብዙ ጥረት ሲደረግ ይታያል፡፡

ከኢስላም ምሁራን ጥቂቶቹን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ፡-

1. **ኢማም አል-በሩጀርዲ**- በቅድስቲቱ ቁም ከተማ የሐውዛ አስተዳዳሪ፣

2. **ሼክ ሙሐመድ ሸልቱት**- በግብጽ የአዝሐር ታላቅ ምሁር የነበሩና በካይሮ ውስጥ ዳር አል-ተቅሪብ (የመቀራረብ ማዕከል) ለማቋቋም ከተንቀሳቀሱ ምሁራን ውስጥ ይገኙበታል፡፡

ሼህ ሙሐመድ ሸልቱት በሺዓ መዝሐብ መሠረት የዒባዳ ተግባራትን መፈጸም እንደማንኛውም ሌሎች የኢስላም መዝሐቦች ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው በማለት ፈትዋ መስጠታቸው ይጠቀሳል፡፡[9]

ይህች መጽሐፍ "ሺዓና ሺዓነትን" በተመለከተ ትንሽ ብርሃን ለመስጠት የተደረገ ሙከራ ሲሆን ባለማወቅም ሆነ አላህን የማይፈሩና ለታሪክ ሂሳቡን የማይሰጡ ሰዎች ቢባሉ የማያንሳቸው ክፍሎች በሚነዙት በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ ማምታታትን ለመጠቆም ያህል ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡

አብዛኛው የአህለ-ሱና ቡድን የሆኑ ወንድሞች ስለ ሺዓ ቡድን በጣም ጥቂት እንጂ የማያውቁ ሆነው እናገኛለን፡፡ ይህ ደግሞ በሁላችንም ጫንቃ ላይ ያለ ግዴታ ነው፡፡ በሱኒና በሺዓ መካካል የተከሰተውን ያለመተዋወቅና መለያየት

---

[9]ለዝርዝሩ *"አል-ተሸዩዕ ወ ዑለማእ አል-ሱናህ"* (ሺዓነት በአህለ-ሱና ምሁራን እይታ) የሚለው ክፍል ይመልከቱ፡፡

ፈተናን ለማርገብ ያለውን ሐቅ ማውጣት አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው ብለን እናምናለን፡፡

የሙስሊሞችን ቃል በአላህ ፍራቻ (ተቅዋ) ላይ አንድ ያደርግ ዘንድና ሁሉንም ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንዲመራ የሚጠየቀው አላህ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየን የመለያየትና የመነቋቆር ጊዜ ላይመለስ መሔዱንና የአንድነትና የመግባባት ዘመን ጮራ መፈንጠቁን ነው፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***وَاذْكُرُوا نِعْمَتَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنْتُمْ أَعْدَاءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُمْ بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا***

**"አላህ የዋለላችሁ ጸጋ አስታውሱ፡፡ እርስ በርሳችሁ ጠላቶች በነበራችሁ ጊዜ፣ ከዚያም በልቦቻችሁ መካከል መግባባትን አደረገላችሁ፣ በጸጋው ወንድማማቾች ለመሆን በቃችሁ"፡፡**[10]

እንዲሁም፡- ***وَلَا تَكُونُوا كَالَّذِينَ تَفَرَّقُوا***

**"እንደዛ እንደተለያዩት አትሁኑ"**[11]

ሙስሊሞች የዓለም ቁንጮ በነበሩ ጊዜ መግባባትና አንድነትን ይሹ ነበር፡፡ ዛሬስ በጠላት ተከበው ከውጭ ሆነው የውስጥ ሰልፋቸውን ለመበታተን በሁሉም አቅጣጫ አደጋ በተጋረጠባቸው ጊዜ ምን ማድረግ አለባቸው?

---

[10] ኣል-ኢምራን ፡ 103

[11] ኣል ኢምራን ፡ 105

እነሆ ኑ እኛ ሙስሊሞች እንቀራረብ፣ እንረዳዳ፣ በአላህና ነብዩ (ሰ) ትዕዛዛትን የሙጥኝ ብለን እንያዝ! ባለስልጣናትንና ከሐዲዎችን ከማገልገል ነጻ ለመውጣት ከተጫነብን የጥርጣሬና ድንቁርና ጨለማ እናምልጥ!

ለአላህ ምስጋና ይድረሰውና አሁን ትንሽ ብልጭታ እየታየ ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተለያዩ ኢስላማዊ ቡድኖች ለመቀራረብና ለመወያየት የአንድነት መድረኮችን ለመፍጠር እንቅስቃሴ መደረግ ተጀምሯል፡፡ በውይይትና መቻቻል ላይ የተመሰረተ ምክር ተጀምሯል፡፡ ነገር ግን መንገዱ ረዥምና ጠመዝማዛ መሆኑ አልቀረም፡፡ ሙስሊሞች ወደ ኢስላም ታሪክ ተመልሰው ትክክለኛውን ዳራ በመከተል ለአንድነት ሊተጉ ይገባል፡፡

ይኸውም፡-

ሀ. ቁርአንና ትክክለኛ ሱናን መሠረት ያደረገ ለአንድነት የሚያበቃ አጠቃላይ ሀይማኖታዊ ባህልን ማቋቋም፤

ለ. ከኋላ ቀርነትና ድንቁርና ለመላቀቅና ከሌላው ዓለም ጋር ለመራመድ የሚያስችል የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ቴክኖሎጂ፣ የህክምናና ሌሎች አውታሮች የሚበለጽጉበትን ባህል በማጎልበት ዓለምን በመምራት ለዱኒያና አኺራ ብልጽግና መትጋት መቻል፡፡

ኢማናችንን እናስተካክል፣ የቀረውን እናጠንክር፣ መልካም ስራዎችን በእጥፍ እንስራ፣ ለአኺራችን በተግባር ስንቅ እናስቀምጥ! ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መራራ ጽዋዎች ተጎንጭተናል፡፡ ከኢስላም በመራቃችን የችግር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀናል፡፡ አሁን ያለንበት ጥፋትና ነዳማ ከማንም የተደበቀ አይደለም፡፡ የብልጽግናና የደህንነት መንገድ ትልቁ መፍትሄና መድሀኒት

ደግሞ ወደ ኢስላም መመለስ ብቻ እንደሆነ ለሁሉም ሙስሊም ግልጽ ሆኖለታል፡፡ ይህንን ደግሞ በግልጽ የሚነግረን የአላህ ኪታብ ሲሆን ነብዩ (ሶ) እና ከእንከን ሁሉ የጠሩት አህለልበይት (ዐ) ግልጽ አድርገውልናል፡፡ ግለሰባዊም ሆነ ማህበራዊ ጉዳዮቻችንን በአላህ ኪታብና በነብዩ (ሶ) ዘረ-ሰብ ብርሃን ማከም ይኖርብናል፡፡ እነሆ ይህም ነብዩ (ሶ) ለኡመቱ ባስተላለፉት የኑዛዜ ቃል ነው፡፡

**إِنِّي تَارِكٌ فِيكُمُ الثَّقَلَيْنِ ما إن تمسَّكتُم بهما لَنْ تَضِلُّوا من بعدي أَبَدً كِتَابَ اللهِ وَعِتْرَتِي أَهْلَ بَيْتِ**

**"ሁለት እጅግ ውድና የከበሩ ነገሮችን በውስጣችሁ እተውላችኋለሁ፡- የአላህ ኪታብና ዘረ-ሰቤ አህለቤይቴን፡፡ ሁለቱን የሙጥኝ ብላችሁ ከያዛችሁ ከኔ በኋላ ፍጹም ለጥመት አትዳረጉም፡፡"**[12]

---

[12] ይህ ሐዲስ (ሐዲስ አስ ሰቀሌይን) ሱኒም ሆነ ሺዓ ዘንድ ፍጹም ትክክለኛ (ሶሂህ እና ሙተዋትር) ከሆኑ ሐዲሶች ነው፡፡ በተለያዩ አገላለጾች (አባባሎች) የተገለጸ አንድ ትርጉምና መልዕክት የያዘ እጅግ ታዋቂ ሐዲስ ሲሆን ይኸውም ነብዩ (ሶ) ለዚህ ኡማ ትተው ያለፉት ነገር የአላህ ኪታብ (ቁርአን) እና አህለልቤይት መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው፡፡ ለዓብይ ያህል የሚከተሉትን ምንጮች ይመልከቱ ፡-

-ሰሂህ ቲርሚዘዚ 5/327 -ዳረል ፊክር ቤይሩት- 13/199፣200 -መክተበህ አል-ሳዊ- ግብጽ እትም፤ 2/308 ቡላቅ ግብጽ እትም፤

-ሶሂህ ሙስሊም 2/362 ዒሳ አል-ሐለቢ እትም -8/122 -ሳቢህ እትም፤ 15/179 – በነወዊ ሸርህ- ግብጽ እትም፤

- ሙሰነድ አህመድ- 3/18፣ 26፣ 59፤ 4/366፣ 371፣ 5/187 - መህመናህ- ግብጽ፤

-ነዝም ዱርር አል-ሲምጠይን፡-አል-ዘርንዲ አል-ሐነፊ 231፣ 232 -ቀዳህ አሳታሚ -አል-ነጀፍ፣

-የናቢዕ አል-መወደህ -አል-ቁንዱዚ አል-ሐነፊ 29፣30፣31፣36፣38፣41፣183፣191፣296፣ 370- ኢስላምቡል፤

-ተፍሲር ኢብን ከሲር 2/113- ዳር አል-ኢህያእ አል-ኩቱብ አል-ዓረቢያ -ግብጽ፤ ----

----መሳቢህ አል-ሱና- አል-በገዊ 203፣206 ካይሮ2/278 ሰቢህ፤
-ጃሚዕ አል-ኡሱል- ኢብን ከሲር 1/187 ግብጽ፤
-ሙዕጀም አል-ከቢር- አል-ጠበራኒ 138፣
-ሚሻከቱል መሳቢህ 3/255 258 -ደማስቆ፤
-ኢህያእ አል-መይት- አል-ሱዩጢ 111፣114፣116፣ -አል-ሐለቢ፤
-ፈትህ አል-ከቢር አል-ነብሓኒ 1/252፣401፣503፣ 3/375 -ዳር አል-ኩቱብ አል-ዓረቢያ- ግብጽ፤
-አሽ-ሸረፍ አል-መእበድ -አል-ነብሓኒ 18 -ግብጽ፤
-አርጀህ አል መጣሊብ 236 ወይም 336- ላሆር፤
-ረፍዕ አል-ለበስ ወሹብሓት- ኢድሪሲ 11፣15- ግብጽ፤
-አል-ሰይፍ አል-የማኒ አል-መስሉል 10 -ደማስቆ፤
-አል-ዱር መንሱር- አል ሱዩጢ 2/60፣ 6/7፣306
-ዘኻኢር አል-ዑቅባ 16፤
-ሰዋዒቅ አል-ሙህሪቃ 147፣226 አል-መህመዲያ ትምእ ፤ 89 መይሙኒያ እትም -ግብጽ፤ -ሙዕጀም አስ-ሰጊር -አልጦበራኒ 1፡135፤
-ኡስድ አል- ጋባ ፊ መዕሪፈት አስ-ሰሓባ -ኢብን አሲር አሽ-ሻፊዒ 2/12፤
-ተፍሲር አል-ካዝን 1፡4፤ -ኢልሙል ኪታብ- ሰይድ ኸዋጃህ አል-ሐነፊ 264- ደህሊ፤
-ሙንተኸብ ታሪክ -ኢብን ዓሳኪር 5/436-ደማስቆ፤
-ሚሽካቱል መሳቢህ -አል-ዑመሪ 3/258፤
-ተይሲር አል-ውሱል -ኢብን አል-በዲዕ 1/16- ኑረ ኪሽሸር፤
-አል-ታጅ አል-ጃሚዕ አል-ዑሱል 3/308 -ካይሮ፤
-መጅመዕ አል-ዘዋኢድ -ሐይሰሚ 9/162፣163፤
-አል-ጀሚዕ አስ-ሰጊር -ሱዩጢ 1/353 -ግብጽ፤
-አርጀህ አል-መጣሊብ -አምሩስታሪ አል-ሐነፊ 335 -ላሆር፤
-መናቂብ ዓሊ ቢን አቢ-ጧሊብ -ኢብን መጋዘሊ አሽ-ሻፊዒ 234፣235፣273 -ቴህራን፤
-አል-መናቂብ -አል-ኸዋሪዝሚ አል-ሐነፊ 223፤
-ፈራኢድ አል-ሲምጣይን -ሐመዋኒ አሽ-ሻፊዒ 2/134፤
-ኢስዓፍ አል-ራጊቢን -ሲባን አሽ-ሻፊዒ (ኑሩል አብሳር) 108 -አስ-ሰዒዲያ፤
-አል-ሲራህ አል-ነበዊያህ -ዘይኒ ደህላን (ሲራ ሐለቢያ) 3/330 -አል-በሒያህ- ግብጽ፤ -አል-ጠበቃት አል-ኩብራ -ኢብን ሰዕድ 2/194 -ዳር ሳዲር -ቤይሩት፤ -----

በአጠቃላይ ትልቁ ነገር መተዋወቅና የኢስላምን ልቅናና ሉዓላዊነት ለማደስ ወደፊት መራመድ ያስፈልጋል፡፡ አላህም እንዲህ ይላል፡-

**وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُو**

**"እንድትተዋወቁ ዘንድ ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ"**[13]

የሙስሊሞች ቃል አንድ ይሆን ዘንድ፣ አላህ ወደ ወደደውና ወደ ፈለገው እንድንመራ ዘንድ እንዲወፍቀን የምንጠይቀው ከሱ ከአላህ ብቻ ነው፡፡ እሱ አላህ በዚህ ላይ ረዳት ነውና!

---

-----አል-መዋሂብ አል-ለዱንያ 7/7 -ግብጽ፤ -ራሙዝ አል-አሃዲስ -ሼክ አህመድ ሐነፊ- 144 -አስታና፤

-አል- አንዋር አል-ሙሐመዲያ- አል-ነብሓኒ 435 -አል-አደቢያህ-ሊባኖስ፤

-ፈራኢድ አስ-ሲምጠይን 2/272፤

-ታሪክ ዲማሽቅ- ኢብን ዓሳኪር- 2/36፤

-አንሳብ አል- አሽራፍ-አል-በላዘሪ -2፡110፤

-ሂልያቱል አውሊያእ 1/355፤

-ከንዝ አል-ዑማል 1/158፣ 2/899 ፣943-947 ፣950-953፣958፣1651፣1658፣1668፤

-ኪፊየት አል-ጣሊብ አል-ከንጂ አሽ-ሻፊዒ 53 -አል-ሐይደሪያ ወዘተ...) ፡፡

ይህ ሐዲስ በሺዓ መጽሐፍት ውስጥ ደግሞ ከዚህም በላይ በርከት ብሎ ይገኛል፡፡ ለአብነት ያህል፡- ዑዩን አኽባር አል-ሪዷ (ዐ) 2/62 259፤

-ሙስተድረክ አል-ወሳኢል 11/374- ክፍል 49 -ሐዲስ 13294)

[13] (ሱራህ ሑጁራት -13)

# -1-

# ሺዓ-በጨረፍታ

ሺዓዎች ማለት አሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊን እና ከእንከን ሁሉ የጠሩትን ልጆቹን የወገኑ ወይም የተከተሉ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ቁጥራቸው ከአምስት መቶ ሚሊዮን ሰዎች በላይ ይሆናል፡፡ በሁሉም የሙስሊም ሀገራት የተሰራጩና በሌሎች የዓለም ክፍሎችም አናሳ ቁጥር ያላቸውን የህዝብ ክፍል ሆነው እናገኛለን፡፡ የኢስላማዊ ፊክራዎች ማበብ ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ፣ የውይይት መድረኮች መፈጠር ከጀመሩ ጀምሮና ጭፍን የሆነ ጥላቻ ቦታ ካጣ በኋላ በየቀኑ ቁጥራቸው እየጨመረ እየሄደ መሆኑን በግልጽ እያየን ነው፡፡

- በአላህ ጌትነት፣ በሙሐመድ (ሶ) ነብይነት፣ በኢስላም ኃይማኖትነት፣ በቁርአን፣ በከዐባ ቂብላነት፣ በነኪርና ሙንከር የቀብር ጥያቄ፣ በየውመል ቂያማ ምርመራ (ሒሳብ)፣ በጀነትና በጀሐነም (እሳት) እንዲሁም ሌሎች ነብዩ (ሶ) ከአላህ ባመጧቸው እምነትና ህግጋት በሙሉ የሚያምኑ ናቸው፡፡

- እንዲሁም ሶላት ይሰግዳሉ፣ ኹምስና ዘካ ያወጣሉ፣ የረመዳን ወር ይጾማሉ፣ የአላህን ቤት ይጎበኛሉ (ሐጅ ይደርጋሉ)፣ የኢስላምን ቃል የበላይ ለማድረግ ለጂሓድ (ትግል) ጥሪ ምላሽ ይሰጣሉ፣ በበጎ ነገር ያዛሉ፣ ከእኩይ ተግባር ይገስጻሉ፣ የአላህን ወዳጆች (አውሊያዎች) ይወዳጃሉ፣ የአላህን ጠላቶች ጠላት አድርገው ይይዛሉ፡፡

▪ በጎ በመስራትና በኸይር ነገሮች መሰማራት ላይ ንቁ ተሳትፎ አላቸው፣ ሱናዎችን እና ተወዳጅ የሆኑ ተግባራትን በመተግበር ላይ ጽኑ ናቸው፡፡ ሐራም ከሆኑ ነገሮችና ከተጠሉ ስራዎች ይታቀባሉ፡፡

▪ የኢስላም ኃይማኖት ለሰው ልጅ ብልጽግናና ደስታ ከአላህ የመጣ ምሉዕ የሆነ ኃይማኖት መሆኑን ያምናሉ፡፡ በኢስላም የመጣ ሁሉም አስተሳሰብና ተግባር በሁሉም የህይወት አውታር መጠበቅ ያለበት ትዕዛዝ መሆኑን ያምናሉ፡፡ የሰው ልጅ ደስታ የሚያገኘው የኢስላም ህግጋትን በመጠበቅ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ከምዕራባውያንና ከምስራቃውያን ህግጋትና አካሄድ መብቃቃት እንደሚያስፈልግ ያምናሉ፡፡

አላህም እንዲህ ይላል፡-

***وَمَنْ يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَنْ يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ***

**"ከኢስላም ውጭ ሌላ ኃይማኖት የሚፈልግ ሰው ተቀባይነት የለውም፡፡ እሱ በመጨረሻው ቀን ከከሳሪዎች ነው፡፡"**[14]

በሐዲስ ደግሞ ፡-

**"የሙሐመድ ሀላል እስከ ቂያማ ቀን ድረስ ሐላል ነው፣ ሐራሙም እስከ ቂያማ ቀን ሐራም ነው፡፡"**[15]

❖ ሙስሊሞች በአንድ ጥላ ስር በመሰብሰብ አንድ መሆን እንዳለባቸው አበክረው ያምናሉ፡፡ አላህ በአንድነት ያዛልና፡-

---

[14] አል-ዒምራን፡ 85

[15] በሳኢር አል-ደረጃት ገጽ 148- ክፍል 13- ሐዲስ 7)

**وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا**

**"ሁላችሁም በአላህ ገመድ ተያያዙ፤ አትለያዩ!"[16]**

እንዲሁም፡-

**وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ**

**"አትጨቃጨቁ! አለበለዚያ ልቦቻችሁ ይሳሳል፣ ኃይላችሁም ይጠፋል፡፡"[17]**

❖ በማንኛውም ሁኔታ የተከሰተውን መለያየትና አለመግባባት በቁርአንና በትክክለኛ የነብዩ (ሶ) ሱና አስታራቂነት ወደ አንድነት በመምጣት ማንኛውንም ዓይነት አለመግባባት መገታት እንዳለበት ያምናሉ፡፡

❖ ቁርአንን የሚቃረን ማንኛውም ህግና መመሪያ ሐራም እንደሆነና በእንዲህ አይነት ህግ መስራትና መዳኘት ህገ ወጥ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

አላህ እንዲህ ይለልና፡-

**وَمَنْ لَمْ يَحْكُمْ بِمَا أَنْزَلَ اللَّهُ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ**

**"አላህ ባወረደው የማይፈርዱ እነሱ ከሐዲዎች ናቸው"[18]**

ታላላቅ የሱና ዑለማዎች የሺዓን መዝሀብ መከተል የሚቻል መሆኑን ፈትዋ ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም የግብጹ ምሁር ሼክ ሙሐመድ ሸልቱት እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

---

[16] ኣል-ዒምራን፡ 103

[17] አል-አንፋል፡ 46

[18] ሱራህ አል-ማኢዳህ- 44

❖ ሺዓዎች ከቁርአን፣ ሱና እና ኢጅማዕ በተጨማሪ የኢጅቲሐድ በር ክፍት መሆኑንና በሸሪዓ ውስጥ ዐቅልም (አዕምሮም) ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ ያምናሉ፡፡

❖ የኢስላም ጎህ ከቀደደ ጊዜ አንስቶ አስከ ዛሬ ድረስ አንጸባራቂ ታሪክ አላቸው፡፡ የኢስላምን ፊክራ በማስፋፋትና ኢስላማዊ ማህበረሰብ በመፍጠር ቀዳሚ ቦታ አላቸው፡፡ የበርካታ መዛግብትና ድርሳናት ባለቤት ናቸው፡፡ ለቁጥር የሚያዳግቱ ድርሳናት አላቸው፡፡ እጅግ በርካታ ት/ቤቶች፣ ቤተ-ሙከራዎች፣ ቤተ-መጻህፍት፣ ዑለማዎችና ኸጢቦች፣ በኢስላም ሀገራትም ሆነ በሌሎች ሀገራት በየቦታው አላቸው፤ በተለያዩ ሀገራትም መንግስት ለመመስረት በቅተዋል፡፡

❖ ከሐዲዎችን፣ መስቀለኞችን፣ አፈንጋጮችን፣ ጽዮናውያንን እና ቅኝ ገዥዎችን በመዋጋትና በመጋፈጥ የታሪክ ድርሳናትን አድምቀዋል፡፡

❖ ከሱኒ ወንድሞቻቸው ጋር የረዥም ግዜ ወንድማማችነት፣ ወዳጅነት፣ መቻቻልና መተሳሰብ ታሪክ ነበራቸው፡፡ ዛሬም በአብዛኛው የዓለማችን ክፍል እንዲያውም በሁሉም ማለት ይቻላል አንድ ላይ ይኖራሉ፡፡ በብዛት ከሚገኙባቸው ሀገራት ውስጥ ኢራቅ፣ ኢራን፣ የባህረ ሰላጤ ሀገራት፣ ፓኪስታን፣ ህንድ፣ አፍጋኒስታን፣ ሊባኖስና ኢንዶኒዥያ ይገኙባቸዋል፡፡

❖ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ሀገራት የዕውቀት ማዕከላት (መርከዞች)፣ የባህል ማዕከላት፣ የመጠቁና የነጠቁ የዲን ምሁራን አላቸው፡፡ ከዚህም ቦታዎች፡- ነጀፍ አል-አሽረፍ፣ ከርበላእ አል-ሙቀደሳ፣ ባግዳድ፣ አል-ካዚሚያ፣ ሳመራእ፣ ቤይሩት፣ ካይሮ፣ ቁም አል-ሙቀደሳ፣ ኹራሳን፣ ቴህራን፣ ካራቺ፣ ቦምቤይ፣ ጃካርታ፣ ኩዌይት፣ ኳታር፣ አል-ኢህሳእ፣ ቀጢፍ፣ አፍጋኒስታን፣ ደማስቆ፣ ሊቢያ፣ ቱኒስ፣ አል-ጀዛኢር፣ ዮርዳኖስ፣ አፍሪካ ሀገራት፣ አውሮፓ፣ አሜሪካና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

# በሺዓና ሱኒ መካከል

በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች በሺዓና ሱንኒ ይከፈላሉ፡፡ ሺዓዎች ከአምስት ሚሊዮን በላይ ሲሆኑ የተቀሩት ሙስሊሞች ሱንኒዎች ናቸው፡፡ በሁለቱም መካከል በሶስት መሰረታዊ የዲን ክፍሎች ላይ ልዩነት የለም፡፡ ይኸውም፡-

*1. ተውሂድ -የአላህ አንድነትና አሐዳዊነት*

*2. ኑቡዋ -ነብይነት*

*3. መዓድ -ትንሳኤ*

ሁሉም ሙስሊሞች ለሁሉም ፍጥረታት (ከውን) አንድና ብቸኛ የሆነ፣ ጅማሮና መጨረሻ የሌለው፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ ህያው፣ ቋሚ፣ ሸሪካ የሌለው፣ አጠቃላይ በጎ ባህርያትና መገለጫወች ያሉት አሐዱ አምላክ እንዳለ ያምናሉ፡፡

አላህ የሰው ልጅ ወደ ቅን መንገድ ይመራ ዘንድና በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ብልጽግናና ደስታን ይጎናጸፍ ዘንድ ወደ ቀና መንገድ የሚጠሩ ነብያትን እንደላከ ሁሉም ሙስሊሞች ያምናሉ፡፡ ነብዩ መሐመድ(ሰ) የመጨረሻውና መደምደሚያው ነብይ እንደሆኑ ያምናሉ፡፡

እንዲሁም የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ ስጋው እንደሚያልቅና ነፍሱ ግን ቀሪ እንደሆነች ያምናሉ፡፡ በምድር ላይ በጎ የሰራ ጀነት ሰዎች እንደሚሆን፣ በምድር ላይ እኩይ ሰሪ የነበረው ደግሞ ቅጣት ከሚቀበሉና የጀሐነብ ሰዎች እንደሚሆኑ ያምናሉ፡፡

ፍትህን (ዐድልን) በሚመለከት ደግሞ ሺዓዎች ከማይገባው ሁሉ የጠራው አላህ ፍትሓዊ እንደሆነ፣ ማንንም እንደማይበድልና ያለዓላማ አንዳች ነገር እንደማይፈጽም ያምናሉ፡፡

ኢማማን (ኸሊፋነትን) በተመለከተ ደግሞ ከነብዩ(ሶ) በኋላ የሳቸው ተተኪ የሚሆኑት አካላት በተመለከተ) ሺዓዎች ነብዩ(ሶ) አስራ ሁለት ተተኪ ኸሊፋዎችን ሰይመው እንዳለፉ ያምናሉ፡፡ ነብዩ(ሶ) እንዲህ ብለዋል፡-

**"ከኔ በኋላ (የሚነሱ) ኸሊፋዎች አስራ ሁለት ናቸው፡፡"**[19]

---

[19] -ሰሂህ ሙስሊም 3/1452-1453 ፤ -ሰሂህ ኢብን ሃባን 15/43-45 -ሁለተኛ እትም -ሙአሰሰት አል-ሪሳላ -ቤይሩት፡፡

-አል-ሙስተድረክ አላ አስ-ሰሂሀይን 3/815-816፣ 4/546- ዳር አል-ኩትብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡

-ሙሰነድ አቢ ዓዋና 4/369፣370፣371፣372፣373 ዳረል መዓሪፍ -ቤይሩት፡፡

-መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ- አል-ሐይሰሚ 5/190 -ዳር አል- ረያን ሊል ቱራስ-ካይሮ፡፡

-ሱነን አቡ ዳውድ 4/106 -ዳረል ፊክር፡፡

-አል-ሙዕጀም አል-አውሰጥ- አል-ጠበራኒ 1/263፣ 6/268- ዳረል ሐረሜይን አትም-ካይሮ፡፡

-ሙስነድ አህመድ ቢን ሀንበል 5/86፣ 87፣88፣89፣90፣92፣93፣89፣100፣101፣106፣107-ሙአሰሰት ቁርጡባ- ግብጽ፡፡

-ሙስነድ አል-ጠያለሲ 1/106፣180- ዳር አል-መዕሪፋ- ቤይሩት፡፡

-ሙስነድ አቢ-ያዕላ 13/406- ዳር አል-ቱራስ ሊልመእሙን- ደማሰቆ፡፡

-አል-አሃድ ወ አል-መሳኒ- አቢ በክር አል-ሸይባኒ 3/126፣128- ዳር-አል-ራያ- ሪያድ፡፡

-ሙስነድ ኢብን ጀዕድ 1/390- ሙአሰሰት ናድር- ቤይሩት፡፡

-አል-ሙዕጀም አል-ከቢር-አልጠበራኒ 2/195፣ 196፣ 197፣ 199፣ 206፣ 208፣ 214፣ 232፣ 253፣ 255- መክተበት አል-ዑሉም ወልሂከም- አል-ሞሱል፡፡

-አል-ሱና- ኢብን አቢ ዓሲም 2/532- አል-መክተብ አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፡፡

-አል ሱናነ አል-ዋሪዳ ፊ አል-ልፈን- አቢ ዐምር ዑስማን ቢን ሰዒድ አል-ሙቅሪእ አል-ዳኒ 2/492፤ 5/955- ዳር አል-ዓሲማ- ሪያድ፡፡

-አል-ፊተን- ነዒም ቢን ሐማድ 1/95- መክተበት አል-ተውሂድ- ካይሮ፡፡

-አል-ፊረዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ- ሺየርዊህ አል-ደይለሚ 5/102- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ-ቤይሩት፡፡

-ፈትህ አል-ባሪ-አል-ዓስቀላኒ አል-ሻፊዒ-13/211፣ 213- ዳር አል-መእሪፈህ- ቤይሩት፡፡

-ዐውን አል-መዕቡድ 11/245፣ 246፣ 248- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ-ቤይሩት፡፡

-ቱህፈት አል-አህወዚ-አልሙባርከፑሪ 6/391፣ 494-ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ-ቤይሩት፡፡

-ሸርህ አል-ነወዊ ዐላ ሰሂህ ሙስሊም 12/201- 2ኛ እትም- ዳር ኢህእ አል-ቱራስ አል-ዓረቢ-ቤይሩት፡፡ -ተፍሲር ኢብን ከሲር 2/33፤ 3/303- ዳር አል-ፊክር- ቤይሩት፡፡

ነብዩ(ሶ) እንዲህም ብለዋል፡-

**"የዘመኑን ኢማም (መሪውን) ሳያውቅ የሞተ ሰው ሞቱ የጃሂሊያ ነው"**[20]

እነዚህ ነብዩ (ሶ) በስማቸው የጠቀሷቸው የሳቸው ተተኪ ኢማሞች ወይም ኸሊፋዎች ናቸው፡፡

---

ከሺዓ ምንጮችም እጅግ በርካታ ሀዲሶች ተዘግበዋል፡፡

[20] -ሙስነድ አህመድ ቢን ሀንበል 4/96- ሙአሰሰት ቁርጡባ- ግብጽ፡፡ እዚህ ላይ፡-
**"ኢማም ሳይኖረው የሞተ ሰው የጃሂሊያ ሞት ሞተ"** የሚል እናገኛለን፡፡ ተመሳሳይ ሀዲስ በ ሙስነድ አል-ሻሚዪን- አል-ጠበራኒ 2/437- ሙአሰሰት አል-ሪሳላ -ቤይሩት እትም ላይ እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በ ሙስነድ አል-ጠያለሲ 1/259- ዳር አል-መዕሪፋ- ቤይሩት፤
በ ሙስነድ አቢ-ያዕላ 13/366- ዳር አል-ቱራስ ሊልመእሙን- ደማሰቆ- **"ኢማም በላዩ ላይ ሳይኖረው የሞተ ሰው ሞቱ የጃሂሊያ ነው"** የሚል ይገኛል፡፡
-አል-ሙዕጀም አል-ከቢር-አልጠበራኒ 19/388- መክተበት አል-ዑሉም ወልሂከም- አል-ሞሱል፡፡
-አል-ሱና- ኢብን አቢ ዓሲም 2/305- አል-መክተብ አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፡፡
--ተፍሲር ኢብን ከሲር 1/518- ዳር አል-ፊክር- ቤይሩት- **"በ አንገቱ ላይ ቤይዓ (ቃል-ኪዳን) ሳይኖረው የሞተ ሰው ሞቱ የጃሂሊያ ነው"** የሚል የገኛል፡፡
-ሰሂህ ኢብን ሒባን 10/434-ሙአሰሰት አል-ሪሳላ -ቤይሩት- **"ኢማም ሳይኖረው የሞተ ሰው የጃሂሊያ ሞት የሞተ ሰው ነው"** የሚል እናገኛለን፡፡
-አል-አሃዲስ አል-ሙኽታራ- ሃንበሊ አል-ሙቀደሲ 8/198- መክተበት አል-ነህዷ አል-ሀዲሳ-መካ አል-ሙከረማ- "ጣዓ (ተገዥነት) በላዩ ላይ ሳትኖረው የሞተ ሰው የጃሂሊያ ሞት ነው የሞተ" የሚል ይገኛል፡፡
-መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ- 5/218፣219፣223፣224 እና 225 -ዳር አል-ረያን ሊል ቱራስ-ካይሮ-በተለያየ አባባል ዘግበዋል፡፡
-ሙስነድ ኢብን አቢ ሽይባህ 7/457- መክተበት አል-ሩሽድ- ሪያድ፡፡
-አል-ሙዕጀም አል-አውሰጥ-አል-ጠበራኒ 1/70፤ 7/287- ዳረል ሐረሜይን አትም- ካይሮ፡፡
-ሒልየት አል-አውሊያእ 3/224፡፡

እነዚህም በቅደም ተከተላቸው፡-

1. *ኢማም አሚረል ሙእሚኒን- ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ(0)*
2. *ኢማም አል-ሙጅተባ- ሐሰን ቢን ዓሊ(0)*
3. *ኢማም አሽ-ሸሂድ- ሁሰይን ቢን ዓሊ(0)*
4. *ኢማም አል-ሰጃድ- ዓሊ ቢን ሁሰይን(0)*
5. *ኢማም አል-ባቂር- መሐመድድ ቢን ዓሊ(0)*
6. *ኢማም አስ-ሷዲቅ- ጃዕፈር ቢን ሙሐመድ(0)*
7. *ኢማም አል-ካዚም- ሙሳ ቢን ጃዕፈር(0)*
8. *ኢማም አል-ሪዷ -ዓሊ ቢን ሙሳ(0)*
9. *ኢማም አል-ጀዋድ- ሙሐመድ ቢን ዓሊ(0)*
10. *ኢማም አል-ሓዲ- ዓሊ ቢን ሙሐመድ(0)*
11. *ኢማም አል-ዓስከሪ- ሐሰን ቢን ዓሊ(0)*
12. *ኢማም አል-ሙንተዘር- መህዲ ቢን ሐሰን(0)*

ከነዚህ ከተጠቀሱት ኢማሞች የመጨረሻው ኢማም አል-መህዲ (0) ሲሆን በዱኒያ ላይ በህይወት ይገኛል፣ ከእይታ ግን ተሰውሯል፡፡ ምድር በጭቆናና በደል ከተሞላች በኋላ በፍትህና እኩልነት ሊሞላት አላህ በፈቀደ ጊዜ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ይገለጣል፡፡ ሕዝቦችና ሀገራት ኢማሙ በሚያቋቁመው ብቸኛና ድንቅ አንድ ኢስላማዊ መንግስት ስር በአላህ ፈቃድ አንድ ይሆናሉ፡፡ ሙተዋትር የሆኑ ሐዲሶች በዚህ ጉዳይ ላይ ተዘግበዋል፣ ተተርከዋል፡፡ *(ለአብይ ያህል-"**አል-መህዲ ፊ አል-ሱንና**" የተሰኘውን የአያቱላህ ሰይድ ሷዲቅ ሺራዚን መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡)*

እነዚህ ሁለቱን የዲን መሰረታውያንን ማለትም ***ዐድል*** እና ***ኢማማን*** (ፈትሓዊነትንና ኺላፋን/መሪነትን) በተመለከተ ሺዓዎች በነቅልና ዐቅል (ከድርሳናትና አዕምሮ) ማስረጃዎች በግልጽ አረጋግጠዋል፡፡

የኢስላም ቅርንጫፎች *(ፍሩዕ አል-ኢስላም)* ማለትም ዒባዳዎችና ተግባራትን እንዲሁም ህግጋትና መመሪያዎችን በተመለከተ ደግሞ የሺዓ ሙስሊሞች አራት ምንጮች እንዳሉ ያምናሉ፡፡ ይኸውም፡-

ሀ. **ቁርአን**- ይህ በሙስሊሞች እጅ የሚገኝ ያልተጨመረበት፣ ያልተቀነሰ፣ ያልተከለሰና ያልተበከለ መጽሐፍ ነው፡፡

ለ. ከነብዩ(ሶ) እና ከጠሩት አህለልበይት(ዐ) **የተያዙ ትክክለኛ ሐዲሶች (ሱና)**

ሐ. የሙስሊሞች አጠቃላይ **ስምምነት (ኢጅማዕ)**

መ. **ዐቅል (አዕምሮ)** ናቸው፡፡

የእጅቲሓድ በር ክፍት ነው ይላሉ፡፡ ሸርጠቱን ጠብቆ ከነዚህ አራቱ ምንጮች እስቲንባጥ አድርጎ በሸሪዓ አህካሞች (ህግጋትና መመሪያዎች) ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ይህንን ተከትሎ መስራትና ፍርዱን መቀበል ይቻላል ይላሉ፡፡

# ሺዓ ምንድን ነው?

# ሺዓዎች እነማን ናቸው?

“ሺዓ” የሚለው ቃል መሰረቱ ከ "ሙሻየዓ" የተገኘ ሲሆን ይህም *መከተል* ወይም *መወገን* (*ሙታበዓ)* የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል፡፡ በቁርአን ውስጥ ሺዓ የሚለው ቃል ለነብዩ ኑህ (ዐ) ተከታዮች የተሰጠ ስያሜ መሆኑን እናያለን፡፡

**وَإِنَّ مِنْ شِيعَتِهِ لَإِبْرَاهِيمَ**

**“እነሆ ኢብራሂም ከሺዓዎቹ /ተከታዮቹ/ ነው፡፡”[21]**

እንዲሁም ነብዩ (ሶ) የኢማም ዓሊን (ዐ) ተከታዮች በዚሁ በስም የጠሯቸው መሆኑን ከሐዲስ እናገኛለን፡፡ ይኸውም የሺዓም ሆነ የሱኒ የታሪክ ምሁራንና የሐዲስ ሊቆች በመጽሀፎቻቸው ውስጥ እንደጠቀሱት ነብዩ (ሶ) ሲናገሩ፡-

**"ዓሊ ሆይ! አንተና ሺዓዎችህ ናቸው ዕድለኞች (የድልና ፈውዝ ባለቤቶች)፡፡"[22]**

---

[21] አል- ሳፋት፡ 73

[22]በሌላም ተመሳሳይ አባባል የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ወደ ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ) እያመለከቱ፡-

**"ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! ይህ ሰው እና ሺዓዎቹ ናቸው ዕድለኞች (የድልና ፈውዝ ባለቤቶች)"** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ ለዝርዝሩ፡-(ታሪክ ዲመሽቅ ኢብን ዓሳኪር አሽ-ሻፊዒ 2/442 ሐዲስ 951 ፤-ገጽ 348 ሐዲስ 849፣851፡፡

-አልመናቂብ -አል-ከዋሪዝሚ -አል-ሐነፊ ገጽ 62፤

-ሸዋሂድ -አል-ተንዚል አል-ሐሰካኒ - አል-ሐነፊ 2/362 ሐዲስ 1139፡፡

-ኪፋየት አል-ጧሊብ አል-ከንጂ አሽ- ሻፊዒ ገጽ 245፣313፣314፡፡

- አል-ዱር አል-መንሱር አስ- ሱዩጢ አሽ-ሻፊዒ 6፡379፤

- ፈራኢድ አስ-ሲምጠይን 1፡1፡፡

---

በተጨማሪም ኩኑዝ አል-ሐቃእቅ ገጽ 92 ላይ፡- **"የቂያማ ቀን አሸናፊ ና ስኬታማ (የፈውዝ ባለቤት) የሚሆኑት ዓሊ እና ሽዓዎቹ ናቸው"** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ምንጭ፡-
-መጅመዕ አል ዘዋኢድ አል-ሐይሰሚ 1/131፡፡
-አስ-ሰዋሂቅ አል-ሙህሪቃ ገጽ 92፡፡
-ተዝከረቱል ኸዋስ-ሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ አል-ሐነፊ ክፍል2/ 56፡፡
-አል-ፊርዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ -ኢብን ሽርዊዩህ አል-ደይለሚ 3/61 -ዳር አል-ኩቱብ ዒልሚያህ -ቤይሩት፡፡

በተጨማሪም ነብዩ (ሶ) ለዓሊ እና ሺዓዎቹ የተናገሩት በርካታ የምስራቾች ዉስጥ ለዓሊ እና ሺዓዎቹ አላህን ምህረት እንደጠየቁና የቂያማ ቀን ነጻ የሚወጡት እነሱ መሆናቸውን በብዙ አጋጣሚዎች ገልጸዋል፡፡

**“የቂያማ ቀን ወደ ዐርሽ ጥላ ከሁሉም ቀድመው የሚመጡት እነዛ ምንኛ የታደሉ ናቸው!”** ሲሉ

**"እንዲያው ማን ይሆኑ?"** ብሎ ጠየቀ፡፡

ነብዩ (ሶ) **"ዓሊ ሆይ! እነዚህማ አንተ፣ ሺዓዎችህ እና ወዳጆችህ ናቸው"** አሉ፡፡

(ሽርህ አል-ዘርቃኒ2/441- ዳሩል ኩቱብ ኢልሚያ- ቤይሩት)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ነብዩ(ሶ) የሚከተለውን ብለዋል፡-

**“ዓሊ ሆይ! አላህ ለአንተ፣ ለዝርዮችህ፣ ለልጆችህ፤ ለቤተሰቦችህ እና ለሺዓዎችህ ምህረትን አጎናጽፏችኋል፡፡ አብሽር! አንተ ነህ በጥበብ እና ዕውቀት ሆዱ የሞላ ደርባባ ሰው ፡፡”**

(አል-ፊርዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ ኢብን ሽርዊዩህ አል-ደይለሚ 5/329 ዳር አል- ኪታብ አል-ዒልሚያ- ቤይሩት)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ነቢዩ (ሶ)፡-

**"ለዓሊ እና ሺዓዎቹ ምህረትን ጠየቅኩኝ"** ብለዋል፡፡
-መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ 9/172- ዳር አል-ረያን ሊልቱራስ-ካይሮ፡፡
-አል-መጅመዕ አል-አውሰጥ -አል-ጠበራኒ 4/212 ዳረል ሐረመይን- ካይሮ፡፡

ከሺዓ ምንጮች ለመጥቀስ ካስፈለገ ደግሞ ከበርካታ ምንጮች ጥቂቱን ለመግለጽ ያህል፡-
-ቢሓር አል-አንዋር፡ 36/283፣284 -ክፍል 41፣ ሐዲስ 106፡፡ አል-አርሻድ1/41፡፡ ከሽፍ አል-ጉማ 1/53፡፡

ከነብዩ (ሶ) ዘመን ጀምሮ የዓሊ ተከታዮችና ደጋፊዎች በዚሁ ስም ይታወቁ ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ስም የጠሯቸው ነብዩ (ሶ) ናቸው፡፡
የነብዩ (ሶ) ንግግር ደግሞ ከአላህ ወህይ የሚመነጭ መሆኑን በቁርአን ውስጥ እናገኛለን፡-

***وَمَا يَنْطِقُ عَنِ الْهَوَىٰ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَىٰ***

**"ከስሜቱ የሆነ አንዳችም ነገር አይወጣውም፤ ከሚገለጥለት ወሕይ እንጂ (ከራሱ የሚናገረው ነገር የለም")**[23]

ስለዚህ የሺዓዎች በዚህ ስም መሰየም ከአላህ በሆነ ወህይ ነው ማለት ነው፡፡ ሺዓዎች ማለት የነብዩን (ሶ) ትዕዛዛት በመቀበል ዓሊንና ከእንከን ሁሉ የጠሩትን ልጆቹን የተከተሉ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ይኸውም ነብዩ (ሶ) ከማለፋቸው በፊት የተናገሩት ኑዛዜ ነው፡፡እንዲህም አሉ፡-

***وَإِنِّي أُوشِكُ أَنْ أُدْعَى فَأُجِيبَ ، وَإِنِّي تَارِكٌ فِيكُمُ الثَّقَلَيْنِ ما إن تمسَّكتُم بهما لَنْ تَضِلُّوا من بعدي أَبَدً كِتَابَ اللهِ وَعِتْرَتِي أَهْلَ بَيْتِي***

***"የመጠራቴ ጊዜ የቀረበ ይመስላል፣ እኔም ጥሪውን እመልሳለሁ፤ ሁለት የከበሩና የከበዱ ነገሮችን (ሰቀለይን) በመካከላችሁ እተዋለሁ፡፡ ሁለቱን አጥብቃችሁ ከያዛችሁ ከኔ በኋላ ጥመት አያገኛችሁም፡፡ እነሆ! እነዚህ ሁለቱ የአላህ ኪታብ (ቁርዓን) እና የኔ ዘረ-ሰብ (ዒጥራዬ)-አህለቤይቴ ናቸው"***[24]

---

[23] አል-ነጅም፡ 3-4

[24] ሰሂህ ሙስሊም-ኪታብ አል ፈዳኢል 2/362 እትም ዲሳ አል-ሐለቢ፣15/179-180 ግብጽ -በነዋዊ ሸርህ፡፡

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሶ) እንዲህ ብለዋል፡-

**"ዓሊ ከሐቅ ጋር ነው፣ ሐቅም ከዓሊ ጋር ነው፡፡"**[25]

---

[25] ተመሳሳይ ትርጉም ያዘሉ በርካታ ሐዲሶችአሉ፡፡ ነብዩ(ሶ) ሲናገሩ፡-

**"ዓሊ ከሐቅ ጋር ነው፣ ሐቅም ከዓሊ ጋር ነው፡፡ የቂያማ ቀን ሐውድ ላይ ወደኔ እስኪመለሱ ድረስ ፍጹም አይለያዩም"** ብለዋል፡፡

-ታሪክ ባግዳድ-ኸጢብ አል-ባግዳዲ 14/321 -የዓሊ ቢን አቢጧሊብ የህይወት ታሪክ፣

-ታሪክ ዲመሽቅ ኢብን ዓሳኪር አሽ-ሻፊዒ 3/19- ሐዲስ 1162፤

-ጋየቱል መራም 539 ክፍል 45፤

-አል-ኢማማህ ወ አል-ሲያሳ -ኢብን ቁተይባ 1/73 -ግብጽ፤

-ሙንተኸብ ከንዝ አል-ዑማል ቢሓምሽ ሙስነድ አህመድ 5/30፤

-ፈራኢድ አስ-ሲምጠይን- ሐመዋኒ 1/177፤

-አርጀህል መጧሊብ- ዑበይዱላህ አል-ሐነፊ 598 ላሆር፤

-አል-መናቂብ- አል-ሸዋሪዝሚ 110 -አል-ሐይደሪያ፤

-መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ -አል-ሐይሰሚ 9/134፤

-መጅመዕ አስ-ሰጊር-ጠበራኒ 1/55፤

-ኪፈየት አል-ጧሊብ -ከንጂ አሽ- ሻፊዒ 399- አል-ሐይደሪያ፤

-ሰዋኂቅ አል-ሙህሪቃ -ኢብን ሐጀር 74-75 -አል-መይመና ግብጽ፤

-ታሪክ አል-ኹለፋእ -ሲዩጢ 173 -አስ-ሰዓዳ -ግብጽ፤

-ኢስዓፍ አል-ራጊቢን ቢሐምሽ ኑር አል-አብሷር -157 -አስ-ሳዕዲያ፤

-ኑር አል-አብሷር -ሺብለንጂ 73፤

የናቢዕ አል-መወዳ -ቁንዱዚ አል-ሐነፊ- 40፤90፣ 175፣ 237፣ 273፣ 275 ኢስላምቡል፤

-ጋየቱል መራም 540 -ክፍል 45፤

-ፈይዱል ቀዲር-ሸውካኒ 4/358፤

-አል-ጃሚዕ አስ-ሰጊር- ሱዩጢ 2፡56፤

-አሰነል መጣሊብ -136፤

-አል-ፈትህ አል-ከቢር-ነብሓኒ-2፡242 ግብጽ፡፡

እንዲሁም ረሱሉ (ሶ) ወደ ዓሊ እያመለከቱ፡-**"ሀቅ ከዚህ ሰው ጋር ነው፣ሀቅ ከዚህ ሰው ጋር ነው"** ብለዋል (አቡ ሰዒድ አለ-ኹድአ አውርቶታል- የኢብን ዓሳኪር ታሪኽ ዲመሽቅ 3/119- ሐዲስ 1161 ላይ በዓሊ ቢን አቢ ጣሊብ የህይወት ታሪክ ስር ያገኙታል፡፡ እንዲሁም መጅመዕ አለ-ዘዋኢድ -አለ-ሐይሰሚ- 7/3፡፡-------

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሶ) እንዲህ ይላሉ፡-

**"ከኔ በኋላ ፈተና (ፊትና) ይከሰታል፣ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ዓሊይ ቢን ዓቢ ጧሊብን የሙጥኝ ብላችሁ ተከተሉ፡፡ የቂያማ ቀን መጀመሪያ የሚያገኘኝና እጅ የሚነሳኝ እሱ (ዓሊ) ነው፡፡ እሱ ከፍ ባለው ሰማይ ውስጥ ከኔ ጋር ነው፤ እሱ ሐሰትን (ባጢልን) ከሐቅ (እውነት) የሚለይ ነው፡፡"[26]**

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሶ) እንዲህ ይላሉ፡-

---

--- እንዲሁም፡- **"አላህ ሆይ! ለዓሊ ራህመትህን ለግሰው፡፡ እሱ በዞረበት ሁሉ ሐቅን ከሱ ጋር አዙራት"** ብለዋል፡፡ (-ሰሒሕ አል-ቲርሚዝ 5፡633 ሐዲስ 3713 ዳር አል-ቱራስ አል-ዓረቢ ቤይሩት፤

-አል-ሙስተድረክ አላ-አስ ሰሂሐይን-አል-ሐኪም አል-ኔይሳቡሪ 3፡134 ዳር አል-ኩቱብ አል-ዓለሚያ ቤይሩት፤

-አል-ሙስተድረክ አላ-አስ-ሰሂሀይን -አል ሐኪም አል-ኔይሳቡሪ 3-134 -ዳር-አል ኪታብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፣

-አል መናቂብ አል-ከዋሪዝሚ አል-ሐነፊ 56፤

-አል-ሙዓጀም አል-አውሰጥ -አል-ጠበራኒ 6፤95 -ዳር አል-ሐረመይን ካይሮ፤

-ሙሰነድ በዛር 3፡52 ሙአሰሰት ዑሉም አል-ቁርአን -ቤይሩት፤

-ጋየቱል መራም 539፤ ሙስነድ አቢ-ያዕላ 1፡418 -ዳረል መእሙን ሊ አል-ቱራስ-ደማስቆ፤

-ሸርህ ነህጁል በላጋ -ኢብን አቢል ሐዲድ 2፤572- ቤይሩት፤ ፈትሁል ከቢር-አል-ነብሓኒ 2፡ 131፤

-ጃሚዕ አል-ኡሱል -ኢብን አሲር 9፡420፤

-ፈራኢድ አል-ሲምጠይን -ሐመወይኒ 1፡176፣

-አል-መሓሲን ወል መሳዊእ -በይሀቂ 41-ቤይሩት፤

-አል-ኢንሷፍ- ባቀላኒ 58 -ካይሮ፤

-ታሪክ አል-ኢስላም -ዘሐቢ 2/198 -ግብጽ፤

-አርጀሁል መጧሊብ -ዑበይዱላህ አል-ሐነፊ 599- ላሆር እና ሌሎች በርካታ ምንጮች፡፡ አረብኛ አንባቢዎች አሪጅናል መጽሀፉን እንዲያነቡ ይመከራል፡፡

ነብዩ (ሶ) እንዲህም ብለዋል፡- **"ዓሊ ቢን አቢ ጣሊብ በዞረበት ሁሉ ሐቅ ከሱ ጋር ነው፡፡"** (ፈራኢድ አል-ሲምጠይን- ሐመዊይኒ፡- 1/177-ሀዲስ 139)

[26]-ታሪክ ዲመሽቅ-ኢብን ዓሳኪር-የዓሊ ቢን አቢጧሊብ የህይወት ታሪክ-42/450-ቁጥር 9026፡፡

**“በሰዎች መካከል ኢክትላፍ (በቡድኖች መለያየት) እና መከፋፈል ይከሰታል፤ ይህ (ሰው) ማለትም ዓሊ እና የሱ ሰሃቦች ናቸው ሐቅ ላይ የሚሆኑት፡፡”[27]**

ሺዓዎች *"ኢማሚያ"* በሚል ስያሜም ይታወቃሉ፡፡ ይኸውም በአሚረል ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ) እና በአስራ አንድ ልጆቹ ኢማምነት ስለሚያምኑ ነው፡፡ እንዲሁም *"ጀዕፈሪያ"* ተብለው ይጠራሉ፡፡ ይኸውም ሐላልና ሐራምን በተመለከተ የአላህን ኪታብ ከሁሉም የበለጠ የሚያውቁትን እና የነብዩን (ሶ) ሱና በቅርብ ሆነው ከሌላው ሁሉ በላቀ ሁኔታ የሚያውቁትን አህለልቤይት (ዐ) በመከተላቸው ነው፡፡ ከአህለልቤይት (ዐ) ኢማሞች ሌሎች ኢማሞች በጊዜው በነበረው አመቺ ያልሆነ ሁኔታ የተነሳ ዲኑን በሚፈለገው ሁኔታ ማስተላላፍና ማስፋፋት ባይችሉም ስድስተኛው ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ(ዐ) ከሌሎች አንጻር ባገኙት ፋታ የኢስላማዊ ሳይንስ መሰረቶችንና ቅርንጫፎችን፣ ስነጽሑፍን፣ ስነ-ምግባራዊ አስተምሮቶችን እና ሌሎችም የእውቀት ዘርፎች በስፋትና በጥልቀት በማስተማራቸውና ሺዓዎች ከሳቸው ስለወሰዱ ይህን ስያሜ ለማግኘት በቅተዋል፡፡

በተጨማሪም "ኢስነ ዐሽሪያ" በመባልም ይታወቃሉ፡፡ ይኸውም ከነብዩ (ሶ) በኋላ የኸሊፋነት ቦታውን በተረከቡ 12 መሪዎች (ኸሊፋዎች) ስለሚያምኑ ነው፡፡

ይህንንም በማስመልከት ነብዩ (ሶ) የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡-

**"ከኔ በኋላ ኸሊፋዎች አስራ ሁለት ናቸው"[28]**

---

[27] ከንዝ አል-ዑማል፡- 6/15

[28] ለዝርዝሩ ገጽ 20-21 የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

# ኢስላም በሺዓ እይታ

በሺዓ መዝሐብ እይታ ኢስላም፡-

**"ዐቂዳ"**

**"ሸሪዓ"**

**"ኒዛም" ናቸው፡፡**

## 1. የሺዓ ዐቂዳ

-ሺዓዎች፡-

አላህ የሁሉ ነገር አስተናባሪ እንደሆነ፣ ፍትሃዊ እንደሆነና ሸሪክ

እንደሌለው፣

-በሙሐመድ ነብይነት፤

-በኢስላም ኃይማኖትነት፤

-በቁርዓን የአላህ ኪታብነት፤

-በካዐባ ቂብላነት፤

-ነብዩ ሙሐመድ ያመጡት ጉዳይ ሁሉ እውነት መሆኑን፤

-አላህ ቀብር ውስጥ ያሉትን እንደሚቀሰቅስ፤

-ጀነትና እሳት (አዛብ) እውነት መሆኑን፣

-ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ሳይገደዱ እና ልቅ የሆነ ምርጫ ሳይኖራቸው (ያለ ጀብር እና ተፍዊድ) ምርጫ (ኢኸቲያር) እንዳለቸውና በጎ ከሰራ ሽልማት፣ መጥፎ ከሰራ ቅጣት (ፍርድ) እንደሚያገኝ ያምናሉ፡፡

-ሺዓዎች ኢስላም ምንም ጉድለት የሌለበት ምሉዕ የሆነ የህይወት መንገድ መሆኑን ያምናሉ፡፡ አላህ ባወረደውና ነብዩ (ሶ) እና ንጹህን ኸሊፋዎች ባስተላለፉት መሰረት ኢስላም ሙሉ ዲን መሆኑን ያምናሉ፡፡

-በዓቂዳም ሆነ በተግባር ሊከተሉት የሚገባ ብቸኛው ኃይማኖት መሆኑን እና በማንኛውም ሁኔታ ከዚህ ዲን ማፈንገጥ የዱኒያና የኣኺራ በላእ እንደሚያስከትል ያምናሉ፡፡

-በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር ዲኑን ተቀብሎ መኖር ደግሞ የዱንያና የአኺራ ደስታን እንዲሚያጎናጽፍ ያምናሉ፡፡

-መላውን የሰው ልጅ በትክክለኛ ጎዳና ላይ የሚመራ ዲን መሆኑን፣ ለመንፈሳዊ እነጻ እንደሚያተኩር ሁሉ ለስጋዊ እደገትም ትኩረት እንዳለው፣ ለስርዓትና ህግ ትኩረት እንደሚያደርግ ሁሉ ለመልካም እሴቶችና በጎ ስብእናም ዘብ የሚቆም ምሉዕ የህወት ጎዳና እንደሆነ ያመናሉ፡፡

## የዲን/ኃይማኖት መሠረቶች (ኡሱል አል-ዲን) ሺዓ ዘንድ አምስት ናቸው፡፡

1. **ተውሂድ** (የአላህ አሀዳዊነትና አንድነት)
2. **ዐድል** (ፍትሐዊነት)
3. **ኑቡወህ** (ነብይነት)
4. **ኢማማህ** (ተተኪነት/መሪነት /ኸሊፋነት)
5. **መዓድ** (ትንሳዔ)

**ተውሂድ** ፡ -አላህ አንድ፣ ብቸኛና ልዩ ነው፤ ሸሪክም ሆነ ብጤ የለውም፡፡

**قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَد اللَّهُ الصَّمَدُ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَد وَلَمْ يَكُنْ لَهُ كُفُوًا أَحَدٌ**

**“በል- እሱ አላህ አንድ ነው፤ አላህ የሁሉም ነገር መጠጊያ ነው፤ አይወልድም፤ አይወለድምም፡፡ ብጤም የለውም፡፡”**[29]

[29] አል-ተውሂድ፡ 1-4

***ዐድል*** ፡-አላህ ፍትሃዊ ነው፤ አይበድልም፤ በደልን አይቀበልም፡፡

**ነብይነት**፡- የሰው ልጅ የኸይር እና የሸር (መጥፎ እና ጥሩ) መንገድ ይለይ ዘንድና ከእኩይ ተግባራት እንዲቆጠብና ለበጎ ተግባራት እንዲነሳሳ ለመርዳት አላህ በርህራሄው ነብያትን ለሰው ልጆች ልኳል፡፡

***ኢማማህ፡***-በአላህ ትእዛዝ መሰረት የአላህ መልእክተኛ (ሶ) 12 ተተኪ ኸሊፋዎች ለይተውና ሰይመው አልፈዋል፡፡ በተዋረድ ተከታትለው የሚነሱ አስራ ሁለት ኢማሞችን በስማቸው፤ በአባትና አያት ስማቸውና በማእረግ ስማቸው (ኩንያቸው) ጠቅሰው ተናዝው አልፈዋል፡፡ የወቅቱ ኢማም ቀጣዩን ኢማም ለይቶ በመተካት መሪነቱ በቀጣይነት እንዲተላለፍ አድርገዋል፤ እነዚህን ኢማሞች መከተልና የዲን እውቀትን ከነሱ መያዝ ግዴታ ነው፡፡ ስም ዝርዝራቸው ቀደምሲል ተገልጿል፡፡

***መዓድ (ትንሳዔ)፡***- አላህ የቂያማ ቀን በጎ የሰሩትን ሰዎች ሊሸልምና መጥፎ ሰሪዎችን ሊቀጣ ፍጥረታትን ዳግም ወደ ሕይወት ይመልሳል፡፡

**فَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُ وَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ**

***"ቅንጣት ያህል በጎ የሰራ ያገኛታል፤ ቅንጣት ያህል መጥፎ የሠራም ያገኛታል፡፡"[30]***

[30] አል- ዘልዘላ፡ 7 እና 8

ለነዚህን የዲን መሰረቶች ዝርዝር በርካታ የሺዓ ማጠቀሻ መጽሀፍት የሚገኙ ሲሆን ለምሳሌ ያህል፡-

**-ሸርህ አል-ተጅሪድ**[31]

**-ዐበቃት አል-አንዋር**[32]

**አል-ገዲር**[33]

**አል-ፉሱል አል-ሙሒማ**[34]

**አል-ሙራጀዓት**[35]

እንዲሁም በሺዓ ዑለማዎች የተጻፉ በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች መጽሐፍት፡፡

---

[31] ዓላማህ አል-ሒልሊ- 648-726 ሂጅራ

[32] ዐበቃት አል- አንዋር ፊ ኢስባት ኢማመት አኢመት አል-አጥሓር -ዓላማህ ሚር ሓሚድ ሁሰይን አል-ሒንዲ 1241-1306 ሂጅራ ወይም 1830-1888 ዓ.ል.መጽሐፉ አንድ መቶ ያህል ቅጽ (ሙጀለድ) ሲሆን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ አንደኛው ክፍል ኢማማን /ኺላፋነትን በተመለከተ የቁርአን አያዎችን ማቅረብና መተንተን ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ አስራ ሁለቱ ኢማሞች የሚያወሱ ሐዲሶችን ማቅረብና መተንተን ነው፡፡

[33] ዓላማህ ሼክ አሚኒ 1320-1390 ሂጅራ- ከ20 በላይ ሙጀለድ (ቅጽ) ያለው ሲሆን አስራ አንድ ሙጀለድ ያህል ታትሞ ይገኛል፡፡

[34] ዓላማህ ሰይድ ዓብደልሁሴን ሸረፈዲን-1290-1388 ሂጅራ (1957 ዓ.ል)

[35] ዓላማህ ሰይድ ዐብደልሁሴን ሸረፈዲን

## 2. ሸሪዓ በሺዓ እይታ

ሸሪዓ ሺዓ ዘንድ፡-

*ሀ.* **ዒባዳዎች፡**- *ወደ አላህ የምንቃረብባቸው ተግባራት፡- ከነዚህም ሶላት፣ ጾም፣ ኩምስ፣ ዘካት፣ ሐጅ፣ ጂሐድ፣ ጠሃራህ፣ ኢዕትካፍ፣ በበጎ ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል . . . ወዘተ ናቸው፡፡*

**ለ.** ***ሙዓመላት፡***- *እንደ ግብይት (መግዛትና መሸጥ)፣ ክራይ፣ ልገሳ (ወቅፍ)፣ ሞረርጌጅ … የመሳሰሉት፡፡*

***ሐ. ሥነ-ምግባር (አኽላቅ)፡-*** *ኢስላም እንደ ግዴታ የሚያዘውና እንደ ዉዴታም የሚያበረታታው እንደ እውነተኝነት (ሐቀኝነት)፣ አማና (አደራ ጠባቂነት)፣ ጀግንነት፣ ተነሳሽነት፣ የመሳሰሉት የመልካም ስነ-ምግባር መገለጫዎችን ያካትታል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ኢስላም ከእኩይ ሥነ-ምግባራት ጎራ የፈረጃቸው እንደ ክህደት፣ ውሸት፣ ስንፍና፣ ምንአለብኝነትና ማንኛውም አፍራሽ የሆኑ አስተሳሰቦችን ይኮንናል፡፡*

***መ. ደንብና ሥርዓቶች፡***- *እነዚህ ኢስላም ስርዓት (አደብ) አድርጎ የሚቀበላቸው ተግባራት ሲሆኑ እንደ የመኝታ (እንቅልፍ) ደንብ፣ ከእንቅልፍ የመነሳት ደንብ፣ የጋብቻ ሥነ ስርዓት፣ የጉባኤ (መጅሊስ) ደንብ፣ የጉዞ ደንብና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡*

***ሠ. አህካሞች (ህግጋት)፡-*** *ይህ ግዴታ (ዋጂብ)፣ እርም የሆኑ ነገሮችን (ሙሐረማት)፣ የሚበረታቱ ተግባራት (ሙስተሐባት)፣ የሚጠሉ ነገሮች (መክሩሓት) እንዲሁም የተፈቀዱ ነገሮች (ሙባሓት) ያጠቃልላል፡፡*

## አምስቱ አህካሞች

1.ዋጅብ (ግዴታ የሆኑ ነገሮች)

2. ሐራም (ፍጹም የተከለከሉ ነገሮች)

3. ሙስተሐብ (የሚበረታቱ/የሚወደዱ ነገሮች)

4. መክሩህ (የተጠላ/የማይበረታቱ ነገሮች)

5. ሙባህ (የተፈቀዱ/ያልተከለከሉ ነገሮች)

**ዋጂብ** ተግባራት ማለት ኢስላም ተፈጻሚነታቸውን ግዴታ ያደረጋቸው እንደ ሶላት፣ ጾም፣ ዘካት፣ ሐጅና ጂሐድ ያሉ ተግባራት ናቸው፡፡

**ሙሐረማት፡-** የሚባሉት ደግሞ ኢስላም እርም ያደረጋቸው እንደ አስካሪ መጠጥ መጠጣት፣ የዓሳማ ስጋ መብላት፣ ቁማር መቆመር፣ የአራጣ ስራ፣ ዝሙትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ሙስተሐባት**፡- ኢስላም የሚያበረታታቸው ነገር ግን አለመተግበሩም የማያስጠይቅ ተግባራት ሲሆኑ እንደ ዕለታዊ ሱንና ሰላቶች (ነዋፍል)፣ ተወዳጅ የሆኑ ሰደቃዎች፣ የሰዎችን ሓጃ (ችግር) መቅረፍና ሌሎች ግዴታ ያልሆኑ በጎ ተግባራት ናቸው፡፡

**መክሩሓት**፡- እነዚህ ተግባራት ደግሞ እንደ የጋብቻ ፍች ያሉ የተፈቀደ ነገር ግን ኢስላም የሚጠላቸው ተግባራት ናቸው፡፡

**ሙባሓት**፡- እነዚህ ደግሞ መስራቱም ሆነ አለመስራቱ እኩል የሆኑ ነገሮች፡፡ ለምሳሌ ውሃ መጠጣት፡፡

## የሺዓ የሸሪዓ ምንጮች

በሺዓዎች ዐቂዳ መሰረት ለሸሪዓ አህካሞች ምንጭነት የሚውሉ አራት ምንጮች ("መሳዲር") አሉ፡፡

**1. ቁርአን፣**

2. ንጹህ የሆኑ የነብዩ (ሰ) ሱና ፡- ይህ የነብዩ (ሰ) **የተገበሩት፣ የተናገሩትና ዕውቅና የሰጡት** እንዲሁም መዐሱም የሆኑት አህለልቤይት **ቃል፣ ተግባራትና ተቅሪር** ያቀፈ ነው፡፡

3. **ኢጅማዕ**፡- በመካከላቸው መዐሱም ከመኖሩ ጋር ሙስሊሞች የተስማሙበት ጉዳይ)፣

**4. ዐቅል (ጤነኛ አዕምሮ)**[36]

ሺዓዎች የአላህን መጽሐፉ (ቁርዓንን)፣ የነብዩንና አህለልቤይት ሐዲሶች እንደምንጭነት የወሰዱት ቀደም ሲል በዝርዝር የተጠቀሰውን ሐዲስ አስ-ሰቀለይንን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

እነዚህ አራቱ የኢስላማዊ ሸሪዓ ምንጮች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ለማንኛውም ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ይህንን የሚጻረር ህግ ማውጣት አይፈቀድለትም፡፡ ከዚህ ውጭ የሚገኝ ማንኛውም ሌላ ህግ ህገ-ወጥ ነው፡፡

---

[36] ኡሱል አል-ካፊ 1/16- ሐዲስ12፤ ቢሓር አል-አንዋር 1/300 -ሐዲስ 3 ይመልከቱ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡-

**"አላህ በሰዎች ላይ ሁለት ማስረጃዎች አሉት፡- ውጫዊ የሆነ ማስረጃና ውስጣዊ የሆነ ማስረጃ፡፡ ውጫዊ ማስረጃ የሚባሉት መልእክተኞች፣ ነብያትና ኢማሞች ሲሆኑ ውስጣዊ ማስረጃ ደግሞ ዐቅል (አዕምሮ) ነው፡፡"**

አላህ እንዲህ ይለናል፦

**وَمَنْ لَمْ يَحْكُمْ بِمَا أَنْزَلَ اللَّهُ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْكَافِرُونَ**

**"አላህ ባወረደው የማይፈርድ እነሱ ከ ከሐዲያን ናቸው"**[37]

ከነብዩ (ሶ) እና ከንጹህን አህለልቤይት (0) የተያዙ ተፍሲሮች፣ ፊቂህና ሐዲሶች፣ ስለ ስነ-ፍጥረት፣ የትንሳዔ ሁናቴ ትንተና፣ የዲን መሰረቶችንና ቅርንጫፎችን በተመለከተ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮችና እንዲሁም ሌሎች በርካታ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የእውቀት በሮችን የሚተነትኑ ምንጮችን እናገኛለን፡፡ ዓላማህ መጅሊሲ (ረ) ብቻ የተወሰኑትን ሐዲሶች ከመቶ በላይ በሚሆኑ ቅጾች (ሙጀለዶች) ለመሰብሰብ በቅተዋል፡፡ የኪታባቸውን ስምም ***"ቢሓር ኣል ኣንዋር"*** ብለው ሰየሙ፡፡ እነዚህ ሐዲሶች ሙስሊሞችን ብሎም የሰው ልጆች በሙሉ በዱኒያም ሆነ በአኺራ ነጃ ለማውጣትና ደስታን ለማጎናጸፍ በቂ እንደሆኑ መናገር ይቻላል፡፡

## ሑክም (አስተዳደር) በኢስላም ውስጥ

ሺዓዎች በቁርዓን እይታ መሠረት ሑክም በሁለት ጎን እንደሚታይ ያምናሉ፡፡ ፤.አንደኛው ጎን አስተዳዳሪ /ገዢ/መሪ (ሐኪም) እና ህግን የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም ሐኪም/መሪ (አስተዳዳሪ) ወንድ፣ ሙእሚን፣ ከዝሙት ያልተወለደና ፊቂህ (ደረጃውን የጠበቀ ዕውቀት ያለው) መሆን አለበት፡፡

[37] አል-ማኢዳ፡ 44

2. ሌላኛው ጎን ደግሞ የሸሪዓ ህግጋቱ በምን መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ነው፡፡ ይህ ኢጅቲሓድ (በሸሪዓ ምንጮች ላይ በመመርኮዝ ለአንድ ጉዳይ መልስ ወይም መፍትሄ ወይም ፍርድ መስጠት የሚጠይቅ ሲሆን) ፉቀሓእ የሆኑ መራጂኦች ሸሪዓዉ በሚጠይቀው መስፈርት መሰረት ሐሳባቸውን ወይም አመለካከታቸው የሚገለጹበት ሁኔታ ነው፡፡

## ኢስላማዊ ኃይል

በሺዓ ዐቂዳ መሰረት ጂሓድ የወል ግዴታ ሲሆን ከጥቃት መከላከል ደግሞ የእያንዳንዱ ግለሰብ ግዴታ ነው፡፡ አንድ ኢስላማዊ የሆነ ሐገር ኢስላማዊ ህግጋቱና መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ደህንነታቸውንና ድንበራቸውን መጠበቅ የሚችሉ በቂ ቁጥር ያላቸውን ሙስሊሞች ለዚህ ተግባር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

ይህ ማለት ወታደራዊ ኃይል ብቻ በማዘጋጀት የሚገደብ አይደለም፡፡ በእውቀት፣ በኢኮኖሚ፣ በኢንዱስትሪና በሌሎች አውታሮች የደረጀ ኃይል መኖር አለበት፡፡ በዚህ መልኩ ሲሆን ነው **"ኢስላም ይልቃል እንጅ አይበለጥም"**[38] የሚለው የነብዩ (ሶ) ሐዲስ ተግባራዊ መሆን የሚችለው፡፡

## የህዝብ የገንዘብ ምንጮች

በእምነቱ መሰረት የፋይናስ ምንጮች፡- ኩሙስ፣ ዘካት፣ ጂዝያ (በኢስላም ጥበቃ ስር የሚኖሩ የሌላ ኃይማኖት ተከታዮች የሚከፍሉት የደህንነት ዋስትና የቀረጥ ዓይነት)፣ ኸራጅ (የመሬት ቀረጥ) ሙቃሰማ (ክፍፍል) ንግድና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

---

[38] ገዋሊ አል-ሊኣሊ፡ 1/226፤ ነሐጁል ሐቅ፡ 515

በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ገንዘብ ለአጠቃላይ ህዝብ ደህንነትና ችግር ለሚገጥማቸው ግለሰቦች እንደሁኔታው ወጭ የሚደረግ ነው፡፡ በሺዓ አንድ ግለሰብ ሐላል በሆነ መንገድ የግል ንብረት ማፍራት ይችላል፡፡ ከሚያገኘው ገቢ ያለበትን የአላህ ሐቅ ይከፍላል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ በሌሎች ንብረትና ገንዘብ ላይ መብት አይኖረውም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢስላም ለሰራተኞችና ለገበሬ እንዲሁም ለአሰሪና ለመሬት ባለቤት የሚገባውን መብት ይሰጣል፡፡ ገንዘብ በተወሰኑ ግለሰቦች ዘንድ ያለ አግባብ እንዲጠራቀምና ሌላው ክፍል ለድህነት እንዲጋለጥ እንዲሁም አንዱ በሌላው ላይ ድንበር እንዲያልፍ አይፈቅድም፡፡

## ኢስላማዊ ነጻነት

ነጻነት ከኢስላም መሰረታዊ ዓላማዎች አንዱ መሆኑን ሺዓዎች ያምናሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ታላቁን መልእክተኛ(ሶ) ከላከበት ምክንያቶች ውስጥ፡-

وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ

**“ሸክማቸውንና በላያቸው ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች ያነሳላቸዋል፡፡”[39]**

አንድ ሙስሊም በአንደበትም ሆነ በብዕር ሐሳቡን የመግለጽ ሙሉ ነጻነት አለው፡፡ በተጨማሪም በተለያየ የስራ መስክ ተሰማርቶ የመስራት የመጓጓዝ፣ የትዳርና የንግድ መብትና ነጻነት አለው፡፡ ሴቶችም ቢሆኑ ሸሪዓው

[39] አል-አዕራፍ፡ 157

በሚፈቅደው መሰረት አካላዊና መንፈሳዊ ሁኔታዎቻቸውን ባገናዘበ መልኩ ነጻነት አላቸው፡፡ አላህም በቁርአኑ ሲናገር፡-

**وَلَهُنَّ مِثْلُ الَّذِي عَلَيْهِنَّ بِالْمَعْرُوفِ**

**"ለእነርሱም (ለሴቶቹ) ያለባቸውን ግዴታ ያህል በበጎ ሁኔታ መብትም አላቸው፡፡"[40]**

ይህ ኢስላማዊው ህብረተሰብ ብልጽግናና ደህንነትን ይጎናጸፍ ዘንድ፣ ዕድገቱ እንዲሳካና ጥረቱ እንዲሰምር ለሙስሊሙ ኡማ መንፈሳዊና ተግባራዊ ዝግጅት በር የሚከፍት ሰፊ ነጻነት ነው፡፡

በመጀመሪያ አራቱን የኋላ ቀርነት መንስዔዎች ይጻረራል፡፡

1. **መሐይምነት**፡- ዕውቀት መፈለግና በመረጃ መታነጽ የኃይማቱ ባህል መሆኑን እና ለማህበረሰቡ ስልጣኔና ንቃተ-ህሊና ተግቶ የሚሰራ በመሆኑ በወንድም ሆነ በሴት ላይ ግዴታ የሆነ ኃላፊነትና ተግባር መሆኑን በአንክሮ ያስቀምጣል፡፡ ይህንንም ከነብዩ (ሶ) አንደበት እንደሚከተለው እናያለን፡፡

**"ዕውቀትን መፈለግ/መማር በእያንዳንዱ ሙስሊምና ሙስሊመት ላይ ግዴታ ነው፡፡"[41]**

በተለያዩ የእውቀት መስኮች ሰፊ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረን እና በጥልቀት መመራመር እንዳለብን ያበረታታል፡፡ በሐዲስ ውስጥ እንዲህ እናያለን፡-

**"የሰው ልጅ ዕውቀት የመፈለግ/የመማር ትሩፋትን ባወቀ ኖሮ በድቅድቅ የባህር ጨለማ ውስጥ በመስመጥና ህይወቱን መስዋዕት በማድረግ እንኳን ቢሆን በፈለጉት ነበር፡፡"[42]**

---

[40] አል-በቀራ፡ 228

[41] ከንዝ አል-ፈዋኢድ 2/107

እንዲሁም ፡-

**"መላኢካዎች ለእውቀት ፈላጊ ክንፋቸውን ይዘረጋሉ፡፡"**

የዕልም ፈዲላን በተመለከተ ሌሎች ብዙ ሪዋያዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡

**2. ድህነት**፡- ኃይማኖቱ ስራ ፈትነትን በመኮነን ለስራ ያበረታታል፡፡ መስራት የሚችሉ ሰዎች በተገቢው የስራ መስክ ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ ያዛል፡፡ መስራት የማይችሉ ሰዎች መንግስት ወኪል ሆኖአቸው እንዲረዳቸው ያዛል፡፡

**3. በሽታ**፡-ሸሪዓው ለብዙ በሽታዎች ፈውስን ማፈላለግና በሽታ የሚወገድበትን ዕውቀትና ተግባር እንድናጎለብት ያበረታታል፡፡ ለህክምና ስራ ቦታ ይሰጣል፡፡ እንዲህ የሚል ሐዲስ እናገኛለን፡፡

**"ዕውቀት ማለት ሁለት ዓይነት ነው፡- የኃይማኖቶች (መንፈሳዊ) ዕውቀትና ስጋዊ (ዐለማዊ) ዕውቀት፡፡"**[43]

**4. እኩይ ስብዕናና ተግባራት፡-**

ማህበረሰቡን በመልካም ስብዕናና ተወዳሽ ተግባራት ላይ ይገነባል፡፡ መጥፎ ስብዕናና እኩይ ተግባራትን ይኮንናል፡፡ እኩይ ተግባራት በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ ደንቡንና ህጉን ባገናዘበ መልኩ ቅጣት እንዲቀበሉ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ የማህበረሰቡ ኑሮ የተሳካና የበለጸገ እንዲሆን ይረዳል፡፡

ሁለተኛ ደግሞ ለእንዱስትሪ፣ ለንግድ ለግብርና፣ ለግንባታና ወ.ዘ.ተ. . . እንቅስቃሴዎች የተመቻቸ ሁኔታ ይኖር ዘንድ ለሰላምና መረጋጋት ተግቶ ይሰራል፡፡ ኢስላም ለእድገትና ብልጽግና ስኬት በየፈርጁ ይሰራል፡፡ የሰው ልጅ ችሎታውን ሁሉ አውጥቶ ተግባር ላይ እንዲያውል ያበረታታል፡፡

---

[42] ገዋሊ አል-ሊኣሊ 4/61

[43]ቢሃር አል-አንዋር 1/21

የሰውን ልጅ ባህርይና ፍላጎት ይረዳል፡፡  ለምሳሌ ያህል ለሰው ልጆች የጋብቻን መንገድ ያገራል፤ ዝሙትን እርም ያደርጋል፤ የቤተሰብ ምስረታን ያወድሳል፤ በዘር መባዛትን ያበረታታል፡፡ የኢስላሙ ኡማ ከሁሉም የላቀ ኃይል እንዲኖረው ያበረታታል፡፡ የከርሰ ምድርና የውሃ ኃይል ጠቀሜታን ያበረታታል፡፡

**"ምድር የአላህና ለልማት ለሚያውሉት ነው**[44]፣  እንዲሁም "**ውሃ ቀድሞ ላቆረ/ለገደበና በጥቅም ላይ ላዋለ ነው፡፡"**

ሁሉም ሙስሊም በተቻለው መጠን የተፈጥሮ ጸጋዎችን በመጠቀም ለልማትና ለዕድገት መልፋት ከመሬት የቻለውን ያህል በመጠቀም በእርሻና መሰል የልማት ስራዎች የበለጸገ ኑሮ የመኖር መብት አለው፡፡

ለልማትና ስራ ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ በኢስላም ሀገሮች መካከል ድንበር አያስቀምጥም፤ ሁሉም ሙስሊሞች እንደፈለጉ በመንቀሳቀስ ሁሉም ቦታ ላይ መስራትና መኖር ይችላሉ፡፡ ሙስሊሞች በሙሉ በአላህ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ በኢስላም ውስጥ ወገንተኝነት፣ ክልል፣ ወረዳ፣ ብሄርተኝነትና ዘረኝነት የለም፡፡ ይህ በተለያየ የህይወት አውታሮች የመላው ሺዓ የአስተሳሰብ መሰረቶች ናቸው፡፡ ይህ ሙስሊሞች ከፍተኛውን የእድገት ጣራ በተቆናጠጡበት በወርቃማው ዘመን የተዘረጉ መስመሮች ናቸው፡፡ ያኔ ደመና ከፍታቸውን ማገድ የተሳነው ዘመን፣ ስፋታቸውን ደመና ሊጋርድ ያልቻለበት ዘመን!

[44]አል-ኢስቲብሷር 3፡108- ክፍል 76- ሐዲስ 52

## 3. ኢስላማዊ ኒዛም (ሥርዓት) በሺዓ እይታ

ሥርዓት ሲባል የሰውን ልጅ ህይወት ከመወለዱ በፊት አንስቶ ከሞት በኋላ እስካለው ሕይወቱ ድረስ የሚመራ ሁለንተናዊ ህግና ደንብ ማለት ነው፡፡ ሺዓዎች የሚያምኑት ይህ ኢስላማዊ ስርዓት ማህበረሰቡን ያደራጃል፤ ለምድራዊ ልማት ቦታ ይሰጣል፤ ሕይወት ይሰጣል፤ ለሰው ልጆች ዓለማዊና መንፈሳዊ ደስታ ይተጋል፡፡ የሰው ልጅ በዚህኛው ዱኒያ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው የአኺራ ዓለም ደስተኛና የበለጸገ ሆኖ እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ የተሟላ ህግና ደንብ አለው፡፡ የራሱ የሆነ የግብይት፣ የኪራይና አክስዮን ህግ፣ የንግድ ደንብና ህግ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ፣ የመከላከያ ኃይል (ወታደር)፣ የሀገር፣ የነዋሪነት፣ የደህንነት፣ የጋብቻ፣ የፍች፣ የፍትህ፣ የውርስ፣ የዝምድና ወ.ዘ.ተ... ህግጋትና መመሪያ ያለው ምሉዕ የሆነ ስርዓት መሆኑን ያምናሉ፡፡ የኢስላምን ሁለንተናዊነት፣ በሁሉም የህይወት አውታር ውስጥ እጅ ያለው ስለመሆኑና ለእያንዳንዱ የሰው ልጆች ፍላጎት ጥሪ ምላሽ የሚሰጥ ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ቁርዓናዊ አንቀጾችንና ሱናዎችን ለዋቢነት እንጠቅሳለን፡፡

### 1. ዐቂዳ (እምነት)

አላህ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

**قُولُوا آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنْزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنْزِلَ إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِنْ رَبِّهِمْ**

***“በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን)፣ ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ አስባጥም (ነገዶቹም) በተወረደው በዚያም ሙሳ እና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት በተሰጡት አምነናል በሉ፡፡”[45]***

## 2.ዒባዳ (አምልኮ)

አላህ በተከበረው ቁርዓኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ***

***“ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡”***

## 3. ሰቃፋህ (ትምህርት)

አላህ በቁርኣኑ ውስጥ እንዲህ ይላል ፡-

***هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُولُو الْأَلْبَابِ***

***“እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይተካከላሉን? በላቸው፤ የሚገነዘቡት ባለ አእምሮዎቹ ናቸው።”[46]***

እንዲሁም በሐዲስ፡-

“ዕውቀትን መፈለግ በሁሉም ሙስሊሞች ላይ ሴትም ሆነ ወንድ ግዴታ ነው፡፡”[47]

## 4. እኩልነት፡-

ከማይገባው ሁሉ የጠራው ጌታ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡፡

---

[45] አል-በቀራህ፡ 136

[46] አል-ዙመር፡ 9

[47] ሙስተድረክ አል-ወሳኢል -ቅጽ 17- ገጽ 249- ክፍል 4- ሐዲስ 21250

***إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ***

***"አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡"[48]***

በሐዲስ ደግሞ **"ሰዎች እንደ ማበጠሪያ ጥርሶች እኩል ናቸው"[49]**

## 5. ሰላም

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا ادْخُلُوا فِي السِّلْمِ كَافَّةً وَلَا تَتَّبِعُوا خُطُوَاتِ الشَّيْطَانِ إِنَّهُ لَكُمْ عَدُوٌّ مُبِينٌ***

***"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም በመታዘዝ (ወደ ኢስላም/ሰላም) ግቡ፡፡ የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፤ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና፡፡"[50]***

## 6. ክብር (ሉዓላዊነት)

***وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُمْ مِنَ الطَّيِّبَاتِ***

**"የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፤ በየብስም በባሕርም አስሳፈርናቸው፤ ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው፡፡"[51]**

---

[48] አል-ሑጁራት፡ 13

[49] ቢሓር አል-አንዋር 78/ 251

[50] አል-በቀራ፡ 208

[51] አል-ኢስራእ፡ 70

## 7. ንግድ

ከሁሉ በላይ የላቀው አላህ እንዲህ ይላል፡-

***يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ إِلَّا أَنْ تَكُونَ تِجَارَةً عَنْ تَرَاضٍ مِنْكُمْ***

**እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ፤ አርስ በርሳችሁ ወዳችሁ ፈቅዳችሁ የሆነችውን ንግድ ካልሆነ በስተቀር፡፡"[52]**

## 8. ፖለቲካ

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***وَأَمْرُهُمْ شُورَىٰ بَيْنَهُمْ***

**"ጉዳዮቻቸውን በመካከላቸው በመመካከር (የሚወስኑ የሆኑ)..."[53]**

በሐዲስ ደግሞ፡- **"ለሰዎች መሪና  ተምሳሌት የሆኑ..."[54]**

## 9. ወታደራዊ ኃይል

አላህ በቁርዓኑ እንዲህ ይላል፡-***وَأَعِدُّوا لَهُمْ مَا اسْتَطَعْتُمْ مِنْ قُوَّةٍ***

**"ከኃይልም የቻላችሁትን ያህል አዘጋጁላቸው፡"[55]**

---

[52]አል-ኒሳእ፡ 29

[53]አል-ሹራ፡ 38

[54]አል-ዱዓእ ወ አል-ዚያራ ገጽ 995- ዚያራ አል-ጀሚዓህ አል-ከቢራህ

[55] አል-አንፋል፡ 60

## 10. የጠፍር ጉዞ

ልቅና የተገባው አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**يَا مَعْشَرَ الْجِنِّ وَالْإِنْسِ إِنِ اسْتَطَعْتُمْ أَنْ تَنْفُذُوا مِنْ أَقْطَارِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ فَانْفُذُوا لَا تَنْفُذُونَ إِلَّا بِسُلْطَانٍ**

***"የጋኔንና የሰው ጭፍሮች ሆይ! ከሰማያት እና ከምድር ቀበሌዎች መውጣትን ብትችሉ ውጡ፡፡ በስልጣን (በእውቀት) እንጂ አትወጡም፡፡"[56]***

እንዲሁም በሐዲስ ውስጥ ፡-

"ዕውቀት እጅግ ሩቅ በሆነው ኮከብ (ሱረያ) ውስጥ የሚገኝ ቢሆን እንኳ እዛም ደርሰው የሚቀስሙ ሰዎች ይኖራሉ"[57]

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ ፡-

"ከምድር መንገዶች ይልቅ የሠማይ መንገዶችን የበለጠ አውቃለሁ፡፡"[58]

## 11.ፍቅር

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**وَجَعَلَ بَيْنَكُمْ مَوَدَّةً وَرَحْمَةً**

**"በመካከላቸው ፍቅርና ምህረትን/መተዛዘንን/ አደረገ፡፡"[59]**

---

[56] አል-ረህማን፡ 33

[57] ቁርብ አል-አስናድ፡ 52

[58] ቢሓር አል-አንዋር፡ 39/ 108- ክፍል-76 -ሐዲስ-13

[59] አል-ሩም፡ 21

## 12. ነጻነት

ከማይገባው ሁሉ የጠራው አላህ በቁርአኑ ውስጥ የነብዩን (ሶ) ስብዕና ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

**وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ**

**"ሸክማቸውንና በላያቸው ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች ያነሳላቸዋል፡፡"[60]**

በሐዲስ ደግሞ ፡-

"ከማንነትህ ወዲያ ባሪያ (የተዋረድክ) ሌላ ሰው አትሁን፣ አላህ ነጻ አድርጎ ፈጥሮሃልና፡፡"[61]

በኢስላማዊ መርህ (ቃዒዳ) መሰረት ደግሞ፡-

"ሰዎች ንብረታቸውና በራሳቸው ላይ ሙሉ ስልጣን አላቸው፡፡"[62]

## 13. ወንጀል መከላከል

**"ድንበር አትለፉ (ግፍ አትፈጽሙ)[63]፡፡"** **وَلَا تَعْتَدُوا**

እንዲሁም በሌላ የቁርአን አያህ፡-

**فَمَنِ اعْتَدَىٰ بَعْدَ ذَٰلِكَ فَلَهُ عَذَابٌ أَلِيمٌ**

**"ከዚህ ወዲያ ድንበር የሚያልፍ /ግፍ የሚፈጽም/ ሰው አሳማሚ የሆነ ቅጣት አለለት፡፡"[64]**

---

[60] አል-አዕራፍ፡ 157)

[61] ሙስተድረክ አል-ወሳኢል፡ 8/231- ክፍል 33- ሐዲስ 8116)

[62]

[63] አል-በቀራህ፡ 190፤ አል መዒዳህ፡ 87

[64] አል-በቀራህ፡ 178፣ አል-ማኢዳህ፡ 94

በሌላ የቁርአን አያህ እንዲሁ፡-

***إِنَّمَا جَزَاءُ الَّذِينَ يُحَارِبُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَيَسْعَوْنَ فِي الْأَرْضِ فَسَادًا أَنْ يُقَتَّلُوا أَوْ يُصَلَّبُوا أَوْ تُقَطَّعَ أَيْدِيهِمْ وَأَرْجُلُهُمْ***

***"የነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ፣ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት፣ መገደል፣ ወይም መሰቀል፣ ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን መቆረጥ..."[65]***

## 14. ንጽህና /ጽዳት

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ التَّوَّابِينَ وَيُحِبُّ الْمُتَطَهِّرِينَ***

***"አላህ ወደሱ ተመላሾችን (ተውባ የሚያደርጉትንና) የሚጥራሩትን (ንጽህናቸውን የሚጠበቁትን) ይወዳል፡፡"[66]***

በሐዲስ ውስጥ ደግሞ፡-

"ንጽህና ከኢማን (እምነት) ነው (ይቆጠራል)፡፡"[67]

## 15. ውበት

አላህ በቁርአኑ እንዲሁ ይለናል፡-

***خُذُوا زِينَتَكُمْ عِنْدَ كُلِّ مَسْجِدٍ***

***"ጌጣቻችሁን በየመስገጃው ሁሉ ያዙ፡፡"[68]***

---

[65] አል-ማኢዳህ፡ 33

[66] አል-በቀራ፡ 222

[67]ሙስተድረክ አል-ወሳኢል 16/ 319- ክፍል 92- ሐዲስ 20016

በሐዲስ ደግሞ፡-

"አላህ ፍጹም ውብ ነው፣ ውበትንም ይወዳል፡፡"[69]

## 16.ጤና

አላህ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***وَكُلُوا وَاشْرَبُوا وَلَا تُسْرِفُوا***

**"ብሉ ጠጡም፣ አታባክኑ/መጠን አትለፉ፡፡"[70]**

በሐዲስ ውስጥ ደግሞ ፡-

"ጹሙ፣ ጤናማም ትሆናላችሁ፡፡"[71]

"ሐጅ አድርጉ፣ ጤናማም ትሆናላችሁ፡፡"[72]

ተጓዙ፣ ጤናማም ትሆናላችሁ"[73]

## 17. ከተፈጥሮ ኃይሎች መጠቀም

አላህ በቁርአን ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

**وَسَخَّرَ لَكُمُ الشَّمْسَ وَالْقَمَرَ دَائِبَيْنِ وَسَخَّرَ لَكُمُ اللَّيْلَ وَالنَّهَار وَآتَاكُمْ مِنْ كُلِّ مَا سَأَلْتُمُوهُ**

---

[68] አል-አዕራፍ፡ 31

[69] አል-ካፊ 6 /438- ሐዲስ-1

[70]አል-አዕራፍ፡ 31

[71] ሙስተድረክ አል-ወሳኢል ቅጽ- 7 ክፍል1- ሐዲስ- 8744

[72]ወሳኢል አል-ሺዓ- ቅጽ 1- ክፍል 1- ሐዲስ 14126

[73] መንላ የህድሩሁ አል-ፊቂህ 2/265 -ክፍል2- ሐዲስ 2387

***"ፀሐይንና ጨረቃንም ዘወትር ውቸራዋህምበ  የሚዞሩ ሲሆኑ ለናንተ አገራላችሁ፤ ሌሊትና ቀንንም አገራላችሁ። ከለመናችሁትም ሁሉ ሰጣችሁ፡፡"[74]***

## 18. እርቅና መግባባት

አላህ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***وَالصُّلْحُ خَيْرٌ***

***"መታረቅም መልካም ነው፡፡"[75]***

***وَإِنْ طَائِفَتَانِ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ اقْتَتَلُوا فَأَصْلِحُوا بَيْنَهُمَا***

**"ከአማኞች የሆኑ ሁለት ቡድኖች ቢጋደሉ /ቢጣሉ በመካከላቸው እርቅን አውርዱ /አስታርቋቸው፡፡"[76]**

***إِنْ يُرِيدَا إِصْلَاحًا يُوَفِّقِ اللَّهُ بَيْنَهُمَا***

**"ሁለቱ (ቡድኖች) እርቅን ከፈለጉ አላህ እንዲሳካላቸው ያደርጋል፡፡"[77]**

---

[74] ኢብራሂም፡ 33-34

[75] አል-ኒሳእ፡ 128

[76] አል-ሑጅራት፡ 9

[77] አል-ኒሳእ፡ 35

## 19. መተጋገዝ/መተባበር/ መደጋገፍ

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላ፡-

**وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَىٰ**

**"በመልካም ተግባርና (አላህን) በመፍራት ላይ ተጋገዙ፡፡"[78]**

## 20. አንድነት

አላህ በቁርአን ውስጥ ሲናገር፡-

**وَإِنَّ هَٰذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً**

**"ይህች ኡማችሁ አንዲት ኡማ/ህዝብ ናት፡፡"[79]**

**وَلَا تَفَرَّقُوا**

**"አትለያዩ!"[80]**

**وَلَا تَنَازَعُوا فَتَفْشَلُوا وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ**

**"አትጨቃጨቁም፤ ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና፡፡"[81]**

## 21. ሥራ

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

---

[78] አል-ማኢዳህ፡ 2

[79] አል-ሙእሚኑን፡ 52

[80] ኣሊ-ዒምራን፡ 103

[81] አል-አንፋል፡ 46

وَقُلِ اعْمَلُوا

**“ስሩ በላቸው!”[82]**

በሐዲስ ውስጥ ደግሞ፡-

**"ለቤተሰቡ ኑሮ የሚተጋ በአላህ መንገድ ውስጥ እንደሚታገል ታጋይ ነው፡፡ "[83]**

## 22. ትሩፋትና መልካም ስብዕና

ከማይገባው ሁሉ የጠራው አላህ የነብዩን (ሶ) ሁናቴ በተመለከተ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ

**“የሚያጠራቸው፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው…”[84]**

وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ

**"አንተማ እጅጉን ከፍ ካለ ስነ-ምግባር በላይ ነህ፡፡"[85]**

ከነብዩ (ሶ) በተያዘ የተከበረ ሐዲስ ውስጥም፡-

**"እኔማ የተላኩት መልካም ስብዕናዎችን ፍጹምና ምሉዕ ለማድረግ ነው"፡፡[86]**

---

[82] አል-ተውባህ፡ 105

[83] ሙስተድረክ አል-ወሳኢል 8/ 378- ክፍል 4- ሐዲስ 8462

[84]አሊ ዒምራን፡ 164፣ አል-ጁምዓ፡ 2

[85] አል-ቀለም፡ 4

## 23.መረጋጋትና አለመጨነቅ

አላህ በተከበረው ቁርአን ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

**أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ**

**"እነሆ ልብ መረጋጋትን የምታገኘው አላህን በማስታወስ (በአላህ ዚክር) ነው"፡፡[87]**

**وَمَنْ يُؤْمِنْ بِاللَّهِ يَهْدِ قَلْبَهُ**

**"በአላህም የሚያምን ሰው ልቡን ይመራዋል፡፡"**

## 24. ፍትህና እኩልነት

አላህ በቁርአን ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

**وَإِذَا قُلْتُمْ فَاعْدِلُوا**

**"ባላችሁ ጊዜ (የምትሉትን) በፍትህ በሉ"፡፡[88]**

**كُونُوا قَوَّامِينَ بِالْقِسْطِ**

**"ለፍትህና እኩልነት የምትቆሙ ሁኑ!"[89]**

**إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ**

**"አላህ በፍትህና በመልካምነት ያዝዛል፡፡"[90]**

---

[86] ሙስተድረክ አል-ወሳኢል 11/ 1871- ክፍል 6- ሐዲስ 1280

[87] አል-ረዕድ፡ 28

[88] አል-አንዓም፡ 152)

[89]አል-ኒሳእ፡ 135

## 25. ኃላፊነትና ህዝባዊ ግዴታ

አላህ በቁርአኑ ውስጥእንዲህ ይላል፡-

**وَلْتَكُنْ مِنْكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى الْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ**

**“ከናንተም ወደ በጐ ነገር የሚጠሩ፣ በመልካም ሥራም የሚያዙ፣ ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ህዝብ ትኑር።”[91]**

በሐዲስ ደግሞ ፡-

"ሁላችሁም ጠባቂዎች (ኃላፊነት ያለባችሁ) ናችሁ፡፡ ሁላችሁም ደግሞ ስለ ኃላፊነታችሁ ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡"[92]

## 26. ግንባር-ቀደምነት

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ**

**"በበጎ ተግባር ላይ ተሽቀዳደሙ"፡፡”[93]**

በሐዲስ ደግሞ ፡-

---

[90] አል-ነህል፡ 90

[91] ኣሊ ዒምራን፡ 104

[92]ቢሓር አል-አንዋር 75/38- ክፍል 35- ሐዲስ 36

[93]አል-በቀራ፡ 148፣ አል-ማኢዳህ፡ 48

"ቀኑ ተመሳሳይ የሆነበት ሰው (አንዱ ቀን ከሌላው ቀን ምንም ለውጥ ሳያመጣበት ተመሳሳይ የሆነበት ሰው) የታለለና ደካማ ሰው ነው፡፡"[94]

## 27. በሁሉም ነገር መካከለኛ/ አማካይ መሆን (ከጽንፈኝነት መጽዳት)

ከማይገባው ሁሉ እጅጉን የጠራው አላህ በቁርአኑ፡-

**وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَاكُمْ أُمَّةً وَسَطًا**

**"እንደዚሁ (ከጽንፈኝነት የጠራ) መካከለኛ ኡማ/ህዝብ አደረግናችሁ፡፡"[95]**

## 28. ሀብት/ንዋይ

አላህ በተከበረው ቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**وَلَوْ أَنَّ أَهْلَ الْقُرَىٰ آمَنُوا وَاتَّقَوْا لَفَتَحْنَا عَلَيْهِم بَرَكَاتٍ مِّنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ**

**"የከተማዋም ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ፣ በነርሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር፡፡"[96]**

በሐዲስ ደግሞ

"ሀብት በዲን ላይ ምንኛ ያማረ ድጋፍ ነው!"[97]

---

[94] ሼክ ሰዱቅ -አማሊ፡- 393

[95] አል-በቀራህ፡ 143

[96] አል-አእራፍ፡ 96

[97] ቢሃር አል-አንዋር 74/155- ክፍል 7- ሐዲስ 1

## 29. ማህበራዊ መደጋገፍና ደህንነት

አላህ በቁርአን ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***وَاعْلَمُوا أَنَّمَا غَنِمْتُمْ مِنْ شَيْءٍ فَأَنَّ لِلَّهِ خُمُسَهُ***

**"ከማንኛውም ነገር ከምታገኙት (ከማረካቻችሁት ገቢ) አንድ አምስተኛው ለአላህ መሆኑን እወቁ[98]...፡፡"**

***إِنَّمَا الصَّدَقَاتُ لِلْفُقَرَاءِ وَالْمَسَاكِينِ***

**"ሰደቃ ብሎ ማለት ለደሃዎችና ለሚስኪኖች ነው[99]፡፡"**

## 30. ገርነትና ይቅርባይነት

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***وَأَنْ تَعْفُوا أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ***

**"ይቅር መባባላችሁ ለ (አላህ) ፍራቻ የቀረበ ነው[100]፡፡"**

## 31. ስልጣኔ

አላህ በቁርአኑ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

***هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا***

---

[98] አል-አንፋል፡ 41

[99] አል-ተውባህ፡ 66

[100] አል-በቀራህ፡ 237

**“እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡”[101]**

**وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا**

**“እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡”[102]**

በሐዲስ ደግሞ፡-

**"በእውቀት የተካናችሁ ሁኑ /እወቁ! አለበለዚያ ገጠሬና ደንቆሮ ሁናችሁ ትቀራላችሁ፡፡"[103]**

## 32. *ሕይወት*– እንደ ቃሉ በ ሙሉ ትርጉሙ

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اسْتَجِيبُوا لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمْ لِمَا يُحْيِيكُمْ**

**“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሕያው ወደሚያደርጋችሁ (እምነት) በጠራችሁ ጊዜ ለአላህና ለመልክተኛው ታዘዙ፡፡”[104]**

---

[101] ሁድ፡ 61

[102] አል- ሑጅራት፡ 13

[103] ቢሓር አል-አንዋር 78/346-ክፍል 26- ሀዲስ 4

[104] አል-አንፋል፡ 24

## 33. ዱኒያ እና አኺራ

**(ምድራዊ ህይወትና የወዲያኛው ዓለም ህይወት)**

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**وَمِنْهُمْ مَنْ يَقُولُ رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي الْآخِرَةِ حَسَنَةً**

**"ከነርሱም ጌታችን ሆይ በዚች ምድርም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ህይወት በጎውን ስጠን የሚሉ አሉ[105]፡፡"**

በሐዲስ ደግሞ፡-

"ለምድራዊ ኑሮህ ዘላለም እንደምትኖር አድርገህ ስራ፤ ለወዲያኛው ዓለም ኑሮህ ደግሞ ነገ እንደምትሞት አድርገህ ስራ[106]፡፡"

## 34. ለሁሉም ነገር ምሉእ የሆነ ህግና መመሪያ መኖሩ

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላ፡-

**الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي**

**"በዛሬው እለት ኃይማኖታችሁን ምሉዕ አደረግኩላችሁ፤ ጸጋየንም በናንተ ላይ ሞላሁ[107]"፡፡**

**وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِكُلِّ شَيْءٍ**

---

[105] አል-በቀራህ፡ 201

[106] መን ላ የህዱሩሁ አል-ፊቂህ 3/156- ክፍል 2- ሐዲስ 3369

[107] አል-ማኢዳህ፡ 3

**"ለሁሉም ነገር ማብራሪያ የሆነውን መጽሀፍ በአንተ ላይ አወረድን፡፡"[108]**

## 35. ኢንዱስትሪ

ከአሚረል ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ)፡-

**"ለነጋዴዎችና አምራቾች /ባለ ኢንዱስትሪዎች አበረታች ምክር ለግስ፣ በመልካምም ምከራቸው፡፡"[109]**

እንዲሁም በሌላ ሀዲስ፡-

**"መላው ማህበረሰብ ያለነጋዴዎችና ባለኢንዱስትሪዎች ቀጣይነት አይኖራቸውምና፡፡"[110]**

## 36. እርሻ

በሐዲስ፡-

**"ገበሬዎች (አምራቾች) በምድር ውስጥ የአላህ ግምጃ ቤቶች ናቸው፡፡"[111]**

---

[108] አል-ነህል፡ 89

[109] ነህጁል በላጋ- ኪታብ 53

[110] ነህጁል በላጋ- ኪታብ 53

[111] ተህዚብ አል-አህካም 6/384- ክፍል22- ሐዲስ 259

## 37. ግንባታና ልማት

በነህጅ አል-በላጋ ውስጥ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡-

**"መሬት ማልማት ላይ ያለህ ሀሳብና ትኩረት የመሬት ግብር ለመሰብሰብ ካለህ ጉጉት በላይ ሊሆን ይገባል፡፡"[112]**

## 38. ዕቅድና ሥርዓት

**"በአላህ ይሁንባችሁ! ጉዳያችሁን በማቀድና ስርዓት በማስያዝ ላይ ትኩረታችሁን አድርጉ!"[113]**

እንዲሁም፡-

**"አላህን በመፍራትና ጉዳያችሁን በማቀድ ላይ አደራ እላችኋለሁ"[114]**

## 39. በመንግስት (ህጋዊ መሪ) እና ህዝቡ መካካል ወዳጅነትና ውዴታ መኖር

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنْكُمْ**

**"አላህና መልእክተኛውን እንዲሁም ከናንተ የሆኑ የአምር ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡"[115]**

---

[112]ሙስተድረክ አል-ወሳኢል 13/166- ክፍል 42- ሐዲስ 15018

[113] ነህጅ አል-በላጋ- ኪታብ 48

[114] ነህጅ አል-በላጋ- ኪታብ 48

[115]አል-ኒሳእ፡ 59

በነህጁል-በላጋ ውስጥ ደግሞ ፡-

**"በስርህ ላሉት (ለምታስተደድራቸው ሁሉ) ልብህ ርህራሄ ያሳይ!"[116]**

እንዲሁም፡-

**"ለተገዢዎችህ ልብህ ይራራ፣ ፍቅርና ሐዘኔታም ይኑርህ! ምግባቸውን የምትዘርፍ ስግብግብ አውሬ አትሁንባቸው፡፡"[117]**

በመጨረሻም፡-

## 40. ሁለገብነት/ዓለም አቀፋዊነት

አላህ በተከበረው ቁርአን ውስጥ እንዲህ ይለናል፡-

**وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِلْعَالَمِينَ**

**"ለሁሉም ዓለማት ረህመት (ምህረትና እዝነት) እንጂ ለሌላ አላከንህም፡፡"[118]**

**وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا كَافَّةً لِلنَّاسِ**

**"ለመላው የሰው ዘር እንጂ አላከንህም"[119]**

በሐዲስ ውስጥ ደግሞ፡-

**(ሰዎች) ሁለት ዓይነት ናቸው፡- አንድም በሐይማኖት ወንድሞችህ ናቸው፣ አለያም እንዳንተው ሰብዓዊ ፍጡሮች ናቸው፡፡[120]**

---

[116] ነህጅ አል-በላጋ- ኪታብ 53

[117] ነህጅ አል-በላጋ- ኪታብ 53

[118] አል-አንቢያእ፡ 108)

[119] ሰበእ፡ 28

እንዲህ ነው እንግዲህ ሺዓዎች ነብዩ (ሶ) እና አህለልቤይቱ (ዐ) ያስተማሩትንና ያሳዩትን ኢስላም በተጨበጭና በተግባር ተቀብለው የዲኑ አርአያ ሆነው የሚገኙት፡፡ ያኔም ነው ሺዓ የሚሆኑት፡፡ በቁርአንና በነብዩ (ሶ) ሱና ውስጥ ለተጠቀሰው ጉዳይ ሁሉ ተጨባጭ አርአያና ማሳያ ናቸው፡፡ ለራሱም ሆነ ለማህበረሰቡ በጎ የሚመኝ ሰው በሙሉ በኢስላማዊ ቡድኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለማከሰም የተቻለውን ሁሉ ማድረግና ኢስላማዊ ሥርዓት ዳግም እንዲያንሰራራ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በሙሉ ማድረግና አሁን ባለንበት ዘመን ተጨማጭ ሥርዓት ለማስፈን መትጋት ግዴታ ይሆናል፡፡

*ወደ ትክክለኛው ጎዳና የሚመራው እሱ አላህ ነው!!*

---

[120] ነህጁል በላጋ- ኪታብ 53

# የሺዓ እምነት መርሆዎች/ሙዕተቀዳት

## የሺዓ ዐቂዳዎች

የሺዓ ዓቂዳ ከሁለቱ የኢስላም ወጥ ምንጮች የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህም፡- **የአላህ ኪታብና ሱና** ሲሆኑ በሚከተሉት ጽንሰ ሃሳቦች ውስጥ ተጠቃለው ይገኛሉ፡፡

### *ተውሂድ*

እኛ ሺዓዎች  ጌታችን አላህ እንደሆነ እናምናለን፤ ይህን በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ከቅንጣጢት እስከ ግዙፍ ፍጥረታት ያቀፈ ዓለማትን የፈጠረ የሁሉም ነገር አስገኝ መሆኑን እናምናለን፡፡ ከነዚህም ዉስጥ መሬትን በሺዎች እጥፍ የምትበልጠዋን ጸሐይን ስድስት ሚሊዮን ግዜ የሚበልጡ እጅግ የገዘፉ ከዋከብት ይገኙበታል፡፡

አላህ ማለት አንዳችም ሸሪክ የሌለው፣ በትእዛዛቱም ሆነ በተግባራቱ ፍትህ የሆነ፣ ቋሚና ዘላለማዊ፣ ህያው እና በጊዜ የማይገደብ፣ ሁሉን አዋቂና ሁሉን ቻይ፣ የፍጥረታት ሁሉ ህይወትና ሞት በእጁ የሆነ፣ የበጎ ነገር ሁሉ ባለቤትና በሁሉም ነገር ላይ ፍጹም ችሎታ ያለው አምላክ እንደሆነ እናምናለን፡፡

### *ኑቡዋህ/ነብይነት*

ሙሐመድ (ሶ) ነብያችን መሆናቸውን፣ አላህ ለዓለማት ሁሉ ምህረት የላካቸው መሆኑን፣ የመጨረሻውና መደምደሚያው ነቢይ መሆናቸውን፣ የተመረጠው የአላህ ሃይማኖት ይሆን ዘንድ ኢስላምን ይዘው ወደዚህ ዓለም የተላኩ መሆናቸውን፣ የሰው ልጆችን በዱኒያም ሆነ በአኺራ ጉዳዮቻቸው ወደ

ተሻለው መንገድ የሚመሩ ለሰዎች ምሪት የተመረጡ እንደሆኑና በተከበረችው መካ በነብይነት ከተላኩ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ነቢይ እንደሆኑ፣ የሳቸው ሃይማኖት ሌሎችን ሃይማኖቶች የሚሽር የፍጻሜው ቃል ኪዳን እንደሆነ እናምናለን፡፡

## ነቢያት (ዐ.ሰ)

በአቂዳችን ውስጥ ከነቢያት አምስቱ ዑሉልዓዝም ይባላሉ፡፡ ይህም ተልኳቸው ዓለምዓቀፋዊ ይዘት ያለው ነቢያት ናቸው፡፡ እነዚህም፡- ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳ እና ሙሐመድ (በሁላቸውም ላይ የአላህ ሰላትና ሰላም ይሁን) ናቸው፡፡ ነቢያት በሙሉ በአላህ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ ሁላቸውንም እናከብራለን፤ እንከተላለንም፡፡

***لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِنْ رُسُلِهِ***

**"ከመልእክተኞቹ በአንዳቸውም መካከል ልዩነት አናደርግም፡፡"[121]**

## ኢስላም

ኢስላም የሰው ልጆችን ከሁሉም ችግሮች ለማዳንና ለመጠበቅ፣ ሰዎች በዱኒያም ሆነ በአኺራ ብልጽግና ይጎናጸፉ ዘንድ ከሰማይ የወረደ የአላህ ሃይማኖት መሆኑን እናምናለን፡፡ በሁሉም የህይወት አውታሮች በኢስላም መርሆ መሰረት መስራት ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በጥበብ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች፣ በሰላም፣ በትግል… በሁሉም

[121] አል-በቀራህ፡ 285

የህይወትና ኑሮ እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በቤት፣ በት/ቤት፣ በመስሪያ ቤት… በሁሉም ቦታዎች ማንኛዉም ተግባርና አስተሳሰብ ኢስላም ባስቀመጠው ደንብና መመሪያ መሰረት መታየት እንዳለባቸውና ኢስላም የሁለንተናችን ሚዛን መሆኑን አምነን እንቀበላለን፡፡

ኢስላም በሁሉም ቦታና ዘመን የሰው ልጆችን ፍላጎትና ጥያቄ ያማከለ ፍጹም እና ምሉዕ ሥርዓት መሆኑን እናምናለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ቁርአኑ እንዲህ ይላል፡፡

***الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا***

**"እነሆ በዛሬው እለት ሀይማኖታችሁን ፍጹም ምሉዕ አደረኩላችሁ፤ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ሞላሁ፤ ከሃይማኖትም ኢስላምን ወደድኩላችሁ፡፡"[122]**

በኢስላም ውስጥ አንዳችም ጉድለትና ጎዶሎ የለም፡፡ ከሃይማኖቶች ሁሉ የላቀ ምሉዕ የሆነ የህይወት መስመር ነው፡፡ የሰው ልጆች ኢስላምን ቢተገብሩና በመመሪያው ጸንተው ቢኖሩ፡-

***لَأَكَلُوا مِنْ فَوْقِهِمْ وَمِنْ تَحْتِ أَرْجُلِهِمْ***

**“ከላያቸውም ሆነ ከእግሮቻቸው ሥር በተመገቡ ነበር (ከሰማይም ሆነ ከምድር በረከት ያለ ልፋት በተንበሸበሹ ነበር፡፡”[123])**

[122] አል-ማኢዳ፡ 3

[123] አል-ማኢዳ፡66

ኢስላም ማለት ከሱ ውጭ ሌላው ሁሉ ተቀባይነት የሌለው የሐቅ ኃይማኖት ነው፡፡ ከኢስላም ውጭ የሰው ዘር በዱኒያ ሀሴትን መቀዳጀት አይችልም፤ በአኺራም ነጃ ሊወጣ አይችልም፡፡ አላህም እንዲህ ይላል፡-

***وَمَنْ يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَنْ يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ***

**"ከኢስላም ውጭ ሌላ ሃይማኖት የሚሻ ሰው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በአኺራ እሱ ከከሳሪዎች ነው፡፡"[124]**

ኢስላም በአለማችን ላይ በአግባቡ ይተገበር ዘንድ ምኞታችን ነው፡፡

ኢስላም ለእያንዳንዱ የሰው ልጅች ፡-

-ትክክለኛ እምነትና አስተሳሰብን (ዐቂዳን)፣

-የግለሰብና የማህበረሰብ ነጻነትን፣

-የሰው ልጆችን ከድህነት፣ ከበሽታ፣ ከመኃይምነትና ወንጀል በማላቀቅ በህይወት ደስተኛ መሆንን፣

-በግለሰቦች፣ በቡድኖችና በህዝቦች መካከል አጠቃላይ ሰላም መስፈንን ያጎናጽፋል፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሁሉም ሰው የማሰብ ነጻነት፣ የመናገር ነጻነት፣ የመስራት ነጻነት፣ የመጓዝና የነዋሪነት ነጻነት፣ የመጻፍ ነጻነት ወ.ዘ.ተ. . . ይኖረዋል፡፡

---

[124] አሊ-ዒምራን፡ 85

ይህ ሁሉ ከጎዶሎ ሁሉ ከጠራው ኢስላማዊ መመሪያ የሚገኝ ትሩፋትና መብት ነው፡፡ ኢስላም ይሄ ነው፡፡

ኢስላም፡- 1. መሰረታውያን (**ኡሱል**)፣ 2. ቅርንጫፎች (**ፉሩዕ**)፣ 3. ህግጋት (**አህካም**)፣ እና 4. ስነ-ምግባራዊ ጉዳዮች (**አኽላቅ**) እንደሚያካትት እናምናለን፡፡ የዲኑን መሰረታውያን የሚያሳተባብል እና የሚክድ አካል ከሓዲና ነጃሳ ነው፡፡ ከተቀሩት 3ቱ ክፍሎች ሳያውቅና ተመሳስሎበት ካልሆነ በቀር አንድን ነገር የሚያስተባብልና የሚክድም ከሀዲ (ካፊር) ነው፡፡ ይህንን ዓይነት ክህደት (ጽኑ የሆኑ መሠረቶችን ማስተባበል */አል-ሙንክር ሊኢድ-ደሩሪ)* ይሉታል፡፡ የኢስላም አህካሞችን (ህግጋትን) በሀሳብ ደረጃ ተቀብሎ (ሳያስተባብል) ግና በግል ህይወቱ ውስጥ መተግበር የተሳነው ሰው ፋሲቅ (ከአላህ ራህመት የራቀ) ተኮናኝ ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

***وَمَنْ لَمْ يَحْكُمْ بِمَا أَنْزَلَ اللَّهُ فَأُولَئِكَ هُمُ الْفَاسِقُونَ***

**"አላህ ባወረደው (ህግጋት) የማይፈርዱ ሰዎች እነርሱ ፋሲቆች ናቸው፡፡"**[125]

የኢስላም መሰረታዊያን የምንላቸው፡- **ተውሂድ** (የአላህ አንድነትና አሐዳዊነት)፣ **ኑቡወህ** (ነቢይነት)፣ ትንሳዔ (**መዓድ**) ሲሆኑ ተውሂድን ተከትሎ ፍትህዊነት (**ዓድል**) እና ኑቡዋን ተከትሎ **ኢማማህ** (መሪነት፣ ዊላያ ወይም ኢማምነት) ናቸው፡፡

---

[125] አል-ማኢዳህ፡ 47

የዲን ቅርንጫፎች ወይም ተግባራት የሚባሉት ደግሞ:- ሶላት፣ ጾም፣ ኹሙስ (ከምናገኘው ገቢ አንድ አምስተኛውን ዲኑ በሚደነግገው መሰረት ለሚገባቸው አካላት መክፈል)፣ ዘካት፣ ሀጅ፣ ጂሃድ፣ በበጎ ተግባራት ማዘዝና ከእኩይ ተግባራት መከልከል፣ ለአላህና አውሊያዎቹ /መሪዎቹ/ኢማሞች) እጅ መስጠትና መታዘዝ/መወዳጀት (**ተወ**^**ሊ**) እና ከአላህ ጠላቶች እና ከአውሊያዎቹ ጠላቶች መጥራት (**ተበ**^**ሪ**) ናቸው ፡፡ እንዲሁም ከነዚህ ጋር የተገናኙ ሌሎች የዒባዳ ክፍሎችና ተግባራት -እንደ ወዱእ፣ ትጥበት (ጉሱል)፣ ተየሙም (ዉሃ በማይገኝበት ሁኔታና ሌሎች ተየሙም የሚያስከትሉ ነገሮች ሲከሰቱ በአፈርና ተያያዥነት ባላቸው ነገሮች ወዱእ እና ጉስል የመፈጸም ተግባር)፣ ኢዕቲካፍ (ለአምልኮ ተግባር በተመረጡ ቦታዎች የተወሰነ ግዜ ወስዶ መቆየት) እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

የኢስላም ህግጋታትና መመሪያዎች (**አህካም**) የምንላቸው ደግሞ ሌሎች የተቀሩትን ህግና መመሪያ የተደረገላቸውን ተግባራት የሚመለከት ሲሆን እንደ የግብይት/ንግድ መመሪያዎች (የግዥና ሽያጭ መመሪያዎች) የኪራይ፣ የፍች፣ የጋብቻ፣ የፍርድ፣ የምስክርነት፣ የውርስ፣ የካሳ፣ የሞርጊጅ (የመኖሪያ ቤት ክራይና ግዥ ጋር የተያያዙ መመሪያዎች)... የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ኢስላም አንድም ነገር ሳያስቀር ለሁሉም የሰው ልጅ ግለሰባዊና ማህበራዊ ፈርጆች በሙሉ ማብራሪያ እንዳለው እናምናለን፡፡ ስለ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ባህል፣ አርት፣ ጥበብ፣ አስተዳደግ፣ ማህበራት፣ ሰላምና እርቅ፣ ጦርነትና ትግል፣ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ ቤተሰብ፣ መንግስትና ሌሎች ሰው ልጆች ከውልደቱ እስከ

ሞቱ የሚያጋጥሙት ጉዳዮችን በሙሉ ያካተተና ሁሉም በኢስላም ውስጥ በግልጽ የተቀመጠ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ለሁሉም የተለየ አካሄድና ስርዓት እንዲሁም ፍትሃዊ የሆነ ህግጋትን የሚያስፈጽሙ ህገ ደንቦችን ያካተተ ሁለንተናዊ ስርዓት ነው፡፡ የሰው ልጅ ለዚህ አድሮ በተግባር ቢተረጉም በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ደስታና ብልጽግና ይጎናጸፍ ነበር፡፡ ይኸውም :-

**"ነብዩ(ሶ) ሐላል/ህጋዊ የተፈቀደ/ አድርገው የደነገጉትን ነገር እስከ ዕለተ ትንሳዔ ድረስ ሀላል ነው፣ ነብዩ(ሶ) ሐራም /ህገ ወጥ/የተከለከለ) አድርገው የደነገጉት ነገርም እስከ ዕለተ ትንሳዔ ድረስ ሀራም ነው፡፡"[126]**

## ቁርአን

መላው ሙስሊሞች በሌሊትም ሆነ በቀን የሚቀሩት/የሚያነቡት/ አል-ቁርአን አልከሪም (የተከበረው ቁርአን) መጽሃፋችን እንደሆነ እናምናለን፡፡

መላው ጂኖችና ሰዎች ተሰባስበውና ተረዳድተው የቁርኣን አምሳያ የሆነን (የመጨረሻ አጭሯን ሱራ እንኳ) መፍጠር የማይቻላቸው የነብዩ (ሶ) ተዓምር መሆኑን እናምናለን፡፡

ቁርኣን ማለት በአሁኑ ዘመን በሁለት ሽፋኖች መካከል የሚገኝ ይህ በግልጽ የሚታወቀው መጽሐፍ ሲሆን በመላው ዓለም ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በሁሉም ቦታ ተሰራጭቶ የሚገኝ፣ በቀንና፣ በሌሊት በየቤቱ፣ በየመስጅዱ፣ በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎችም የመረጃ ዘርፎች የሚደመጥ ዕውቅ ሰማያዊ ኪታብ ነው፡፡ ከመበረዝ፣ ከመቀየር፣ ከመቀነስና መጨመር

---

[126] በሳኢር አል-ዲን -ገጽ 148፣ ክፍል 13፣ ሀዲስ7

የጠራ ነው፡፡ አንዷትንም ፊደል መቀነስና መጨመር አልተቻለቸውም፡፡ ይህንንም በማስመልከት አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

**إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ**

**"እኛ ራሳችን ዚክርን (ቁርኣንን) አወረድን፣ እኛ ጠባቂዎቹም ነን፡፡"[127]**

ቁርኣን በዚህ አኳኋን መሰብሰቡን እናምናለን፡- የመጀመሪያው ሱራህ አል-ፋቲሓ (የመክፈቻይቱ ምዕራፍ)፣ የመጨረሻው ሱራ አል-ናስ (ቁል አዑዙ ቢረብ አል-ናስ) ነው፡፡ ይህም የሆነው በነብዩ (ሰ) ዘመን በአላህ(ሱ.ወ) ትዕዛዝ፣ በመልክተኛው (ሰ) አማካይነት ሳይበረዝና ሳይቀየር፣ ቅደም ተከተሉ ሳይዛነፍ አሁን ባለበት ሁኔታ የተሰበሰበ መሆኑን እናምናለን፡፡ አንዳንዶች እንደሚሉት ከነብዩ (ሰ) ህልፈት በኋላ ነው የተሰበሰበው የሚለው አስተሳሰብ ትክክል አይደለም፡፡

መላው የሰው ልጅ ከመሃይምነት ጨለማ፣ ከድህነትና ወንጀል ተላቀው ወደ እውቀት ብርሃን፣ ወደ ሀቅና ደስታ ይመሩ ዘንድ አላህ (ሱ.ወ) በመልክተኛው ሙሐመድ ቢን አብደላህ (ሰ) ላይ ያወረደው የመጨረሻው ሰማያዊ መጽሃፍ ነው፡፡ ሸሪዓው የተደመደመበት፣ እስከቂያማ ቀን ድረስ ለመላው የሰው ልጅ መመሪያነት የተሰጠ የህይወት መጽሀፍ ነው፡፡

ቀደምት ሙስሊሞች የህይወት መመሪያ አድርገው በመያዝ በተግባር ስለተጠቀሙበት የአሸናፊነትና የብልጽግና ምንጫቸው ነበር፡፡

---

[127] አል-ሂጅር፡ 9

የዚህ ዘመን ሙስሊሞችም እድገት፣ ስልጣኔን እና ተቀዳሚነትን ከፈለጉ ቁርኣንን የህይወት መመሪያ አድርገው ተረድተው በተግባር መተርጎም ግድ ይላቸዋል፡፡ ይህንን ካላደረጉ ግን በጥመትና በፈርጀ ብዙ የችግር አረንቋ ዉስጥ ይዘፈቃሉ፡፡

***وَمَنْ أَعْرَضَ عَنْ ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنْكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ***

**"ከእኔ ዝክር (ቁርኣን) ያፈነገጠ አነሆ የተወሳሰበ (የተጨናነቀ) ኑሮ አለለት፡፡ የቂያማ ቀንም ዕውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን፡፡"[128]**

ሺኣዎች ለቁርኣን ትልቅ ትኩረት አላቸው፤ ቁርኣንን በመማር፣ በተጅዊድ (ቁርኣንን ደንቡንና ህጉን ጠብቆ በሚፈለገው መልኩ አሳምሮ መቅራት)፣ በተፍሲር (ትርጉምና ትንታኔ)፣ በሂፍዝ (በሽምደዳ በልብ በመያዝ)፣ በተግባር በመተርጎም፣ የሙጥኝ ብሎ በመያዝና የሚገባውን ክብር በመስጠት… የጠለቀ ትኩረትና ቦታ ይሰጡታል፡፡ ለቁርዓን ሂፍዝ አጅግ በርካታ ት/ቤቶችና ማዕከላት አላቸው፡፡ መንህጆቻቸውም (አካሄዳቸውና ግባቸውም) ቁርኣንን በህይወታቸው ውስጥ መተግበርና መላውን ዓለም ወደሱ መጥራት ነው፡፡

## ቂብላ

ቂብላ የተከበረው ካዕባ መሆኑን ወደ ከዕባ አቅጣጫ ውጭ መስገድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እናምናለን፡፡

---

[128] ጧሓ፡ 124

# ኢማማህ

የአላህ መልክተኛ (ሰ) ኸሊፋወች (ተተኪ መሪዎች) ነብዩ እራሳቸው በአላህ ትዕዛዝ መሰረት በነስ (በቃል ማስረጃ) ለይተው ያስቀመጧቸው አስራ ሁለት ኢማሞች መሆናቸውን እናምናለን፡፡[129]

ነብዩ (ሰ) እንዲህ ብለዋል፡-

**"የዘመኑን ኢማም ሳያውቅ የሞተ ሰው የጃህልያ ሞት ነው የሞተው፡፡"[130]**

እንዲሁም ነብዩ (ሰ) እንዲህ ብለዋል፡-

"ከኔ በኋላ አስራ ሁለት ኸሊፋዎች ይሆናሉ (ይነሳሉ)"

*(ለዚህ ሐዲስ ቀደም ሲል የተዘረዘሩትን ማጣቀሻዎች ደግመው ይመልከቱ)*

የአስራ ሁለቱ ኢማሞች ስም ዝርዝርም እንደሚከተለው ነው፡-

1. *አሊ ቢን አቡ ጧሊብ- አሚር አል-ሙእሚኑን (0)*
2. *ሐሰን ቢን አሊ- አል-ሙጅተባ (0)*
3. *ሑሴይን ቢን አሊ- ሰይድ አሽ-ሹሃዳእ (0)*
4. *ዓሊ ቢን ሁሴይን - ዘይነል ዓቢዲን (0)*
5. *ሙሐመድ ቢን አሊ- አል-ባቂር (0)*
6. *ጃዕፈር ቢን ሙሐመድ- አስ-ሷዲቅ (0)*
7. *ሙሳ ቢን ጃዕፈር-አል ከዚም (0)*

---

[129] ለዝርዝር መረጃ- የቁንዱዚ አል-ሀነፊ-የናቢዕ አል-መወደህ ገጽ 529- ክፍል 76- አስራ ሁለቱን ኢማሞች ስሞቻቸውን በመጥቀስ በሚገልጸው ንዑስ ክፍል፤ ፈራኢድ አስ-ሲምጠይን- ቅጽ2፣ ገጽ 132፣ ሀዲስ 431፤ ጋየተል መራም -ገጽ 1743፣ ሐዲስ 57፤ ቢሓር አል-አንዋር -ቅጽ 36፣ ገጽ 279፣ ክፍል 41 ሐዲስ 111 ይመልከቱ፡፡

[130] ይህን ሃዲስ በተመለከተ ቀደም ሲል የቀረቡትን በርካታ ምንጮች ይመልከቱ፡፡

*8. ዓሊ ቢን ሙሳ-አል-ሪዷ (ዐ)*

*9. ሙሐመድ ቢን ዓሊ- አል ጀዋድ (ዐ)*

*10. ዓሊ ቢን ሙሐመድ- አል-ሓዲ( ዐ)*

*11. ሐሰን ቢን ዓሊ አል-ዓስከሪ (ዐ)*

*12. አል-መህዲ ቢን ሐሰን- አል-ሙንተዘር (ዐ)*

## ኢማም መህዲ አል-ሙንተዘር (ዐ)

አስራ ሁለተኛው ኢማም መህዲ (ዐ.ተ.ፈ.ሸ.) /አላህ የመገለጫውን ዘመን ያፋጥነውና/ በዱንያ ላይ በህይወት እንዳለና በአላህ ትዕዛዝ ከእይታ እንደተሰወረ፣ አላህ በፈቀደና ባሻ ጊዜ (ነብዩ (ሰ) የሙተዋትር ደረጃ በተቀናጁ በርካታ ሐዲሶች በነገሩን መሰረት) ይህች ምድር በበደልና ጭቆና ከተሞላች ብኋላ በፍትህና ነጻነት ሊሞላት የሚገለጥ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህንን ጉዳይ ደግሞ መላው የሙስሊም ዑለማወች ሺዓና ሱኒ በአጠቃላይ- በእውቅ መጻህፎቻቸው ውስጥ ያሰፈሩት ግልጽ ጉዳይ ነው፡፡[131]

---

[131]ለዝርዝር መረጃ :--ሰሒህ ኢብን ሒባን15/236-237- ሙአሰሰት ሪሳላህ-ቤይሩት፡፡ አል-ሙስተድረክ አላ አስ-ሰሒሐይን 4/600፣ ሐዲስ 8669 -ዳር አል-ኩቱብ አል ዳልሚያ-ቤይሩት፡፡ -መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ-7/313 -ዳር አል-ሪያን ሊቱራስ -አል-ቃሂራ፡፡ -ሱነን አቡዳውድ 4/106 -ዳር አል ፊክር፡፡ -ሱነን ኢብን ማጃህ 2/1366፣ ዳር አል-ፊክር-ቤይሩት፡፡

-ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባህ- 7/513 እና 514 -መክተበት አል-ሩሽድ-ሪያድ፡፡

-አል ጃሚዕ መዓመር ቢን ራሽድ 11/371 እና 373 -መክተብ አል -ኢስላሚ -ቤይሩት፡፡ -ሙስነድ አል ባዝር8/256 -ሙአሰሰት ዑሉም አል-ቁርኣን -ቤይሩት፡፡ -ሙሰነድ አህመድ3/3፣26፣37፣52፣ -ሙአሰሰት ቁርጡባ -ግብጽ፡፡ -ሙሰነድ አል-ሓሪስ 2/873፣ መርከዝ ኸድመት አስ-ሱና ወአስ-ሲረት አል-ኑቡወህ -መዲና አል- ሙነወራ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ***ሙንተኸብ አል-አሰር***[132] እና ***አል-መህዲ***[133] (ዐ) የተሰኙትን መጽሐፍት ላየ ሰው ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከነብዩ (ሰ) እና ከፍጹማን አህሉልበይት (ዐ) የተያዙ እጅግ በርካታ የሆኑ ሀዲሶችን ያገኛል፡፡

---

-ሱነት አል-ዋሪዳ ፊል-ፊተን 5/1032- ዳር አል-ዓሲማ -ሪያድ፡፡ -ዐውን አል-መዕቡድ 11/ 247 እና 250 -ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ -ቱህፈት አል-አሕወዚ 6/403-ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ -ፈይድ አል-ቀዲር1/363 እና 5/262፣5/332፣ 6/278 -አል-መከተበት አል-ቲጃሪያ አል-ኩበራ -ግብጽ፡፡ -የናብዕ አል-መወዳ 2/318፣ ሐዲስ 917፣ ገጽ100፣ ሐዲስ 258፣264፡፡ -ኑር አል- አብሷር-ክፍል2፣ ገጽ154፡፡ -ሙንተኸብ ከንዝ አል-ዑማል6/ 29፡፡

-ኢስዓፍ አል-ራጊቢን 2/137፡፡ -ጋራኢብ አል-ቁርአን "እነዛ በገይብ (በሩቅ ሚስጥር) የሚያምኑ" በሚለው የቁርአን አያህ ትርጉም ውስጥ፡፡

-አል-አስቲዕያብ ፊ አስማእ አል-ሰሓብ 1/223፣ -አል-መላሂም ወልፊተን -ክፍል 27፡፡

ከሺዓ ምንጮች ደግሞ ፡-

-ቢሓር አል-አንዋር-ቅጽ 28፣ ክፍል4፣ገጽ119፣ ሐዲስ 99፤ ቅጽ 33፣ ክፍል 16፣ ገጽ 157፣ ሐዲስ 421፡፡

-ወሳኢል አል-ሺዓ -ቅጽ 16፣ ክፍል 33፣ ገጽ 241፣ ሐዲስ 21462፡፡ -ሙስተድረከ አል-ወሳኢል -ቅጽ12፣ ክፍል 31፣ ገጽ 283፣ ሐዲስ 14099፡፡ -አል-ካፊ ቅጽ1፣ ገጽ 338፣ ሐዲስ 7፡፡ -መንላ የህድሩሁል ፈቂህ -ቅጽ 4፣ ክፍል 2፣ ገጽ 174፣ ሐዲስ 540፡፡

-ዒለል -አሽ-ሽራዒእ-ገጽ 161፡፡ -መዓኒ አል-አኽባር -ገጽ 124 ረዲፍ -2067፡፡

-ዑዩን አኽባር አል-ሪዳ (ዐ) -ቅጽ፣2 ገጽ 66፣ ረዲፍ 2742፣ ሐዲስ 293፡፡ -ከማል አል-ዲን ገጽ 251፡፡ -ሲፋት አል-ሺዓ -ገጽ 49፡፡ -አል-አርሻድ -ቅጽ 2፣ ገጽ 340፡፡ አል-አከቲሷስ -ገጽ 209 … ወ.ዘ.ተ

132 አል -ሙንተኸብ አል-አሰር ፊ አል-ኢማም አል-ሳኒ ዓሽር -አያቱላህ ሼኽ ሉጥፈላህ አል-ሷፊ አል-ገልፓየጋኒ፣

133 አል-መህዲ (ዐ) -አል ሰይድ ሶድይ አል-ዲን አል-ሰድር፤ እንዲሁም አል-መህዲ ፊ ሱና የተሰኘውን የአያቱላህ አል ሰይድ ሷዲቅ አል -ሺራዚን መጽሃፍ ይመልከቱ፡፡

ነብዩ (ሶ) ባበሰሩት መሰረት ከአላህ (ሱ.ወ) የምንከጅለው እና የምንፈልገው የተከበረውን መገለጫውን ነው፡፡[134]

ሙስሊሞች ያለባቸው ግዴታ የመገለጫውን ጊዜ በጉጉት መጠባባቅ፣ ፈረጃውን መጠበቅና በቀንና በሌሊት ለሱ ዱዓ ማድረግ ነው፡፡
ዓለምን ከጥፋትና ፈሳድ የሚያጸዳት እሱ ነውና፡፡ (አላህ ሆይ! ፈረጃውን አፋጥንልን፣ መገለጫውን ገር አድርግልን፣ ከነሱ ከሚሰለፉት አንሷሮቹ አድርገን!!)
እነሆ የሀዲስ ዕውቀት እና የቁርዓን ታሪክ ዕውቀት ሰዎች ለሺህ ዓመታት በህይወት መቆየት እንደሚችሉ ያስገነዝበናል፡፡ ነብዩ ኑህን (ዐ) በተመለከተ በቁርአን ውስጥ እንዲህ እናገኛለን፡-

**فَلَبِثَ فِيهِمْ أَلْفَ سَنَةٍ إِلَّا خَمْسِينَ عَامًا**

**"ለሺህ ዓመት ሃምሳ ዓመት ሲቀር በነርሱ ውስጥም ኖረ፡፡"[135]**

---

[134] ይህንን በሚመለከተ *ከማል-አል-ዲን* -ገጽ287፣ ክፍል25፣ ሐዲስ 4 ይመልከቱ፡፡ እዚህ ላይ ነብዩ (ሶ) እንዲህ ብለዋል፡-

*"መህዲ ከኔ ዝርያ ከልጄ ነው፣ ስሙ ስሜ፣ የክብር ስሙ የክብር ስሜ (ኩንያው የኔ ኩንያ)፣ በተክለ ቁመናውም ሆነ በስነ ምግባሩ ከኔ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ለሱም ከዕይታ መሰወር (ጊባ) ይሆናል፣ በዚህም የተነሳ ሰዎች ከሃይማኖታቸው ያፈነግጣሉ፤ በዚህን ጊዜ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ከተፍ ይላል፤ ከዚያም ምድር በበደልና ጭቆና የተሞላችውን ያህል በፍትህና ነጻነት ይሞላታል፡፡"*

[135] አል-ዓንከቡት፡ 14

## አል-ዕስማህ (እንከን-የለሽነት)

የተከበሩት ነብዩ (ሶ)፣ ፋጢመት ዘህራ (ዐ) እና አስራ ሁለቱ ኢማሞች (ዐ) ከማንኛውም ወንጀል፣ ሀጢአት፣ ጥፋት፣ ስህተት እና መርሳት የተጠበቁና የጠሩ መሆናቸውን እናምናለን፤ አላህ ከሁሉ እንከን የጠበቃቸው እንከን-የለሾች እንደሆኑ እናምናለን፡፡ ይህንንም በሚመለከት የዓቅልና የመረጃ (ነቅል) ማስረጃዎች ማቅረብ እንችላለን፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

***إِنَّمَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنْكُمُ الرِّجْسَ أَهْلَ الْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِيرًا***

**"አህለልቤይት ሆይ! አላህ የሚሻውማ ከናንተ ላይ ብቻ ማንኛውንም ቆሻሻና እንከን ሊያስወግድና ፍጹም የሆነ ንጽህናን ሊያነጻችሁ ነው፡፡"**[136]

አያቱ የወረደው አህለልበይቱን (ዐ) በተመለከተ ስለመሆኑ በርካታ የተፍሲር መጽሃፍትን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡[137]

---

[136] አህዛብ፡ 33

[137]ተፍሲር አል-ጠበሪ22/6 -8 ዳረል ፊክር -ቤይሩት፡፡

-ተፍሲር አል-ቁርጡቢ 14/182-183 -ዳር አል-ሸዕብ -ካይሮ፡፡

-ተፍሲር ኢብን ከሲር -3/484-487 -ዳረልፊክር-ቤይሩት፡፡ -ሶሂህ ሙስሊም -4/1883፡፡ -ሰሂህ ኢብን ሕባን 15/432- ሙአሰሰት ሪሳላህ-ቤይሩት፡፡

ሙክተድረክ አላ አስ-ሰሒሐይን 2/541፣ 3/143፣ 158፣159፣172፣ -ዳር አል ኩቱብ አል ዒልሚያ-በይሩት፡፡ -ሱነን አል ቲርሚዚ 5/351፣352፣663 -ዳር አል-ኢህያእ አል-ቱራስ-ቤይሩት፡፡ መዋሪድ አል-ዘመኣን -ቅጽ 1/555 -ዳርል ኩቱብ አል-ዒልሚያ-ቤይሩት፡፡

-መጀመዕ አል-ዘዋኢድ 7/91፣ 8/215 ፣ 9/119፣ 121፣ 167፣ 168፣ 169፣ 172 -ዳር አል-ረያን ሊቱራስ -ካይሮ፡፡ -ሱነን አል-ቤይሐቂ አል-ኩብራ 2/149፣ 150፣ 152 - መክተብ

በተጨማሪም የሸሪዓ ህግጋት ምንጭና ዋቢ የሆነ አካል ለስህተትና ጥፋት ወይም ሐጢአት የመጋለጥ ዕድል መኖሩን ትክክለኛ የአዓምሮ አስተሳሳብ (ዐቅል) አይቀበልም፡፡ ከስህተትና እንከን ሁሉ የጸዱ እንከን-የለሾች ካልሆኑ ቃላቸውና ተግባራቸው አይታመንምና፡፡

እነዚህ አስራ አራቱ እንከን የለሾች አላህ መሪ አድርጎ የሰየማቸው የአላህ አውሊያዎች ሲሆኑ እነሱን የተከተለ ነጃ የሚወጣ፣ ከነሱ ያፈነገጠ የሚጠፋ

---

ዳር አል-ባዝ -መካ አል-ሙከረማ፡፡ ሱነን አል-ኩብራ-ነሳኢ 5/107- ዳር አል ኩቱብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ ሙስነድ ቢን አቢ ሽይባህ 6 /380፣ 388 -መክተብ አል-ሩሽድ፡፡ -ሙዕተስር አል-ሙክተሰር -የሱፍ ቢን ሙሳ አል-ሐነፊ 2/266፣ 268 -ዓለም አል-ኩቱብ-ቤይሩት፡፡ -ሙሰነድ አል-በዛር 6/210 -ሙአሰሰት ዑሉም አል- ቁርአን- ቤይሩት፡፡ -አል ሙዕጀም አል-አውሰጥ-አል-ጦበራኒ 3/166፣ 380፣ 4/134፣ 8/112- ዳር አል-ሀረመይን -ካይሮ፡፡

ሙስነድ አህመድ-1/330፣ 3 /259፣ 285፣ 4/ 108 ፣ 6/292፤ ሙአሰሰት ቁርጡባህ -ካይሮ፡፡ ሙሰነድ ኢስሐቅ ቢን ረዊየህ -3 /678- መክተብ አል-ኢማን - መዲና አል-ሙነወራ፡፡ አል-ሙዕጀም አሰ-ሰጊር-ጦበራኒ 1/231-መክተብ አስለሚ- ቤይሩት፡፡

-ሙስነድ ጠያለሲ- 1/274፣ ዳር አል መዕሪፋ - ቤይሩት፡፡ -አል ኣሃደ ወል መሳኒ- አቢ በክር ሽይባህ- 5/360፣ -ዳር አል-ራያህ -ሪያድ፡፡ ሙስነድ ዐብድ ቢን ሐሚድ -1/ 173፣ 367 -መክተብ አል ሱና -ካይሮ፡፡ -አል ሙዕጀም አል-ከቢር ጦበራኒ -3/52፣ 53፣ 55፣ 56፣ 93፤ -9/25፤ -12/103፤ -22/66፣ 200፣ 402፤ -23/249፣ 286፣ 327፣ 333፣ 337፣ 357፡፡ -አል-በያን ወ አል-ተዕሪፍ -1/150፣ -ዳረል ኪታብ አል-ዓረቢ-ቤይሩት፡፡ -ፈትህ አል-ባሪ -7/138፣ ዳረል መዕሪፋ -ቤይሩት፡፡ ሽርሕ አል-ዘርቃኒ-1/349፣ -ዳር አል- ኩትብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ -ቱህፈት አል-አሕወዚ-9/48፣ 49 -ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ -ሽዋሂድ አል-ተንዚል -አል-ሐሰካኒ -አል-ሐነፊ - 2/11-92፣ ሐዲስ 637-641፣ 644፣647-653፣657-661፣663-667፡፡ ታሪክ ዲመሽቅ-ኢብን ዐሳኪር-1/185 ፣ ሐዲስ 250፣272፣320፣321፣322፡፡ አል-ዒሳባህ -ኢብን ሐጀር 2/503 እና ሌሎች በርካታ ምንጮች…

ነው፡፡ በማንኛውም ቃል፣ ተግባርና ውሳኔያቸው በሙሉ ልንከተላቸው ግዴታ ነው፡፡ በአዋቂዎች ቋንቋ ሱና ማለት ይኼ ነው፡፡

እነዚህ ንጹሃን በኃያሉ አላህ ምሪት ለክቡር ህይወት የተመረጡ ፍጹም ተምሳሌት ናቸው፡፡ ከሁሉም የፈጠራ ምሁራን፣ ፖለቲከኞች፣ አዋቂዎች፣ ተመራማሪዎችና የመሳሰሉት አካላት የላቁና የመጠቁ ናቸው፡፡

## ነብዩ (ሰ) እና የሩቅ ሚስጥር (ገይብ) ዕውቀት

ነብዩ (ሰ) በአላህ ፍቃድና መሻት የሩቅ ሚስጥር (ገይብ) ያውቃሉ ብለን እናምናለን፡፡ ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን አላህ (ሱ.ወ) ባሳወቃቸው መሰረት ያውቃሉ ብለን እናምናለን፡፡ አላህም (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

***فَلَا يُظْهِرُ عَلَىٰ غَيْبِهِ أَحَدًا إِلَّا مَنِ ارْتَضَىٰ مِنْ رَسُولٍ***

**"የሩቅ ሚስጥራቱን ለማንም አይገልጽም፣ ከመልክተኛው ለወደደው በቀር፡፡"[138]**

አላህ (ሱ.ወ) መልክተኛውን (ሰ) ገይብ (የሩቅ ሚስጥራት) እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ነብዩ (ሰ) ደግሞ ይህንን አላህ ያሳወቃቸውን የሩቅ ሚስጥራት ዕውቀት በአላህ ትዕዛዝ ለፈለጉት ሰው ያስተምራሉ፡፡ በርግጥም ይህንኑ ለአህለልበይቱ (ዐ) አስተምረዋል (አሳውቀዋል)፡፡

[138]አል-ጅን፡ 26-28

***ተወሊ እና ተበሪ*** *(አላህን፣ ነብዩንና የአላህን አውሊያዎች መወዳጀት እና ከአላህ ጠላቶች፣ ከነብዩና አውሊያዎች ጠላቶች መጥራትና ጠላት አድርጎ መያዝ)*

አላህን (ሱ.ወ) ነብዩን (ሰ) እና የአላህን አውሊያዎች (ወዳጆች) መወዳጀትና ከአላህ ጠላቶች፣ ከነብዩና አውሊያዎች ጠላቶች መጥራትና ጠላት አድርጎ መያዝ ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡

## መዓድ (ትንሳዔ)

የቂያማ ቀን ደግሞ ህይወት በመዝራት መቀስቀስ እንዳለ እናምናለን፡፡ ይህ ቀን ታዛዥ ሙእሚኖች ነጃ የሚወጡበትና ይዘቱ የሰማያትና ምድር ያህል የሆነን ጀነት የሚመነዱበት ዕለት ነው፡፡ እንዲሁም አፈንጋጭና አልታዘዘም ባይ ከሀዲዎች (ካፊሮች) ለኪሳራ የሚዳረጉበት ቀንና አሳማሚ የጀሀነም እሳት በአካልና በነፍስ ቅጣት የሚቀጡበት ቀን ነው፡፡

## በዳእ

*"በዳእ"* በትክክለኛ ትርጉሙ መሰረት እውን መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህም፡-

**يَمْحُو اللَّهُ مَا يَشَاءُ وَيُثْبِتُ**

**"አላህ የፈለገውን ነገር ይሰርዛል፣ የፈለገውን ያጸናል፡፡"**[139] የሚለውን የቁርአን አያህ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ "በዳእ" ማለት 'አንድ ድብቅ የነበረ ወይም ግልጽ ያልነበረን ነገር ከዚያ በኋላ ግልጽ ማድረግ' በሚለው ትርጉም እንጂ አላህ (ሱ.ወ) "አንድ ነገር አያውቅም ነበር ከሆነ ጊዜ በኋላ ግን አወቀ"

---

[139] አል-ረዕድ፡ 39

በሚለው ትርጉም አይደለም፡፡ ይህኛው አስተሳሰብ አንድ ሙስሊም ፍጹም የማይለው ግልጽ የሆነ ክህደት (ኩፍር) ነው፡፡

## ጀብር እና ተፍዊድ

*ጀብር* ማለት አንድ ሰው በራሱ የሚያደርገው/በፈቃዱ የሚፈጽመው አንዳች ነገር እንደሌለና ማንኛውንም ተግባሩን ሳይፈቅድ ወይም ምንም ፈቃዱ ሳይኖረው ተገዶ ወይም ስለተወሰነበት ብቻ የሚያደርገው ሲሆን፣ *ተፍዊድ* ደግሞ አንድ ሰው ሌላ ማንም አካል በምንም ሁኔታ ጣልቃ ሳይገባበት የሰው ልጅ ማንኛውንም ነገር የሚያደርገው ሙሉ በሙሉ በፈቃዱ እንደሆነና ሙሉ ውክልና ያለው የሚል እንድምታ ያለው አስተሳሰብ ሲሆን እኛ ሺዓዎች በእንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አናምንም፡፡ ይልቁንስ ጉዳዩ በሁለቱ ጽንፎች መካከል የሆነ መሆኑን ነው የምናምነው፡፡ ይህም በተከበረው ሀዲስ ውስጥ በተገለጸው መልኩ ሲሆን የሀዲሱ ትርጉም የሰው ልጅ የሚሰራቸው ተግባራት በግዴታ ተጭኖት እንዳልሆነና በተመሳሳይ መልኩ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዳልሆነ (ፍጹም የሐነ ምርጫ እንደሌለው) ነው እምነታችን ፡፡ የሰው ልጅ አካላቱ፣ ህዋሳቱና ኃይሉ ወይም ችሎታው ያለ ምርጫው ከአላህ የተቸረው ሲሆን መልካምና እኩይ ተግባራት የመፈጸሙ ምርጫ ግን የራሱ የሰው ልጅ ነው፡፡ በጎ ከሰራ በአላህ ተውፊቅ (ቸርነት) ሲሆን ክፉ ከሰራ ደግሞ ከራሱ ነው፡፡

## ቱቂያ

ቱቂያ በሸርዓዊ ዐውደ ትርጉሙ መሰረት ከኢስላም አስተምህሮዎች አንዱ መሆኑን እናምናለን፡፡ ትርጉሙም የሰው ልጅ ነፍሱን፣ ገንዘቡን፣ ክብሩንና የሌሎችን ሙእሚኖች ነፍስ፣ ገንዘብና ክብር ከካህዲዎች (ካፊሮች)፣ ከዛሊሞች (በደዮችና ጨቋኞች) የመጠበቅ ግዴታን ለመወጣት የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ቁርአንና ከታላቁ የአላህ መልክተኛ (ሶ) እንዲሁም በእንከን የሌሾቹ ኢማሞች (ዐ) የታዘዘ ጉዳይ ነው፡፡

በቁርዓን ውስጥ እንዲህ እናገኘለን፡-

**لَا يَتَّخِذِ الْمُؤْمِنُونَ الْكَافِرِينَ أَوْلِيَاءَ مِنْ دُونِ الْمُؤْمِنِينَ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَلَيْسَ مِنَ اللَّهِ فِي شَيْءٍ إِلَّا أَنْ تَتَّقُوا مِنْهُمْ تُقَاةً**

**"ምእምናን ከሓዲዎችን ከምእምናን ሌላ ረዳቶች አድርገው አይያዙ፡፡ ይኼንንም የሚሠራ ሰው ከአላህ (ሃይማኖት) በምንም ውስጥ አይደለም፡፡ ከእነርሱ መጥጠበቅን ብትጠበቁ እንጂ (ጥንቃቄ ለመውሰድና ለመጠበቅ ካልሆነ በቀር)፡፡"[140]**

በሌላ የቁርዓን አያህ ደግሞ ፡-

**وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ**

**"በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡"[141]**

---

[140] ኣሊ-ዒምራን፡ 28

[141] አል-ሀጅ፡ 78

## የሙትዓ ኒካህ[142]

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ ውስጥ በገለጸው መሰረት የሙትዓ ኒካህ (ጋብቻ) ሸርዓዊ (ህጋዊ) መሆኑን እናምናለን፡-

**فَمَا اسْتَمْتَعْتُمْ بِهِ مِنْهُنَّ فَآتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ**

**"ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን ስጧቸው፡፡"[143]**

ነብዩ (ሶ) በመሰናበቻው ሀጅ ወቅት ሰሀቦቹን ያዘዙበትን የሀጅ ሙትዓ እንዲሁ የእስላም አስተምህሮ መሆኑን እናምናለን፡፡

ሙትዓ እንደሌሎች የእስላም ሸሪዓ (ህግጋት) ሁሉ እስከ ዘለዓለም ጸንቶ የሚቆይ መሆኑን፤[144] ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ) ሐላል ያደረጉት ነገር እስከ ቂያማ

---

[142]ለዝርዝሩ የ ተውፊቅ አል-ፈኪኪ ***"ሙትዓ"*** የተሰኘውን መጽሃፍ ዕንዲያነቡ ይመከራል፡፡

[143] አል ኒሳዕ፡ 24

[144]ተፍሲር አል ጦበሪ 2/388፤ ሙስሊም ከ ዒምራን ቢን ሀሲን እንደዘገበው እንዲህ ይላል፡ -*"የሙትዓ አንቀጽ ማለትም የሐጅ ሙትዓ በ አላህ ኪታብ ውስጥ የወረደ ነው፤ እንድንተገብረው ያዘዙንም የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) ናቸው፤ ከዚያ በኃላም የሐጅ ሙትዓን የሚሽር አንቀጽ አልወረደም፤ የአላህ መልዕክተኛም (ሶ) በህይወት እስከነበሩ ድረስ አልከለከሉም፡፡ ከዚያ በኃላ ነው የሆነ ሰው ዝም ብሎ ከራሱ መላምት የፈለገውን ያለው፡፡"*
*ከዚያ ደግሞ ጠበሪ የቲርሚዚን ሪዋያ በዋቢነት በመጥቀስ እንዲህ አለ፡-"ቲርሚዚ እንዳወራው- ቁተይባ ቢን ሰዒድ ከ ማሊክ ቢን አነስ- ከ ኢብን ሺሃብ- ከ መሀመድ ቢን ዓብደላህ ቢን ሃሪስ ቢን ነውፈል ከ ሰዕድ ቢን ወቃስ እና ከ ደሃኽ ቢን ቀይስ ሰምቶ፣ ሙዓዊያ ቢን አቢ ሱፊያን ሀጅ ባደረገ ዓመት፣ ዑምራን እስከ ሐጅ ወቅት ማጣቀምን በተመለከተ ሁለቱ ሲያወሩ፣ ደሃክ ቢን ቀይስ እንዲህ ሲል ሰምቻለሁ ይላል፡- 'ስለ አላህ ትዕዛዛት ምንም የማያውቅ መኃይም ካልሆነ በቀር ማንም እንዲህ ዓይነት ነገር አያደርግም፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዕድ፡-*

ቀን ድረስ ሐላል እንደሆነና የሙሀመድ (ሶ) ሐራም እስከ ቂያማ ቀን ድረስ ሐራም መሆኑን እናምናለን፡፡[145]

## አፈር (ቱርባ) ላይ ሱጁድ ማድረግ[146]

ሱጁድ መደረግ ያለበት መሬት (አፈር) ላይና ከሚበላና ከሚለበስ ነገር ሌላ መሬት ላይ የሚበቅል ነገር ላይ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይኸውም የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) ባሉት መሰረት ነው፡-

---

"ያለከው ነገር ምንኛ የከፋ ነው የወንድሜ ልጅ!"አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ደሃክ፡- "እንዴ! ዑመር ቢን ኸጣብ ይህንን ነገር ከልክሏል እኮ!"አለው፡፡ ሰዕድ ደግሞ ሲመልስ፡- "ታዲያ እኮ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) ተግብረውታል፤ እኛም ከሳቸው ጋር አድርገነዋል" ብሎ ነገረው፡፡ ይህ ሀዲስ ሰሂህ ነው ተብሏል፡፡"

እንዲሁም ኢብን ኢስሃቅ ከ ዙህሪ፣ ዙህሪ ከ ሳሊም በዘገበው መሰረት እንዲህ ተብሏል፡-
"በአንድ ወቅት ኢብን ዑመር ጋር ቁጭ ብዬ እያለሁ አንድ የሻም ሰው መጣና ስለ ሃጅ ሙትዓ ጠየቀው፡፡ በዚህ ጊዜ ኢብን ዐመር፡- "ጥሩ ነው፣ መልካም ነገር ነው" ብሎ መለሰለት፡፡ ጠያቂውም፡- "ታዲያ እኮ አባትህ ከለክሎታል" ሲለው---------
-----ኢብን ዑመርም መልሶ፡-"አንተ ሰው ወየውልህ ብቻ ዛሬ! ታዲያ አባቴ ቢከለክልም የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) ተግብረውት እኛንም እንዲናደርገው አዘዉናል፡፡ የአባቴን ቃል ነው ወይስ የረሱሉን ትዕዛዝ ነው መውሰድ ያለብኝ ታዲያ!? አቦ ሂድልኝ ከዚህ!" አለው፡፡ ሃዲሱን ዳረቁጥኒ አውጥቶታል፤ እንዲሁም አቡ ዒሳ አል-ቲርሚዚ ከ ሳሊህ ቢን ከይሳን ሐዲስ፣ ከይሳን ከ ኢብን ሺሃብ፣ ኢብን ሺሃብ ከ ሳሊም በተያዘ ሀዲስ መዘገቡን አትቷል፡፡
እንዲሁም በሰሂህ ሙስሊም 2/900፤ -በ ነሳዒ -ሱነን አል -ኩብራ -6/300 -ሐዲስ ቁጥር 11032፤ -ጦበራኒ -ሙዕጀም አል-ከቢር 18/135 -ሐዲስ 283፤ -ሶሂህ ቡኻሪ 3/569 -ሐዲስ 1494. . . ሙትዓ ከ አላህ ኪታብና ከነቢዩ (ሶ) ሱና የተያዘ ስለ መሆኑና ህጉን የሚሽር አንቀጽ ያለመውረዱን በዚሁ ሁኔታ እያለ ረሱሉ (ሶ) ማለፋቸውን የሚያትቱ በርካታ ሐዲሶችን እናገኛለን፡፡

[145] በሳኢር አል-ደረጃት ገጽ 148፣ ክፍል 13፣ ሐዲስ 8

[146] ለዝርዝሩ የ ሰይድ ሙሀመድ ኢብራሂመ አለ-ሙወሀድ የሆነውን "አል-ሱጁድ ዐላ አል-ቱርባ ወ አል-ጀመዕ በይን አል-ሶላተይን/ አፈር ላይ ሱጁድ ማደረግና ሁለት ሶላቶችን አጣምሮ መስገድ" የተሰነውን መጽሐፍ ያንብቡ፡፡

## “መሬትን መስጂድ (የሱጁድ ቦታ) ተደርጎልኛል፣ አፈርም ንጹህ ተደርጎልኛል፡፡”[147]

አብዛኛውን ጊዜ ንጹህና የጸዳ የሆነ የመሬት ቁራጭ ላይ (አፈር ላይ) በሶላት ወቅት ለአላህ (ሱ.ወ) ሱጁድ በማድረግ ላይ እንጠባበቃለን፡፡ ምክንያቱም በሁሉም ቦታ ላይ ሁል ጊዜ ንጹህ አፈር ማግኘት ላይመች ስለሚችልና ንጹህ ይሁን ነጃሳ በውል በማናውቀው ሁሉ ቦታ ላይ ስለማንሰግድ ንጽህናው አስተማማኝ የሆነ ቁራጭ መጠቀም ምርጫ እናደርጋለን፡፡

ብዙውን ጊዜ ይህ አፈር የሚሆነው ከተቀደሰችው የከርበላ ምድር ነው፡፡ ይህውም ይህ ቦታ የነብዩ (ሰ) ሲብጥ (የልጅ ልጅ) የሆኑት የኢማም ሁሴን (ዐ) ማረፊያ ቦታ ስለሆነና በከርበላ ምድር ላይ ሱጁድ ማድረግ ሙስተሀብ (የተወደደ ተግባር) መሆኑን በአህለልበይት (ዐ) ሀዲሶች ስለተነገረና ኢስላምን ነስር ማድረግ (መታደግ) በአላህ መንገድ ላይ የመሰዋት ጉዳይን

---

[147]ተፍሲር አል-ቁርጡቢ- 2/51- ዳር አል-ሽዕብ -ካይሮ ተፍሲር ኢብ ን ከሲር 4/3 -ዳረል ፊክር -ቤይሩት፤ ሙሰነድ አቢ ዓዋና 1/303 -ዳረል መዕሪፋ -ቤይሩት፤ ሙሰነፍ ዓብደረዛቅ- 1/32 - መርከዝ ኢስላሚ -ቤይሩት፤ ተምሂድ -ኢብን ዓብደልበር 1/168 -ሞሮኮ፤ ሰሂህ ሙስሊም 1/380 -ዳር ኢህያዕ ቱራስ ዓረቢ-ቤይሩት፤ ሙልተቃ-ኢብን አል-ጃሩድ 1/41፤ ሱነን አል- ዳረሚ 1/374 -ዳረል ኪታብ ዓረቢ-ቤይሩት፤ ሱነን አል- ቤይሐቂ- ኩብራ (1/212 -መካ ሙከረመህ፤ ሰሂህ ቡኻሪ 1/128 -ሐዲስ 328፤ ሱነን አል-ቲርሚዚ፣ ሱነን ቢን ማጃህ፣ ሱነን አል-ነሳዒ . . . ሌሎችንም ማየት ይቻላል፡፡

ከሺዓ መጽሀፍት ደግሞ :-

-ወሳኢል አል-ሺዓ 3/423 -ክፍል1 -ሐዲስ 5፤ -ወሳኢል (2/969 -ክፍል 7 ሐዲስ 2፤ -መንላ የህዱ-ሩሁል ፈቂህ 1/240-ሐዲስ 724፤ -አማሊ-አል-ሷዱቅ -216 -ሐዲስ 6 እና ሌሎች በርካታ መስደሮች፡፡

ስለሚያስታውሰን ነው፡፡ ይኸውም ኢማም ሁሴን (ዐ) ዛሊሞችንንና አምባ ገነኖችን የተፋለመበት ምድር ስለሆነ ነው፡፡

## ሁለት ሰላቶችን ጀምዕ አድርጎ (አጣምሮ) መስገድ

ሁለት ሶላቶችን (ሁለቱን ዙህሮችና ሁለቱን ዒሻዎች ማለትም ዙህርና ዐስርን በማከታተል እንዲሁም መግሪብና ዒሻን አጣምሮ ወይም አከታትሎ መስገድ የሚበቃ (የሚቻል) መሆኑን እና አፈራርቆ (ለያይቶ) መስገድም እንደሚቻል እናምናለን፡፡ ምክንያቱም ነብዩ (ሶ) አንዳንድ ጊዜ ሶላቶችን አጣምረው (አከታትለው) እንደሰገዱ በርካታ ሀዲሶችን መጥቀስ ይቻላልና፡፡[148]

ሰላትን አጣምሮ (አከታትሎ) መስገድ ውስጥ ለበጎ ነገር (ኸይር) መፍጠን ወይም መሽቀዳዳም ይገኝበታል፡፡

وَسَارِعُوا إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ

---

[148] ዒለል አል-ሸራዒዕ 312-ከ 11- ሐዲስ 1፤ ከአቡ ዓብዳላህ (ዐ) በተያዘ ሃዲስ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡- **“የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) ዙህር እና ዐስርን በአንድ ቦታ ያለ ምንም ምክንየትና ችግር ሰግደዋል፡፡** በዚህ ጊዜ ነቢዩን (ሶ) በመዳፈር ከሚታወቁ ስዎች ግንባር ቀደም የነበረው ዑመር ቢን ኸጣብ፡- “ምነው ሶላትን አስመልክቶ የተከሰተ አዲስ ነገር አለ?” አላቸው፡፡

እሳቸውም፡-“በጭራሽ! ነገር ግን በ ኡመቴ ላይ ለማቀለልና ለማስፋት ፋልጌ ነው” አሉት፡፡

ተመሳሳይ መልዕክት ያላቸው በርካታ ሃዲሶችን ማየት የፈለገ በሰሂህ ሙስሊም 1/489፣ 490፣491፣492-ሰሂህ ኢብን ሒባን 4/471 -ሐዲስ 1596፤ -ሰሂህ አል-ቲርሚዚ (1/354፤ -መጀመዕ አል-ዘዋኢድ -ጦበራኒ 2/161፤ -ሱነን አቢ ዳውድ 2/4)፤ -ሱነን አል-ኩብራ1/491፤ -ሱነን አል ነሳኢ 1/290፤ -ሙወጠእ-ማሊክ 1/144)፤ -ሱነን አል-በይሐቂ 3/168… ሉሎች ብዙ ዋቢ መጽሐፍት ማየት ይቻላል፡፡

***"ከጌታችሁ ወደሆነው ምህረት (መግፊራ) ተቻኮሉ፡፡"***[149]

እንዲሁም በሌላ የቁርአን አያህ ፡-

***فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ***

***"ለኸይር ነገር (በጎ ነገር) ተሽቀዳደሙ፡፡"***[150]

በተጨማሪም ለአላህ ባሮች ነገሮችን ማቃለል ወይም ማመቻቸት ጋር ይያያዛል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይላልና፡-

***يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ***

***"አላህ ለናንተ ማግራትን ይፈልጋል፤ ለናንተ መጨነቃችሁን ወይም መቸገራችሁን አይፈልግም፡፡"***[151]

በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ የፊቅህ ቅርንጫፎች ላይ በቂ የሆኑ ማስረጃዎች አሉን ፡፡ ለምሳሌ ውዱእን በተመለከተ - እኛ ጋር በሚታወቀው ከይፊያ (የውዱእ አደራረግ ሁኔታ)፣ አዛን -እኛ ጋር በሚታወቀው ሁኔታ- ወይም በሶላት ወቅት እጅን ስለማጣመር ወይም መልቀቅ በተመለከተና ሌሎች በመተግበር ላይ ያለን መሰል ነገሮች ላይ ከዲኑ መመሪያዎችና የአፈጻጸም ስርዓቶች ጋር የሚጣጣም ግልጽ ማስረጃዎች ያሉን ነን፡፡

የሸሪዓ አህካሞችን (በዲኑ የተቀመጡ መመሪያዎችንና ህግጋትን) ከትናንሽ እስከ ትላልቅ አህካሞች -ከኪታብና ሱና ወይም በኢጅማእና ዐቅል የተሰበተ

---

[149]አሊ-ዒምራን፡ 133

[150] አል-በቀራ ፡ 148፣ አል ማኢዳ፡ 48

[151] አል-በቀራ፡ 185

(የተረጋገጠ) ከሆነ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል ብለን እናምናለን ፡፡ ስለዚህም ከነዚህ ምንጮች ብቻ ለመውሰድ የተገደብን ነን፡፡

# ሽፋዓ (ምልጃ)

በቁርኣን እና ትክክለኛ በሆኑ (ሀዲሶች ስ) በተገለጸው መሰረት ሽፈዓ (ምልጃ) በዲኑ የመጣ ትክክለኛ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን፡፡[152]

አላህ (ሱ.ወ) በቁርኣኑ፡-

---

[152] ሽፈዓን በሚመለከት ከሐዲስ መኣድሮች ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡- ከሱኒ መጽሐፍት፡-- ሰሂህ ሙስሊም (1/172-ኢስባት አል-ሽፈዓ) በሚለው ክፍል -ዳር አህያእ ቱራስ ዓረቢ- ቤይሩት፣ እንዲሁም በሶሂህ ሙስሊም 1/177-ሐዲስ 191 ከነዚህም ውስጥ ጥቂት ሐዲሶችን ለመጥቀስ ያህል፡-

***"...ከዚያም ሽፈዓ ይፈቀድና በልቡ ውስጥ ከበን ነገር (መልካም ነገር) ጥቂትም ቢሆን ያለውና ላ ኢላ ሐ ኢ ለላህ (ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም) ብሎ የመሰከረ ሁሉ ከጀሀነም እሳት እስኪወጡ ድረስ ያማልዳሉ (የሽፈውን)፡፡"***

እንዲሁም በሰሂህ ሙስሊም (1/183-ሐዲስ፣193፣1/188) ነቢዩ (ሶ)፡- ***"በጀነት ውስጥ ሽፈዓ በማድረግ (በማማለድ) የመጀመሪያው ሰው ነኝ፡፡ ከነቢያት ውስጥ በርካታ ተከታዮችን በመጎናጸፍ ቀዳሚ ነብይም ነኝ፡፡"***

እንዲሁ በሶሂህ ቡኻሪ 1/128-ሐዲስ 328- ዳር ኢብን ከሲር -ቤይሩት- ከጃቢር ቢን አብደላህ በተያዘ ሐዲስ ሌሎች ነብያት ያልተሰጡትን አምስት ነገሮች እንደተሰጣቸው ነብዩ (ሶ) በተናገሩት ውስጥ ሽፈዓ (ምልጃ) አንዱ እንደሆነ እናገኛለን፡፡

በተጨማሪም የአቢ በክር አል-በይሀቂ በሆነው **ሹዕብ አል-ኢማን** በተሰኘው መጽሀፍ 3/496-ዳር አል- ኩትብ ዒልሚያ-ሐዲስ 4180 ላይ ሰልማን ከነብዩ (ሶ) በሰማው መሰረት፡- ***"ከሁለቱ ሐረሞች (መካና መዲና) በአንዱ ቦታ ለሞተ ሰው ሽፈዓዬ (ምልጃዬ) ዋጅብ ነው (አይቀሬ) ይሆንለታል፤ የቂያማ ቀን የደህንነት ዋስትና ከተጎናጸፉት ሰዎች ውስጥም ይሆናል"*** የሚል እናገኛለን፡፡

ሌሎች በርካታ ማጣቀሻወችንም ማቅረብ ይቻላል ፤ ሰሂህ ቡኻሪ(1/168-ሐዲስ 468፣ 3/1226 ሐዲስ 3182፣4/1748 . . . ለተጨማሪ ማስረጃ ማየት ይቻላል፡፡

**وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ارْتَضَىٰ**

**"ውዴታን ላገኘ (ለሚገባው) እንጂ አያማልዱም፡፡"[153]**

## በነብዩ(ሶ) እና በንጹህን ቤተሰባቸው ተወሱል ማድረግ

ነብዩን እና ንጹሃን ቤተሰቦቻቸውን ወደ አላህ መቃረቢያ (ተወሱል )አድርጎ መያዝ ይበቃል (ይፈቀዳል) ብለን እናምናለን፡፡

አላህ በቁርአኑ መቃረቢያ አድርገን እንድንወስዳቸው አዟልና፡፡

**وَابْتَغُوا إِلَيْهِ الْوَسِيلَةَ**

**"ወደሱም መቃረቢያን (ወሲላ) ፈልጉ፡፡"[154]**

ከአላህ (ሰ.ወ) ሀጃዎቻችንን በመፈለግ ውስጥ በነሱ እስቲምዳድ ማድረግ (መመጀንና መደድ መፈለግ) ትክክለኛ አካሄድ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በቁርአን ውስጥ ሸሂዶችን (በአላህ መንገድ ላይ የተሰውትን) አስመልክቶ በተገለጸው መሰረት ነብዩና አህለልበይት አላህ ዘንድ ህያውያንና ሲሳይ የሚረዘቁ ናቸውና፡፡ ከነብዩ (ሶ) በደረጃ ያነሱ ሸሂዶች በዚህ መልኩ በቁርአን ውስጥ ከተገለጹ እሳቸው (ሶ) ደግሞ በዚህ ባህሪ ቀዳሚ ናቸው፡፡[155]

---

[153]አል-አንብያእ: 28

[154] አል-ማኢዳህ: 35፡፡

የ ኢብን ሸህር ኣሹብ የሆነውን *ሏል-መናቂብ* የተሰኘ መጽሐፍ 3/75 ላይ አሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ)፡- "ወደሱም መቃረቢያን (ወሲላ) ፈልጉ" ያለው ውስጥ፡- **"እኔ ነኝ ወሲላው፣ እኔና ልጄ"** ማለተቸው ተጠቅሷል፡፡

[155]አንዳንድ የአህለሱና ዑለማዎች ነብያት (ዐ.ሰ) ህያው እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ አል-ሱዩጢ አል-ሻፊዒ ነብያት (ዐ.ሰ) ህያው ስለመሆናቸው የሚያመላክቱ ሐዲሶች ሙተዋትር (ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡ) ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ ነብያት (ዐ.ሰ) ህያው እንደሆኑና

ነብዩ (ሶ) በዱንያ ላይ በህይወት በነበሩ ግዜ ሰህባዎች በሳቸው (ሶ) ተወሱል በማድረግ ሐጃዎቻቸውን ይፈልጉ እንደነበር[156] ሁሉ በአሁኑ ወቅት ደግሞ

---

የመቃብሮቻቸው ውስጥ እንደሚሰግዱ የሚገልጽ ሀዲስ አመላክተዋል፡፡ እንዲሁ በይሐቂ ነብያት (ዐ.ሰ) ከተያዙ (ከሞቱ) በኋላ ሩሀቸው (ነፍሳቸው) እንደምትመለስና እንደ ሻሂዶቹ ህያው እንደሚደረጉ በሚያትተው መጽሀፍ ውስጥ ገልጸዋል፡፡

ከነብዩ(ሶ) በተያዘ ሐዲስ፡-

***"ማንም ሰው በኔ ላይ ሰላምታ አያወርድም (አያቀርብም) አላህ (ሱ.ወ) ሩሄን (ነፍሴን) ወደኔ መልሶ ምላሹን (የሰላምታውን አጸፋ) ካልመለስኩኝ በስተቀር"*** የሚል እናገኛለን ፡፡

(ዐውን አል-መዕቡድ 6/19-`ዚያረቱል ቁብር` በሚለው ክፍል ስር ይመልከቱ፡፡--------------

------በተጨማሪም በዚሁ (ዐውን አል-መዕቡድ 6/21- አል-ኹፋጂ  የሚከተለውን እላለሁ በማለት እነደሚከተለው ማተታቸው ተወስቷል፡፡ ይኸውም፡-

“ከሀዲሱ ትርጉም ግልጽ የሚሆነው ጉዳይ ነብያትና (ዐ.ሰ) ሸሂዶች ህያው እንደሆኑና የነብያት ህያውነት ደግሞ የበለጠ መሆኑን ነው ካሉ በኋላ በመቀጠል "አቡ በክር ቢን አቢ ሸይባ እንዲሁም በይሐቂ በ አል-ሽዐብ ውስጥ ከአቡሁሬይራ በተያዘ ሀዲስ ነብዩ (ሶ)፡- ***"ቀብሬ (መቃብሬ) አጠገብ ሆኖ በኔ ሰለዋት ያወረደን ሰው እሰማዋለሁ፤ ከሩቅ ሆኖ ሰለዋት ያወረደብኝንም እደርሰዋለሁ"*** እንዳሉ ዘግቧል፡፡  እንዲሁ በገጽ 22 ከአቡሁሬይራ በተያዘ ሀዲስ ቀብራቸው አጠገብ ሆኖ ሰለዋት ያወረደን ሰው እንደሚሰሙና ከሩቅ ሆኖ ሰለዋት ያወረደ ሰውም (ምላሹን) እንደሚያደርሱት ተናግረዋል፡፡

እንዲሁ ´ፋይድ አልቀዲር´ በተሰኘ ኪታብ 2/479 ላይ አል-ስብኪ ኢብን በሻር እንዲህ ማለቱን ዘግቧል፡፡ይኸውም፡-

***“ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር መጣሁና ሰላምታ ሳቀርብላቸው ከተከበረው መቃብራቸው ውስጥ ´ወአሌይከ ሰላም´ የሚል ምላሽ ሰማሁ፡፡”***

እንዲሁ በ´ፋይደል ቀዲር´6/386 ላይ ዳውድ እንዲህ ማለቱን ዘግበዋል፡፡ ይኸውም፡-

“መርዋን ቢን አልሀከም መጣና የሆነ ሰው በነብዩ (ሶ) ቀብር ላይ በፊቱ ተደፍቶ አየ፡፡ በዚህ ጊዜ ***‘ምን እያደረክ እንደሆነ ታውቃለህ´*** አለው፡፡ ወደ ሰውየው እየቀረበ ሲመጣም አቡ አዩብ መሆኑን አወቀ ፡፡ አቡ አዩብም ***"አዎ ወደ አላህ መልክተኛ (ሶ) ነው የመጣሁት ለድንጋዩ አይደለም አመጣጤ"*** ብሎ መለሰለት፡፡

[156]ዝርዝር ማስረጃ ለፈለገ ሰው ከብዙ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

በአኺራ ህያዉ ሆነው ባሉበት ወቅት ሙስሊሞች በሳቸው (ሶ) ተወሱል ማድረግና ሐጃቸውን መጠየቅ ይበቃላቸዋል (ይችላሉ)፡፡

ነብዩ (ሶ) እና ንጹህን አህለልበይቱ (ዐ) አላህ ዘንድ የእውቅናና ደረጃ ባለቤቶች በመሆናቸው ሁሉን ቻይና አሸናፊው አላህ ሀጃችንን ያወጣልን ዘንድ እነሱን መቃሪቢያ አድርገን ሃጃችንን ከአላህ እንዲጠይቁልን ተወሱል እናደርጋለን፡፡

ከሁሉ በላይ የላቀው አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

***وَلَوْ أَنَّهُمْ إِذْ ظَلَمُوا أَنْفُسَهُمْ جَاءُوكَ فَاسْتَغْفَرُوا اللَّهَ وَاسْتَغْفَرَ لَهُمُ الرَّسُولُ لَوَجَدُوا اللَّهَ تَوَّابًا رَحِيمًا***

**"እነሆ እነሱ ነፍሶቻቸውን በበደሉ ግዜ (ጥፋት ባጠፉ ግዜ) ወዳንተ መጥተው አላህን ምህረት በጠየቁ ኖሮ እና መልክተኛው (ሶ) ምህረት በጠየቁላቸው ኖሮ ፣ አላህን ተውባ ተቀባይና መህሪ ሆኖ ባገኙት ነበር፡፡"[157]**

---

በሰሀቦች ዘመን ዝናብ በጠፋበት ወቅት ወይም በድርቅ ግዜ ዝናብ ላማግኘት በነብዩ(ሶ) ተወሱል ያደርጉ እንደነበር ከነብዩ (ሶ) በኋላም በነብዩ አጎት በዓባስ . . . ይወሰሉ እንደነበር፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የአቡ ጣሊብ ስንኝ (ግጥም) ለማስረጃ እንደሚነሳና ሌሎች በርካታ ምሳሌዎች በተለያዩ ሙሳድሮች ተጠቃሽ ስለመሆናቸው የሚከተሉትን መጽሀፍት ማየት ይቻላል፡፡

-ፈትሁል ባሪ -አስቀላኒ-2/494-የዐረብ ገጠሬዎች ወደ ነብዩ (ሶ) እየመጡ ለዝናብ ተወሱል ያደርጉ እንደነበር ያወሳል፡፡ በዑመር ቢን ኸጣብ ዘመን ተመሳሳይ ሁኔታ መኖሩን ከመሳድሮች ማየት ይቻላል፡፡

[157] አል-ኒሳእ: 64

(በቀብሩ ሳይሆን) የቀብሩ ባለቤት በሆኑ ነብያትና አውሊያዎች አላህ ዘንድ ባላቸው ቦታና ደረጃ ወደ አላህ መቃረብ ይቻላል፡፡
ይኸውም በኪታብና ሱና እንዲሁም ኢጅማዕና የሙስሊሞች ታሪክ ትክክለኛነታቸው በማያጠራጥር ቁርጥ ማስረጃዎች የሰበተ (የተረጋገጠ) ጉዳይ ነውና፡፡[158]

---

[158]በሱነል አል ዳርሚ- 1/56፤ ሀዲስ 92 ላይ ማየት እንደሚቻለው የመዲና ሰዎች ድርቅ በገጠማቸው ግዜ የነብዩ ባለቤት አዒሻን ሲያማክሩ ወደ ነብዩ (ሶ) እንደመራቻቸውና በቀብራቸውና በሰማይ መካከል ጣራ እንዳይኖር እንዲያደርጉና በነብዩ ምልጃነት እንዲማጸኑ በጠቆመቻቸው መሰረት ይህንን አድርገው ዝናብ እንደዘነበላቸው ተዘግቧል፡፡
-በሙሰነፍ ቢን አቢ ሸይባ 6/356- ሐዲስ 32002 ላይ ደግሞ በዑመር ዘመን ድርቅ በተከሰተ ጊዜ አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር መጥቶ ***"የአላህ መልክተኛ ሆይ! ኧረ ህዝቦን ያጠጡ! በድርቅ ሊያልቁ ነው"*** ብሎ እንደተማጸነና ነብዩ (ሶ) በህልሙ መጥተው ወደ ዑመር ሄዶ ህዝቡ ዝናብ እንደሚያገኙ እንዲነግረው እንዳዘዙትና ሰውየውም ይህንኑ እንዳደረገ ፣ ዑመርም እንዳለቀሰ ወዘተ. . . የሚያትት ዘገባ እናገኛለን፡፡

-በሸዕብ አል-ኢማን- አቢ በክር አል-በይሐቂ (3/492- ሐዲስ 4168 እንዲሁም ሐዲስ 4169 ደግሞ ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር መጥቶ (አህዛብ 56) ማለትም ***"አላህና መላዒካዎቹ በነብዩ ላይ ሰለዋት ያወርዳሉ፤ እናንተ ያመናችሁ ሆይ እናንተም በሱ ላይ ሶለዋት አዉርዱ፣ ሰላምታም በሉ"*** ያለውን የቁርዓን አያህ በመቅራትና ሰለዋት በማውረድ ለሀጃዎቻቸው ተወሱል እንደሚያደርጉና ይህንን ያደረገ ሰው ሰባ ግዜ ሶለዋት ካወረዳ በኋላ አንድ መላዒካ ወርዶ፡-
***"እከሌ ሆይ" በእርግጥ አላህ (ሱ.ወ) አንተም ላይ ሰለዋት አወረደ፣ ከሀጃህም አንድም የወደቀ የለም"*** እንዳለው እናነባለን፡፡

በተጨማሪም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መጽሀፍ (3/495-ሐዲስ 4177 ላይ ደግሞ መጥፎ ነገር ሲፈጽም አይቶ ለመከላከል ሁኔታው ያልፈቀደለት አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር መጥቶ ሰላምታ ካወረደባቸው በኋላ ስሞታውን ነግሮአቸው እንደተመለሰ የሚያትት ዘገባ እናገኛለን፡፡
እንዲሁ የአቢ ሙሀመድ አል-መቅደሲ "አል-ሙግኒ"በተሰኘው መጽሀፍ 3/298 ውስጥ አንድ የገጠር ሰው ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር በመምጣት ***፦"አሰላሙአሌይከ ያረሱለላህ"*** ካለ በኋላ

አላህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፡-

***وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ***

**"እነዛን በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ እንዳታስባቸው፤ እነሱማ በእረግጥ ጌታቸው ዘንድ ህያውያን ናቸው፤ ይረዘቃሉም (ርዝቅ/ሲሳይ ያገኛሉ)፡፡"[159]**

እንዲሁ በሌላ የቁርአን አያህ

---

***"ነፍሶቻቸውን በበደሉ ግዜ ወዳንተ መጥተው የአላህን ምህረት በጠየቁና መልእክተኛው ምህረት ቢጠይቅላቸው አላህን መሐሪና አዛኝ ሆኖ ባገኙት ነበር"*** (አል-ኒሳእ 64) የሚለውን የአላህ ቃል ሰማሁ ፡፡ እናም ይኸው ለወንጀሌ እስቲግፋር ላደርግ ወደ አንቱ መጣሁ፡፡ ወደ ጌታዬም አማላጅ አድርጌዎት ቀረብኩ" ማለቱንና በመጨረሻም ነብዩን (ሶ) ያወደሰበትንና የቀብራቸውን ክብርና ታላቅነት የገለጸበትን ስንኝ በተለያዩ መሷድሮች ላይ መስፈሩን የሚጠቁም ዘገባ ዕናገኛለን፡፡የዚህ ራዊ (ተራኪ) የሆነው ዑትባ የተባለ ሰው ይህ ሁሉ ሲፈጸም የነብዩ (ሶ) ቀብር አጠገብ ተቀምጦ ስለነበር ገጠሬው ጉዳዩን ከጨረሰ በኋላ እዛው እንቅልፍ ወስዶት (ዑትባ ማለት ነው) ነብዩን (ሶ) በህልሙ እንዳየና ገጠሬውን ሰው ፈልጎ ከጥፋቱ ሁሉ ምህረት ማግኘቱን እንዲነግረው መታዘዙን ጨምሮ ገልጿል፡፡

ለተመሳሳይ ክስተቶች ዝርዝር ማስረጃ ለፈለገ ሰው፡-

-ሱነን ቢን ማጃ (ሸርህ) -አል-ሱየጢ፣ ዓብደልገኒ እና አል-ዳህላዊ-ገጽ 99፤ የበይሐቂ እና የኢብን አቢ ሸይባህ ሐዲሶችን ማየት ይቻላል፡፡

-ፈትህ አል-ባሪ- ዓስቀላኒ አል-ሻፊዒ-3/66፤ -ተፍሲር ኢብን ከሲር (1/521)፤ -ሚስባህ አል-ዙጃጃህ-አህመድ ቢን አባበክር አል-ኪናኒ 4/178 እና ሌሎች በርካታ መሳድሮች፡፡

[159] አል-ኢምራን፡ 169

***وَلَا تَقُولُوا لِمَنْ يُقْتَلُ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتٌ بَلْ أَحْيَاءٌ وَلَكِنْ لَا تَشْعُرُونَ***

**"በአላህ መንገድ ላይ የሚገደልን ሙታን ናቸው አትበሉ፡፡ እነሱማ በእርግጥ ህያውያን ናቸው፤ ነገር ግን እናንተ አይገባችሁም (አትረዱም)፡፡"[160]**

## መሻሂዶችን (መቃብሮችን) መዘየርና በረካ መሻት (ተበሩክ)

በበርካታ ትክክለኛ ሀዲሶች[161] በተገለጸው መሰረት የነብዩን (ሶ) ቀብርና የንጹሀን አህለልበይት (0) የቀብር ቦታዎች መዘየር ተወዳጅ ተግባር መሆኑን

[160] አል-በቀራ: 154

[161] ፈትህ አል-ባሪ- አል-ዓስቀላኒ አል-ሻፊዒ-3/66- ዳር አል-መዕሪፋ- ቤይሩት፡፡
-በ ኢብን ከሲር ተፍሲር 1/521 ውስጥ ከ ዑትባ በተያዘ ሐዲስ፡-"አንድ ቀን የረሱሉ (ሶ) ቀብር አጠገብ ቁጭ ብዬ ሳለሁ አንድ የገጠር ሰው ወደ ቀብራቸው መጣና እንዲህ ሲል ሰማሁት፡-'አስሰላሙ ዓለይከ ያ ረሱለላህ! እነሆ ***አላህ (እነሆ እነሱ ነፍሶቻቸውን በበደሉ ግዜ (ጥፋት ባጠፉ ግዜ) ወዳንተ መጥተው አላህን ምህረት በጠየቁ ኖሮ እና መልክተኛው (ሶ) ምህረት በጠየቁላቸው ኖሮ ፣ አላህን ተውባ ተቀባይና መሀሪ ሆኖ ባገኙት ነበር*** እንዳለ ሰምቻለሁ፤ እናም ይኸው ከወንጀሌ ተጸጽቼ አንተን አማላጅ አድርጌ መጥቻለሁ" ማለቱ ተዘግቧል፡፡
-ፋጢመቱ ዘሀራ (ረ.0) ከነብዩ (ሶ) ቀብር ጭብጥ አፈር ወስዳ አይኗ ላይ እንዳደረገችና እና የቀብራቸውን አፈር በማወደስ ስንኝ እንደተቀኘች በአቢ ሙሀመድ አል-መቅድሲ- "አል-ሙግኒ" በተሰኘው ኪታብ-2/213 ውስጥ እናገኛለን፡፡
-እንዲሁ በዚሁ መጽሀፍ 3/299 ላይ ኢብን ዑመር ነብዩ (ሶ) ይቀመጡበት የነበረውን ሚንበር ላይ እጁን በማስቀመጥ ከደባበሰ በኋላ ፊቱን ያብስበት እንደነበር ተገልጿል ፡፡
-በአቢ በክር አል-በይሐቂ *ሸዕብ አልኢማን* ገጽ 492-493- ሐዲስ 4180 ላይ ደግሞ ከዕብ አልአህባር ባወራው ሀዲስ መሰረት በየቀኑ ሰባ ሺህ መላኢካዎች ወደ ነብዩ (ሶ) ቀብር በመምጣት ሰለዋት እንደሚያወርዱና ጧት ላይ የመጡ ሰባዎቹ መላኢካዎች አመሻሽ ላይ በሌሎች ሰባ ሺህ እንደሚተኩ ተዘግቧል፡፡ በሱራ አል-ተህሪም -6 በቁርአን እንደተገለጸው መላኢካዎች አላህ ያዘዛቸውን ነገር ፍጹም አሻፈረን እንደማይሉና ያዘዛቸውን እንደሚፈጽሙ እናውቃለን፡፡

እና በነዚህ በተከበሩ ቦታዎች መባረክ (ተበሩክ መደረግ) የተፈቀደ ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡ አላህ በቁርአኑ እንደተናገረው እነሱ አላህ ዘንድ ህያውያን እንደሆኑና ከአላህ የሆነ ርዝቅ እንደሚረዘቁ እናምናለን፡፡

**وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ**

**"እነዛን በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ እንዳታስባቸው፤ እነሱማ በእረግጥ ጌታቸው ዘንድ ህያውያን ናቸው፤ ይረዘቃሉም (ርዝቅ/ሲሳይ ያገኛሉ)፡፡"[162]**

የአላህ መልክተኛ (ሰ) እና ቤተዘራቸው ደግሞ ከሸሂዶች በላይ በደረጃ የላቁ መሆናቸውን ቀደም ሲል አንስተናል፡፡

ስለዚህ ቀብራቸውን እንዘይራለን፣ በቅርሶቻቸው እንባረካለን፣ ዶሪሆቻቸውን እንስማለን፡፡ ይህ ደግሞ ለአላህና ለአውሊያዎቹ፣ ያለንን ፍቅርና ዕሽቅ በገሀድ የምናሳይበት ተግባር ነው ፡፡ ይህ ተግባር ከአላህ ውጭ የሆነን አካል መገዛት (ዒባዳ ማድረግ) አይደለም፡፡ አንድ ሰው በበግ ቆዳ የተለበደን የቁርአን መጽሀፍ የሚየከብረውና የሚስመው ቆዳውን አስቦ ሳይሆን ለቁርአኑ ላለው

---

-ሀጀረል አስወድ (ጥቁሩ ድንጋይ) በተመለከተ ድግሞ ነብዩ(ሶ) እና ሰሀቦች ይስሙት እንደነበርና በዲኑ የመጣ ጉዳይ ስለመሆኑ ዝርዝር ማሽረጃ ካስፈለገ ደግሞ፡-
-ሰሂህ ሙስሊም-3/925
-ሰሂህ ሙስሊም -3/926
-ሰሂህ ኢብን ኹዘይማ 4/212
-ሰሂህ ኢብን ሒባን 9/130 እና 9/132
-አል-ተምሂድ -ኢብን ዓብድል ባር 22/262
-ሰሂህ ቡኻሪ 2/579 ሐዲስ 1520
-አል ሙስተረድክ ዓላ ሶሂሀይን 1/328 . . . ወ.ዘ.ተ ይመልከቱ፡፡
[162]አሊ ዒምራን፡ 169

ክብር እንደሆነ ሁሉ እኛም ክብራችንንና ፍቅራችን የሚናሳው ለቀብሩና ዶሪሁ ሳይሆን ለዶሪሁ ባለቤት ነው፡፡ ጥቁሩን ድንጋይ እንድናከብር እና እንድንስመው ኢስላም ያዘዘን ከአላህ ዲን መገለጫ ምልክቶች አንዱ ስለሆነ ነው እንጅ ድንጋይ መገዛት እንዳልሆነ ሁሉ ማለት ነው፡፡

የንጹሀን ዶሪሆችን ማክበርና መሳም ውስጥ ሰዋብ (ምንዳ)እና ቁርባ (ወደ አላህ የመቃረብ ተግባር) አለ፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶ) ጥቁሩን ድንጋይ (ሐጀረል አስወድ) እንደ ሳሙ ሁሉ ይህም ተመሳሳይ ተግባር ነው፡፡

-በነብዩ (ሶ) ቀብር ተበሩክ ማድረግና መዘየርን በተመለከተ በርካታ ሐዲሶች ቢኖሩም እዚህ ላይ ጥቂቱን ብቻ ለማስረጃ ጠቅሰናል፡፡

## ዶሪሆችን መገንባት

መቃብሮችን መገንባት ያልተከለከለ ተግባር መሆኑን፣ በነብዩ (ሶ) እና በአህለልበይት ኢማሞች (0) መቃብሮች ዙሪያ እንዲሁም በሙእሚን ሰሀቦችና በኢስላም ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦች መቃብሮች ዙሪያ መሳጅዶችን፣ ቁባዎችንና ዶሪሆችን መገንባት የተወደደ ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡ ወደ አላህ (ሱ.ወ) መቃረቢያ ተግባራት ውስጥ ብልጫ ያለው ቦታ እንዳላቸውና የአላህ (ሱ.ወ) ምልክቶች (የዲን መገለጫዎች) ማክበርና ማላቅ ከልቦች ተቅዋ እንደሆነ የሚገልጸው የአላህ ቃል ውስጥ እንደሚካተት እናምናለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፡-

**ذَٰلِكَ وَمَنْ يُعَظِّمْ شَعَائِرَ اللَّهِ فَإِنَّهَا مِنْ تَقْوَى الْقُلُوبِ**

**"የአላህን ሻዓኢሮች (ምልክቶች) /የዲን መገለጫዎች ) የሚያልቅ ሰው፣ እነሆ ይች ልባቸው በተቅዋ የተሞላ ሰዎች ባህሪይ ናት፡፡"[163]**

ከሚከተለው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ጋርም የተያያዘ በመሆኑ:-

***قَالَ الَّذِينَ غَلَبُوا عَلَىٰ أَمْرِهِمْ لَنَتَّخِذَنَّ عَلَيْهِم مَّسْجِدًا***

**እነዚያ በጉዮቻቸው ላይ ያሸነፉት:- "በእነሱ ላይ በእርግጥ መስጊድን እንሠራለን"** አሉ፡፡[164]

እንዲሁም በትክክለኛ ሀዲሶች የተደገፈ በመሆኑ ኢስላማዊ ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡ ከዚህም በላይ ከሰለፎች እስከ ኸለፎች መላው የሙስሊሞች ታሪክ ከመጀመሪያው የኢስላም ታሪክ ጀምሮ በቀብሮች ላይ መገንባትና ማሰማመር የነበረና የሚኖር እንደሆነ ያስረግጣል፡፡

በመዲና ያለው የነብዩ (ሶ) ቀብር፣ በተለያዩ የዓለማት ክፍል የሚገኙት የኢማሞች (ዐ) የዑለማዎችና የሷሊሆች መካነ መቃብሮች በዚህ ጉዳይ ላይ ህያው ምስክሮች ናቸው[165]፡፡

---

[163] አል-ሐጅ: 32

[164] አል-ከህፍ፡ 21

[165]በዚህ ጉዳይ ወይም ለመካነ መቃብሮች ትኩረት መስጠትንና በነሱ ላይ መገንባትን በተመለከተ በርካታ ሐዲሶችን በአህለሱና መጽሀፍትን ብናገኝም ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል:-

-ነብዩ (ሶ) የልጃቸው የኢብራሂምን ቀብር ውሃ ያጠጡ እንደነበር (ውሃ ይረጩ እንደ ነበር)፣ አንዳንድ ነገሮችን እላዩ ላይ ያስቀምጡ እንደነበረና ቀብሩንም አንድ ስንዝር ያህል ከፍ እንዳደረጉ ማስረጃ ካስፈለገዎ :-ሱነን አል-በይሀቂ (3/411) ሀዲስ 6528 ማየት ይቻላል፡፡

እንዲሁ ዑስማን ቢን መዝዑን በተቀበረ ግዜ ነብዩ (ሶ) ለምልክት ማስቀመጥ የፈለጉትን ድንጋይ እንዲመጣላቸው ሲጠይቁ ድንጋዩ ትልቅ በመሆኑ የተነሳ የታዘዘው ሰው ድንጋዩን ማንሳት ባለመቻሉ ነብዩ (ሶ) እራሳቸው አንስተው የሚቹ (የተቀበረው ሰው) ራስ በኩል እንዳስቀመጡና:-

***"የወንድሜ ቀብር እንዲታወቅና ከቤተሰቤ የሆነ ሰው ሲሞት አጠገቡ እንድቀብረው እፈልጋለሁ፡፡"*** ስለማለታቸው ሱነህ አል-በይሀቂ 3/412-ሐዲስ 6530 ይመልከቱ፡፡

ቀብርን ማሳመርና ቅርጽ እያወጡ ማስተካከልን (ከፍ ማድረግን) በተመለከተና የነብዩ (ሶ) ቀብር እንዲህ እንደተደረገ ደግሞ፡- *ሱነን አል-በይሐቂ፡* 413 -ሐዲስ 6551 እና 6552፣ ቡኻሪ ያወራውንም በመጥቀስ እንዲያውም የነብዩ (ሶ) ቀብር ግድግዳ በወሊድ ቢን ዓብደል መሊክ ዘመን ወይም (በዑመር ቢን ዓብደልዓዚዝ ዘመንም ተብሏል) እንደፈረሰና መልሰው አስተካክለው እንዳደሱት ተጠቅሷል፡፡

ቀብርን ከፍ አድርጎ መስራትና እድሳቱን መከታተል የተወደደ ተግባር መሆኑን፣ የአቡ በክርና ዑመር ቀብሮችም ምስክር መሆናቸውንና በዚህ ጉዳይ ላይ አቡ ሐኒፋ፣ ማሊክና አህመድ እንዲሁም አብዛኛው ሻፊዒዎች ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው፣ *በፈትህ አልባራ- አል-ዓስቀላኒ አል-ሻፊዒ (3/257* ይመልከቱ፡፡

በተጨማሪም በ *ዐውን አል-መዕቡድ-* 9/29 ላይ ቡኻሪ የዘገበውን ሐዲስ በመጥቀስ የነብዩ (ሶ) ቀብር *ሙሰነም* ወይም *ሙርተፈዕ* (ከፍ የተደረገ) ስለመሆኑ በሰነድ መጠቀሱን እናያለን፡፡

ስለ ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ መሷድሮችን መጥቀስ ካስፈለገ፡-

-ተህፋት አል-አህወዚ 4/130፣ -ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባ 3/28- ሐዲስ 11801፣ -አል-ሙሐላ- አቢ ሙሃመድ አል-ዟሂሪ (5/134)፣ ነይል አል-አውጧር -ሸውካኒ (4/132)፣ አል-ሙስተድረክ ዐላ-አስ-ሶሂሀይን አል-ሀኪም (1/524)፣ ሱነን አል-ቲርሚዚ (3/368)

---

በተለይ ቀብርን መለሰን (መምረግን) በተመለከተ አንዳንድ ምሁራን (ለምሳሌ ሀሰን አል-በስሪ) እንዳልተቃወሙና አል-ሻፊዒ ምንም ችግር እንደሌለበት መጠቀሱን እናያለን ፡፡

-ቀብርን በጨርቅ/ልብስ መጠለልን በተመለከተ ነብዩ (ሶ) የሰዓድን ቀብር በልብስ ስለመጠለላቸው ደግሞ በሱነን አል-በይሀቂ 4/54 እናገኛለን በተጨማሪም፡-

- ሙሰነድ ኢብን አቢ ሸይባ 3/16 ሐዲስ 11667፣ -ሙሰነድ ኢብን ጀዕድ 1/192 ሐዲስ 1286፣ -መዕጀመዕ አል-ከቢር-ጦበራኒ 12/228- ሐዲስ 12963፣ -ሱነን አል በይሐቂ 4/56 ሐዲስ 6860፣ -ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባ 3/22 ሐዲስ 11826፣11827፣11828፣ 11829፣11830፣11831፣11832፣11833፣11834፣11835፣11836፣11837፤ በ3/23 እንዲሁ ሐዲስ 11840፣11845፣11846፣11847፡፡ በ3/24 ደግሞ ሐዲስ 11850 እና 11851፡፡ -በሙሰነፍ ዓብደረዛቅ አል-ሰንዓኒ 3/478 ሐዲስ 6389፤ 3/502 ሐዲስ 6484፤ 3/503 ሐዲስ 6485፤ 3/504፤ 3/574 ሐዲስ 6818::

## የቀብር ዚያራ

ቀብሮችን መዘየር ጃኢዝ (የተፈቀደ) መሆኑን እና ብሎም የተወደደ (ሙስተሃብ) ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡

ቀብር መዘየር ውስጥ ማስተንተንና መፍራት ለፈለገ ሰው ጠቃሚ ትምህርትና ተግሳጽ አለ፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በርካታ የሆኑ ሐዲሶችን ይገኛሉ፡፡[166]

---

[166]በርካታ የሆኑ የአህለልቤይት ሀዲሶች እንዳሉ ሁሉ በአህለሱና መፏድሮችም ብዙ እናገኛለን፡፡

-በሙሰነፍ አብደረዛቅ አል-ሰነዓኒ 3/569 ሐዲስ 6708 ላይ ነብዩ (ሶ) ቀብር መዘየርን ከልክለው እንደነበርና ከዚያ ግን እንደፈቀዱና አኺራን እናስታውስ ዘንድ መዘየር እንዳለብን መናገራቸው ተጠቅሷል፡፡ በ3/580፣3/581 ሐዲስ 6809 ላይ ደግሞ ነብዩ (ሶ):-

***"ወደ ሙታናችሁ (ወደ ሞቱባችሁ ሰዎች) ሂዱና በነሱ ላይ ሰላምታ ቅሩ (በሉ)፣ በዚህ ውስጥ ትምህርትና ተግሳጽ አለላችሁ"*** ማለታቸውን እናገኛለን፡፡

በተጨማሪም በዚሁ ምንጭ ላይ ዓኢሻ በሀብሻ አከባቢ ሞቶ በመካ የተቀበረውን ወንድሟን አብድረህማን ቢን አቢበክር ቀብርን ስትዘይር ኢብን አቢ ሙለይካ አይቶ መናገሩ ተጠቅሷል፡፡ በሐዲስ 6812 ላይ ደግሞ የነብዩ (ሶ) ባለቤት ዓኢሻ ነብዩ (ሶ) ሲያደርጉ ባየችው እና በተረከችው ረዥም ታሪክ ውስጥ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) በአንድ ወቅት ሌሊት ላይ ተቻኩለው ከእንቅልፋቸው በመነሳት ተጣድፈው እንደወጡ፣ ሁኔታውን ለማየት ተከትላቸው እንደወጣችና በመቃብር ስፍራ ላይ እጃቸውን ዘርግተው በቂዕ ለተቀበሩት ሙታን ዱዓ ሲያደርጉ እንዳየች፣ ከዚያም ተጣድፈው ወደ ቤት ሲመለሱ ተከታትላ ሮጣ ቀድማቸው ቤት እንደደረሰች፣ ለምን ተከትላቸው እንደወጣች እንደጠየቋት፣ ብዙ ከተነጋገሩ በኋላ በመጨረሻም ለምን ተከትላቸው እንደወጣች እንደተናገረችና እንደገሰጿት ከተረከች በኋላ ነብዩ (ሶ) ወደ በቂዕ ተጣድፈው ለምን እንደወጡ እንደሚከተለው እንደነገሯት ተርካለች፡፡ እንዲህም አሏት፡-

***"በርግጥ ጅብሪል መጥቶኝ ነበር፡፡ ልብስሽን አውልቀሽ ስለነበር ወደ ቤት አይገባም፡፡ አንቺ እንዳትሰሚ አድርጎ ጠራኝ፡፡ እኔም ካንቺ ደብቄ ምላሽ ሰጠሁ፡፡ የተኛሽ ስለመሰለኝ ልቀሰቅስሽ አልወደድኩም፤ ብቻሽን እንዳትፈሪም ፈራሁ፡፡ ከዚያም ወደ በቂዕ ሰዎች ሂጄ እስቲግፋር እንዳረግላቸው ጠየቀኝ፡፡*** እሷም፡-***"እኔስ እንዴት ነው ማለት ያለብኝ"?*** አልኩ አለች፡፡

ነብዩም (ሶ) ***"አሱሰላሙ ዓላ አህለ አል-ዲያር ሚነል ሙእሚኒን ወልሙሰሊሚን ወረህመላሁ አል-ሙስተቀድሚነ ሚንና ወል ሙስተእኺሪን ወኢንና ኢንሻአላሁ ለላሂቁን"*** በይ አሏት፡፡

እንዲሁም በሙሰነፍ ዓብደረዛቅ አል-ሰንዓኒ 3/572- ሐዲስ 6814 ላይ በአንድ ወቅት ነብዩ (ሶ) ወጥተው ሲሄዱ ሰሀቦች እንደተከተሏቸውና በአንድ የመቃብር ስፍራ ሲደርሱ እንዲቆሙ እንዳዘዟቸው፣ ከዚያም ነብዩ (ሶ) ከመቃብሮች ውስጥ አንድ ቀብር ላይ ሲደርሱ ቁጭ ብለው ለረዥም ጊዜ ዱዓእ ሲደርጉ ቆይተው ስቅስቅታቸው ከፍ ብሎ እስከሰማ ድረስ ስቅስቅ ብለው ሲያለቅሱ ሰሀቦች እጅግ ተደናግጠው ከሳቸው ጋር እንዳለቀሱ ተተርኳል፡፡

ከዚያ በኋላ ነብዩ (ሶ) መለስ ሲሉ ዑመር ቢን ኸጣብ አገኛቸውና፡- ***"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ምንድን ነው ያስለቀሰዎ? እኛም አለቀስን፣ ተደናገጥን እኮ"*** አላቸው፡፡ በዚህን ጊዜ የዑመር ቢን ኸጣብን እጅ ያዝ አድርገው ወደሳቸው እንድንመጣ ምልክት ሲሰጡን ወደ እሳቸው ቀረብን፡፡ ከዚያም ነቢዩ (ሶ)፡- ***"ለቅሶዬ አስደነገጣችሁ"?*** ብለው ጠየቁ፡፡

እነሱም ***"አዎ የአላህ መልእክተኛ ሆይ"*** አሉ፡፡

እሳቸውም (ሶ)፡- ***"አጠገቡ ያያችሁኝ ቀብር የእናቴ አሚና ቢንት ወህብ ቀብር ነው፡፡ እንድዘይራት ከጌታዬ ፈቃድ ጠይቄ ፈቀደደለኝ"*** አሏቸው፡፡

-ቀብር ላይ የሚቀራ ሰላምታ እንዴት እንደሆነ ደግሞ በ3/574 ሐዲስ 6718 እንዲሁም በ3/575 ሐዲስ 6719 ላይ እናገኛለን፡፡

በሐዲስ 6720 ላይ ደግሞ ነብዩ (ሶ) ከሰሀቦቻቸው ጋር ሆነው በቂዕ የመቃብር ስፍራ ላይ እያሉ በሙታኑ ላይ ሰላምታ ከቀሩ በኋላ ከሳቸው (ሶ) በኋላ ከሚከሰተው ፈተናና ከዲኑ የማፈንገጥ ኪሳራ እንደዳኑ እያሞገሷቸው ሲናገሩ ተሰምቷል፡፡

ከዚያም ወደ ሰሀቦቹ ዞር ብለው (በዚህ ጊዜ የቀደምትና ታላላቅ የሚባሉ ሰሀቦቹም እንዳሉ ተጠቅሷል) የሚከተለውን እንዳሏቸውም ተዘግቧል፡፡

***"ለመሆኑ ከናንተ እና ከነዚህ (ሙታን) ማን የሚሻል (የሚበልጥ) ይመስላችኋል?"***

ሰሃቦቹም፡-***"ከኛ የተሸሉ እንደማይሆኑ እንመኛለን፤ እኛም ልክ እንደነሱ ተሰደናል፣ እነሱ እንደታገሉ እኛም ታግለናል"*** አሉ ፡፡

ከዚያም እንዲህ ይሏቸዋል፡-

***"በእርግጥ ከናንተ በጣም ይሻላሉ፡፡ ከደሞዛቸው ምንም ሳይበሉ ሞቱ፡፡ እናንተ ግን ከደሞዛችሁ እየበላችሁ ናችሁ፡፡ እነሱ በእርግጥ አለፉ፤ እኔም በመልካም መሰከርኩላቸው፡፡ እናንተ ግን ከኔ በኋላ ምን መጥፎ ነገር እንደምትፈጥሩና መጨረሻችሁ ምን እንደሚሆን አላውቅም!!"***

-በሐዲስ 6721 ደግሞ ኢብን ዑመር በመቃብር ስፍራ ባለፈ ቁጥር ሰላምታ ሳይል አልፎ እንደማያውቅ የሚያትት ሀዲስ እናገኛለኝ፡፡

-በ3/576 ሐዲስ 6723 እንዲሁ አቡ-ሁሬይራ ከአንድ ጓደኛው (ሰሃባ) ጋር ሆነው በበቃብር ቦታ ሲያልፉ አቡ-ሁሬይራ ጓደኛው በቀብሩ ላይ ሰላምታ እንዲያወርድ እንደነገረው እና ሰውየው ለምን ቀብር ላይ ሰላምታ ማለት እንዳለበት ሲጠይቅ አንድ ሟች በዱኒያ ላይ አንድ ጊዜ እንኳን ቢሆን አይቶት የሚያውቅ ከሆነ አሁን ከቀብሩም ሆኖ ጠያቂውን እንደሚያውቅ ያስረዳበትን ዘገባ እናገኛለን፡፡

በሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሐይን 1/526 ሐዲስ 1373 ላይ ዑስማን ቢን ዓፉን በቀብር ቦታ ሲያልፍ ሁልጊዜ ጺሙ እስኪርስ ድረስ እንደሚያለቅስና ጀነትና ዐዛብን ባስታወሰ ጊዜ እንደዚያ ሳያለቅስ ቀብር ላይ ግን ለምን እንዲያ አምርሮ እንደሚያለቅስ ሲጠየቅ፣ ቀብር ማለት የጀነትም የዐዛብም መጀመሪያ (መግቢያ) እንደሆነና እዛ ያለው ጉዳይ ቀላል ከሆነ ሌላው ሁሉ ገር እንደሚሆን የተናገረበት ዘገባ እናነባለን፡፡ በአጠቃላይ አንድ ሰው ቀብር ቦታ ሲሄድ ምን ማለት እንዳለበት፣ ነብዩ(ሶ) አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ ከስፍራው ከመመለሳቸው በፊት የተወሰነ ጊዜ ወደ ቀብሩ ዞሮ በመቀመጥ እንደሚቆዩ፣ ነብዩ (ሶ) ሆኑ ሰሀቦች መቃብር ስፍራ ሄደው ያለቅሱ እንደነበር እናያለን፡፡

እንዲሁም ከቀብር ዚያራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ክስተቶችን ለማወቅ ተጨማሪ ዝርዝር ካስፈለገ ከብዙ ጥቂቱን ለመጥቀስ፡-

-ሱነን አል-ቲርሚዝ 3/309 ሐዲስ 1053፣3/370-371 ሐዲስ 1054::

-ሱነን አቡ ዳውድ 3/217 ሐዲስ 3230 ፣3/218-219 ሐዲስ 3234፣3235፣ 3237፡፡

-ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባህ 3/27 ሐዲስ 11782፣11783፣ 11784፣11785፣ 11786፣ 11786፣ 11787፣ 11788፣ 11789.11790፤ 3/29 ሐዲስ 11804፣ 11805፣ 11806፣ 11807፣ 11808፣ 11809፣ 11810፤ 3/30 ሐዲስ 11813::

-በአቢ-በክር አል-በይሐቂ -*ሹዐብ አል-ኢማን* 3/484 -ሐዲስ 4137፣ 3/491 ሐዲስ 4164፡፡

-ሸርህ አል-ዘርቃኒ 1/477:: -ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ 5/249 ሐዲስ 10077::

-ተፍሲር አል-ጠበሪ -13/142:: -ተፍሲር ኢብን ከሲር 2/512::

-አል-ሙስተድረክ ዓለ አል-ሰሂሐይን 3/331 ሐዲስ 4320::

-አል -ሐንበሊ አል-ሙቀደሲ -አል-አሀዲስ አል-ሙኪታር 3/14::

-ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ 5/249:: -ሙሰነፍ ዓብደረዛቅ 3/573 ሐዲስ 6716፡፡

-አቢል መሐሲን አል-ሐነፊ በአል-ሙክተሰር አል-ሙክተሰር 2/349::

-ሙሰነድ አል-ባዛር 3/169:: -ሙሰነድ አህመድ 1/161 ሐዲስ 1387::

-ኢብን ዓብድል በር አል-ተምሒድ 20/245-246:: -ተፍሲር አል-ቁርጥቢ 10/381:: -ሱነን አል-ቲርሚዚ 3/371 ሐዲስ 1055፣ በርካታ ምንጮች...

## ሴቶችና የቀብር ዚያራ

ሴቶች የበቂዕ መቃብር ስፍራና ሌሎች የነብያት፣ የንጹሀን ኢማሞችና የሷሊሆች መርቀዶች መግባታቸው በሸሪዓው የተወደደ ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡

ይኸውም ቁርጥ ባለ ደሊል (ማስረጃ) በልዩነት የተደነገገ ሲቀር በሸሪዓ አህካሞች (ህግጋትና መመሪያዎች) ወንድና ሴት እኩል በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሞ ስለመፈቀዱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንጅ ስለ መከልከሉ ምንም ደሊል የለም፡፡[167]

---

[167]-በተፍሲር አል-ቁርጥቢ 10/381 ላይ የአላህ መልክተኛ (ሶ) ልጅ ፋጢማ አል-ዘሕራ የሀምዛ ዓብደል ሙጣልቢን ቀብር ሁል ጊዜ ጁምዓ ቀን ትዘይር እንደነበርና ቀብሩን ለይታ የምታውቅበት ትልቅ ድንጋይ ለምልክት እንደነበረው እናያለን፡፡

በሱነን አል-ቲርሚዝ 3/377 -ሐዲስ 1056 ደግሞ ነብዩ (ሶ) በአንድ ወቅት ሴቶችን ቀብር ዚያራን ይከለክሉ እንደነበር፣ እንዲያውም እንደዛ የሚያደርጉትን ይራገሙ እንደነበርና በኋላ ላይ ግን እንደፈቀዱላቸው እናያለን፡፡ ሴቶች የተከለከሉበት ምክንያትም ትግስታቸው አነስተኛ ስለሆነና እጅግ ስለሚደነግጡ መሆኑን አንዳንዶቹ አስተያየታቸውን መስጠታቸውን ተጠቅሷል፡፡

-በዚህ ክፍል በሐዲስ 1055 ደግሞ ዓኢሻ የወንድሟን የዓብድረህማን ቢን አቢ በክርን ቀብር ትዘይር እንደነበርና በአንድ የዚያራ ወቅት የተቀኘችውም ግጥም ተጠቅሶ እናያለን፡፡

-እንዲሁ በሙሰነፍ ዓብዱረዛቅ አል-ሷንዓኒ -3/572 ሐዲስ 6713 ላይ የነብዩ (ሶ) ልጅ ፋጡማ አል-ዘሐራ በየሳምንቱ ጁሙዓ ቀን የሐምዛ ቢን ዓብደል ሙጠሊብ ቀብር ትዘይር እንደነበር በድጋሚ እናገኛለን፡፡

በተጨማሪም በ3/571 -ሐዲስ 6711፤ በ3/576 ሐዲስ 6722፣ እንዲሁም በሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባህ 3/29- ሐዲስ 11811 የነብዩ (ሶ) ባለቤት አዒሻ ከመካ በአስራ ሁለት ማይል ላይ በሚገኘው ቦታ ሞቶ በመካ የተቀበረውን ወንድሟን ትዘይር እንደነበርና ለቀብር ዚያራ ሲኬድ ምን ማለት እንዳለባት ነብዩን (ሶ) ጠይቃ እንደነገሯት የሚያትቱ ሐዲሶችን እናገኛለን፡፡

እንዲሁም *"ነዋደር አል ኡሱል ፊ አሓዲስ አል-ረሱል"* በተሰኘው የአብደላህ አል-ሐኪም አል-ቲርሚዚ መጽሀፍ 1/126 ላይ ፋጢማ አል-ዘሀራ የሀምዛ ቢን ዓብደልሙጣልቢን ቀብር

## በበቂዕ የመቃብር ስፍራ ውስጥ መስገድ

በበቂዕ ውስጥ ወይም በነብያት፣ በንጹሀን ኢማሞች እና በሷሊሆች (ዐ) መርቀዶች (የመቃብር ቦታዎች) ውስጥ መስገድ በሸሪዓው የተወደደ ተግባር እንደሆነና የሚከለክል ደሊል አለመኖሩን እናምናለን፡፡[168]

አላህ (ሱ.ወ) በአስሀብ አል-ከህፍ ታሪክ ውስጥ እንዲህ ብሏል፡-

لَنَتَّخِذَنَّ عَلَيْهِمْ مَسْجِدًا

---

በየዓመቱ ታድስና ታስተካክል እንደነበርና በርካታ ሴቶችም ቀብሩን ይዘይሩ እንደነበረ ተጠቅሷል፡፡

-በሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/331- ሐዲስ 4320 ላይ አል-ዓጣፍ የተባለ ሰው (ሰሀባ) አክስቱ ያጋጠማትን ነገር እንደ ነገረችው ሲተርክ፣ አክስቱ የሸሂዶችን ቀብር ትዘይር እንደነበር በሸሂዶቹ ላይ ሰላምታ ስትቀራ አጸፋውን እንደመለሱላትና እርስ በርሳቸው እንደሚተዋወቁ ሁሉ በህይወት ያሉትንም እንደሚያውቁ ሲነግራት እንደ ደነገጠችና ሁለት እረኛ ህጻናት ብቻ ከሷ ጋር እንደነበሩ፣ ከቀብሩ ውስጥ በሰማቸው መልስና ንግግር ተደናግጣ አንዱ ልጅ በፍጥነት በቅሎዋን እንዲያቀርብላት መጠየቋንና ከዛ ቦታ በድንጋጤ ተውጣ በቅሎዋ ላይ ወጥታ እንደሄደች የሚተርክ ሀዲስ እናገኛለን፡፡

[168] በዚህ ጉዳይ ላይ ከተጠቀሱ ሀዲሶች ውስጥ፡-

-*አል አሓዲስ አል-ሙክታራ* በተሰኘ የሀንበሊ አል መቅዲሲ ኪታብ 4/106 እንዲሁም *መዋሪድ አል-ዘምዓን* በተሰኘው የሄይሰሚ ኪታብ 1/485 ላይ ደግሞ ኡሳማ ቢን ዘይድ የነብዩ (ሶ) ቀብር አጠገብ ይሰግድ እንደነበረ ያዩ ሰዎች የተናገሩትን እናነባለን፡፡

እዚህ ላይ አንዳንድ የአህለሱና ዑለማዎች የመቃብር ስፍራን የመስገጃ ቦታ አድርጎ መያዝ የተከለከለ ነው ሲባል በቦታው ፈሳድ (መጥፎ) የሆነ ተግባር መፈጸም ጋር የተያያዘ ከሆነ እንጅ ጭራሹኑ የተከለከለ ማለት እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

ከታማኝ ታቢኢኖች የሆነውና አል-ኒሳኢ ሐዲስ የዘገቡለት ሐሰን ቢን ሐሰን በሞተ ግዜ ባለቤቱ መቃብሩ ላይ ዳስ ቀልሳ ለዓመት ያህል እዛ ቦታ እንደኖረች ተዘግቧል፡፡ በዳስ ውስጥ ያን ያህል ዘመን የኖረ ሰው ደግሞ ሰላት ከመስገድ መወገድ አይችልም፡፡ ስለዚህ የመቃብር ስፍራውን የመስገጃ ቦታ አድርጎ መያዙ የግድ ይሆናል ማለት ነው፡፡ (ፈትሁል ባሪ-3/200 ይመልከቱ)፡፡

**"በነሱ ላይ መስጅድ በእርግጥ እንይዛለን (እናደርጋለን)፡፡"[169]**

ይህም ማለት ለብዙ ዓመታት የሞቱ መስለው የተኙት ቦታ ላይ መስጅድ እንሰራለን ማለታቸውን በቁርዓን ተተርኳል፡፡

## በኢማም ሁሴን (ዐ) ላይ ማልቀስና ማዘን

በነብዩ (ሶ) እና በንጹሃን አህለልበይቱ ላይ የደረሰውን በደልና መከራ በመዘከር ማዘን የሚበቃ (ያልተከለከለ) ተግባር መሆኑንና እንዲያውም የተወደደ ተግባር መሆኑን እናምናለን፡፡ ለዚህም ነው በተለይም ሸሂድ በሆኑት በኢማም ሁሴን ቢን ዓሊ ቢን አቢጣሊብ (ዐ) የሀዘንና ለቅሶ ስርዓት የሚካሄድባቸውን ቦታዎች መርሃግብሮች የምናዘጋጀው፡፡ በእርግጥ ነብዩ (ሶ) ለአጎታቸው ሐምዛ (በኡሁድ ትግል ላይ የተሰው) እንድናለቅስ አዘዋል፡፡

ነብዩ (ሶ) እራሳቸው ኢማም ሁሴን (ዐ) ገና ሸሂድ ከመሆናቸው በፊት አልቅሰዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ ከመጀመሪያው የኢስላም ዘመን ጀምሮ ይሄንኑ የነብዩን ሱና ልምዳቸው አድርገው ይዘዋል፡፡

-በሙክተድረክ ዓለ አል-ሰሂሀይን 3/218፣ ሐዲስ 4893 ላይ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ሐምዛ በሞቱ ጊዜ እጅግ እንዳለቀሱና የደረሰበትን የጭካኔ ተግባር ገልጠው ሲያዩ  እስኪተናነቃቸው ድረስ አምርረው ማልቀሳቸውን እናያለን፡፡ በ 1/537፣ ሐዲስ 1408 ላይ ደግሞ ነብዩ (ሶ) ከኡሁድ ዘመቻ ሲመለሱ የአንሷር ሴቶች ሲያለቅሱ በሰሙ ጊዜ፡-

---

[169] አል-ካህፍ: 21

***"ለሐምዛ ግን የሚያለቅስለት የለም"*** ሲሉ ሶቶች ይህን በሰሙ ግዜ ለሐምዛ እንዳለቀሱ ተዘግቧል፡፡ ከዚያ ጊዜ አንስቶ የመዲና ሴቶች ለሞቱባቸው ሰዎች ሲያለቅሱ በመጀመሪያ በሐምዛ ይጀምሩ እንረደነበርና እስከ ዘመናችን ድረስ ዘልቆ የመጣ ልምድ መሆኑን የሀዲስ ተራኪ ያወሳል፡፡ በተጨማሪም ለሞተ ሰው ማልቀስና ሐዘን መግለጽን በተመለከተ በዓብደላህ ቢን ዑመር እና አብደላህ ቢን አባስ መካከል ክርክር በተፈጠረ ወቅት ጉዳዩን ወደ ዓዒሻ በወሰዱ ግዜ፡-

***“በአላህ እምላለሁ! የአላህ መልክተኛ (ሰ) አንድ ሟች በቤተሰቡ ለቅሶ የተነሳ ይቀጣል አላሉም፡፡ ነገር ግን ነብዩ (ሰ) ያሉት አንድ ካፊር (ከሐዲ) በሞተ ጊዜ በቤተሰቡ ለቅሶ የተነሳ ቅጣቱ (አዛብ) ይጨምራል ነው ያሉት፡፡ በርግጥ የሚያስቅም (የሰው ልጅ እንዲስቅ የሚያደርግ) እንዲሁም የሚያስለቅስ አላህ ነው፡፡ አንዱ የሌላውን ወንጀል አይሸከምም፡፡ (የአንድ ሰው ወንጀል ወደ ሌላው አይደርስም)”*** ማለቷን እናነባለን፡፡

-በዚሁ የአል-ሐኪም አል-ኔሳቡሪ በሆነው *ሙስተድረክ ዓለ አል-ሰሒሐይን* በተሰኘው ኪታብ 1/507፣ ሐዲስ 1406 ላይ ደግሞ በአንድ ወቅት ነብዩ (ሶ) ወደ አንድ ጀናዛ (የሞተ ሰው) በወጡ ጊዜ ሴቶች እያለቀሱ እንደነበርና በቦታው የነበረው ዑመር ቢን ኸጣብ ሴቶችን በተቆጣቸውና ከለቅሷቸው ለመከልከል በሞከረ ግዜ ነብዩ (ሶ)፡-

***"ዑመር ሆይ!ተዋቸው! በእርግጥ ዓይን ታለቅሳለች፣ ነፍስም ታዝናለች፣ ቀጠሮው ቅርብ ነው"*** ማለታቸውን በሁለቱ ሸይኮች (ቡኻሪና ሙስሊም) መርህ መሰረት ሰሂህ በሆነ ሀዲስ መጠቀሱን እናያለን፡፡

እንዲሁም ተመሳሳይ ሐዲስ ከተጨማሪ ዝርዝር ጋር ቀደም ሲል በተጠቀሰው መስደር 3/219፣ ሐዲስ 4900 ላይ እናገኛለን፡፡ የሐምዛን መሰዋት ተከትሎ ነብዩ (ሰ) የወሰዱትን እርምጃ በተመለከተ ከብዙ መሷድሮች ጥቂት ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለመጥቀስ ያህል፡-

*መጅመዕ* አል-ዘዋኢድ 6/118 እና 119፣ አቡ በክር አል-ኪናኒ- *ሚስባህ አል-ዙጃጃ* 2/47 እና 48፣ ሸርህ *መዓኒ* አል-ኣሳር 4/293፤ *ሙ*ስነድ አል-ሻሺ 2/413፤ አል-ጦበራኒ *ሙ*አጀም አል-ከቢር 3/142፡፡

በኢማ ሁሴን (ዐ) ላይ ማልቀስ ያለውን ፈዲላ በተመለከተ በርካታ የአህለል በይት (ዐ) ሪዋያዎች እንዳሉ ሆኖ በአህለ ሱና ኪታቦች የተጠቀሱትን ሐዲሶች በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፡-

-በሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል 1/86፣ ሐዲስ 648 ላይ አንድ ሰሃባ (የሐዲሱ ተራኪ) ከኢማም ዓሊ (ዐ) ጋር ለጉዞ በወጡበት ወቅት ወደ ሲፊን በሚወስደው መንገድ ላይ የምትገኝ ነይነዋ (ነነዌ) የምትባል ቦታ ሲደርሱ ኢማም ዓሊ (ዐ) ፡-

***"አባ ዓብደላህ ሆይ! ታገስ፣ አባ ዓብደላህ ሆይ ታገስ በኢፍራጥስ ዳርቻ"*** እያለ መጣራቱንና ስለ ጉዳዩ አብሮት የነበረው ሰው በጠየቀው ግዜ የሚከተለውን እንደነገረው እናያለን፡፡

"በአንድ ወቅት ወደ ነብዩ (ሰ) ገባሁ፤ የነብዩ (ሰ) ዓይኖችም እንባ ያዘንቡ ነበር፡፡ እኔም እንዲህ ስል ጠየቅኳቸው፡- ***"ምነው የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ያስለቀሰዎት ሰው አለ እንዴ? ዓይኖችዎ እንባ እያዘነቡ ነውሳ?"***

እሳቸውም (ሶ)፡- ***"ሁሴን በኢፍራጠስ ዳቻ እንደሚገደል ጅብሪል አሁን ነው ነግሮኝ የሔደው"*** አሉ፡፡

ቀጠል በማድረግም ***"አፈሩን ታሸት ዘንድ ልስጥህን?"*** አሉት፡፡

ኢማም ዓሊም (ዐ) "አዎን!" አላቸው፡፡

ከዚያም ኢማም ዓሊ (ዐ)፡-***"ከዚያም ነብዩ (ሶ) እጃቸውን ዘርግተው የተወሰነ አፈር ከዘገኑ በኋላ ሰጡኝ፤ በዚህ ጊዜ እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም፤ አይኖቼ እምባ አፈሰሱ"*** በማለት መተረኩን እናነባለን፡፡

-ተመሳሳይ ሐዲስ በሐንበሊ አል-ሙቅዲሲ አል-አሓዲስ አል-ሙኽታራ 2/375 ላይ እናገኛለን፡፡

-እንዲሁ በመጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/178 ላይ ከዓኢሻ በተያዘ ሐዲስ የሁሴንን "ጠፍ" በተባለ ቦታ መገደል ጅብሪል በነገራቸው ጊዜ እጅግ ማልቀሳቸውን፣ ጅብሪልም ኢማም ሁሴን (ዐ) ከሚገደልበት ቦታ ያመጣውን አፈር እንደሰጣቸውና ጅብሪል ከሄደ በኋላ ነብዩ (ሶ) አፈሩን ይዘው እንዳለቀሱ፣ ወደ ሰሃቦቻቸው እንደወጡና ከሰሃቦቻቸው መካከልም ዓሊ፣ አቢ በክር፣ ዑመር፣ ሑዘይፋ፣ ዐማር እና አቡዘር እንደነበሩ፣ ለምን እነደሚያለቅሱ ሲጠይቋቸው ታሪኩን በዝርዝር እንደነገሯቸው እናነባለን፡፡

ይህን ሐዲስ የ አል-ጦበራኒ *አል-ከቢር*እና *አል-አውሰጥ* ውስጥ እናገኛለን፡፡

-በተመሳሳይ ሁኔታ በመጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/178 ላይ ኡሙ ሰለማህ በምትተርከው ሐዲስ ውስጥ ይህንኑ ታሪክ በዝርዝር እናያለን፡፡

ተጨማሪ ምንጭ ካስፈለገም፡- -ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሼይባህ 7/477፣ ሐዲስ 37366 እና 37367፤ ሙሰነድ አል-በዛር 3/101፣ ሙስነድ ኢብን ያዕላ

1/298፣ አል-አሃድ ወ አል-መሳኒ 1/308፣ አል-ሙዕጀም አል-ከቢር 3/105 እና ሌሎችም፡፡

በሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሐይን 3/194 ሐዲስ 4818 ላይ ደግሞ ኡሙል ፈድል ቢንት ሓሪስ ያየችውን ህልም ለነብዩ (ሶ) በተናገረች ጊዜ ስለ ሁሴን መወለድ መሆኑን እንደነገሯትና በተወለደም ጊዜ ነብዩ (ሶ) እንዳለቀሱ፣ ጅብሪል የከርበላን አፈር እንደሰጣቸውና አፈሩን እያሸተቱ ምርር ብለው እንዳለቀሱና የሁሴንን አሟሟት ለኡሙልፈድል የተረኩበትን በሁለቱ ሼኮች (ቡኻሪና ሙስሊም) መርህ መሰረት ሰሂህ የሆነን ሐዲስ እናገኛለን፡፡በመጅምዕ አል-ከቢር- አል-ጦበራኒ 23/289 እንዲሁ ከኡሙ ሰለማህ የተያዘ ተመሳሳይ ዘገባ እናገኛለን፡፡

## ታዲያ ስድብና ማከፈርን ምን አመጣው ?

ለዚህ ሁሉ ሸሪዓዊና ዐቅላዊ (አዕምሮአዊ) ማስረጃዎችና ደሊል እያለን፣ በሁሉም የኢስላም ሀገራት ውስጥ የተሰራጩ የተለያዩ ለህትመት የበቁ በርካታ መጽሀፍት ውስጥ የተጠቀሱ በቂ ማስረጃዎች እያሉንና ለእምነታችንና አስተሳሰባችን ሸርዓዊ የሆነ መሰረት ያለን ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ክፍሎች የሺዓ ኢማሚያ አማኞችን በኩፍርና በፊስቅ መፈረጃቸው ለምንድን ነው!?

አንድ ሙስሊም ሌላውን ሙስሊም ማከፈር፣ መሳደብና በፋሲቅነት መፈረጅ አይገባም፡፡ በኢጅቲሀድ ውስጥ በተፈጠረ መለያየት (ኢክትላፍ) ብቻ እንደዚህ መወነጃጀል ፍጹም አይገባም፡፡ መሆን ያለበት አንዱ ክፍል የሌላውን ደሊል (ማስረጃዎች) እና የሸሪዓ ምንጮች ማወቅና መረዳት ነው፡፡

ሙስሊሞች እርስበርሳቸው በመከፋፈር፣ በመሰዳደብና አንዱ ሌላውን በፋሲቅነት በመፈራረጅ ኃይላቸውን ከማባከን ፋንታ አንድነት ፈጥረው ኃይላቸውን በማሰባሰብ የኢስላም ጠላቶችን በጋራ መከላከልና ሀገራቸውን ከዘራፊዎች መታደግ ግዴታ አይደለም እንዴ!?

## ግዴታ የሆኑ ተግባራትና ኢስላማዊ ህግጋት

ሶላት መስገድ፣ ጾም መጾም፣ ኹምስና ዘካ መክፈል፣ ሐጅ፣ ጂሓድ፣ በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል፣ የአላህ ወዳጆችን መወዳጀት፣ ከአላህ ጠላቶች መጥራት (የአላህን ጠላቶች ጠላት አድርጎ መያዝ)፣ ዋጂብ የሆኑ (ግዴታ የሆኑ) ትዕዛዛትን መፈጸም፣ ሐራም (እርም) ከሆኑ ነገሮች መታቀብ፣ ከብልሹ ባህርያትና ተግባራት መጽዳት፣ በምስጉን ባህርያትና ተግባራት መታነጽ ግዴታና አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን፡፡

በሁሉም ክፍል ያሉትን ሁሉንም የኢስላሞ አህካሞች (መመሪያዎችና ህግጋት) መታዘዝና መተግበር ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡ ከዒባዳዎች፣ከሙዓመላት፣ ከፍርድ፣ ምስክርነት፣ ከፍትሃብሔርና ወንጀል ፍርድ ቅጣት፣ ካሳ፣… ሌሎች በኢስላማዊ ፊቅህ ውስጥ ተደንግገውና ተጽፈው ያሉትን እስከ አንድ መቶ ሺ የሚደርሱ ህግጋትን በሙሉ በተግባር ላይ ማዋል ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡

በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ ህዝብና ሀገር፣ ስነ-ስርዓትና ስነ-ምግባር ነክ ጉዳዮች፣ በማህበራዊ ትስስር ኑሮ፣ በጋብቻና በፍች ስርዓቶች፣ በወንጀልና ፍርድ (ቅጣት) እና ሌሎችም… በሁሉም ማህበራዊና ግለሰባዊ ጉዳዮች ከኢስላም ጋር የሚጣጣም መሆኑንም እናምናለን፡፡

## ኢስላማዊ ሥነ-ምግባር

በምስጉን ባህርያትና በኢስላማዊ አደብ (ሥነ-ስርዓት) መታነጽና ከማንኛውም እኩይ ምግባርና በሸሪዓው እርም (ሐራም) ከሆኑ ባህርያትና ተግባራት መታቀብና መራቅ ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህ ባህላችን (ልማዳችን) ነው፡፡ በተግባርም የምናሳየው ይህንኑ ነው፡፡

ኢስላማዊ አኽላቅ (ስነ-ምግባር) ማለት ኢስላም ያዘዘው ወይም ግዴታ ያደረጋቸው እንደ እውነተኛነት (ሐቀኝነት)፣ አደራ ጠባቂነት (አማና)፣ ሐያዕ (ይሉኝታ/ህፍረት)፣ ጨዋነት፣ ጀግንነት፣ ለጋስነት፣ ተነሳሽነትና ጉብዝና፣ ስራና ታታሪነት፣ መልካም ጸባይ፣ ሰላምታ ማብዛት፣ የተጣሉ ማስታረቅ፣ መተሳሰብና መታዘዝን፣ ወንድማማችነት፣ ዙሁድ (ለዓለማዊ ኑሮ አለመስገብገብና አለመሳሳት) እና የመሳሰሉት ባህርያትና ተግባራት ናቸው፡፡

የተኮነኑ ወይም የተጠሉ ሥነ-ምግባራት (አኽላቅ) የሚባሉት ደግሞ እስላም እንዲንታቀብ ያዘዛቸው፣ የተጠሉ ወይም እርም (ሐራም) የተደረጉ እንደ ውሸት፣ ሐሜት፣ ማታለልና ማጭበርበር፣ ክህደት፣ መጥፎ ጸባይ፣ ስንፍና፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣት፣ ሀራም መብላት፣ አራጣ፣ ሌብነት፣ አመንዝራነት፣ ግብረሶደምነት፣ ስም አጥፊነት፣ ብልሹነት፣ ስግብግብነትና ስስታምነት፣ ፈሪነት፣ ጋጠ ወጥነት (ከመጠን ያለፈ ግልጽነትና ድፍረት)፣ አዝማሪነት፣ ዘፈን፣ ነገር ማመላለስ (ነሚማ) ብልግናና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ስነ-ምግባር በሰው ልጆች ህይወትና አኗኗር ውስጥ ፍትሀዊነትና መልካምነት የሚመዘንበት ዕይታ ሲሆን እንደ ሲድቅ (ሐቀኝነትና እውነተኝነት)፣ ቃል መጠበቅና ጽናት ያሉ ህግ አውጭው አካል ያረጋገጣቸው/የወሰናቸው ምስጉን

ባህርያትና እንደ ውሸት፣ ሙስና፣ አጭበርባሪነትና አፈንጋጭነት ያሉ ልንርቃቸው የሚገቡ በመጥፎነት የተፈረጁ ባህርያት ናቸው፡፡

## አንድ ኡማ/ህዝብ

ሙስሊሞች ከተለያዩ መዝሀቦቻቸውና ፊርቃዎቻቸው ጋር አንድ ህዝብ መሆናቸውንና በዲኑ ወንድማማቾች መሆናቸውን እናምናለን፡፡ ይኸውም አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ብሏልና፡-

**كُنْتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ**

**"ለሰዎች የወጣችሁ (የተመደባችሁ) መልካም ህዝብ ሆናችኋል"፡፡**[170]

**فَأَصْبَحْتُمْ بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا**

**"በጸጋው ወንድማማቾች ለመሆን በቃችሁ"**[171]

**إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ**

**"ሙእሚኖች ወንድማማቾች እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ በወንድሞቻችሁ መካከል እርቅ አስፍኑ (አስታርቁ)፡፡"**[172]

በአናሳነት ወይም በብሄር ወይም በዘር ወይም በቡድነት (ጧኢፊያ) ስም መለያየትን (ፊርቃን) ለመፍጠር ወይም ለመከፋፈል የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ በሸሪዓም ሆነ በዐቅል ክልክል ነው (አይበቃም)፡፡

---

[170] አሊ-ዒምራን፡ 110

[171] አሊ-ዒምራን፡ 103

[172] አል-ሑጅራት፡ 10

ቁርአንና ሱናን የሚከተሉ ሙጅተሂዶችን መከተልን ባገናዘበ መልኩ ከኢጅቲሓድ የሚመነጭ በተለያዩ ቡድኖች (ጧኢፍያት) መካከል ቅርንጫፍ የሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚከሰቱ ልዩነቶች (ኢክቲላፋት) በህዝቡ ውስጥ መከፋፈልን ማስከተል የለባቸውም (አይችሉም)፡፡

በቁርአን እና በንጹህ ሱና ማእቀፍ ስር ለሙስሊሞች አንድነት የተቻለውን ጥረት ሁሉ ማድረግና ለዚህ ዓላማ መትጋት ግዴታ አድርገን እናያለን፡፡ ከነዚህ ሁለቱ መሷድሮች (ምንጮች) ያልመነጨ ማንኛውም ህግጋት ባጢልና (ተቀባይነት የሌለው) ውድቅ መደረግ የሚገባው ነው፡፡

እስላምን ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በመላው የምድር አጥናፍ ለማስፋፋት፣ ለማዳረስና ወደ ሁክም (መንግስት) ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ኃይልና ችሎታ ማሰባሰብ ግዴታ ከሆኑ ተግባራት ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ግድ ይላል፡-

1. የመላው የሙስሊሞችን ግንዛቤ ማሳደግና ብሄራዊ መግባባት እንዲፈጠር በመባድረግ በሂደት ወደ አንድ ራዕይ የሚመራቸውን አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤ እንዲያዳብሩና እንዲያበለጽጉ ዲንና ዱኒያ አጣምሮ በያዘ ዕውቀትና ክህሎት መታነጽ፡፡

2. ቀጣይነት ላለው ገንቢና ልማታዊ ስራ ተነሳሽነት ያለው ኢስላማዊ አእምሮና አስተሳሰብ በህዝቡ ውስጥ መፍጠር፡፡

3. በአንድ ሥርዓት ስር ለአንድ ዓላማ የሚተጋ ለሁሉም የህይወት አውታሮች የሚሰራ ኢስላማዊ መዋቅርና መርሀ ግብር ለመዘርጋት መታገል፡፡

4. ባህላዊ፣ ትምህርታዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ግብረገባዊና የመሳሰሉ ሌሎች እሴቶች በተለያዩ ገጽታቸው የሚዳብሩበትንና ለስራ አመራርና ስምሪት መነሻ የሚሆኑ የመገናኛ ማዕከላትና ኢስላማዊ ተቋማትን በስፋትና በብዛት በሁሉም ዓለማት መመስረት፡፡

5. ኢስላማዊ ሀገራትን በቀላልና ግዙፍ ፋብሪካዎችና አምራች ማዕከላት በማበልጸግ ከባዕድ አካላት መብቃቃትና በዚህ መልኩ ለሌሎች እጅ ከመስጠትና ከመገዛት ኡማውን መታደግ፡፡

**وَلِلَّهِ الْعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِ وَلِلْمُؤْمِنِينَ**

**"ድልና ማሸነፍ የአላህ፣ የመልእክተኛውና የሙእሚኖች ነው፡፡"[173]**

ነብዩ(ሶ)፡-**"ኢስላም የበላይና አሸናፊ ይሆናል እንጅ የበታችና ተሸናፊ አይሆንም፡፡"[174]**

## *ሀገራትን ከእኩይ ተግባራት ማጽዳት*

እንደ ኸምር (አስካሪ መጠጥ)፣ ቁማር፣ አመንዝራነት፣ አራጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ (ሞኖፖሊ)፣ ሙስና፣ አጭበርባሪነት፣ ሌብነት ግድያና የመሳሰሉት በኪታብና ሱና የተከለከሉ ኢስላም ሐራም (እርም) ካደረጋቸው እኩይ ተግባራትና ባህርያት ሀገራትን ማጽዳት ግዴታ (ዋጅብ) መሆኑን እናምናለን፡፡

[173] አል- ሙጠፍፊን፡ 8

[174] ወሳኢል አል-ሺዓ 26/125-ሐዲስ 32640

*መንግስታትና ህዝቦች እነዚህን እኩይ ተግባራት በማስወገድ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው እምነታችን ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፡፡*

***كُنْتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ***

**"በመልካም ነገር ሁሉ እንድታዙና ከመጥፎ ሁሉ ትከለከሉ ዘንድ ለሰዎች የተወጣችሁ (የተመደባችሁ) ምርጥ ህዝብ ሆናችኋል፡፡"[175]**

## የኢስላም ክብርና ሉዓላዊነት መመለስ

የኢስላምን ክብርና ሉዓላዊነት መመለስ ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህ ደግሞ ይቻላል፡፡ በእርግጥ አላህ (ሱ.ወ) ለዚህ ቃል ገብቷል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

***وَعَدَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنْكُمْ وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَيَسْتَخْلِفَنَّهُمْ فِي الْأَرْضِ كَمَا اسْتَخْلَفَ الَّذِينَ مِنْ قَبْلِهِمْ وَلَيُمَكِّنَنَّ لَهُمْ دِينَهُمُ الَّذِي ارْتَضَىٰ لَهُمْ وَلَيُبَدِّلَنَّهُمْ مِنْ بَعْدِ خَوْفِهِمْ أَمْنًا يَعْبُدُونَنِي لَا يُشْرِكُونَ بِي شَيْئًا***

*“አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን፣ እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለእነሱም*

---

[175] ኣሊ-ዒምራን፡ 110

*ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፡፡ በእኔ ምንንም የማያጋሩ ኾነው ይግገዙኛል፡፡"*[176]

ይህ ግን እውን የሚሆነው የተሰጡት ሸርጦች (ቅድመ ሁኔታዎች) ሲሟሉ ነው፡፡ ይኸው ትክክለኛ ኢማን (እምነት) እና መልካም በመስራት የተገደበ ነው፡፡ ከመልካም ተግባራት መካከል መተሳሰብና መተባባር፣ መከፋፈልንና መለያየትን ማጥፋት (መከላከል)፣ በአላህ መንገድ ላይ በገንዘብ፣ በምላስና በእጅ መታገል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለቱ ሸርጦች- ኢማንና መልካም ተግባር- እስከተሟሉ ድረስ አላህ ቃል የገባው ውጤት በእርግጠኘነት ይፈጸማል፡፡

## ወደ ኢስላም መጣራት

ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በመላው ዓለም ውስጥ ወደ ኢስላም መጣራት (ዳዕዋ ማድረግ) ግዴታ የሆነ ኃላፊነት መሆኑን እናናለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዳለው:-

**وَلْتَكُنْ مِنْكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى الْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنْكَرِ وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ**

**"ከናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ በመልካም *ሥራም* የሚያዙ ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ሕዝቦች ይኑሩ፡፡ እነዚያም እነሱ የሚድኑ ናቸው፡፡"**[177]

---

[176] አል-ኑር፡ 55

ታላቁ መልዕክተኛ (ሶ) ባሉት መሰረት፡- **“አንድን ሰው ወደ እስላም መምራት ከጸሀይ በታች ካሉ ነገሮች ሁሉ የተሻለና የበለጠ ነው፡፡”**[178]

ተቋማትን መመስረት፣ ከበጎ አድራጊዎች (ሰደቃ) መሰብሰብ፣ ሙበሊጎችን (ዳዕዋ አድራጊዎችን) ማሰማራት፣ መጽሀፍትን ማሰራጨት፣ ከኢስላማዊ ሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የኢስላም ጠላቶች በኢስላም ላይ የሚቃጡትን ጥቃቶችና ተግዳሮቶች መቋቋም እጅግ ወሳኝ የሆኑ ግዴታዎች መሆኑን እናምናለን፡፡

## ሙስሊሞችን ማነቃቃትና ማነሳሳት

ነብዩ (ሰ)፡- “ሁላችሁም እረኞች ናችሁ (ኃለፊነት የተሰጣችሁ ናችሁ)፡፡ ሁላችሁም ደግሞ ስለ እረኝነታችሁ (ስለ ኃላፊነታችሁ) ተጠያቂዎች ናችሁ”[179] ባሉት መሰረት ሙስሊሞች ወደ ነበሩበት ስልጣኔና ሉዓላዊነት ተመልሰው የዓለም መሪ መሆን እስኪችሉ ድረስ ለህዳሴ ማነሳሳት የእያንዳንዱ ሙስሊም ግዴታ መሆኑን እናምናለን፡፡

---

[177] አል ኢምራን፡ 104

[178]ሚሽካቱል አንዋር- 107- ክፍል 9 ለዝርዝሩ ይመልከቱ፡፡ እዚህ ላይ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብሏል "በአንድ ወቅት የአላህ መልእክተኛ(ሶ) ወደ የመን ላኩኝና እንዲህ አሉኝ፡-***"ዓሊ ሆይ ! ወደ አላህ እስከትጣራ ድረስ ከአንድም ሰው ጋር አትጋደል፡፡ አላህ በአንተ እጅ ላይ (በአንተ አማካኝነት) ለአንድ ሰው ሂዳያ መስጠት (ወደ ቅን መንገድ መምራት) ጸሀይ ከወጣችበት ወይም ከጠለቀችበት ነገር ሁሉ የበለጠና የተሸለ ነው፡፡***"

[179] ጃሚዕ አል-አኽባር፡ 119- ክፍል 75

ይህ ደግሞ የሚቻል ጉዳይና ጥራቱና ትጋቱ ካለ የተመቻቸ ሁኔታ በመኖሩ እውን የመሆኑን ጉዳይ ቀላል ያደርገዋል፡፡ ሙስሊሞች የበርካታ ምቹ ሁኔታዎች ባለቤት ናቸው፡-

-እምቅ ኃይል ያለው ትውልድ (ምቹ ግንደ-ዘር)፣

-እስትራቴጅካዊ ቦታዎችና ምቹ መልከዓምድር፣

-እምቅ ተፈጥሮ ሀብት፣

-ህያውና ብሩህ የሆነ መንሐጅ (የኑሮ ስልት)፣

-ለስልጣኔና ልማት የሰጠ ኃይማኖት...

መላው ሙስሊም ፡-

- ኢማናቸውን (እምነታቸውን) ለማበልጸግ ከተጉ፣
- መጥፎና ብልሹ ነገሮችን (ሙንከራት) ካስወገዱ (ከነዚህ ውስጥ ኢስላማዊ ያልሆኑ ህግጋት አንዱ ነው)፣
- ለፍትህና ነጻነት ከቆሙ፣
- ከኪታብ፣ ከሱና፣ ከዒጅማዕና ዐቅል የኢጅትሓድ በርን ክፍት ካደረጉና እነዚህን ብቸኛ የሸሪዓ ምንጭ ካደረጉ፤
- የአስተዳደርና መንግስታዊ እንቅስቃሴዎችን መሰረት ስለ አጠቃላይ ህይወትና ዘመኑ የሚፈለገውን ነገር ጠንቅቀው የሚያውቁ ፍትሃውያን የሸሪዓ ፉቀሃዎች (ምሁራንን) ማማከርና በቅርበት አብሮ መስራት ላይ ከገነቡ፣

- በዘር፣ በጎሳ፣ በቀበሌ፣ በቡድን… ወዘተ ከመከፋፈል ይልቅ ኢስላማዊ ወንድማማችነትና አንድነትን ዳግም አንሰራርተው ወደ ትክክለኛው ቦታ ከመለሱ፣

ሙስሊሞችን ወደ መሪነትና የበላይነት የመመለሱ ጉዳይ  የዓይን ጨርፍታ ያህል የፈጠነ ይሆናል ኢንሻአላህ!!

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላልና ፡-

***إِنْ تَنْصُرُوا اللَّهَ يَنْصُرْكُمْ وَيُثَبِّتْ أَقْدَامَكُمْ***

**"ለአላህ ድል ከተጋችሁ (አላህን ከነሶራችሁ) እሱም ድልን ያጎናጽፋችኋል (የንሱርኩም)፤ ጾንታችሁ እንድትቆሙም ያደርገችኋል፡፡"[180]**

*ስኬት የሚያጎናጽፍ (ተወፊቅ) የሚሰጥ እሱ አላህ ብቻ ነው!!*

[180] ሙሐመድ፡ 7

# የሺዓ ስልጣኔ

**አጠቃለይ የህዝብ ብዛት(ቁጥር)**

በቅርብ ጊዜ ቆጠራ ውጤት መሰረት *(ቢያንስ ከሀያ ከዓመታት በፊት በተደረገ ቆጠራ መሆኑ ነው)* የሺዓ ብዛት ከአምስት መቶ ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ (በአጠቃላይ የሙስሊሞች ብዛት (ሺዓና ሱና) ሁለት ቢሊዮን ገደማ እንደ ሚደርስ ይታወቃል)፡፡

በአብዛኛው የዓለማችን ክፍል በምስራቅም ሆነ በምዕራብ በሁሉም የእስላም ሀገራትና ኢስላማዊ ባልሆኑ በርካታ ሀገራትም ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ ከቁርአን፣ ከንጹህ ነብያዊ ሱናና በንጹሀን አህለልበይት(ዐ) ታሪክ የመነጨ የራሳቸው ስልጣኔ አላቸው፡፡

በኢራቅ፣ በኢራን፣ በህንድ፣ በፓኪስታን፣ በባህረሰላጤ (ኸሊጅ)፣ በሊባኖስ፣ ሶሪያ፣ በአፍጋኒስታን፣ በቱርክ፣ በኢንዶኒዝያ፣ በሰኡዲያ፣ በየመንና በአንዳንድ የአፍሪካና ሌሎች ሀገራት በርካታ ዑለማዎችና መራጅዕ፣ የኃይማኖት ትምርት ቤቶች፣ የትምህርት ማዕከላት፣ መስጂዶች፣ ሁሴንያዎች፣ የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ መርከዞች፣ የተለያዩ ዓይነት መጽሀፍት፣ የቁርዓን ተህፊዝ ማእከላትና ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ኢስላማዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በርካታ ተቋማት አሏቸው፡፡ በኢስላማዊ የኳታር ሀገር እንኳ ሩብ ሚሊዮን ገደማ የሚደርሱ ዑለማዎች፣ ኸጢቦች፣ ፀሐፍትና ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡

በሁሉም ዘመናት የኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ የራሳቸው መንግስታት፣ ምሁራን (ዑለማዎች)፣ ጸሐፍት፣ ገጣሚዎች፣ ፈላስፋዎች፣ ሙፈክሮች፣ ት/ቤቶች፣ ቤተ መጽሀፍት፣ ቢሮዎች፣ ድርሳናት፣ ኸጢቦችና መጋቢዎች አሏቸው፡፡

ከታላቁ መልእክተኛ (ሶ) ዘመን አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ እንጸባራቂ የዲን አቋም አላቸው፡፡ በሰፊው ሊያውቃቸውና ያላቸውን የዕውቀት፣ የጂሓድና የኢኽላስ እምቅ ቅርሶቻቸውን አይቶ መደመም የፈለገ ሰው የሚገኙባቸውን ሀገራት መጎብኘትና ማጥናት ይመከራል፡፡

## ሺዓና ኢስላማዊ ታሪክ

በኢስላማዊ ፉቱሓቶች (ኢስላማዊ ሀገራትን ድል በማድረግና በመክፈት)፣ በኢስላምና ሙስሊሞች ላይ የተቃጡ ወረራዎችን በመመከት ድል አድርጎ፣ ለተለያዩ ሀገራት የእርዳታና ድጋፍ እጅ በመዘርጋት፣ አብሳሪዎችንና ሙበሊጎችን በማሰማራትና የቁርአን ትምህርትን በማሰራጨት ረገድ በሁሉም ዘመናት የኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ አንጸባራቂ ገጾችን መልተው እናገኛለን፡-

- የቡዌይ ቤተሰብ ነገሥታት በኢራቅና ወዳጆች ሀገራት ውስጥ ኢስላምን በማስፋፋት የአንበሳ ድርሻ አላቸው፤
- የሐመዳን ቤተሰብ ነገስታት በሶሪያና አከባቢዎቹ ትልቅ ሚና ነበራቸው፣
- የሰፈዊዎች ነገስታት በኢራን፣ አፍጋኒስታንና አከባቢው ላይ እስከዛሬ ድረስ ተጽእኖው የሚገኝ ታላቅ አገልግሎት አበርክተዋል፡፡
- የአል-ቁጥብ ሻሒዩህ ነገስታት በህንድና አከባቢዎች እንዲሁም በሌሎች. . . ላይ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

- የመንጎል ወራሪ ሀይላትን በመመከት አያቱላህ ነሲር አል-ዲን አል-ጡሲ[181] እጆች ትልቅ ሚና እንዳላቸው አይዘነጋም፡፡
- ዓላማህ አል-ሒሊ[182] ሀገርን ከኢንሒራፍ (ከጥፋትና አፈንጋጭነት) በመጠበቅና የኹዳበንዴ ክስተትን በተመለከተ ያበረከቱት ግልጋሎትም ሳይጠቀስ የሚታለፍአይደለም፡፡
- ሰይድ አል-ሙጃሒድ[183] በሶሪያ ቄሳራውያንና መስቀለኞች ላይ ያደረጉት ጀሓድም በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡
- ኪፋህ አል-ሙጀድድ[184] ትንባሆን በተመለከተ በምእራብውያን ቅኝ ገዢዎች ላይ የቀሰቀሱት አብዮት ተጠቃሽ ነው፡፡

---

[181]አል-ጡሲ-(597-673 ሂጅራ/1201-1274 ዓ.ል)- በስነ ጠፈር/ፈለክ፣ በሂሳብና በከላም ዕውቅ ምሁር ነበሩ፡፡ ዕውቅ የሆነ የጠፈር ምርምር ጣቢያና በሙራጋ በርካታ ቢሮዎች /ማዕከላት የመሰረቱ ታላቅ ምሁር ናቸው፡፡ በርካታ መጽሀፍትን የደረሱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ፡-ተጅሪድ አል-ኢዕቲቃድ፣ ሸክል አል-ቂጣዕ፣ ሸርህ አል-ኢሻራት፣ አል-ተዝኪራ፣ ተህሪር ኡሱለ አቅሊዶስ እና ተኽሊስ አል-መህሱል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

[182]ዓላማህ አል-ሒልሊ- ሐሰን ቢን የሱፍ ቢን ዓሊ ቢን አል-ሙጠሐር አል-ሒልሊ ሲሆኑ በተለምዶ ዓላማህ በሚለው የማዕረግ ስም ይታወቃሉ፡፡ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ በርካታ መጽሀፍት የደረሱ ሲሆን *አል-ተዝኪራ ፣አል-ሙክተሊፍ* እና *ኒሐያት አል-አህካም* ይጠቀሳሉ *(አዕያን አል-ሺዓ 1/145)፡፡*

[183]ሰይድ አል-መጃሒድ- ሰይድ ሙሐመድ (1180-1242 ሂ) ቢን ሰይድ ዓሊ (የአል-ሪያድ ደራሲ) አል-ጠባጠባኢ አል-ሓኢሪ ሲሆኑ የተቀደሰችው ከርበላ ተወላጅ ናቸው፡፡ ከሙሰነፋቶች ውስጥ፡- ሙፍቲህ ኡሱል፣ አል-ወሳኢል ፊ አል-ኡሱል፣ ጀሚዕ አል-ዓባኢር ፊ አል-ፊቅህ . . . ይገኙበታል (አዕያን አል-ሺዓ 9/443)፡፡

[184]ኪፋህ አል-ሙጀድድ -አል-ሚርዛ ሐሰን አል-ሺራዚ የሳመራእ ነዋሪ የነበሩ ሲሆን በዘመናቸው የኢማሚያ መሪነት ሹመት በሳቸው ላይ የሚያበቃ የነበሩና በቲንባሆ ሐራምነት--

- ሶሪያና ሊባኖስን ከፈረንሳይ ቅኝ ገዥነት ለማጽዳት ሸረፈዲን[185] ያደረጓቸው ጂሃዶች (ትግሎች) እንዲሁ በኢስላም ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡
- ኢማም አል-ሺራዚ[186] ቅኝ ገዥዎች ከኢራቅ በማስወጣት ያቀጣጠሉት የዒሽሪን አብዮትም ተጠቃሽ ነው፡፡

ሌሎች በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ሁሉ በተከታታይ ያደረጉት ትግል (ጂሀድ)፣ ሀገር መጠበቅ ላይ ያላቸው ትኩረት፣ ኢስላምን ለማስፋፋት፣ ሉአላዊነቱን ለማስጠበቅ ያደረጉት ተጋድሎ፣ መስዋትነትና ወራሪዎችን ለመመከት ያሳለፉት የጀግንነትና ቁርጠኝነት ተግባር ከታላላቅ ምስክሮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
በአሁኑ ዘመን ያለውን ትግል በተመለከተም ታዋቂ የሺዓ ምሁራንና አንጋፋ የሆኑ ሰዎቻቸው ኢስላምና ሙሰሊሙን ኡማ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ

--- ላይ ፈትዋ የሰጡና የእንግሊዞችን መሰሪ ዓላማ ያከሸፉ ጀግና ናቸው (አዕያን አል-ሺዓ- 1/147)፡፡

[185]ሰይድ አብደል ሁሴን ቢን ሰይድ የሱፍ ሸረፈዲን አል-ሙሰዊ (1290-1377) ሲሆኑ ከበርካታ ድርሳናቸው መካከል ታዋቂ መጽሐፋቸው ***አል-ሙራጀኣት*** *ኣና አል-ፉሱል አል-ሙሂማህ ፊ ተአሊፍ አል-ኡማ፣ ፈልሰፈት አል-ሚሳቅ ወልዊላያ…* ወዘተ ይገኙበታል (አዕያን አል-ሺዓ 7/457)፡፡

[186]አል-ሚርዛ ሙሐመድ ተቂይ አል-ሺራዚ- የዘመናቸው እውቅ ፈቂህ የነበሩ ሲሆን ከ 1338 የ የዝዲ ህልፈት በኋላ የመሪነት ሹመት የተረከቡ ታላቅ ሙጃሂድ ነበሩ (አዕያን አል-ሺዓ 1/147) ፡፡

ባደረጉት ተጋድሎ የተነሳ ውድ ዕደሜያቸውን በግዞት፣ በእስር ቤቶችና በአፈና ያሳለፉ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡

ከፍልስጤምና ከተከበረው ቁዱስ እንዲሁም ከሌሎች በጠላት ወረራ ስር ካሉ መሬቶች ጠላትን ለመከላከል ያደረጉት ተጋድሎ መግለጽ የሚያሻው ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህ ላይ *ኪፋሀ አል-ዑለማእ አል-አዕላም፣ መዋቂፍ ዑለማእ አል-ኢስላም ሚን አል-የሑድ፣ አል-ሐቃኢቅ አል-ነሲዓህ* የተሰኙ መጽሀፍትን ማገላበጥ ስለ ተጋድሎአቸውና ጥረታቸው በጥቂቱ ለማወቅ በቂ ናቸው፡፡

በትምህርትና፣ በኢኮኖሚና፣ በሰላም፣ በፖለቲካ፣ በሀገር ግንባታ፣ በኢንዱስትሪና በመሳሰሉት ሺዓዎች ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ በርካታ በመሆኑ ብዙ ሙጀለዶች (ቅጾች) ማገላበጥን ይጠይቃል፡፡

## ሺዓና ኢስላማዊ ሳይንሶች (ዕውቀት)

ሺዓዎች ለኢስላማዊ ሳይንሶች መሰረት የጣሉ ናቸው፡፡[187] ከብዙ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

***-አቢል አሰወድ አል-ዱአሊ[188]-*** በአሚረልሙእሚኒን ኢማ ዓሊ (ዐ) ጥቆማ መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ነህው (ሰዋሰው) የጻፉ፣

---

[187] ለዝርዝሩ *አል-ሺዓ ሊተእሲስ ዑልም አል-ኢስላም* የተሰኘው በዓላማህ ሠይድ ሐሰን ሰድር የተጻፈውን መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡

[188] አል-ዱአሊ-35 ቅ.ሂ እስከ 48 ድ.ሂ /605 እስከ 688 ል.)::

**-ኸሊል ቢን አህመድ**[189]**-** የቋንቋ ባህርያት ጥናት (prosody) ሳይንስ መስራች፣

**-ጃቢር ቢን ሐያን**[190]- የኢማም አል-ሷዲቅ (ዐ) ተማሪ የነበረ የብዙ ፈጠራዎችና ግኝቶች አባት፣

ከፈጠራዎቹና ግኝቶቹ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፡-

-ዘመናዊ ኬሚስትሪ፡- በዚህ ጉዳይ ላይ እስከ ሰባት መቶ የሚደርሱ ጽሁፎችን ያበረከተ ሲሆን በቀደምት የኬሚስትሪ ስራዎች ላይ ቤተ-ሙከራ በመመስረት በሙከራ (እስፕሪመንት) ስራ ፈር ቀዳጅ በመሆን የኬሚስትሪ አባት በመሆን የኬሚስትሪ አባት ለመባል በቅቷል፡፡

-በተጅሪባ (ሙከራ) ስራው ብዙ ግኝቶች ያስገኘና ቤተ-ሙከራው ከዘመኑ የኬሚስትሪ ቤታ ሙከራ መመሳሰሉ ዓለምን ጉድ አሰኝቷል፡፡

-በምርምሩ በርካታ ኬሚካል ሪአክሽንኖችን ውጤታ ያስገኘ ሲሆን እንደ ሪዳክሽን (ኤሌክትሮኖችን የማራባት/ ማግኘት ሥርዓት)፣ አክስዴሽን (ብረት በማቃጠልና በማቅለጥ የማጣተራትና የመለየት ስራ የሚካሄድበት ስርዓት በማስገኘት በዘመናዊው ኬሚስትሪ ዛሬ ላይ በርካታ ስራዎች ተግባር ላይ የዋሉ የኬሚካል ስራዎችን የወጠነ ታላቅ ምሁር ነው፡፡ ሁለት ጠርሙሶችን

---

[189] አል-ኸሊል 180ሂ. /786ል.ገደማ ያለፈ- የበስራ ነዋሪ የነበረ፣ የሲባዌ እና አስመዒ መምህር የነበረ፣ በፊደላት ተርታ የተሰራ የመጀመሪያው የዐረብኛ ኢንሳይኮሎፒዲያ የሆነ "አል-ዓይን" የተሰኘ ድርሳን ባለቤት፡፡

[190] (ኢብን ሐያን -በ78 ሂ./697 ል. ያለፈ)- በኩፋ ከተማ የኖረ፡፡ ከድርሳናቱ መካከል፡- አሰራር አል-ኬይሚያእ/የኬሚስትሪ ሚስጥራት፣ ኡሱል አል-ኬይሚያእ/የኬሚስትሪ መሰረታውያን፣ ዒልም አል-ሐይአ፣ አል-ረህማህ፣ አል-ሙክተሰብ፣ መጁሙእ ረሳኢል ተጠቃሽ ሲሆኑ ስራዎቹ ወደ ላቲን ተተርጉመው የምዕራባዊያን ምሁራን የሚተማመኑበት በርካታ ሳይንሶች መሰረት ለመሆን የበቁ ናቸው፡፡)

በቲዩብ (ፒዩብ) በማገናኘት በቀላሉ የድስትሌሽን ስራ ለማከናወን የሚረዱ ´አሶሞሲስ´ የሰራና ይህ ስራ ማዕድናት ዘይቶችን (ሜኔራል አይል) ወደ ኬሮዚን በመቀየር ለሙብራ ኃይል ጥቅም ያዋለ ባለ ውለታ ነው፡፡

በአቶም ቲዮሪውና በሞሎኪዩል ቲዮሪው እውቅና ለማግኘት ከበቃው ኢንግሊዛዊው ጆን ዳልተን ከመፍጠሩ ከአስር ምዕተ ዓመታት በፊት ጃቢር በኤለመንቶች መካከል አገናኝ መስመር የሆነውን የኬሚካል ቦንድ ምስል ፈጥሮ ነበር፡፡ ይህም ማለት በዓይን የማይታዩ የሆኑ ኢምንት ቅንጣጢቶች መካከል ያለውን ቦንድ ማሳያ (መግለጫ) ምስል (ኢሜጅ) ማለት ነው፡፡ እነዚህ ግኝቶች ለዘመናዊው ኬሚስትሪ ብሎም ለኬሚካል እንዱስትሪው አማራጭ ያልተገኘላቸውን የቴክኖሎጂ መሰረት የጣለ ነው፡፡ በተጨማሪም በዘመናችን የመንደሊቭ ፔሬዮዲክ ገበታ ተብሎ የሚታወቀውን የኤለመንቶች ገበታ አሁን በሚታወቀው መልኩ በየፊናቸው ከፋፍሎ ለይቶ ያስቀመጠ ፈር ቀዳጅ ምሁር እንደ ነበረ የሚያውቅ ያውቃል፡፡

እንዲሁም በርካታ አዳዳስ ሰብስታንሶች ግኝት ባለቤት እንደሆነና በዘመናዊው ኬሚስትሪ ዓለም እጅግ ወሳኝ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ያስገኘ ሳይንትስት ነው፡፡ ጃቢር ቢን ሐያን እንደ ሰልፈሪክ አሲድ፣ ሃይድሮክሎሪክ አሲድ፣ ናይትሪክ አሲድ ያሉ ጠንካራ አሲዶችን ያገኘ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ እነዘሂህ ግኝቶች ደግሞ በዘመናችን ለኬሚካል እንዱስትሪው ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም፡፡

በሰውነት ውስጥ ዘልቀው የሚገቡ ራዲዮ አክቲቭ የተሰኘ ንጥረ ነገር ማስገኘቱ ይናገራል፡፡ ቀደም ሲል ከሚታወቁት ኤለመንቶች በተጨማሪ አዳዲስ ንጥረ ነገሮችን ስለ መኖራቸው እንደጠቆመና በሙከራው ወቅት አፈር ውስጥ ሌሎች

ያልታወቁ ኤለመንቶች ቢኖሩም በጊዜው ለይቶ ለማውጣት በቂ መሳሪያ እንዳልነበረው ይናገር እንደነበር ታሪክ ያወሳል፡፡

ጃቢር ቢን ሐያን ትናንሽ ሳጥኖች የሚመስሉ የመገናኛ መሳሪያዎች አበርክቶ እንደነበርና አንዱ ሳጥን ያለው ሰው በሌላኛው ሳጥን የሚገኘውን ሰው በመካከለቻው ያለው ርቀት ከፍተኛ ቢሆን እንኳ በሽቦዎቹ (ስልክ) አማካኝነት ይገናኙና ይነጋገሩ እንደ ነበር ያሳየበት የቴሌፎን ወይም ቴሌግራፍ ቴክኖሎጂ እንደነበረው የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

እንዲሁም ኻሊድ አል-በርመኪ የሚባል ሰው ተቀምጦ ይበርበት የነበረ ትንሽ ጠያራ (አውሮፕላን) ሰርቶ እንደነበርና ለረጅም ጊዜ አየር ላይ መቆየት ትችል እንደ ነበር ይጠቀሳል፡፡ ምናልባትም ድምጽ አልባ ከሚባሉት ጠያራዎች ዓይነት የሚመደብ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ከዚህም አልፎ ከብረት የተሰራ አውቶማቲክ ሮቦት ሰርቶ በአንዱ ሚኒስቴር መኖሪያ ቤት ላይ እንደ ዘበኛ ያገለግል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ ሮቦት ወዲህ ወዲያ በመንቀሳቀስ መሄድ ይችል እንደ ነበርና ያለ ፈቃድ ሰርጎ ለመግባት የሚሞከሩ ሰላዮችን ይገድል እንደ ነበር ይነገራል፡፡ በአጠቃላይ ጃቢር ቢን ሐያን ለአብዛኛው ዘመናዊ ግኝቶች ትልቅ መሰረት የጣለና በኬሚስትሪው ዓለም ለዚህ ዘመንም ታላቅ ብልጫ ያለው ታላቅ ሰው ነው፡፡

***-ነሲር አል-ዲን አል-ጡሲ*** (አጭር የህይወት ታሪኩ ቀደም ሲል ተጠቅሷል)፡- የሙራጋ የጠፍር ምርምር ማዕከል ባለቤት ሲሆን በስነ ጠፍር ምህዋሮች ዙሪያ ለመጀመሪያ ግዜ አዲስ አስተሳሰቦችን ያመነጨ ታላቅ ምሁር ነበር፡፡

የሶስት ማዕዘናት (ጎን) /ትሪያንግል መሰረታዊ ህግጋት ዕውቀት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀመረ ሰው ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የምዕራቡ ዓለም ለሚሳይል ቴክኖሎጂ መሰረት የጣለ ምሁር እንደነበረ ያምናሉ፡፡ በሌሎች በርካታ የሂሳብ ቀመሮችና

ዕውቀት ላይ አዳዲስና ጠቃሚ አስተሳሰቦች የነበሩት እንደሆነ ይነገራል፡፡ በምርምር ጣቢያው ውስጥ ስራ ላይ የዋሉ በርካታ አዳዲስና ጠቃሚ የሆኑ መሳሪያዎችን የፈለሰፈ ታላቅ ምሁር መሆኑንም ታሪክ ያረጋግጣል፡፡

***-ሼይኽ በሐኡዲን አል-ዓሚሊ፦*** (በ1031ሂ./1622 ል. የሞተ፣ በ በዓለበክ (በልቤክ) ተወልዶ በአስፈሃን የሞተ ሲሆን ምንጩ ከዓሚል ተራራ (ጀበል ዓሚል) ነው፡፡ በአረብኛና ፈርሲ (ፔርሽያ) ቋንቋዎች በርካታ ድርሰት (መጽሀፍት) ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ፡- *አል-ከሽኩል፣ አል-ኽላት፣ አስራር አል-በላጋ፣ ተሽሪሀ አል-አፍላክ፣ ኹላሰት አል-ሒሳብ* እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በሒሳብና ስነ-ሕዋ (ጠፍር) ላይ የጻፋቸው መጽሀፍት እንደ ዋና ማጣቀሻወችና እጅግ ጠቃሚ ምንጮች የሚያገለግሉ ናቸው፡፡
ይህ ታላቅ ሰው አንዳንድ የድምጽ ሞገድ ህግጋት ባለቤት ለመሆን የበቃና የድምጽ ሞገድ ስርጭትና ውህደት ላይ በመስራት በአንዳንድ የአስፈሃን መስጅዶች ውስጥ ለጥቅም እንደዋለ ይነገራል፡፡ እንዲሁም የውሃ ግፊት ህግጋት በመጠቀም በመናፈሻዎች ውስጥ ለመዝናኛነት የሚውሉ የውሃ እንቅስቃሴዎችን ዑደት ጥቅም ላይ አውሏል፡፡
በሒሳብ ላይ አዳዲስ ህግጋትን ያስቀመጠና በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ታላቅ ምሁር እንደሆነ በርካታ የመጽሀፍት ገጾችን የሞላ ገድል ያሳለፈ ጀግና ነበር፡፡

# የረሱሉ (ሶ) ኸሊፋዎች

## የረሱሉ (ሶ) ኸሊፋዎች

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሺዓዎች የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ከሳቸው በኋላ ተተኪ (ኸሊፋ) የሚሆኑትን አስራ ሁለት ኸሊፋዎች በግልጽ አስቀምጠው እንዳለፉ ያምናል፡፡ እነዚህን ኸሊፋዎች መታዘዝ፣ መከተል እነሱን ማስረጃ አድርጎ ማንኛውንም ነገር ወደነሱ መመለስን በህዝባቸው ላይ ዋጂብ (ግዴታ) አድርገው ነው ያለፉት፡፡ ይህንንም በተመለከተ ነብዩ (ሶ) በመላው ሙስሊሞች ዘንድ ሙተዋቲር በሆነ ሐዲስ፡-

**"ሁለት የከበዱና የከበሩ ነገሮችን *(ሰቀሌይን)* በናንተ ውስጥ እተዋለሁ፤ የአላህ ኪታብ እና ዒትራዬ አህለልቤቴ፣ ሁለቱን የሙጥኝ ብላችሁ ከያዛችሁ ከኔ በኋላ ፍጹም አትጠሙም (ለጥመት አትዳረጉም)፡፡"**

(ይህ ሐዲስ በሁለቱ ፊርቃዎች (ሺዓና ሱና) የተዘገበ ሙትዋትር የሆነ ሐዲስ ነው፡፡ *(ለዝርዝር ቀደም ሲል በዚሁ መጽሐፍ ላይ በዚህ ሐዲስ ላይ የተሰጡትን ምንጮች ይመልከቱ፡፡)*

ኸሊፋዎቹን በተመለከተ ደግሞ ከጃቢርና[191] ከሌሎች[192] በተተረከ ሐዲስ መሰረት ነብዩ (ሶ)በቁጥር ገልጸው በግልጽ ስለ ማስቀመጣቸው እንዲሁ ቀደም ሲል ከተሰጠው ምንጭ ዝርዝሩን ማግኘት ይቻላል፡፡

---

[191] ለተጨማሪ ዝርዝር ዘገባ ደግሞ፡- *የናቢዕ አል-መውዳ* አል-ቁንዱዚ አል-ሐነፊ (1220-1294 ሂ.) 3/251 ክፍል 76፤ *ፊራኢድ* አል-ሲምጠይን -2/132 -ሐዲስ 431፤ *ጋያት* አል- *መራም*- 734 -ሐዲስ 57፡፡

የመዕሲሞቹን (እንከንየለሾቹን) ስም ዝርዝር፣ የትውልድና ህልፈት (መቃብር) ቦታ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል፡፡ ሠንጠረዡ በመጀመሪያ የመልዕክተኛውን (ሰ) እና የልጃቸው ፋጢማ አል-ዘህራ ላይ ያተኩርና ቀጥሎ አሥራ ሁለቱን ኢማሞች ይዘረዝራል፡፡

[192] ዳለአል-ኢማማ-መሐመድ ቢን ጀሪር አል-ጠበሪ፣ኪታብ አል-ጠራኢፍ 1/172፣ከሽፍ አል ጉማ 2/505 ፣አል-ኢስቲንሷር ፊ አል-ነስ ዓላ አኢመት አል-አጥሐር-አል-ከራጃኪ. . . እና ሌሎች በርካታ ምንጮችን ለዋቢነት ማግኘት ይቻላል፡፡

| **የመዕሱም ስም** | **የትውልድ ዘመን** | **የህልፈት ዘመን** | **የቀብር ቦታ** |
|---|---|---|---|
| ታላቁ ነብይ ሙሀመድ ቢን አብደላህ (ሰ) | ረቢዕ አል-አወል 17 | 28 ሶፈር | መዲና አል-ሙነወራ |
| የመልእክተኛው ልጅ ፋጢማ አል-ዘህራ (ዐ.ሰ) | ጁማድ አል-ሳኒ 20 | ጁማድ አል-ሳኒ 3 | መዲና አል-ሙነወራ |

| **አስራ ሁለቱ ኢማሞች** | **የትውልድ ዘመን** | **የህልፈት ዘመን** | **የቀብር ቦታ** |
|---|---|---|---|
| 1. ኢማም ዓሊ አሚረል ሙእሚኒን (ዐ.ሰ) | ረጀብ 13 | ረመዳን 21 | ነጀፍ አል-ሽረፍ |
| 2. ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ (ዐ.ሰ) | ረመዳን 15 | ሰፈር 7 | መዲና አል-ሙነወራ |
| 3. ኢማም ሁሴን ቢን ዓሊ (ዐ.ሰ) | በሻዕባን 3 | ሙሀረም 10 | ከርበላእ |
| 4.ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን (ዐ.ሰ) | ጁማድ አል-ኡላ 15 | ሙሀረም 25 | መዲና አል-ሙነወራ |
| 5. ኢማም መሐመድ ቢን ዓሊ አል-ባቂር (ዐ.ሰ) | ሰፈር 3 | ዙል ሂጃ 7 | መዲና አል-ሙነወራ |
| 6. ኢማም ጃዕፈር ቢን ሙሐመድ አል-ሷዲቅ (ዐ.ሰ) | ረቢዕ አል-አወል 17 | ሸዋል 25 | መዲና አል-ሙነወራ |
| 7. ኢማም ሙሳ ቢን ጀዕፈር አል-ካዚም (ዐ.ሰ) | ሰፈር 7 | ረጀብ 25 | አል-ካዚሚያ |
| 8. ኢማም ዓሊ ቢን ሙሳ አል-ሪዷ (ዐ.ሰ) | ዙልቂዕዳ 11 | ሰፈር መጨረሻ | ኹራሳን |
| 9. ኢማም መሐመድ ቢን ዓሊ አል-ጀዋድ (ዐ.ሰ) | ረጀብ 10 | ዙልቂዕዳ መጨረሻ | አል-ካዚሚያ |
| 10. ኢማም ዓሊ ቢን መሀመድ አል- ሓዲ(ዐ.ሰ) | ረጀብ 2 | ረጀብ 3 | ሳመራእ |
| 11. ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ አል-ዓስከሪ (ዐ.ሰ) | ረቢዕ አል-ሳኒ 10 | ረቢዕ ኢል-አወል 8 | ሳመራእ |
| 12. አል-ሑጀት ቢን ሐሰን አል-መሀዲ አል-ቃኢም (ዐ.ሰ) | ሻዕባን 15 | አሁን በህይወት ያሉ- አጀለላሁ ፈረጀሁ አሽ-ሽሪፍ!! | |

እነዚህ አስራ ሁለቱ ኢማሞችና ፋጢመቱ ዘህራ ቢንት ረሱሊላህ (ሶ) በዕልም፣ በትግስት፣ በምስጉን ስነ ምግባር፣ በንጽህናና እንከን-የለሽነት (ዕስማ)፣ በሁሉም ውስጣዊና ውጫዊ ፈዲላዎችና መንፈሳዊ ፍጹምነት፣ ነብዩ (ሶ) በብቸኝነት የተለዩበት ነብይነት በስተቀር በአጠቃላይ ባርያትና ተግባራት ልክ እንደ ታላቁ የአላህ መልእክተኛ(ሶ) ናቸው፡፡

ሁላቸውም አንድ ኑር (ብርሃን) ናቸው፡፡ እነሱን አጥብቆ የያዘ ነጃ ወጣ (ይድናል)፣ ከነሱ ወደ ኋላ የቀረና ያፈነገጠ ጠፋ፤ ሰመጠ፡፡[193]

ፋጢመት አል-ዘህራ (ዐ.ሰ) የኢማም ባለቤትና የንጹሀን ኢማሞች እናት ናት እንጂ እሷ ኢማም አትባልም፡፡

## የኢማሞች ታሪክ በጨረፍታ

ታላቁ የአላህ መልእክተኛ(ሶ)፣ ልጃቸው ሲደቃ አል-ጠሒራ (ዐ.ሰ) እና ነብዩ (ሶ) እንድንታዘዛቸውና እንድንከተላቸው ያዘዙን አስራ ሁለቱ ኸሊፋዎች ለሰዎች ልጆች የተቃናና ምቹ ህይወት የተሟላ መስመር ዘርግተዋል፡፡ እነዚህ ንጹሀን ኢማሞች ለተሻለና ለተመቻቸ የሰው ልጅ ህይወት ኑሮ ምሉዕ የሆነ የኑሮ ቀመር ምንጭ ናቸው፡፡ በሁሉም ዘመናት ለመላው የሰው ልጅ አጠቃላይ የህይወትና ኑሮ አውታሮች መልካም ተምሳሌታ ናቸው፡፡

በተለያዩ የሰው ልጆች የህይወት እርከን፣ በአስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ንግድና ኢንዱስትሪ፣ ሥነ-ምግባራዊ፣ ወታደራዊ፣ እርሻ፣ ባህላዊ፣

---

[193]ይህ አባባል ከነብዩ (ሶ) የተያዘ ሐዲስ መሰረት ያደረገ ሲሆን እንዲህ አስቀምጠውታል፡-
***"የአህለልቤቱ ምሳሌ እንደ ኑህ መርከብ (ሰፊና) ነው፤ በመርከቡ የተሳፈረ ነጃ ወጣ፣ ከመርከቡ ወደ ኋላ የቀረና ያፈነገጠ ጠፋ፡፡"***
(ሂልያተል አውሊያእ 4/306፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/168፤ አል-ጃሚዕ አል-ሰጊር አል-ስዩጢ 2/132 እና ሌሎች በዚህ መጽሀፍ ላይ ወደፊት የሚቀርቡ ዝርዝር ምንጮች፡፡

ፍትህና ፍርድ፣ ግለሰባዊ፣ ቤተሰባዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለመላው የሰው ዘር ተምሳሌትና ፋና ወጊ መሪዎች ናቸው፡፡

ይኸውም ኢማሞች በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሚና የነበራቸው ሲሆን በአስተዳዳሪነት፣ በእንደራሴነት፣ በመሪነት፣ በውትድርና፣ በአብዮተኝነት፣ በመምህርነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በተቃዋሚነት፣ በነጋዴነት፣ በገበሬነትና፣ በእስረኝነት፣ በተዋጊነት፣ በሰላም ስምምነት፣ በማሸነፍ፣ በመሸነፍ፣ በእምቢተኝነት፣ በእጅ ሰጭነት. . . የሰው ልጆችን ሊያጋጥም በሚችል በአጠቃላይ የኑሮ አውታር ተምሳሌት የሚሆን ፍጹም የሆነ ሚና በመጫወት የመልካም ተግባራት ሁሉ ቁንጮ በመሆን ህይወታቸውን ያሳለፉ እንከን-የሌሾች ናቸው፡፡

መላው ዓለም እነዚህን መሪዎች ሙጥኝ ብሎ የያዘና የተከተለ ቀን ዓለማችን ምድራዊ ገነት ትሆናለች ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ኢማም ማህዲን (ዐ.ሰ) ለእንዲህ ዓይነቱ ብሩህ ዘመን አስቀምጦልናል፡፡

ስለዚህ የእነዚህን ኢማሞች (ዐ.ሰ) ማንነትና ሁኔታ አጠር ባለ መልኩ ለማስታወስ ያህል ለነብዩ (ሶ) ልጅና የነብዩ ወሲይ ባለቤት በሆነችው ፋጢመት አል-ዘሐራ (ዐ.ሰ) እንጀምራለን፡፡

## *ቢንት አል-ነብይ (ሶ) /የነብዩ (ሶ) ልጅ (ዐ.ሰ)*

-እሷም፡- **ፋጢመት አል-ዘሕራ (ዐ.ሰ)**

-አባቷ፡- የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ሙህመድ ቢን ዓብደላህ

-እናቷ፡-ታላቋ ሰይዳ ኸዲጃ- ኡሙል ሙእሚኒን

-ልጆቿና የልጅ ልጆቿ ፡-ንጹሀን ኢማሞች (ዐ.ሰ)

በጁማዱል አኺራ 20 ቀን በ45ኛው የነብዩ (ሶ) ዓመተ ልደት ተወለደች፤ በጁማዱል አኺራህ 3 ቀን 11 ዓመተ ሂጅራ ማክሰኞ ዕለት በ18 ዓመቷ ተበድላ ህይወቷ አለፈ፡፡

አሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) የተቀደሰ ሰውነቷን ለቀብር ካዘጋጀ በኋላ በኑዛዜዋ መሰረት የመቃብር ቦታዋ እንዳይታወቅ በሚስጥር በመዲና ቀበራት፡፡ በዒባዳ፣ በዙህድና በፈዲላ ልክ እንደ አባቷ (ሶ) ነበረች፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እሷን አስመልክቶ የቁርአን አያህ አውርዷል (ለዝርዝሩ *"ፋጢመቱ አል-ዘህራ (ዐ.ሰ) ፊል ቁርአን"* የተሰኘውን አያቱላህ ሰይድ ሷዲቅ አል-ሺራዚ መጽሀፍ ይመልከቱ፡፡ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ እሷን (ዐ.ሰ) በተመለከተ በአህለሱና መሷድሮች ውስጥ የተጠቀሱትን በርካታ የቁርአን አያዎች አስቀምጠዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ፋጢማ ዘህራ (ዐ.ሰ) ***"ሰይደቱ ኒሳእ አል-ዓለሚን"* (የዓለማት የሴቶች አለቃ)** እንዲሁም ***"ሰይደቱ ኒሳዕ አህሊል ጀናህ" (የጀነት ሴቶች አለቃ)*** በማለት ሰይመዋታል፡፡[194]

---

[194]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሐይን 3/170 -ሐዲስ 4740 ላይ ከዓኢሻ በተያዘ ሐዲስ ነብዩ (ሶ) ለሞት በዳረጋቸው በሽታ ታመው በተኙ ጊዜ ለፋጢመት አል-ዘህራ እንዲህ ሲሉ መናገራቸው ተጠቅሷል፡-

***"ፋጢማ ሆይ! የዓለማት ሴቶች ሁሉ አለቃ፣ የዚህ ኡማ ሴቶች አውራ፣ የሙእሚን ሴቶች ሁሉ ዓይነታ (አለቃ) መሆን አያስደስትሽምን?"*** ያሉ ሲሆን የሐዲሱ ሰነድ ሰሂህ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁ በተፍሲር አል-ቁርጥቢ 3/73፣ አል-ሱነን አል-ኩብራ 4/25፣ 5/146፣ ሙዕተሰር አል-ሙኽተሰር 2/247፣ ሙስነድ አል-ጠያለሲ 1/196፣ ፈትህ አል-ባሪ 7/105፣ 7/136፣ 9/324፣ ዐውን አል-መዕቡድ 6/114፣ ፈይድ አል-ቀዲር 3/107፣ 4/124፣ 4/422፤ ሰሂህ ቡኻሪ 3/1374 … ይመልከቱ፡፡

የፋጢመት ዘህራን ሌሎች በርካታ ፈዲላዎችን ማስረጃ ማየት ከፈለጉ፡------

ነብዩ (ሶ) እጅግ አብዝተው ፋጢማን ይወዷት ነበር፡፡ ፋጢማ (ዐ.ሰ) ወደርሳቸው በምትመጣበት ጊዜ በክብር እንደሚቀበሏት፣ ተነስተው በቦታቸው ላይ እንደሚያስቀምጧትና እጇንም ሳይስሙ እንዳልቀሩ ይነገራል፡፡ እንዲህም ይሉ ነበር፡-

***"እነሆ አላህ (ሱ.ወ) ለፋጢማ ዉዴታ ይወዳል፣ ለቁጣዋ ይቆጣል*** *(ኢንነላሀ የርዷ ሊሪዷ ፋጢማ ወ የግዷቡ ሊገዷቢሃ)*፡፡"[195] ይህም ማለት አላህ (ሱ.ወ) ፋጢማን የሚያስደስታት ነገር ያስደስተዋል፣ እሷን የሚያስቆጣ ነገር ደግሞ ያስቆጣዋል ማለት ነው፡፡

እንዲሁም ነብዩ(ሶ) ስለ ፋጢማ ሲናገሩ፡-

"ፋጢማ የአካሌ ክፋይ ናት (ፋጢሙቱን ቢዷአቱን ሚንኒ)"[196] ብለዋል፡፡

---

----አል-ሙስተድረክ 3/164፣ ሰሂህ ሙስሊም 4/1904፣ ሰሂህ ቡኻሪ 3/1360፣ ሰሂህ ኢብን ሒባን 15/401፣ መዋሪድ አል-ዘምዓን 1/549፣ ሱነን አል-ቲርሚዚ 5/698፣ ሰሂህ ቡኻሪ 3/1374 ማየት ይቻላል፡፡

[195]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/167 ሐዲስ-4730 ላይ የአላህ መልእክተኛ(ሶ) ለፋጢመት አል ዘህራ፡-
***"እነሆ አላህ ለቁጣሽ ይቆጣል፣ ለደስታሽ ይደሰታል"*** እንዳሏት ተጠቅሷል፡፡ ሐዲሱም በሰነዱ ሰሂህ መሆኑ ታክሎ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም፡-አል-ሐይሰሚ-በመጀመዕ አል-ዘዋኢድ 9/203፣ አቡ በክር አል-ሸይባኒ -አል-ኣሓድ ወልመሳኒ5/363፣ አል-ጠበራኒ-ሙዕጀም አል-ከቢር 1/108›22/401፣ ኢብን አል-አሲር-ኡስድ አል-ጋባ 2/522፣ ኢብን ሐጀር-አል-ኢሳባ 8/109፣ ተህዚብ አል-ተህዚብ 12/441፣ ከንዝ አል-ዑመል 7/11፣ 6/219፣ ሚዛን አል-ኢዕቲዳል አል-ዘሐሪ 2/72፣ ዘኻኢር አል-ዑቅባ/39 ...
[196]ሶሂህ ሙስሊም 4/1902፣1903 ላይ ነብዩ ***(ሶ)፡-"እነሆ ልጄ ፋጢማ የአካሌ ክፋይ ናት፣ እሷን የሚያስፈራና የሚጎዳ ነገር እኔንም ያስፈራኛል፣ ይጎዳኛል፣ እሷን አዛእ የሚያደርጋት ነገር/የሚያስቀይማት ነገር እኔንም አዛእ ያደርገኛል/ያስቀይመኛል "*** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡--

ፋጢማ አል-ዘሐራ (ዐ.ሰ) ለአሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) ኢማም ሐሰንን (ዐ.ሰ)፣ ኢማም ሁሴን (ዐ.ሰ) እና ሙህሲኒን (ባጋጠማት አዛእ/በደል የተነሳ አስወረዳት እንጂ) እንዲሁም ሰይዳ ዘይነብንና ኡሙ ኹልሱምን ወልዳለታለች፡፡

## የመጀመሪያው ኢማም

እሱም ፡- ኢማም ዓሊ ቢን አቢ-ጣሊብ (ዐ.ሰ) ነው፡፡

እናቱ ፡-ፋጢማ ቢንት አሰድ ናት፡፡

እሱ፡-የነብዩ (ሶ) አጎት ልጅ፣ የልጃቸው ባል፣ ከነብዩ (ሶ) በኋላ በሰዎች ላይ ኸሊፋ፣ የሙእሚኖች አዛዥ/አሚር አል-ሙእሚኒንና የንጹሀን ኢማሞች አባት ነው፡፡ በመካ ከተማ በታላቁ ካዕባ ውስጥ ጁምዓ ቀን በረጀብ ወር 13ኛው ሌሊት ከነብዩ (ሶ) ልደት ብኋላ በ30ኛው ዓመት ተወለደ፡፡

---

---ሶሂህ ቡኻሪ3/1361 ሐዲስ 3510 ላይ ነብዩ(ሶ ፡-"***እነሆ ፋጢማ የአካሌ ክፋይ ናት፣ እሷን የሚያስቆጣ ነገር እኔንም ያስቆጣኛል***"ብለዋል፡፡

በተለያዩ አባባሎች ተመሳሳይ ሀሳብ በሰሂህ አል-ቡኻሪ 3/1364 ሐዲስ 3523፤ 3/1374-ሐዲስ 3556፣ 5/2004- ሐዲስ 4932፣ ሰሂህ ኢብን ሒባን 15/406-535፣ ሙስተረድክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/172፣ 3/173፣ አል-አሓዲስ አል ሙኽታራ 9/315፡፡

በተጨማሪም፡- -ሙሰነድ አቢ-ዐዋናህ 3/80-81፤ ሱነን አል-ቲርሚዝ 5/698፤ መጅምእ አል-ዘዋኢድ 4/255፣9/203፤ ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ7/307፣308፣ 10/201 እና 288፤ ሱነን አቢ ዳውድ 2/226፤ ሱነን ኢብን ማጃህ 1/643 እና644፤ ሙስነድ ኢብን አቢ ሸይባህ 6/388፤ ሙሰነፍ ዓብደረዛቅ 7/301 እና 302፤ ሙዕተሰር አል-ሙኽተሰር 1/307፤ ሙሰነድ አል-ሐሪስ 6/910፤ ሙስነድ አቢያዕላ 13/134፤ አል-ኣሓድ ወልመሳኒ 5/361-362፤ ሙዕጀም አል-ከቢር 20/18-19፣ 22/404-405፤ ነዋድር አል-ኡሱል ፊ ሐዲስ አል-ረሱል 3/182-183፤ አል-ፊርዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ 1/232፣ 3/142፤ አል-በያን ወ አል-ተዕሪፍ 1/270-271፡፡

ጁምዓ ሌሊት በኩፋ መስጂድ ምእራብ ውስጥ በእርጉሙ የኢብን ሙልጀም አል-ኻሪጂ ሰይፍ በ19ኛው የረመዷን ወር ተወግቶ ከሶስት ቀናት በኋላ ተሰውቶ ወደ ላቀው ጉርብትና አለፈ፡፡ የተባረከ እድሜው ስድሳ ሶስት ነበር፡፡ ሁለቱ ኢማሞች ኢማም ሐሰን (ዐ) እና ኢማም ሁሴን (ዐ) ለቀብር ካሰናዱት በኋላ መርቀዱ ባለበት ቦታ በተከበረው ነጀፍ ተቀበረ፡፡

## ***ከአሚረል ሙእሚኒን (ዐ.ሰ) ፈዷኢሎች በጥቂቱ፡-***

አሚረል ሙእሚኒን ኢማም ዓሊ ቢን አቢ-ጧሊብ (ዐ.ሰ) ተቆጥረው የማይዘለቁ በርካታ ፈዷኢሎች አሉት፡-

ኢሚኑ፡- በአላህና በመልእክተኛው (ሶ) በማመን የመጀመሪያውና ቀዳሚ ሰው ነበር፣ ለጣኦት ፈጽሞ ሰግዶ አያውቅም፡፡[197]

*-በአላህ መንገድ ያደረጋቸው ጂሀዶች(ትግሎች)፡-*

***የበድር ቀን***- በዚህ ዘመቻ ላይ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) እንዲሁም ሐምዛ ቢን አብዱልሙጠሊብ የነበራቸውን ሚና በተለያዩ መሷድሮች ላይ መጥቀስ እንችላለን፡፡

---

[197] ለዝርዝር መረጃ፡-

አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/147- ሐዲስ- 4662፣ 3/528 ሐዲስ 5963፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/102፣ 119፣ 220፣ 247፤ ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ 6/206፤ አል-መዕጀም አል-አውሰጥ 3/166፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል 4/368- ሐዲስ 19300፤ አል-ኣሓድ ወል-መሳኒ 1/149 እና 151፣ 5/384፤ ሙሰነድ ኢብን አል-ጀዕድ 1/87፤ አል-ሙዕጀም አል-ከቢር 11/25፣ 11/406፣ 12/98፣ 19/291፣ 22/452፡፡

-ዓሊ (ዐ.ሰ) ከወሊድ ቢን ዑትባህ ጋር ያደረገው ግጥሚያና እንደገደለው፣ ሐምዛ (ረ.ዐ) ደግሞ ዑትባን እንደገደለ ከዚያም የቁረይሽ ሰይጣኖች እስከ መባል የደረሱ አል-ዓስ ሰዒድ ቢን አል-ዓስ፣ ሐንዘላ ቢን አቢ-ሶፊያን፣ ጠዒማህ ቢን ዐዲይ፣ ነውፈል ቢን ኹዌይሊድ እና ሰባ የሚደርሱ ሙሽሪኮችን በመግደል በመካ ኩፋሮች ውስጥ ትልቅ ፍራቻና መረበሽን በመፍጠር ለኢስላም ልቅና በር ከፋች ተግባራትን አህዱ ያለ ጀግና ነው፡፡[198]

***የኡሑድ ቀን፡-*** ሶሀቦች የነብዩን (ሶ) ትዕዛዝ በመጣሳቸው ሽንፈት በገጠማቸውና በጥቂት ሰሃቦች በስተቀር አብዛኛዎቻቸው ነብዩን (ሶ) ለጠላት አሳልፈው በመስጠት ከትግሉ ፈርጥጠው የሸሹበት ዘመቻ፡፡ በዚህ ወቅት ነብዩ (ሶ) ጎን በመቆም እስከ መጨረሻው በመፋለም ሽንፈቱን ቀልብሰው ወደ ድል የቀየሩ ጥቂት ሰሃቦች መካከል የአንበሳ ድርሻ የነበረው ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ነው፡፡ በዚህ ዘመቻ ሰባ ያህል ሙስሊሞች ተገድለዋል፡፡ በዚህ ቀን ነው መላኢካ ከሰማየ ሰማያት ፡-

**"ከ ዙልፊቃር በቀር ሌላ ሰይፍ የለም! ከዓሊ በቀር ወጣት ጀግና የለም!"** በማለት አዋጅ የነገረው ***(አዕላም አል-ወራ/190*** ላይ ዝርዝሩን ይመልከቱ፡፡)

***የኸይበር ቀን፡-*** በዚህ ዘመቻ ወቅት በሌሎች ሰሃቦች መሪነት ድል ማግኘት ያለተቻለበትና በዓሊ አማካኝነት ድል ማግኘት እንደሚቻሉ ረሱሉ (ሶ) ቀድመው የተናገሩበትና በዚህ አጋጣሚ የዓሊን (ዐ.ሰ) ማንነትና ፈዲላ

[198] ሰሂህ ቡኻሪ 4/1459- ሐዲስ 3749፣ 3751፤ አዕላም አል-ወራ/191 እና ሌሎች ምንጮች፡፡

ያወጁበት ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ነበር፡፡ ነብዩ (ሶ) በዚህ እለት ነው የሚከተለውን ያሉት ፡-

***“አላህ (ሱ.ወ) በእሱ አማካኝነት ድል የሚያጎናጽፈን ለሆነ፣ አላህንና መልእክተኛውን (ሶ) የሚወድ እና አላህና መልዕክተኛውም (ሶ) ለሚወዱት አንድ ሰው፣ እነሆ በነገው ዕለት ይህንን ባንዲራ እሰጣለሁ፡፡"***

ያቺን ሌሊት ሰዎች ሁሉ ላማን ይሆን የሚሰጡት እያሉ እያሰቡ አደሩ፡፡ ሁሉም ሰው እየቋመጠ ልባቸው እንደተንጠለጠለ ሌሊቱ ነጋ፡፡ ተራኪው እንዲህ እያለ ቀጠለ፡- ***"ለሊቱ እንደ ነጋ ሁሉም ሰው ወደ አላህ መልእክተኛ (ሶ) በመሄድ እያንዳንዳቸው በታላቅ ምኞት ተሞልተው ይጠባበቁ ነበር፡፡"***

ከዚያም ነብዩ (ሶ)፡- **"ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ የት ነው" ብለው ጠየቁ፡፡** እነሱም፡- **"የአላህ *መልእክተኛ ሆይ!* እሱ ዓይኑን እንደ*ታመመ* ነው"** አሉ፡፡ ነብዩም (ሶ)፡- **"ላኩበትና ይምጣ"** አሏቸው፡፡

ከዚያም ዓይኖቹ ላይ ተፉለትና ዱአዕ አደረጉለት፡፡ እሱም ምንም ህመም እንዳልነበረበት ሆኖ ከዓይኖቹ ህመም ሙሉ በሙሉ ተፈወሰ፡፡ ባንዲራውንም ሰጡት፡፡ ዓሊም (ዐ.ሰ)፡- **“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛን እስኪመስሉ ልዋጋቸውን?** ብሎ ጠየቀ፡፡

ነብዩም (ሶ)፡- ***“የመሸጉበት ቦታ እስክትደርስ ተረጋግተህ ሂድና እንደደረስክ ወደ ኢስላም ጥራቸው፡፡ ከአላህ ሐቅ ያለባቸውን ግዴታ አብራራላቸው፡፡ በአላህ እምላለሁ! ቀያይ ውድ ግመሎች ከሚኖሩህ ይልቅ አላህ (ሱ.ወ) በአንተ አማካኝነት አንድን ሰው ወደ ቀና መንገድ መምራቱ እጅግ የበለጠና የተሻለ ነው"*** አሉ፡፡ (-ሰሂህ ሙስሊም 4/1872 ሐዲስ 2406- ከ ሱሔይል ቢን ሰዕድ በሆነ

ሰነድ፣ ከሐዲስ ቁ. 2407 ደግሞ ከሰልማህ ቢን አውከዕ በሆነ ሰነድ በከፊል በተለየ አባባል ተመሳሳይ ትረካ እናገኛለን፡፡)

**የሑነይን ቀን**:- በዚህ ዘመቻ አስር ሰዎች ብቻ ከነብዩ (ሶ) ጋር ሲቀሩ ሁሉም ሙስሊሞች ተሸንፈው የሸሹበት እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ከነብዩ (ሶ) ጎን ጸንተው ከተፋለሙት ጀግኖች ውስጥ ዘጠኙ በኒ ሃሺሞች ሲሆኑ አስረኛው አይመን ቢን ኡሙ አይመን ነበር፡፡ አይመን በዚሁ ፍልሚያ ውስጥ ሲገደል ዘጠኞቹ ከነብዩ (ሶ) ጎን ጸንተው ቆዩ:: በነቢዩ (ሶ) ትዕዛዝ መሰረት ዓባስ ቢን አብደልሙጠሊብ አዋጅ እንዲናገርና ከትግሉ የሸሹ ሙስሊሞች ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ ዓባስ ከፍ ባለ ድምጽ፡-

***"እናንተ የበይዓ አል-ሸጀራ (በዛፏ ስር ቃልኪዳን የገቡ) ሰዎች ሆይ! እናንተ የሱራ አል-በቀራ ሰዎች ሆይ! ወዴት ነው የምትሸሹት? እስቲ ለነብዩ (ሶ) የገባችሁትን ቃል አስታውሱ!*** "አላቸው፡፡

ይህንን ሲሰሙ ደንግጠው ሁሉም መሬት ላይ ተደፉ፡፡ ከዛም እንደምንም ወደ ነብዩ (ሶ)ተ መልሰው በሙሽሪኮች ላይ የማታ ማታ ድል አገኙ፡፡

ከነብዩ (ሶ) ጎን ሳይለዩ ጸንተው የተፋለሙ ስምንቱ በኒ ሀሽሞች፡-

-*ዓባስ ቢን አብደልሙጠሊብ*- በነብዩ (ሶ) ቀኝ በኩል፣

-*ፈድል ቢን ዓባስ*-በነብዩ (ሶ)ግራ በኩል፣

-*አቡ ሱፍያን ቢን ሐሪስ*-የነብዩን (ሶ) በቅሎ ልጓም የያዘ፣

-*አሚረል ሙእሚኒን ዓሊ* (0) ከነብዩ (ሶ) ፊት፣

*-ነውፈል ቢን አል-ሐሪስ፣ ረቢዓ ቢን አል-ሐሪስ፣ ዓብደላህ ቢን ዙቤይር ቢን ዓብደልሙጣሊብ፣ ሙዕተብ እና ዑትባ* ኢብና አቡ-ለሃብ- በነብዩ (ሶ) ዙሪያ የቆሙ ነበሩ፡፡

አሚረል ሙእሚኒን ዓሊን (ዐ.ሰ) እና ከነብዩ (ሶ) ጋር ጸንተው የቆዩ ስምንቱን በኒ ሐሺሞች አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) የቁርአን አያህ አወረደ፡-

**ثُمَّ أَنْزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَىٰ رَسُولِهِ وَعَلَى الْمُؤْمِنِينَ**

**"ከዚያም አላህ በመልእክተኛውና በሙእሚኖቹ ላይ ሰኪናውን (መረጋጋቱን) አወረደ፡፡"[199]** *(ለዝርዝሩ አዕለም አል-ወራ ገጽ 198 ይመልከቱ)*

***የአሕዛብ ቀን፡-***

በ **አዕላም አል-ወራ** 193-195 ላይ የተጠቀሰው በዚህ ዘመቻ ላይ ከሚጠቀሱ ዋና ክስተቶች ውስጥ የዓምር ቢን ዓብድ ውድ መገደል ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል፡፡

በ ረቢዓህ አል-ሰዕዲ እና በ ሁዘይፋ ቢን የማን መካከል ስለ ኢማም ዓሊ የተደረገውን ቃለ ምልልስ በዚሁ መስደር (ምንጭ) ላይ እናገኛለን፡፡ ነገሩ እንደዚህ ነው *፦"አባ አብደላህ ሆይ! ስለ ዓሊ ስናወራና ፈዲላዎቹን እያነሳን ስንናገር የ በስራ ሰዎች እናንተ ደግሞ ስለ ዓሊ ስታወሩ ታበዙታላችሁ፣ ከድንበር ታልፉላችሁ"* ይሉናል፡፡ *"አንተስ ስለ ዓሊ የምትለው አለህ?"* ሁዘይፋም፡- ***"ረቢዓህ ሆይ! ሙህመድን (ሶ) በላከው ጌታ እምላለሁ፣ አላህ (ሱ.ወ) መሐመድን (ሶ )ነብይ አድርጎ ካስነሳበት ጊዜ አንስቶ እስከ ቂያማ ቀን ድረስ የመላው ሰሀቦች ስራ በአንድ ሚዛን ጆሮ (ክንፍ) ላይ ቢደረግና የዓሊ***

---

[199] አል-ተውባ፡ 26

***(ዐ.ሰ) ደግሞ በሌላኛው ጆሮ ላይ ቢደረግ የዓሊ (ዐ) ስራ ሚዛን እንደሚደፋ ቅንጣት ጥርጥር የለውም"*** በማለት መለሰለት፡፡

ራቢዓም ***"አላስቆም አላስቀምጥ ያለን ይሄ ነው እንግዲህ"*** አለ፡፡

ሁዘይፋም ቀበል አድርጎ፡- ***"እንዴት ሆኖ ነው ይሄን ማሰብ ያቃታቸው?" ዓምር ቢን ዓብድ ውድ ሰሃቦቹን በሙሉ ለግጥሚያ እየፎከረ ሲጠራ ከዓሊ (ዐ.ሰ) በስተቀር ሁሉም ፈርቶ አላቀረቀረም? ያኔ አቡ በክር፣ ዑመር፣ ሁዘይፋ ... ጠቅላላ የሙሐመድ ሰሃቦች የት ነበሩ? ዓሊ (ዐ.ሰ) ብቻ ነው በፍጹም ጀግንነት ገጥሞት አላህ (ሱ.ወ) በሱ እጅ ላይ የገደለው፡፡ የሁዘይፋ ነፍስ በእጁ ውስጥ በሆነው ጌታ እምልለሁ፣ የዛች እለት የዓሊ ስራ መላው የመሐመድ ሰሃቦች እስከ ቂያማ ቀን ከሚሰሩት ስራ ይበልጣል፡፡"***

እንዲሁ አል-ዋቂዲ በዘገቡት ሐዲስ ዓብደላህ ቢን ጃፈር ከ አቢ ዐውን፣ አቢ ዐውን ደግሞ ከአል-ዙህሪ በሆነ ሰነድ- ዓምር ቢን ዓብድውድ፣ ዒክሪማ ቢን አቢ-ጀህል፣ ሁቤይራ ቢን አቢወህብ፣ ነወፈል ቢን ዓብደላህ... ወደ ኸንድቁ መጥተው አሳቻ ቦታ ይዘው ለፍልሚያው ሲፎካከሩና የተካነ ፈረሰኛና እንደ አንድ ሺህ ሰው የሚቆጠረው ዓምር ቢን ዓብድውድ፡- "በሉ እንጂ የሚገጥመኝ ሰው ይውጣልኝ" እያለ በትዕቢት ሲያቅራራ አንድም ሰሃባ መልስ ሳይሰጥ ቀርቶ ዓሊ ሊገጥመው ተነሳ፡፡ በዚህ ጊዜ እድሉ ለሌሎች ሰሃቦች ይሰጥ ዘንድና ፈተናውን የሚያልፍ ካለ ለማየት ነብዩ (ሶ) ዓሊ ለአፍታ እንዲታገስ አዘዙት፡፡ በመጨረሻም ዝር የሚል ሰሃባ ሲጠፋ ነብዩ (ሶ) ጥምጣማቸውን ከራሳቸው ላይ አንስተው ለዓሊ ጠመጠሙለትና ሰይፋቸውን ዙልፈቃርንም ሰጡት፤ ከዚያም ዓሊ (ዐ.ሰ) ለግጥሚያው ተዘጋጀ:: ጃቢር ቢን

ዓብድላህ የሚሆነውን ለማየት ከዓሊ ጋር ነበሩ፡፡ በመጨረሻም ዓሊ (ዐ.ሰ) ዓምር ቢን ዓብድውድን ሊገጥመው ወደ እሱ ሲያመራ ነብዩ ***(ሰ)፦"ኢማን በጠቅላላው ኩፍርን በጠቅላለው ሊጋፈጥ ወጣ"***ብለው ተናገሩ፡፡

በዚህ ሁኔታ ዓሊ (ዐ) አይበገሬ የተባለውን ዓምር ቢን ዓብድውድ እና አጃቢዎቹን ወደ ጀሀነም ላካቸው፡፡ ጃቢር ቢን ዓብደላህ ክስተቱን ሁሉ ካስተዋለ በኋላ የ ዓሊንና የዓምር ቢን ዓብድውድን ጉዳይ ከዳውድና ጃሉት ታሪክ ጋር እንጂ ከሌላ ጋር አይመሳሰልም በማለት ከቁርአን አንቀጽ እንዲህ ሲል ቀራ፡-

**فَهَزَمُوهُمْ بِإِذْنِ اللَّهِ وَقَتَلَ دَاوُودُ جَالُوتَ**

**"በአላህ ፈቃድ አሸነፋቸው፣ ዳውድም ጃሉትን (ጎልዲያን) ገደለው፡፡"[200]**

***ሌሎች ዘመቻዎች፡-***

እንደሚታወቀው በሁሉም ዘመቻዎች ድል ከዓሊ (ዐ.ሰ) ባንዲራና ትግል ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ከተሳተፈባቸው የትግል ሜዳዎች በአንዳችም ሽንፈት ገጥሞት አያውቅም፡፡

በ *ኢዕለም አል-ወራ* 195-196 ላይ ዝርዝሩን ማግኘት የሚቻል ሲሆን ከዘመቻዎቹ አንዱ የ *ዋዲ አል-ረምል* (የ *ሲልሲላህ* ዘመቻ ተብሎም ይጠራል) ዘመቻ ነው፡፡ ለዚህ ዘመቻ በመጀመሪያ ኃላፊነት ተሰጥቶት የተላከው ዓሊ (ዐ) ሳይሆን ሌላ ሰሃባ ነበር፣ ያ ሰሃባ ሃላፊነቱን ሳይወጣ በሽንፈት ተመለሰ፡፡ ከዚያም እንዲሁ ለመጀመሪያው ሰሃባ ወዳጅ የነበረ ሌላ ሰሃባ ወደ ዘመቻው

[200] አል-በቀራ፡ 251

ከዋጣ በኋላ በሽንፈት ተመለሰ፡፡ በመጨረሻም ዓሊ (ዐ) ለዚህ ዘመቻ ወጣ፡፡ ዘማቾቹን አስከትሎ ከቦታው ሲደርስ የቀትር ሶላት ከሰገዱ በኋላ በሰይፉ ላይ ደገፍ ብሎ፡-

***"እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ) መልእክተኛ ነኝ፤ "ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ" ነው እንድትሉ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ካልሆነ ግን በሰይፍ እንድመታችሁ ታዝዣያለሁ"*** አላቸው ፡፡

ከዚያም ሰዎቹ፡- ***"ጓደኛህ እንደተመለሰ ሁሉ አንተም ተመለስ"*** አሉት፡፡ ዓሊም (ዐ)፡- ***"እኔ ልመለስ? በአላህ እምላለሁ በጭራሽ አላደርገውም፡፡ ትሰልማላችሁ ወይም በዚህ በምታዩት ሰይፌ እመታችኋለሁ፤ እኔ ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ቢን አብደልሙጠሊብ ነኝ"*** አላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ተርበደበዱ፡፡ ዓሊም ገጠማቸው፡፡ ሽንፈት ተከናንበው ዘመቻው ተጠናቀቀ፡፡ ሙስሊሞችም ምርኳአቸውን ተከፋፍለው ተመለሱ፡፡

በዚሁ ምንጭ ውስጥ ከ ኡሙ ሰለማህ በተያዘ ሐዲስ የዓሊን (ዐ ) ከዘመቻው መመለስ ጅብሪል ለነብዩ (ሶ) እንደነገራቸው ለ ኡሙ ሰለማህ እንደነሯትና ሰዎች በሰልፍ ወጥተው ዓሊን (ዐ) እንዲቀበሉት ማድረጋቸውን እናያለን፡፡ ዓሊ (ዐ)ሙስሊሞች በሁለት ሶፍ (ሰልፍ) ሆነው ነብዩ (ሶ) ጋር እየጠበቁት መሆኑን ሲያይ ከፈረሱ ወርዶ በእግሩ እየሄደ ወደ ነብዩ (ሶ)ቀርቦ እግራቸውን ለመሳም አጎነበሰ፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ (ሶ)፡-

***"በል ፈረስህ ላይ ውጣ፤ አላህና ነብዩ (ሶ) ተግባርህን ወደዋል፣ በአንተ ደስተኛ ናቸው"*** አሉት፡፡

ዓሊም (ዐ) በደስታ እያለቀሰ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ አንዳንድ የታሪክ ጸሐፍት ***"ወል ዓዲያት ዷብሀን"*** የተሰኘው የቁርአን ሱራ በነብዩ (ሶ) ላይ የወረደው በዚህ ዘመቻ ላይ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

በሂጅራ (ስደት) ሌሊት ላይ ዓሊ (ዐ) በነብዩ (ሶ) ፍራሽ ላይ ማደሩን *ሙስተድረክ ዐላ አል-ሰሂሀይን* 3/5 -ሐዲስ 4263 ላይ ከኢብን ዓባስ በተያዘ ዘገባ የተጠቀሰ ሲሆን ቁረይሾች ነብዩን (ሶ) ለመግደል በዶለቱ ጊዜ ዓሊ (ዐ) የነብዩን (ሶ) ልብስ ለብሶ እሳቸውን መስሎ ህይወቱን ለነብዩ (ሶ) ፊዳ አድርጎ በቦታቸው ላይ መተኛቱንና ነብዩን (ሶ) ለመግደል የሞከሩ ሰዎች በሳቸው ቦታ ዓሊ (ዐ) መሆኑን እንዳወቁ እናነባለን፡፡ እንዲሁ በሐዲስ ቁጥር 4264 ሥር ከሀኪም ቢን ጁበይር በሆነ ሰነድ ከ ዓሊ ቢን ሁሴን በተያዘ ሐዲስ መሰረት ***"የአላህን ውዴታ በመሻት ለመጀመሪያ ግዜ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ቢኖር ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ነው"፡፡***

ይኸውም ነፍሱን ለአላህ ሸጦ በነብዩ (ሶ) ፍራሽ ላይ በተኛ ጊዜ በዛች ሌሊት ላይ ዓሊ (ዐ) ስንኝ ቋጥሮ ነበር፡-

*ምድር ከረገጡ ሰዎች ሁሉ የላቀውን ያን ክቡር ሰው፣*
*በ በይተል ዓቲቅና በድንጋዩ ጠዋፍ ካደረጉት ሁሉ ያየለው፣*
*ነፍሴን ሰጥቼ ፊዳው ሁኜ ህይወቱን በህይወቴ ለተካሁት፤*
*ውዴን መስዬ ውዴን ሆኘ መኝታውን መኝታዬ አደረኩት፡፡*
*በአላህ መልእክተኛ ላይ ሲዶልቱ ከሀዲዎቹ፣*
*መሐሪው ጌታ ኃያሉ አላህ አዳነዋ ከሸረኞቹ፡፡*
*በአላህ ጥበቃ መልእክተኛው በሰላም አደሩ በዋሻው፣*
*ሞቱን በሞቴ ድል ላደርግ በሞት መኝታው ልሆን ቤዛው፣*
*ነፍሴን ለነፍሱ ሸጬ አቆየሁት ያንን ውድ ሰው፡፡*

በተጨሪም ነብዩ (ሶ) ዓሊን ብዙ እንዳስተማሩትና በሁሉም የህይወት አውታሮች አምሳያቸው አድርገው እንደቀረጹት ከራሳቸው ከነብዩ (ሶ) አንደበት በርካታ ማስረጃዎች እናገኛለን፡፡

ነብዩ(ሶ)

***"እኔ የጥበብ መንደር ነኝ፣ ዓሊ ደግሞ በሯ ነው፡፡"***[201]

እንዲሁም በርካታ ዑለማዎች (በመናቂብ ውስጥ የዘገቡት አህመድ ቢን ሐንበል ከነዚህ ዑለማዎች ውስጥ አንዱ ነው) በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ሶ)

***"እኔ የዕውቀት ከተማ ነኝ፣ ዓሊ ደግሞ በሯ ነው"***[202] ብለዋል፡፡

እንዲሁ ቅንና ትክክለኛ የሆነ ፍርድ (ቀዷእ) በመስጠት አቻ የማይገኝለትና በሁሉም ላይ ብልጫ የተቸረው ስለመሆኑ ነብዩ (ሶ) ሲናገሩ፡-

***"ከሁላችሁም በላይ የተሸለና የበለጠ ፈራጅ ዓሊ ነው"***[203] ብለዋል፡፡

---

[201]ሰሂህ አል-ቲርሚዚ 5/637 -ሐዲስ 3723፤ ቱህፋት አል-አህወዚ-10/155፤ ፋይድ አል-ቀዲር 3/46፤ ታሪኽ ዲመሽቅ 2/459- ሐዲስ 983፤ ሂልያት አል አውሊያእ 1/63፡፡

[202]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/137-138 -ሐዲስ 4637 እና 4639፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/114፤ አል-መጅማዕ አል-ከቢር 11/65 -ሐዲስ11061፤ አል-ፊርዶስ ቢ መእሱር አል ኺጣብ1/44፤ ፋይድ አል-ቀዲር 1/36፣3/46፤ ታሪከ ባግዳድ 2/377 -ሐዲስ 887፤ 4/348 ሐዲስ 2186፤ 7/172 ሐዲስ 3613፤ 11/49-50፤ ታሪኽ በግዳድ 11/203 ***ላይ-"እኔ የጥበብ ከተማ ነኝ ዓሊ ደግሞ በሯ ነው"*** በሚል ለፍዝ (አባባል) ተጠቅሷል፡፡

[203]ተፍሲር አል-ቁርጥቢ 10/162-164፤ አህካም አል-ላመዲ 4/244፤ ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ 10/269 ***ላይ፡-"እነሆ ዓሊ በሁላችሁም የላቀ ፈራጅ ሆነ"*** ማለታቸው

ዓሊ (ዐ) በተጣለበት ኃላፊነት ላይ ፍትሃዊ (ዐድል)፣ በእኩል የሚከፋፍል ሐቀኛ፣ ከዓለማዊ ብልጭልጭ የራቀ ዛሂድ ነበር፡፡ ወደ ገንዘብ ግምጃ ቤት (በይት አል-ማል) ሄዶ የወርቅና ብር ክምችት ባየ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፡- ***"አንቺ ቢጫ ሆይ፣ አንቺ ነጭ ሆይ! ሌላውን አታልዪ፤ እኔን ግን አታታልዪኝም፡፡"***[204] ይልና ለሰዎች አከፋፍሎ ይጨርስ ነበር፡፡

ለሚስኪኖች አዛኝ፣ከደሃዎች ጋር የተወዳጀ፣ለሰዎች ችግርና ሐጃ እልባት ለመስጠት የማይሰስት፣በሐቅ የሚፈርድ፣በፍትህ የሚወስን የነብዩ(ሶ) ምትክ ነበር ፡፡

በአጠቃላይ ከነብይነት ውጭ በመላው ባህርያቱ እንደ ነብዩ (ሶ)ነበር፡፡አላህ (ሱ.ወ) በአያት አል-ሙብሐላ (ኣሊ-ዒምራን 61) የነብዩ (ሶ) ***"ነፍስ"*** አድርጎ ገልጾታል፡፡

***فَمَنْ حَاجَّكَ فِيهِ مِنْ بَعْدِ مَا جَاءَكَ مِنَ الْعِلْمِ فَقُلْ تَعَالَوْا نَدْعُ أَبْنَاءَنَا وَأَبْنَاءَكُمْ وَنِسَاءَنَا وَنِسَاءَكُمْ وَأَنْفُسَنَا وَأَنْفُسَكُمْ ثُمَّ نَبْتَهِلْ فَنَجْعَلْ لَعْنَتَ اللَّهِ عَلَى الْكَاذِبِينَ***

**"ዕውቀቱም ከመጣልህ በኋላ በርሱ (በዒሳ) የተከራከሩህን ሰዎች 'ኑ ልጆቻችንንና ልጆቻችሁን፣ ሴቶቻችንንና ሴቶቻችሁንም፣ ነፍሶቻችንንና**

---

ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም አል-ሙሐላ 9/29 ፣ሙስተረድ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/616፤---- -----ፈትህ አል-ባሪ-ዓስቀላኒ 8/167፤ አል-ሪያድ አል-ነዲራ 2/198፤ ዘኻኢር አል-ዑቅባ/83 እና ሌሎችም...

[204]አል-መናቂብ 3/257፤ ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሼይባህ 6/458፤ ፈትህ አል-ባሪ 12/309፡፡

**ነፍሶቻችሁንም እንጥራ፡፡ ከዚያም አጥብቀን አላህን እንለምን፤ የአላህንም ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናድርግ በላቸው፡፡"[205]**

## *ከፈዷላዎቹ በጥቂቱ*

በቡኻሪ፣ ሙስሊምና በሌሎችም የተዘገበው ***"ሐዲስ አል መንዚላ"***፡-

***"ዓሊ ሆይ !አንተ እኔ ዘንድ ያለህ ቦታና ደረጃ (መንዚላ) ሐሩን ሙሳ ዘንድ ያለው ቦታ ነው፡፡ ልዩነቱ ከኔ ብኋላ ነብይ ያለመኖሩ ብቻ ነው፡፡"[206]***

---

[205] ኣሊ-ዒምራን፡ 61- (ለዝርዝሩ፡-ተፍሲር ኢብን ከሲር 1/371-372 ይመልከቱ፡- በአያተል ሙብባሐላ ውስጥ ነሷራዎች (የነጅራን ክርስትያኖች) ልኡካን ከነብዩ (ሶ) ጋር ---- ለመረጋገም ቀጠሮ ይዘው በቀረቡ ጊዜ ነብዩ (ሶ) ዓሊን፣ ፋጢማን፣ ሐሰንን እና ሁሴንን ይዘው የመረጋገሚያው ቦታ በቀረቡ ጊዜ በአንቀጹ መሰረት ***"ልጆቻችን እና ልጆቻችሁ"*** በሚለው ***ሀሰንና ሁሴንን፣ "ሴቶቻችንና ሴቶቻችሁ"*** በሚለው ***ፋጢማን*** ***"ነፍሶቻችሁንና ነፍሶቻችሁ"***፣ ለሚለው ደግሞ ***ዓሊን*** ማቅረባቸው ዓሊ የነብዩ (ሶ) ነፍስ ሆኖ መቅረቡንና በርካታ ሙፈሲሮች ይህንኑ ማስቀመጣቸውን እናያለን፡፡)

[206] ለዝርዝሩ ምንጭ፡- ሰሂህ አል-ቡኻሪ 3/1359- ሐዲስ 3503፣ 4/1602- ሐዲስ 4153- የ ዳር ኢብን ከሲር እትም፤ ሰሂህ ሙስሊም 4/1870-1871- የዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ፈዷላዎች በሚለው ክፍል- ዳር ኢህያእ አል-ቱራስ አል-ዓረቢ፡፡

-ይህ ሐዲስ በሺዓም ሆነ በሱኒ መሷድሮች ሙተዋትር የሆነ ዕውቅ ሐዲስ ሲሆን ከቡኻሪና ሙስሊም በተጨማሪ በበርካታ ምንጮች ላይ ማግኘት ይቻላል፡-
ሰሂህ ኢብን ሂባን 15/369-370 ሐዲስ 6643፣ 6926፣ 6967- ሙአሰሰት አል ሪሳላህ-ቤይሩት፤ አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 2/367- ሐዲስ 3294፣ 3/117 -ሐዲስ 4575 ፣3/143 ሐዲስ 4652- ዳር አል-ኪታብ አል-ዒልሚያ -ቤይሩት፡፡ ሱነን አል-ቲርሚዚ 5/638፣ 640፣ 641 ዳ.ኢ.ቱ.ዓ. ቤይሩት፡፡ ሱነን ኢብን ማጃህ 1/42፣45፤ ሙስነድ አህመድ 1/173፣ 174፣ 175፣ 176፣ 177፣ 179፣ 182፣ 184፣ 185፣ 330፤ 3/32፣ 338፤ 6/369፣ 438- ሙአሰሰት አል-ቁርጥባ -ግብጽ፡፡ አል-አሓዲስ አል-ሙኽታራ 3/151፣ 207 እ.መካ አል- ሙከረማ፡፡ መዋሪድ አል-ዟመኣን 1/543- ዳር ኪታብ አል-

ሐሩን (ዐ) የሙሳ (ዐ) ወንድም ና ወዚር (እንደራሴ)፣ ወኪልና ጉዳይ አስፈጻሚ፣ ምትክና ረዳት. . . እንደ ነበረ ሁሉ ዓሊ (ዐ) ከነብዩ (ሶ) ጋር ያለው ደረጃና ቦታ የተገለጸበት በነብዩ (ሶ) አንደበት የተቀመጠ ህያው ቃል ነው፡፡

በ *ሰዋዕቅ አል-ሙእሪቃ*/107 ላይ ደግሞ አህመድ ባወጡት ትረካ፣ አንድ ሰው ሙዓውያን የሆነ ጥያቄ ሲጠይቅ፣ ጉዳዩን ዓሊ (ዐ) ከማንም በላይ

---

ዓልሚያ- ቤሩት፡፡ መጅምእ አል ዘዋኢድ 9/109፣ 110፣ 111- ዳር አል ረያን ሊቱራስ-ካይሮ፡፡ አል ሱነን አልኩብራ አል-ነሳኢ 5/44፣ 107፣ 108፣ 113፣ 119፣ 120፣ 121፣ 122፣ 123፣ 124፣ 125፣ 144፣ 240- ዳር አል-ኪታብ አል-ዓልሚያ፡፡ ሱነን አል-በይሐቂ አል-ኩብራ 9/40 እ.መካ አል-ሙከረማ፡፡ ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባህ 6/366፣ 7/424- እ.መክተበት አል-ሩሽድ-ሪያድ፡፡ ሙሰነፍ ዓብደረዛቅ 5/406- መክተብ አል-ኢስላሚ-ቤይሩት፡፡ ሙስነድ ኢስሃቅ ቢን ራሐዌይ 1/37 መክተበት አል-ኢማን መዲና ሙነወራ፡፡
ሙስነድ አል-በዛር 4/33፣38 -ሙአሰሰት ዑሉም አል-ቁርአን- ቤይሩት፡፡ ሙስነድ አል-ሻሺ 1/128፣ 147፣ 161፣ 165፣ 166፣ 186፣ 188፣ 195- እ.መዲና ሙነወራ፡፡ አልሙዕጀም አል-አውሰጥ 2/126፣ 3/139፣ 4/296፣ 5/287፣ 6/77፣ 83፤ 7/311፣ 8/40- ዳር አል-ሐረሜይን-ካይሮ፡፡ ሙዕጀም አቢ-ያዕላ 1/70፣ 167፣ 214 እ.ፈይሰል አባድ፡፡
-ሙሰነድ ሰዕድ 1/51፣ 103፣ 136፣ 139፣ 176፣ 177- ዳር አል-በሻኢር ኢስላሚያህ-ቤይሩት፡፡ ሙሰነድ አል-ሑመይዲ 1/38 ዳ.ኩ.ዒ- ቤይሩት፡፡ ሙዕጀም አል-ሰጊር 2/84፣ 137- አል ኩቱብ አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፡፡ ሙሰነድ አል-ጠያለሲ 1/28፣ 29- ዳር አል-መዕሪፉ- ቤይሩት፡፡ አል-ኣሓድ ወ አል-መሳኒ 5/172- ዳር አልረያን- ቤይሩት፡፡ ሙሰነድ ኢብን አል-ጀዕድ /301-ዳረል መእሙን ሊልቱራስ- ደማስቆ፡፡ አል-ሱና ኢብን አቢዓሲም 2/565፣566፣ 600- አል-መክተብ አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፡፡ ወል-ፊርዶስ ቢመእሱር አል-ኺጣብ- 5/315፣ 327- ዳር አል ኩቱብ አል-ዒልሚያ- ቤይሩት፡፡ ፈትህ አል-ባሪ 7/47፣ 9/65 ዳር አል-መዕሪፉ- ቤይሩት፡፡ አል-ተምሂድ-ኢብን አብደልበር- 22/132 እ.ወዘረት ዑመም አል-አውቃፍ ወአል-ሽኡን አል-አሰላሚያህ- ሞሮኮ፡፡ ቱህፈት አል-አህወዚ 10/157፣ 166 ዳ.ኪ.ዓ. ቤይሩት፡፡ ፈይድ አል-ቀዲር 4/358- መክተበት አል-ቲጃሪያ አል-ኩብራ-ግብጽ፡፡ተፍሲር አል-ቁርጥቢ 1/266፣ 7/277፡፡8/280- ዳር አል-ሹዕብ- ካይሮ . . . እና ሌሎች በርካታ ምንጮች፡፡

ስለሚያውቅ እሱን እንዲጠይቀው ነገረው፡፡ ሰውየው ግን ከዓሊ (ዐ) መልስ ይልቅ የሙዓውያ መልስ እንደሚያስደስተው ነገረው፡፡ ከዚያም እንዲህ *አለው፡-"በጣም ክፉ ነገር ነው ያልከው፣ ነብዩ (ሰ) በዕውቀትና በጥበብ ያነጹትን ሰው ነው የጠላሀው፡፡ በእርግጥ የአላህ መልእክተኛ(ሰ) ለዓሊ እንዲህ ብለውታል፡-*

***'አንተ እኔ ዘንድ ያለህ ቦታና ደረጃ ሐሩን ሙሳ ዘንድ ያለው ቦታ ነው፡፡ ልዩነቱ ከኔ በኋላ ነብይ አለመኖሩ ነው፡፡ ዑመር የሆነ ነገር በቸገረው ጊዜ መፍትሄና መልሱን የሚያገኘው ከዓሊ ነበር"*** አለው፡፡

## *ሐዲስ ሰድ አብዋብ (የበሮቹ መዘጋት ሐዲስ)*

በአላህ ትእዛዝ መሰረት ነብየ (ሰ) ወደ መስጅድ የሚያስወጣ ሁሉንም በሮች ሲዘጉ የዓሊ (ዐ) ቤት በር ግን ክፍት ሆኖ እንዲቆይ አድርገዋል፡፡ ይህንን ክስተት ሁሉም ዑለማዎች ያወሩትና የዘገቡት ሲሆን ከነዚህም አል-ሐኪም በ ሙስተድረክ የዘገበው ተጠቃሽ ነው፡፡

(ይህንን በተመለከተ ከዒብን ዓባስ በተያዙ አስር የሚሆኑ የዓሊን (ዐ) ትሩፋቶችና ገድሎች በዘረዘረበት ረዥም ሐዲስ ውስጥ፡- ***"የአላህ መልእክተኛ (ሰ) ከዓሊ ቤት በር በስተቀር የሁሉም ቤት በሮች ተዘግተዋል"***[207] ማለታቸው ተጠቅሷል፡፡

---

[207]ሙሰነድ አህመድ ቢን ሐንበል 5/25- ሐዲስ 3062- ዳር አል-መዓሪፋ- ግብጽ፡፡

ይህንን በሚመለከት ዑመር ቢን ኸጧብ እንኳ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

***"ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ሶስት ነገሮች ተሰጥቷል፤ ከነዚህ ውስጥ አንዱን እንኳ ማግኘት ብችል ከቀይ ውድ ግመሎች ይበልጥብኝ ነበር፡፡ እነሱም፡- የአላህ መልእክተኛ (ሰ) ልጅ ፋጢማ ባለቤቱ መሆኗ፣ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ) ጋር ለሳቸው የመጣ ነገር ሁሉ ለሱም የተገባ ሆኖ በመስጅድ ውስጥ እንዲቆይ መደረጉና የኸይበር ዕለት የተሰጠው ባንዲራ ናቸው" ፡፡***[208]

በተጨማሪም፡-

***إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَهُمْ رَاكِعُون. وَمَنْ يَتَوَلَّ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا فَإِنَّ حِزْبَ اللَّهِ هُمُ الْغَالِبُونَ***

---

መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/120፡፡ ከሳኢስ አሚር አል-ሙእሚኒን- አል-ነሳኢ/ 61-64 እ.አል-ሐይደሪያ፡፡ ዘኻኢር አል-ዑቅባ/ 87፡፡ ኪፍየት አል-ጧሊብ- አል-ከንጂ አል-ሻፊዒ /240- እ.አል- ሐይደሪያ፡፡ አል-መናቂብ አል-ኸዋሪዝሚ /72፡፡ አል-ኢሳባ- ኢብን ሐጀር አል-ዓስቀላኒ 2/509፡፡ የናቢዕ አል-መወዳ- አል-ቀንዱዚ አል-ሐነፊ/ 34- እ.እስላምቡል፣ አንሳብ አል-አሽረፍ አል-በላዘሪ 2/106 ሐዲስ 32፣ አል-መናቂብ አል-መጋዚሊ/257፡፡ ተዝኪረት አል-ኸዋስ/ 417፡፡ አል-ሪያድ አል-ነዲራህ- 3/253፡፡

[208] ሙስነድ አህመድ7/21 ሐዲስ 4797 ዳረል መዓረፍ ግብጽ፡፡ የናቢዕ አል-መወደህ- አል-ቁንዱዚ/ 210- እ.እስላምቡል፡፡ አል-መናቂብ አል-ኸዋሪዝሚ አል-ሐነፊ/ 238- እ.አል-ሐይደሪያ፡፡ አል-ሰዋዕቅ አል-ሙህሪቃ/776- እ.አል-የመኒያ፡፡ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/120፡፡ ታሪኽ አል-ኹለፋእ አል-ስዩጢ /172፡፡ ነዝም ዱረር አል-ሲምጢይን -አል-ዘረንዲ አል-ሐነፊ /129፡፡ ከንዝ አል-ዑመል 15/101- ሐዲስ 291፡፡ አል-ሪያድ አል-ነዲረህ 2/254፡፡

*"እነሆ ወሊያችሁ (መሪያችሁ) አላህ፣ መልዕክተኛውና እነዛ ያመኑ በሩኩዕ ላይ ሆነው ሳሉ ዘካ የሚሰጡ ናቸው፤ ለአላህ ለመልእክተኛውና ለነዛ ላመኑት ያደረ ሰው፣ እነሆ የአላህ ህዝቦች እነሱ ናቸው አሸናፊዎች"*[209] የሚለው ቁርአን አያህ ዓሊን (ዐ) አስመልክቶ የወረደ አያህ መሆኑን ሙፈሲሮች[210] የተስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

[209] አል ማኢዳ፡ 55 እና 56

[210] ለ እማኘ ያህል የተወሰኑ የተፍሲር መጽሀፍትን መጥቀስ ይቻላል፡-

-ሸዋሂድ አል-ተንዚል አል-ሐሰካኒ አል-ሐነፊ- 1/161-184 ሐዲስ 216-241፣ አስባብ አል-ኑዙል አል-ዋሂዲ- 113 እና 114፤ አል-ከሻፍ አል-ዘመኽሸሪይ 1/649፤ መናቂብ ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ- ኢብን አል-መጋዚሊ /311 ሐዲስ 354-358፤ ኪፋየት አል-ጧሊብ አል-ከንጂ- 228፣ 250፣ 251፤ ዘኽኢር አል-ዑቅባ-88፣ 102፤ መናቂብ አል-ኸዋሪዝሚ- 187፤----

---አል-ፉሱል አል-ሙሒማ- ኢብን አል-ሲባግ አል-ማሊኪ 123፣108 አል-ዱር አል-መንሱር አስ-ሱዩጢ 2/293፤ ፈትህ አል ቀዲር አል-ሸውካኒ 2/53፤-------

አል-ተስሂል ሊዑሉም አል-ተንዚል 1/181፤ ተፍሲር አል-ቁርጥቢ 6/219-220፤ተፍሲር አል ጠበሪ 6/288-289፤ ዛድ አል-መሲር ፊ ዒልሚ አል-ተፍሲር- ኢብን አል-ጀውዚ 2/383፤ ፈትህ አል-በያን ፊ መቃሊድ አል-ቁርአን 3/51፤

ተዝከረት አል-ኸዋስ 18፣208፤ ኑር አል-አብሷር አል-ሸብለንጂ- 71፤ የነቢዕ አል-መውዳ 115፤ ተፍሲር ፈኽር አል-ራዚ 12/26፤ ተፍሲር ኢብን ከሲር 2/71፤ አህካም አል-ቁርአን አል-ጃሷስ 4/102፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 7/17፤ ነዝም ዱርር አል-ሲምጠይን- 86-88፤ ሸርህ ነህጀል በላጋ- ኢብን አብ አል-ሐዲድ 13/288፤ አል-ሰዋሂቅ አል-ሙህሪቃ 24፤ አንሳብ አል-አሽረፍ 2/150፤ አል-ሐዊ ሊልፈትዋ አል-ሱዩጢ 1/139-140፤ ጀሚዕ አል-ኡሱል 9/478፤ አል-ሪያድ አል-ነዲራ 2/273፣302፤ መጣሊብ አል-ሰኡል ኢብን ጦለሃ አል-ሻፊዒ- 31፤ ፈራኢድ አል-ሲምጠይን 1/11፣190- ሐዲስ 150፣151፣ 153. . . እንዲሁም በከንዝ አል-ዑመል 15/146 ሐዲስ 416፣ ገጽ 95 ሐዲስ 269 . . . ሌሎችም፡፡

***ሁለተኛው ኢማም***

ሁለተኛው ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ) ነው፡፡ እናታቸው ፋጢማ አል-ዘሕራ ቢንት ሙሀመድ (ሶ) ናቸው፡፡ ኢማም ሐሰን የነብዩ (ሶ) ሲብጥ (የልጅ ልጅ)፣ ሁለተኛው የነብዩ (ሶ) ኸሊፋ (ተተኪ) ሆኖ ኢማም ተደርጎ በወህይ የተሾሙ መሪ ናቸው፡፡

በመዲና አል-ሙነዋራ ማክሰኞ ቀን በረመዷን ወር አጋማሽ ላይ በሁለተኛው ወይም በሶስተኛው ዓመተ ሂጅራ ተወለዱ፡፡ በሰፈር ወር ሰባተኛው ቀን፣ በዕለተ ሐሙስ በአርባ ዘጠንኛው ሂጅራ ተመርዘው (በመርዝ) ሸሂድ ሆነው ሞቱ፡፡ ወንድማቸው ኢማም ሁሴን (ዐ) የተከበረው ሰውነታቸውን ለቀብር አዘጋጅተው ቀበሩት፡፡ በበቂዕ የመቃብር ሥፍራ በመዲና ሙነወራ ተቀበሩ፡፡

በዘመኑ በዒባዳ ከሁሉም የበለጡ፣ በዒልም ላይ ብልጫ ያላቸው (አፍደል) ታላቅ ኢማም ነበሩ፡፡ ከነብዩ (ሶ) ጋር የሚመሳሰሉ፣ በዘመኑ ከአህለልበይት (ዐ) እጅግ ለጋስና በትእግስታቸው አቻና ወደር የለሽ የነበሩ የነብዩ (ሶ) ኸሊፋ ነበሩ፡፡[211]

በአንድ ወቅት ከአገልጋዮቻቸው አንዷ አገልጋይ አንድ ዘንቢል ትርንጎ በቀረበላቸው ወቅት እንዲህ እንዳሏት ይጠቀሳል፡-"ከዛሬ ወዲያ ለአላህ ፊት ስል ነጻ ሆነሻል" ካሉ በኋላ “አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ አድርጎ ነው በምግባር ያነጸን” በማለት የሚከተለውን የቁርአን አያህ አወሱ፡፡

**وَإِذَا حُيِّيتُم بِتَحِيَّةٍ فَحَيُّوا بِأَحْسَنَ مِنْهَا أَوْ رُدُّوهَا**

---

[211] ለተፍሲሩ የኢብን አባ በክርን “ታሪክ ደመሽቅ” የኢማም ሐሰን የህይወት ታሪክ ክፍል ስር ይመልከቱ፡፡
-እንዲሁም አል-መናቂብ-ኢብን ሸሕር ኣሹብ 4/18፤ ከሽፍ አል-ጉማ 2/31

**"በአንድ ሰላምታ ሰላም በተባላችሁ ግዜ የተሻለና የበለጠ አድርጋችሁ አጸፋውን መልሱ፤ ወይም ተመሳሳይ አጸፋውን መልሱ፡፡"[212]**

### *ከትእግስተኝነታቸውና ቻይነታቸው*

በአንድ ወቅት ከሻም ሀገር የሆነ ሰው ኢማም ሀሰን (ዐ) በፈረስ ሲሄዱ አያቸውና የእርግማን መዓት ያወርድባቸው ገባ፤ ኢማም ሀሰን (ዐ) ግን ምንም መልስ (አጸፋ) ሳይመልሱለት ዝም ብለው ይሰሙት ነበር፡፡ ሰውየው የተናገረውን ሁሉ ተናግሮ ካበቃ በኋላ ኢማም ሐሰን (ዐ) ወደ ሰውየው ቀርበው ሰላምታ ካቀረቡለትና ፈገግታ ካሳዩት በኋላ እንዲህ አሉት፡-

***"አንተ ሼይኽ ሆይ! እዚህ ሀገር እንግዳ ሳትሆን አትቀርም፤ የተመሳሰለብህ ነገር ሳይኖር አይቀርም፡፡ ብትጠይቀን እንሰጥሀለን፣ ምሩኝ ብትል እንመራሃለን፣ እንድንሸከምህ ከፈለክ እንሸከምሃለን (ለመጓጓዝ ብትፈልግ እናጓጉዝሃለን)፣ ርቦህ ከሆነ እናጠግብሃለን፣ የሚለበስ ከሌለህም እናለብስሃለን፣ ሐጃ ካለብህ እናብቃቃሀለን፣ ተባረህ ከሆነም እኛ እናስጠጋሃለን፣ የምትፈልገው ነገር ካለ እናደርግልሀለን..."***

ሰውየው ንግግራቸውን በሰማ ግዜ አለቀሰ፡፡ እንዲህም ኣለ:-***"እነሆ አንተ በምድር ላይ የአላህ ኸሊፋ እንደሆንክ እመሰክራለሁ፡፡"***

**اللَّهُ أَعْلَمُ حَيْثُ يَجْعَلُ رِسَالَتَهُ**

**"አላህ መልእክቱን የት ማድረግ እንደለበት ኩሉም በላይ አዋቂ ነው፡፡"[213]**

[212]አል-ኒሳእ፡ 86

***ሶስተኛው ኢማም***

ሶስተኛው ኢማም ደግሞ ሁሴን ቢን ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ፋጢማ ቢንት ሙሀመድ (ሰ) ናቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሲብጥ ናቸው፡፡

ሶስተኛው ኸሊፋና ከሳቸው በኋላ ያሉት የዘጠኝ ኢማሞች አባት ናቸው፡፡ ከወንድማቸው ሀሰን (ዐ) በኋላ የሰዎች ሁሉ ኢማም ናቸው፡፡

በሸዕባን ወር ሶስተኛው ቀን ኢማም ሀሰን (ዐ) በተወለዱበት ዓመት (ኢማም ሐሰን ተወልደው አመት ሳያልፈው ማለት ነው) በመዲና ሙነወራ ተወለዱ፡፡ በታዋቂው የዓሹራ ቀን ክስተት በሙሀረም አስር፣ በስድሳ አንደኛው ዓመት ሂጅራ ተበድለውና በዛ በረሃ ውስጥ ተጠምተው በክፉዎች ሰይፍ ተገድለው ተሰዉ፡፡ ከተገደሉ ከሶስት ቀናት በኋላ ልጃቸው ዘይን አልዓቢዲን (ዐ) ሀላፊነቱን ወስደው ቀብሯቸው ባለበት ስፍራ በተቀደሰው ከርበላ፣ በኢራቅ ውስጥ አሳረፏቸው፡፡

ፈዷላቸው ከመበርከቱ የተነሳ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ነብዩ (ሰ) እንዲህ ይላሉ፡-

***"ሁሴን ከኔ ነው፤ እኔም ከ ሁሴን ነኝ፡፡"[214]***

---

[213]አል-አንዓም: 124፤ ኢብን ሸህር አሹብ 4/19

[214]-ሰሂህ ኢብን ሒባን 15/428- እ.ሙአሰሰት ሪሳላህ ቤይሩት፤ -ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/134- እ.ኩቱብ ዒልሚያ- ቤይሩት፤ -መዋሪድ አል-ዘመኣን/554- እ.ዳረል ኩቱብ ዒልሚያ- ቤይሩት፤ -ሱነን አል-ቲርሚዚ 5/554 እ.ዳረል ቱራስ ዓረቢ- ቤይሩት፤ -ሱነን ኢብን ማጃህ 1/51- እ. ዳረል ፊክር ቤይሩት፤ -ሙሰነድ አህመድ 4/172 እ.ሙአሰሰት ቁርጡባ- ግብጽ፤ -ሙሰነፍ ኢብን አቢ-ሸይባ 6/380- መክተብ ሩሽድ- ሪያድ፤ -አል-መዕጀም አል-ከቢር 3/33፣ 22/274 እ.መክተበት አል-ዑልም ወልሂከም- ሞሱል፤

እንዲሁም ኢማም ሁሴንና ወንድማቸው ሐሰንን በተመለከተ ነብዩ (ሶ) እንዲህ ብለዋል፡-

***"እነዚህ ሁለቱ ከዱንያ (ከዚች ዓለም) የዓይኔ ማረፊያና ምርጥ መዓዛዎቼ ናቸው፡፡"[215]***

በሌላ ሐዲስ እንዲሁ ነብዩ (ሶ)፡-

***"ሐሰንና ሁሴን የጀነት ወጣቶች አለቆች ናቸው፡፡"[216]***

---

-ከንዝ አል-ዑማል 6/221፣ 7/108፣ -ኢብን ከሲር -ኡስድ አል- ጋባ 2/19፣5/130፤ (ቡኻሪ በ አል-አደብ አል-ሙፍረድ ውስጥ "ሙዓነቀት አል-ሶቢይ" በሚለው ክፍል ስር ዘግቦታል፣

[215]ሰሂህ ቡኸሪ 3/1371፤5/2234 እ.ዳር ኢብን ከሲር ቤይሩት፤ ሱነን አል-ቲርሚዝ 5/657 እ.ዳር አህያእ ቱራስ አል-ዓረቢ፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/181፤ ሙሰነድ አል-ጠያለሲ 260- እ.ዳር አል- መዕሪፋ- ቤይሩት፤ ሙሰነድ አቢ ያዕላ 10/106፤ አል-ሙዕጀም አል-ከቢር 3/128፣ 4/155፤ሙሰነድ አህመድ ቢን ሐንበል 2/85፣ 93፣ 114፣ 153፤ ሙሰነድ አቢ ዳውድ 8/160፤ አቡ ነዒም- ሂልያት አል- አውሊያእ 5/70፤ አል-ነሳኢ አል-ኸሷኢስ 37፤ ፈትህ አል- ባሪ ፊ ሸርህ ቡኻሪ 1/100፤ ኢብን ዓሳኪር- ታሪኽ ድመሽቅ በኢማም ሁሴንና ኢማም ሐሰን (ዐ) የህይወት ታሪክ ክፍል፡፡

[216]ሰሂህ ኢብን ሒባ 15/411፣412፣413፤ ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሐይን 3/182፣ 429- እ.ዳረል ኩቱብ አል-ዒልሚያ፤ አል አሓዲስ አል-ሙኽታራ 1/99- እ.መከተል ሙከረማ፤ ሱነን አል-ቲርሚዚ 5/656፣ 660- ዳር ኢህያእ አል-ቱራስ አል-ዓረቢ፤ መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 9/165፣ 182፣ 183፣184፣ 201- ዳር አል- ረያን ሊቱራስ- አል ቃሒራ፤ አል-ነሳኢ ሱነን አል-ኩብራ 5/50፣ 80፣ 90፣ 145፣ 146፣ 148፣ 149፣ 150- ዳር አል- ኩቱብ አል ዒልሚያ፤ ሱነን ኢብን ማጃህ 1/44- እ.ዳር አል-ፊክር ቤይሩት፤ ሙሰነፍ ኢብን አቢ ሸይባ 6/378- እ.መከተበት አል-ሩሽድ- ሪያድ፤ ኢብን ዓሳኪር ታሪኽ ዲመሽቅ (የኢማም ሐሰንና ኢማም ሁሴን (ዐ) የህይወት ታሪክ ክፍል ስር፡፡)

እንዲሁም በሌላ ሀዲስ ነብዩ(ሶ)፡-

**"ሐሰንና ሑሴን ቆመውም ሆነ ተቀምጠው ኢማሞች ናቸው፡፡"**[217]

ከኢማም ሁሴን ወደር የለሽ ለጋስነት አንዱን ክስተት ለመጥቀስ ያህል፡- በአንድ ወቅት አንድ ገጠሬ ከሳቸው ስጦታ ፈልጎ ስንኝ በቋጠረላቸው ጊዜ የሰጡት ምላሽ ተጠቃሽ ነው፡፡

*አንቱን ከጅሎ የለም ያፈረ፣*

*በሮን አንኳኳቶ ጸጋ ያልሰፈረ፣*

*አንቱ ነሁ ለጋስ ጋሻ መከታ፣*

*አምሳያ የለሽ የሰው ዓይነታ።*

*ነበር አባትዎ የፋሲቆች ደምሳሽ፣*

*የዲን ምሰሶ የልብ ኢድራሽ፡፡*

*ቀደምቶቻችሁ ባይኖሩን ኖሮ፣*

*ሆነን ቀርተን ነበር የእሳት ጭራሮ፡፡*

በዚህ ግዜ ኢማም ሁሴን (ዐ) አራት ሺ ዲናር ከሰጡት በኋላ እንዲህ በማለት (ቀጣዩን ሐሳብ በያዘ ስንኝ) ይቅርታ ጠየቁት፡፡

*በጄ ያለችውን ይችን ተቀበለኝ*

*ላንተ ያለኝን ውዴታ እወቅልኝ*

*እጄ በማጠሩ ይቅርታ አድርግልኝ*

*ታሪካችን ከስሞ ጊዜው ተቀይሮ*

*እጃችን አጠረ ዘመኑ ተሸሮ* [218]

---

[217]ኢብን ሸህር ኣሹብ 3/394፤ ከሽፍ አል-ጉማ 1/533፣ 2/36፤ አል-ፉሱል አል-ሙኽታራ/303፡፡

[218] *መናቂብ-* ኢብን ሸሕር ኣሹብ 1/65

ኢማም ሁሴን (ዐ) በታሪክ ውስጥ አምሳያ በልተገኘለት ትግላቸው የኢስላም ሸሪዓንና ዲንን ህያው አደረጉ የአያታቸውን (ሶ) ኋይማኖት ብሎም ዓለሙን ሁሉ እስከ ቂያማ ቀን ህያው ያደረገ፣ የሸሂዶች ሁሉ አውራና ከወንድሙ በኋላ የሰዎች ሁሉ በላጭ የሆነ የኢስላም ጀግና ናቸው፡፡

## 4. አራተኛው ኢማም

አራተኛው ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው የንጉስ የዝደጀር ልጅ ሻህ ዚናን ነች፡፡ በመዲና አል-ሙነወራ በጁማድ አል-ኡላ ወር አጋማሽ ላይ በሰላሳ ስድስተኛው ዓመተ ሂጅራ፣ ኢማም ዓሊ( ዐ) በስራን ድል አድርገው በከፈቱበት እለት ተወለዱ፡፡ በዕለት ሰንበት (ቅዳሜ) በሙሀረም ወር ሀያ አምስተኛው ቀን በዘጠና አምስት ዓመተ ሂጅራ በሃምሳ ሰባት ዓመታቸው ተመርዘው ሞቱ፡፡ በልጃቸው ኢማም አል-ባቂር (ዐ.ሰ) አዘጋጅነት በመዲና አል-ሙነወራ በ በቂዕ የመቃብር ስፍራ ተቀበሩ፡፡

በዒልም፣ በዒባዳ፣ በፈዲላ፣ በተቅዋና ችግረኞችን በመርዳት በዘመናቸው አምሳያ የሌላቸው ብቸኛው ሰው ነበሩ፡፡

ሊቃውንቶች ከሳቸው ያወሩትና የዘገቡት ቅርስ ከመበርከቱ የተነሳ ለቁጥር ያዳግታል፡፡ በርካታ ወዕዝ (ምክር፣ ንግግር፣ ተግሳጽ) እና ዱዓዎች ተዘግበዋል፡፡

ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን (ኢማም አል-ሰጃድ/ዘይነል ዓቢዲን) (ዐ) በድቅድቅ ጨለማ በየሌሊቱ በጀርባቸው ላይ በ ድርሀምና በዲናሮች የተሞላ ከረጢት ተሸክመው፣ እንዲሁም ምግብና የማገዶ እንጨት ተሸክመው የእያንዳንዱን የድሃ በር በማንኳኳት ላገኙት ሰው በሙሉ ይለግሱ ነበር፡፡ ይህንን ሲያደርጉ

ሰዎች እንዳያውቋቸው ፊታቸውን ይሸፋፈኑ ነበር፡፡ እሳቸው በሞቱ ጊዜ ነበር የመዲና ሰዎች *ባለ ከረጢቱ* መሆናቸውን ያወቁት፡፡

በምግብ ማዕዳቸው ላይ ወላጅ አልባዎች፣ ሚስኪኖችና ችግርተኞች እንዲገኙ ማድረግ ያስደስታቸው ነበር፡፡

ከመልካም ድንቅ ስብዕናቸው፡- የረመዷን ወር በገባ ቁጥር አገልጋዮቻቸውን (ኻዲሞቻቸውን) ይጠሩና እንዲህ ይሏቸው ነበር፡-

***"ከናንተ ውስጥ ትዳር የምትፈልግ ካለች እድራታለሁ፣ መሸጥ የምትፈልግም ካለች አሸጣታለሁ፣ ነጻ መውጣት የምትፈልግ ካለችም ነጻነቷን አውጃለሁ፡፡"***

አንድ ጠያቂ (የኔ ቢጤ) ወደሳቸው (ዐ) በመጣ ጊዜ፡-

*"መርሐበን! ስንቄን ወደ አኺራ ተሸክምልኝ የምትሄድ ሰው ሆይ እንኳን ደህና መጣህ!"* ይሉ ነበር፡፡

ከዒባዳቸውና ከተቅዋቸው (ወረዕ) ወደር የለሽነትና ጥንካሬ የተነሳ በቀንና ሌሊት ውስጥ አንድ ሺህ ረከዓ ይሰግዱ ነበር፡፡ የሰላት ወቅት በቀረበ ጊዜ ሰውነታቸው ይብረከረክና መልካቸው ይገረጣ ነበር፡፡ በግንባራቸው፣ በመዳፎቻቸውና፣ በጉልበቶቻቸው በሚታየው የሱጅድ ምልክት የተነሳ *"ዙ አሱ-ሰፊናት"* በሚሰኝ ቅጥል ስም ይታወቁ ነበር፡፡

በአንድ ወቅት አንድ ሰው በሚያስጠላ ቃላት በግልጽ ሰደባቸው፡፡ እሳቸውም ምንም ሳይሉ በዝምታ አለፉት፡፡ ከተወሰነ ቀናት በኋላ ኢማሙ (ዐ) ወደ ሰውየው ሄዱ፡፡ በዚህ ወቅት በቦታው የነበሩ ሰዎች የባለፈውን ስድብ አጸፋ ሊመልሱለት መስሏቸው ነበር፡፡ እሳቸው (ዐ) ግን የሚከተለውን የቁርአን አያህ ቀሩና፡-

**وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ**

**"እነዛ ቁጣቸውን ዋጥ የሚያደርጉና ለሰዎች ይቅር የሚሉ፣ አላህ በጎ የሚውሉትን ይወዳል፡፡"[219]**

ቀጠል በማድረግ ለሰውየው እንዲህ አሉት፡-

***"ያልከኝ ነገር በእርግጥም በኔ ላይ ካለ፣ አላህን ምህረት እጠይቃለሁ፡፡ በሌለብኝ ነገር ወንጅለህኝ ከሆነም አላህ ምህረቱን ይለግስህ (ይቅር ይበልህ)፡፡"[220]***

### አምስተኛው ኢማም

አምስተኛው ኢማም ደግሞ መሐመድ ቢን ዓሊ አል-ባቂር (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ፋጢማ ቢንት ኢማም ሐሰን (ዐ) ናት፡፡ በዕለተ ሰኞ፣ በሶስተኛው የሰፈር ወር (በመጀመሪያው ቀን ረጀብ ወር እንደሆነም ይነገራል) በሃምሳ ሰባት ዓመተ-ሂጅራ ተወለዱ፡፡ ከዐላዊዎች መካከል የመጀመሪያው ዐላዊ ነበሩ፡፡ በዕለተ ሰኞ፣ ሰባተኛው ቀን ዙልሂጃ ወር በመቶ አስራ አራት ዓመተ-ሂጅራ በመርዝ ተመርዘው በሃምሳ ሰባት ዓመታቸው አለፉ፡፡ በልጃቸው በኢማም አል-ሷዲቅ (ዐ.ሰ) አዘጋጅነት በመዲና አል-ሙነወራ በበቂዕ የመቃብር ስፍራ ተቀበሩ፡፡

---

[219]አል-ዒምራን: 134

[220]ለዝርዝሩ የ ኢብን ሸህር ኣሹብ *አል-መናቂብ*፣ የ አርቢሊን *ከሽፍ አል-ጉማ* እና የመጅሊሲን *ቢሓር አል-አንዋር* ይመልከቱ፡፡

የታላቅ ፈድል፣ የማይነጥፍ ብርታት፣ ጥልቅ እውቀት፣ ድንቅ ስብዕና፣ ሰፊ ትዕግስትና ቻይነት፣ ወደር የለሽ ዒባዳና መተናነስ፣ የከበረ ልግስናና ይቅር ባይነት ባለቤት ነበሩ፡፡

ከመልካም ስብዕናቸው ወደር የሌሽነት አንድ ክስተት ለመግለጽ ያህል በአንድ ወቅት አንድ ነስራኒ (የክርስታን ሃይማኖት ተከታይ) የሆነ ሰው፡-

"አንተ በቀር (ለም) ነህ" አላቸው

እሳቸውም (ዐ) ፡-"እኔ ባቂር ነኝ" አሉት፡፡

ሰውዬውም፡- "አንተ የገረድ (የምግብ አብሳይ) ልጅ ነህ "አላቸው፡፡

ኢማሙም (ዐ)፡-"እሱ እንኳ አንተ ያዛባህው ነው" አሉት፡፡

ሰውየው "አንተ የዛች ዋልጌ ጠቋራ ልጅ ነህ"አላቸው

እሳቸውም(ዐ)፡- ***"ያልከው እውነት ከሆነ አላህ ይማራት፣ ዋሽተህ ከሆነ ደግሞ አላህ ይማርህ"*** አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ያ ነስራኒ (ክርስትያን) ሰለመ፡፡[221]

እውቀታቸው እንደ ጥልቅ ባህር ነበር፡፡ ለሚጠየቁት ጥያቄ በሙሉ ያለምንም ማንገራገርና አፍታ እንኳ ሳይቆዩ አጥጋቢ ምላሽ ይሰጡ ነበር፡፡

ኢብን ዓጧእ አል-መኪ ስለ ኢማሙ (ዐ) ያሉትን ባጭሩ ለመጥቀስ ያህል፡-

*"ታላላቅ የሚባሉ ዑለማዎች አቢ-ጃዕፈር ሙሐመድ ቢን ዓሊ ቢን ሁሴን (ዐ) ዘንድ የሚተናነሱትን ያህል ዬትም ሲተናነሱና ትንሽ ሆነው ሲታዩ አንድም ዓሊም የትም አይቼ አላውቅም፡፡ አል ሐኪም ቢን ዑትባህ የቱን ያህል በህዝብ*

221 አል-መናቂብ 4/207

*ውስጥ የታወቀና የተከበረ ቢሆንም ሙሀመድ ቢን ዓሊ አል ባቂር (ዐ) ዘንድ ግን በመምህሩ ፊት እንደቆመ ህጻን ልጅ ሆኖ አገኘቼዋለሁ፡፡"*[222]

መሐመድ ቢን ሙስሊም እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡-

*"ወደ አዕምሮዬ የመጣን ማንኛውንም ጥያቄ አቢ-ጀእፈርን ሳልጠይቅ የቀረሁበት አንድም ጥያቄ አልነበረኝም፡፡ በዚህ መልኩ ሰላሳ ሺህ የሚደርሱ ሐዲሶችን ለመጠየቅ በቅቻለሁ፡፡"*[223]

ኢማም አል-ባቂር ሀሌም ዝክር ያደርጉ ነበር፡፡ አንደበታቸው አላህን ከመዘከር ቦዝኖ አያውቅም፡፡ ይህንን በተመለከተ ኢማም አል-ሷዲቅ ሲናገሩ፡፡

*"አባቴ ዚክርን እጅግ ያበዙ ነበር፡፡ ከሳቸው (ዐ) ጋር መንገድ ስሄድ ይዘክሩ (ያወድሱ) ነበር፡፡ ምግብም ከሳቸው ጋር እመገብ ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ ሁሉም ውዳሴ አይለያቸውም ነበር፡፡ ሰዎችን በሚያነጋግሩበት ጊዜ እንኳ አላህን ከመዘከር ከልክሏቸው አያውቅም፡፡"*[224]

ተሐጁድና ኢባዳ እጅግ ያበዙ ነበር ፤ለቅሶና እምባም ተለይቷቸው አያውቅም ነበር፡፡

***ስድስተኛው ኢማም***

ስድስተኛው ኢማም ጀዕፈር ቢን መሐመድ አል-ሷዲቅ (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ፋጢማ ስትሆን *ኡሙ ፈርወህ* በሚል ቅጽል ስም ትታወቃለች፡፡ በዕለተ ሰኞ፣ በ ረቢዕ አል-አወል ወር አስራ ሰባተኛው ቀን-በነብዩ (ሶ) የልደት

---

[222]አዕላም አል-ወራ 269 ክፍል 4፤ አል ኢርሻድ 2/160

[223]አል-ኢኽትሳስ /210

[224]ዑደት አል-ዳዒ /248 ክፍል 5

ቀን- በሰማያ ሶስት ዓመተ-ሂጅራ በመዲና ተወለዱ፡፡ በዕለተ ሐሙስ፣ ሸዋል ወር ሀያ አምስተኛው ቀን፣ በመቶ አርባ ስምንት ዓመተ-ሂጅራ በስልሳ አምስት ዓመታቸው በመርዝ ተመርዘው ሞቱ፡፡ በልጃቸው በኢማም አል-ካዚም (ዐ) አዘጋጅነት በመዲና አል-ሙነወራ በ በቂዕ የመቃብር ስፍራ ተቀበሩ፡፡ በዒልም፣ በፊድል፣ በጥበብና ፊቂህ፣ በዙህድና ተቅዋ፣ በሐቀኝነትና ፍትሃዊነት፣ በልግስና፣ በጀግንነት፣ በድንቅ ስብዕናና በሌሎች መልካም ትሩፋቶች ተንታኞች ተንትነው የማይደርሱበት የሆነ የታላቅ ዕውቀትና ተግባር ባለቤት ነበሩ፡፡

አል-ሙፊድ (ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡-

*"ዑለማዎች ከሳቸው (ዐ) ነቅል ያደረጉትን (የዘገቡትን) ያህል ከ ሌሎች አህለልበይቶች አልዘገቡም፡፡ ከአህለልበይቱ ጋር ግንኙነት ከነበራቸው የታሪክና የአኽባር (ሐዲስ) ሊቃውንት ከዓቢ አብደላህ ማለትም ከአል-ሷዲቅ (ዐ) የዘገቡትን ያህል ከማንም አልዘገቡም፤ የሐዲስ ሰዎች ባደረጉት ጥናት መሰረት አቢ-አብደላህን ምንጭ በማድረግ ሐዲስ የተረከሉ አራት ሺህ የሚደርሱ ታማኝ ራዊዎች (ተራኪዎች) ዝርዝር ማስቀመጣቸውን ድርሳናት አሳይተዋል. . ."*[225]

የሐነፊያ መዝሐብ ባለቤት አቡ-ሐኒፋና የማሊኪያ መዝሐብ ባለቤት ኢማም ማሊክ ከተማሪዎቻቸው ውስጥ ነበሩ፡፡

---

[225] አል-አርሻድ 2/179

ከዛሂድነታቸው መገለጫዎች ውስጥ ምግባቸው ኮምጣጤና ዘይት ነበር፡፡ ወፍራምና ከርዳዳ ሸሚዝ ይለብሱ ነበር፡፡ በጓሯቸው ውስጥ ራሳቸው ይሰሩ ነበር፡፡

ከዒባዳቸው ደግሞ እጅግ ሶላት ያበዙ ነበር፡፡ ሶላት ውስጥ እራሳቸው እስከ መሳት ይደርሱ እንደነበርም ይነገራል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ሌሊት ላይ ሐሩን አል-ዓባሲ ኢማሙን (ዐ) ባስጠራቸው ጊዜ ተላላኪው ያየውን ሲተርክ፡-

*"ወደ ቤታቸው በር ተጠግቼ ሳይ በግል ክፍላቸው ውስጥ ሆነው ጉንጫቸውን አፈር ውስጥ ደብቀውና መዳፎቻቸውን ዘርግተው አገኘኋቸው፡፡ ፊታቸውና ጉንጫቸው በአፈር ተለውሰው ይታዩ ነበር፡፡"*

ልግስናቸው የላቀ፣ ድንቅ ስብዕናና መልካም ጸባይ የተቸሩ፣ አንደበታቸው ለስላሳ፣ አብሮነታቸው የሚያስደስት፣ ማህበራዊ ኑሮአቸው ያማረ ድንቅ ሰው ነበሩ፡፡

## *ሰባተኛው ኢማም*

ሰባተኛው ኢማም ሙሳ ቢን ጀዕፈር አል-ካዚም (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ሐሚዳ አል-ሙሰፋት ትባላለች፡፡ በመካና መዲና መካከል በሚገኝ *አል-አብዋእ* በተሰኘ ቦታ በእለተ እሁድ፣ በሰፈር ወር ሰባተኛው ቀን፣ በመቶ ሀያ ስምንት ዓመተ ሂጅራ ተወለዱ፡፡ በሐሩን አል-ዓባሲ እስር ቤት እያሉ በእስር ላይ በበደልና ጭቆና ለአስራ አራት አመታት ከቆዩ በኋላ  በረጀብ ወር ሃያ አምስተኛው ቀን፣ በመቶ ሰማንያ ሶስት ዓመተ-ሂጅራ በመርዝ ተመርዘው ሞቱ፡፡ በልጃቸው ኢማም አል-ሪዷ (ዐ) አዘጋጅነት አሁን የተከበረው መርቀዳቸው ባለበት ቦታ በኢራቅ-ካዚሚያ ተቀበሩ፡፡

በዘመናቸው በዕውቀት፣ በፊድል፣ በልግስና፣ በጀግንነት፣ በመልካም ስብዕና፣ በርህራሄ፣ በዒባዳ ብዛት፣ በሱጁድ ርዝመት፣ በትእግስትና በቻይነት የተነሳ **"አል ካዚም"** (ታጋሽና ቻይ) የሚል ስም እስከ መታወቅ የደረሱ፣ እንዲሁም እርቅ በማውረድና ፍትህን በማስፈን በነበራቸው ታላቅ ስብዕና እና ጽድቅ **"አል ዓብድ አስ-ሷሊህ"** በሚል ቅጽል ስም የታወቁ አቻ የሌላቸው ታላቅ ሰው ነበሩ፡፡

በተለያዩ የዕውቀት አውታሮች የዘመናቸውን ህዝብ ያስደመሙ የዕውቀት ውቅያኖስ ነበሩ፡፡ ከነዚህም የታዋቂው ነሷሪ (የክርስትና ሀይማት ተከታይ የነበረ) የቡሬሃ ክስተት (ሐዲስ) ተጠቃሽ ሲሆን፣ ኢማሙ በብዙ ጉዳዮች ላይ ገለጻ ሲያደርጉለት በእውቀታቸው ተደምሞ የሰለመ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡[226]

በልግስናቸው (ዐ) ደግሞ  በአንድ ወቅት አንድ ድሃ መጥቶ ድርሐም በጠየቃቸው ጊዜ ኢማሙ (ዐ) የሰውየውን የዕውቀት ደረጃ ለመፈተን አንድ ጥያቄ ጠየቁት መልሱን በትክክል በመመለሱ ሁለት ሺህ ዲርሃም ሰጥተውታል፡፡

ቁርአን በሚቀሩበት ወቅት በድንቅ ድምጻቸው ይታወቁ ነበር፡፡ በዒባዳና ቁርአን በመቅራት አቻ አልነበራቸውም፡፡ እንዲሁም በሱጅድ ርዝመት በለቅሶና እምባ ወደር የለሽ ነበሩ፡፡ የሞቱትም በሱጁድ ውስጥ እያሉ ነው፡፡

---

[226] ቢሐረል አንዋር 10/235፣ ክፍል 16 ሐዲስ 1፤ የሼኽ ሰዱቅ አል-ተውሂድ 270፤ በሷኢር አል-ደረጃት 136

## *ስምንተኛው ኢማም*

ስምንተመኛው ኢማም ዓሊ ቢን ሙሳ አል-ሪዷ (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ሰይዳ ነጅማ ናት፡፡ በዕለተ ጁምዓ፣ ዙልቃዕዳ ወር አስራ አንደኛው ቀን፣ መቶ አርባ ስምንት ዓመተ-ሂጅራ በመዲና አል-ሙነወራ ተወለዱ፡፡ በሰፈር ወር የመጨረሻው ቀን፣ ሁለት መቶ ሶስት ዓመተ-ሂጅራ በመርዝ ተመርዘው ሞቱ፡፡ በልጃቸው ኢማም አል-ጀዋድ አዘጋጅነት አሁን መርቀዳቸው በሚገኝበት ስፍራ በኹራሳን ተቀበሩ፡፡

ስለ ዒልማቸው፣ ፈዷላቸው፣ ልግስናቸው፣ መልካም ስብእናቸው፣ መተናነሳቸው፣ ዒባዳቸውና ድንቅ ቱርፋታቸው ዘርዝሮ መጨረስ የማይታሰብ ነው፡፡

አል-ሙእሙን የኢስላማዊ ኸሊፋነቱን ቦታ ተክተውት እንዲይዙ ጋብዟቸው ነበር፡፡ እሳቸው (ዐ) ግን በዱንያ ውስጥ ዛሂድ በመሆን ግብዣውን አልተቀበሉትም ነበር፡፡ በዚህ ውስጥ ዑዝር መኖሩን ስላወቁና አያታቸው አሚር አል-ሙእሚኒንም (ዐ) በሹራ የመጣላቸውን ኺላፋ ያለመቀበል ከወሰዱት ውሳኔ ጋር ተያይዞ ተመሳሳይ የደባና ውሸት ግብዣ መሆኑን ስለተረዱ ነበር ወድቅ ያደረጉት፡፡ ልክ ኢማም ዓሊ (ዐ) ኺለፋውን ለመያዝ የተቀመጠላቸው ቅድመ ሁኔታ በአላህ ኪታብ፣ በረሱል ሱና እና በሁለቱ ሸይኮች አካሄድ መሆን እንዳለበት ባስቀመጡ ጊዜ አሚር አል-ሙእሚኒን (ዐ) ግን በአላህ ኪታብና ከረሱል ሱና በኋላ በራሴ ኢጅቲሃድ እንደሚሄድ በወሰነ ጊዜ እንደነበረው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ግልጽ ነበር፡፡

ኢማም አል-ሪዷ (ዐ) የኺሊፋውን ቦታ ለመቀበል ያልፈቀዱ መሆኑን ሲያውቅ አል-ሙእሙን ዊላያት አል-ዐህድ (በጊዜያዊነት ምክትል ሆነው ቀጣይ ኸሊፋ

እጩነታቸውን) እንዲቀበሉ ጠየቃቸው፡፡ ይህንንም በማንኛውም የሐገር ጉዳይ ጣልቃ ላይገቡ ቅድመ ሁኔታ (ሸርጥ) ካስቀመጡ በኋላ ለመቀበል ተስማሙ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሙእሙን ኺላፋ ህጋዊ አለመሆኑን አጋለጡ፡፡

አል-ሙእሙን ባዘጋጃቸው የውይይትና ክርክር መድረኮች ላይ ኢማሙ (ዐ) ስለ ሓይማኖቶች፣ መዝሐቦች እና መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የነበራቸው የመጠቀ ዕውቀትና እልህ አስጨራሽ መልሶች ህዝቡን ያስደመመ ነበር፡፡
ስለ ዒባዳቸው ሲነሳ ደግሞ አብዛኛውን ሌሊቶች ያለ እንቅልፍ የሚያሳልፉ፣ ቁርአንን በየ 3 ቀኑ የሚያኸትሙ፣ አብዛኛውን ጊዜ በቀንና ሌሊት ውስጥ እስከ አንድ ሺህ ረከዓዎች የሚሰግዱ፣ አብዛኛው ሱጁዳቸው ለሰዓታት ያህል የረዘሙና መጾምን እጅግ የሚያበዙ ታላቅ የአላህ ባሪያ ነበሩ፡፡
ከመልካ አደባቸውና ድንቅ ስብዕናቸው አንድንም ሰው በምንም ነገር (ንግግር) አስቀይመው እንደማያውቁ ይነገራል፡፡ መጥፎ ንግግር ወጥቶአቸው የማያውቅ፣ በሚቀመጡበት ጊዜ ምንም ነገር ተደግፈው የማያውቁ፣ በሰው ፊት አስለውና ጉሮሯቸውን ለመጥረግ ድምጽ አውጥተው የማያውቁ በድንቅ ስብዕና የተካኑ ታላቅ ኢማም ነበሩ፡፡ ምግብ በቀረበላቸው ጊዜ ቤተሰባቸውና ኸዳሞቻቸው (አገልጋዮቻቸው) በሙሉ ቀርበው በአንድ ላይ ይበሉ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

## ዘጠነኛው ኢማም

ዘጠነኛው ኢማም ሙሐመድ ቢን ዓሊ አል-ጀዋድ (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ሰይዳ ሰቢካ ወይም ሱበይካ ትባላለች፡፡ በረጀብ ወር አስረኛው ቀን፣ በ መቶ ዘጠና አምስት ዓመተ-ሂጅራ፣ በመዲና አል-ሙነወራ ተወለዱ፡፡ በዙልቃዕዳ

ወር መጨረሻ ላይ፣ በሁለት መቶ ሃያ ዓመተ-ሂጅራ፣ በሃያ ዓመታቸው በመርዝ ተመርዘው በ ባግዳድ ውስጥ ሞቱ፡፡ በልጃቸው አል-ሃዲ አዘጋጅነት፣ ከአያታቸው ሙሳ ቢን ጀዕፈር (ዐ) ጎን በ አል-ከዚሚያ- ኢራቅ ውስጥ አሁን ቀበራቸው ባለበት ቦታ ተቀበሩ፡፡

በመዘመናቸው ካሉት ሰዎች በሙሉ በዕውቀት የበለጸጉ ወደር የለሽ ብልጫ ያላቸው፣ እጅግ ለጋስ የሆኑ፣ መጅሊሳቸው እጅግ ያማረ፣ ስብዕናቸው የመጠቀና አንደበተ-ርቱእ ነበሩ፡፡ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ (በፈረስ ሲጓዙ) ሁሌ ወርቅና ብር ይዘው ይጓዙ እንደነበርና ለጠየቋቸው ሁሉ ሳይሰጡ እንደማያልፉ ይታወቃል፡፡ ከአጎቶቻቸው ለጠየቃቸው (ለለመናቸው) ሰው ከሀምሳ ዲናር በታች ሰጥተው አያውቁም፡፡ ከአክስቶቻቸው ለጠየቋቸው ደግሞ ከሃያ አምስት ዲናር በታች ሰጥተው አያውቁም፡፡

ስለ ዒልማቸው (ዕውቀታቸው) ሲነሳ ደግሞ በአንድ ወቅት ከተለያዩ ቦታዎች የተውጣጡ ሰማንያ የሚሆኑ ታዋቂ ምሁራን ከሐጅ መልስ የተለያዩ ጥያቄዎችን በጠየቋቸው ጊዜ ለሁላቸውም በቂ ምላሽ በመስጠት ህዝቡን ማስደነቃቸው ይነገራል፡፡ ስለ እሳቸው ከሚወሱ አስደናቂ ክስተቶች መካከል በአንድ ወቅት ከፖለቲከኞችና ታዋቂ ምሁራን የተውጣጡ እጅግ በርካታ ሰዎች ተሰብስበው በአንድ መጅሊስ ላይ ብቻ እስከ ሰላሳ ሺህ የሚደርሱ ጥያቄዎችን ጠይቀዋቸው ያለምንም መሳሳትና መቀላቀል ለሁሉም አጥጋቢ ምላሽ እንደሰጡ ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት እድሜያቸው ዘጠኝ ዓመት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ አይነት ክስተት የወህይና ተንዚል ባለቤት ለሆኑ አህለልበይቶች ብዙም የሚያስገርም አይደለም፡፡ (ይህ ጥያቄና መልስ መጅሊስ በዘመናችን ኮንፈረንስ ተብሎ እንደሚጠራው ዓይነት የተወሰኑ ቀናት የወሰደ ነበር ተብሎም ይታመናል፡፡ ሙእሙን አል-ዓባሲ እጅግ ወሳኝ በሆኑ ጥያቄዎች

ከፈተናቸው በኋላ  ለጥያቄዎቹ አጥጋቢ ምላሽ በመስጠታቸው አንዷን ልጁን ዳሯቸው፡፡

### *አስረኛው ኢማም*

አስረኛው ኢማም ዓሊ ቢን መሐመድ አል-ሐዲ (ዐ) ናቸው:: እናታቸው ሰይዳ ሰማነህ ትባላለች:: በዙልሒጃህ ወር 15ኛው ቀን ወይም በረጀብ ወር 2ኛው ቀን፣ በ212 ዓመተ-ሂጅራ በመዲና አል-ሙነወራ ተወለዱ፡፡ በዕለተ ሰኞ ረጀብ ወር ሶስተኛው ቀን፣ ሁለት መቶ ሃምሳ አራ ዓመተ ሂጅራ በአርባ ሁለት ዓመታቸው በመርዝ ተመርዘው በሳመራእ ሞቱ፡፡ በልጃቸው አል-ዓስከሪ (ዐ) አዘጋጅነት አሁን ማረፊያቸው በሚገኝበት ቦታ በኢራቅ- ሳመራእ ተቀበሩ፡፡

በዘመናቸው ከነበሩ ሰዎች ሁሉ በፈድል፣ በዒልም፣ በበጎ ስነምግባርና በልግስና የመጠቀ ባህሪ የተላበሱ ታላቅ ሰው ናቸው፡፡ አንደበታቸው ለስላሳ፣ ለልግስና እጃቸው ሰፊ፣ ዒባዳቸው የበረከተና መላውን መልካም ጸባይ የተጎናጸፉ ድንቅ ሰው ነበሩ፡፡

ከልግስናቸው ለመጥቀስ ያህል አል-አርቢሊ ባወሩት ሐዲስ በአንድ ወቅት አንድ ኸሊፋ ሰላሳ ሺህ ድርሃም በላከላቸው ጊዜ ሁሉንም ለአንድ ገጠሬ ከሰጡት በኋላ “እዳህን ከፍለህ የቀረህን ለቤተሰቦችና ዘመዶችህ አድርግ፡፡ በተረፈ ይቅርታ አድርግልን አሉት፡፡”

ገጠሬውም፡- “የአላህ መልእክተኛ ልጅ ሆይ! በአላህ እምላለሁ እኔ ምኞቴ የነበረው አሁን ከሰጡን አንድ ሶስተኛው ያነሰ ነበር፤ አላህ (ሱ.ወ) ግን

መልእክቱን የት ማድረግ እንዳለበት ያውቃል" ካላቸው በኋላ ገንዘቡን ይዞ እንደተመለሰ መዘገቡን እናያለን፡፡[227]

## *አስራ አንደኛው ኢማም*

አስራ አንደኛው ኢማም ሀሰን ቢን ዓሊ አል-ዓስከሪ (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ሰይዳ ጀዳህ ትባላለች፡፡ በዕለተ ሰኞ ረቢዕ አል-አኺር ወር በ አስረኛው ቀን፣ በሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ዓመት-ሂጅራ ተወለዱ፡፡ በእለተ ጁምዓ ረቢዕ አል-አወል ወር ስምንተኛው ቀን፣ ሁለት መቶ ሰላሳ ዓመት-ሂጅራ በሃያ ስምንት ዓመታቸው በመርዝ ተመርዘው ሞቱ፡፡ በልጃቸው በኢማም አል-ሑጃህ አዘጋጅነት አባታቸው ጎን አሁን ማረፊያቸው ባለበት ቦታ በሳመራእ ተቀበሩ፡፡

የመጠቀ ዓልማቸው፣ ፈድላቸው፣ ክብራቸው፣ ዒባዳቸው፣ መተናነሳቸውና ሌሎች መልካም ስብዕናቸው ከማንም የተደበቀ አይደለም፡፡

ኢማ አል-ዓስከሪ (ዐ) ያማረ ቁመና፣ ውብ ፊት፣ የተስተካካለ ሰውነት ያላቸውና ገና እድሜያቸው ትንሽ እያለ የተለየ ስጦታና የከበረ ስብዕና የተቸሩ በስነ-ምግባራቸው ከነብዩ (ሶ) ጋር የተመሳሰሉ ነበሩ፡፡

ልግስናቸውን በተመለከተ ከተወሩት ሐዲሶች መካከል ኢስማኢል ባወሩት መሰረት "በአንድ ወቅት አቢ መሐመድን (ዐ) መንገድ ላይ ሆኜ ጠበቃቸውና አጠገቤ ሲደርሱ ምንም ገንዘብ እንደሌለኝ- አንድ ዲርሀም እንኳ እንደሌለኝና

---

[227]ከሽፍ አል-ጉማ- አል-አርቢሊ 2/375

ምሳም ሆነ እራት እንደሌለኝ በአላህ ምዬ ነገርኳቸውና ችግሬን እንዲቀርፉልኝ ተማጸንኳቸው፡፡"

ታዲያ በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉ፡-"ሁለት መቶ ዲናር ቀብረህ (ደብቀህ) በአላህ ትምላለህ? ይህን ማለቴ ግን ላልሰጥህ ፈልጌ አይደለም" ካሉኝ በኃላ "አንተ ልጅ! የያዝከውን ስጠው" አሉ፡፡ ልጁም መቶ ዲናር ሰጠኝ፡፡[228]

እንዲሁም በአንድ ወቅት አንድ ሰው የኢማሙን ልግስናና ይቅር ባይነት ባህሪ በሰማ ግዜ እርዳታ ሊያገኝ ፈለገ፡፡ ሰውየው የሚፈልገው አምስት መቶ ዲርሀም ነበር፡፡ እሳቸውም (ዐ) አምስት መቶ ዲርሀሙን ከሰጡት በኋላ ሶስት መቶ ዲርሀም ጨምረው ሰጡት፡፡ አንዲት ነሷሪ (ክርስትያን) ኢማሙ (ዐ) በፈዲላቸው፣ በዒልማቸውና በተዓምረኝነታቸው እንደ መሲሁ (እየሱስ) እንደሆኑ መመስከሯ ተዘግቧል፡፡[229]

ኢማ አል-ዓስከሪ(ዐ) ዒባዳቸው የበረከተ፣ ተሀጁድ የሚያዘወትሩ፣ እርቅና ሰላም በማውረድ የተካኑና ግርማ ሞገስ የተላበሱ ታላቅ ኢማም ነበሩ፡፡

## *አሥራ ሁለተኛው ዒማም*

አሥራ ሁለተኛውና  የመጨረሻው ኢማም አል-ሑጀት አል-መህዲ ሙሀመድ ቢን ሐሰን (ዐ) ናቸው፡፡ እናታቸው ሰይዳ ነርጅስ ናት፡፡ በሻዕባን ወር አጋማሽ ላይ በሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ዓመተ-ሂጅራ በሳመራእ ተወለዱ፡፡

---

[228] አል-አርሻድ 2/332

[229] ቢሓር አል-አንዋር- *"ታሪኽ ኢማም ሐሰን አል-ዓሰከሪ"*

ኢማም መህዲ (0) በምድር ላይ የመጨረሻ የአላህ (ሱ.ወ) ሁጃ (ማስረጃ)፣ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ኸሊፋዎች መደምደሚያና ከአሥራ ሁለቱ የሙስሊሞች ኢማም (መሪዎች) የመጨረሻው ኢማም የመጨረሻው ኢማም ናቸው፡፡ አላህ(ሰ.ወ) በመሺአውና በችሮታው በዱኒያ ላይ እድሜያቸውን አርዝሞ ህያው ሆነው እንዲኖሩ ያደረጋቸው የዘመኑ የሙስሊሙ ኡማ ኢማም ናቸው፡፡ ከእይታ የራቁ (ጋዒብ የሆኑ) ኢማም ሲሆኑ ምድር በበደልና ጭቆና ከተሞላች በኋላ በፍትህና እኩልነት ለመሙላት በመጨረሻው ዘመን የሚገለጡ የመላው ዓለም መሪ ናቸው፡፡ መላውን ዓለም የሚገዛና ምድራችንን በፍትህ የሚሞላ፣ አምባገነኖችንና ጨቋኞችን የሚያጠፋና ምድር የነጻነት፣ የሰላምና የብልጽግና ቤት የምትሆንበትን ዘመን የሚያበስር የዓለም ተስፋ ነው፡፡

አላህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ እንደገለጸው:-

***هُوَ الَّذِي أَرْسَلَ رَسُولَهُ بِالْهُدَىٰ وَدِينِ الْحَقِّ لِيُظْهِرَهُ عَلَى الدِّينِ كُلِّهِ***

**"ሙሽሪኮች ቢጠሉ እንኳ በሁሉም ኃይማኖት ላይ የበላይ ሊያደርገው"[230]**

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከነብዩ (ሶ) እና ከንጹሀን ኢማሞች (0) የተያዙ የሆኑ ሐዲሶች በሺዓና ሱኒ ዑለማዎች የተዘገቡ በርካታ ማስረጃዎችን ለመጥቀስ የሚቻል ሲሆን ራሱን በቻለ መጽሀፍ ውስጥ በዝርዝር የቀረበውን የሰይድ አል-ሰድር ***"አል-መህዲ"*** የተሰኘ ኪታብ ማየቱ ይመከራል፡፡

[230] አል ተውባ: 33

በተጨማሪም የሰይድ ሷዲቅ አል-ሺራዚን ***"አል-መህዲ ፊ አል-ሱና"*** የተሰኘ መጽሐፍ ማየት ይቻላል፡፡

ከአህለ ሱና ዑለማዎችና ሙሐዲሶች ለእማኝ ያህል ለመጥቀስ ፡-

*-ሱነን አል ቲርሚዝ 4/505- ባቡ ማጃእ ፊል መህዲ- እ.አህያእ ቱራስ ዓረቢ::*

*-ሱነን አቢ-ዳውድ 4/106- ኪታብ አል-መህዲ- እ.ዳር አል-ፊክር፡፡*

*-ሱነን ኢብን ማጃህ 2/1366- ባብ ኹሩጅ አል-መህዲ -እ.ዳር አል-ፊክር፡፡*

*-ሙሰነድ አህመድ 3/21፣ 26፣ 37፣ 5/277- እ.ሙአሰሰት ቁርጥባ- ግብጽ፡፡*

*-ሙሰነድ አቢ-ያዕላ 1/359- ዳረል ሙእሚን ሊልቱራስ- ደማስቆ፡፡*

*-ሰሂህ ኢብን ሂባን 15/236- ባብ ዚክር አል-ቢያን ቢአነ ኹሩጅ አል-መህዲ የኩኑ በዕደ ዞሁር አል-ዙልም ወል-ጆውር ፊ አል-ዱኒያ- እ.ሙአሰሰት አል-ሪሳላ- ቤይሩት፡፡*

*-አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 4/600- እ.ዳር አል-ኩትብ አል-ዒልሚያ፡፡*

*-መዋሪድ አል-ዘመአን 463- እ.ዳር አል-ኩትብ አል-ዒልሚያ፡፡*

*-መጅምዕ አል-ዘዋኢድ 7/313- ባብ ማ ጃአ ፊ አል-መህዲ- እ.ዳር አል- ረያን ሊልቱራስ-ካይሮ፡፡*

*-አል-መዕጀም አል-አውሰጥ 8/178 -ዳር አል ሐረመይን- ካይሮ፡፡*

*ፊይድ አልቀዲር 5/262- እ.ግብጽ፡፡*

*-አል-ሙዕጀም አል-ከቢር 18/51- እ.መክተበት አል-ዑሉም ወል ሒከም- ሞሱል፡፡*

*-ተፍሲር አል-ቁርጡቢ 8/122፣ 10/222- እ.ዳር አል- ሸዕብ- ካይሮ፡፡*

*ተፍሲር አል- ጠበሪ 1/501- ዳር አል-ፊክር*

*ተፍሲር ኢብን ከሲር 1/158 -እ.ዳር አል-ፊክር*

*ኡስድ አል-ጋባ 2/259::*

*የአቡ ኑዔይም ሂልያት አል- አውሊያእ 3/177 እና ሌሎች በርካታ ምንጮች።*

የአንድ ሰው ዕድሜ ይህን ያህል መርዘምና በህይወት መቆየት እንግዳ ሊሆን አይችልም፡፡ የአላህ (ሰ.ወ) ቁድራ (ችሎታ) ሁሉንም ነገር ያካተተ ነውና፡፡

وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

**"እሱ (አላህ) በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡"[231]**

ነብዩ ኑህ (ዐ) በቁርአን ነስ መሰረት ለ አንድ ሺህ ዓመት ሃምሳ ዓመት ብቻ ሲቀር (950) ዓመት አልኖረምን?

فَلَبِثَ فِيهِمْ أَلْفَ سَنَةٍ إِلَّا خَمْسِينَ عَامًا

**"ለአንድ ሺህ ዓመት ሃምሳ ዓመት ሲቀር በነሱ ውስጥ ኖረ፡፡"[232]**

በተጨማሪም አንድ ሰው ወይም ፍጥረት ዕድሜው መርዘም እንደሚችልና ለበርካታ ሺህ ዓመታት በህይወት መቆየት እንደሚችል የሐዲስ ዕውቀት ይህንኑ ሐቂቃ (እውነታ) ያረጋግጣል፡፡

በዚሁ መልኩ ይህ ታላቅ ኢማም ከአላህ በሆነ አምር ባለበት ሆኖ ከእይታ ተሰወረ ሙስሊሞቹም ከኢማሙ(ዐ) ጋር ተያይዞ ሳምራእ ወይም ሰርደብ አል ገይብ ተብሎ የሚታወቀውን ስፍራ የሚዘየርና የዒባዳ ቦታ አድርገው ያዙ፡፡

አላህ ሆይ!የመገለጫውን ግዜ አፋጥንልን !መወጣቱንም ቀላል አድርግለት፣ እኛንም ከረዳቱና ተከታዩ አድርገን!፡፡

---

[231] አል-ማኢዳ፡- 120፤ ሁድ፡- 4፤ አል-ሩም፡- 50፤ አል-ሀዲድ፡- 2፤ አል-ተጋቡን፡- 1፤ አል-ሙልክ፡- 1

[232] አል-ዓንከቡት፡ 14

## *የሺዓ ኢማሞችን አስመልክቶ የተሰጡ የምስክር ቃሎች (እዕትራፉት)*

እዚህ ላይ የአህለልበይትን ወይም የንጹሃን ኢማሞችን ማንነትና ደረጃ አስመልክቶ ታላላቅ ዑለማዎችና ታዋቂ ሰዎች ብሎም አንዳንድ ጠላቶች እንኳ ሳይቀሩ የሰጡትን የምስክርነት ቃል በጨረፍታ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ በዚህ መልኩ የቁርአን አናቅጽና ሐዲሶች ባሸገር ንጹሀን ኢማሞቹ በሙስሊሞች አዕምሮና አስተሳሰብ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ለመጠቆምና እነሱን የሙጥኝ ብሎ የያዘና ፋናቸውን የተከተለ፣ ቃላቸውን ያከበረና ተግባራቸውን የተቀበለ በዱኒያም ሆነ በአኺራ ነጃ ከሚወጡትና ደስታ የሚጎናጸፉ መሆናቸው ግልጽ ይሆን ዘንድ ለማሳወቅ ነው፡፡

### 1. ኢማም አሚር አል-ሙእሚኒን ዓሊ ቢን አቢ-ጧሊብ (ዐ)

-አቡ በክር ስለ አሚር አል-ሙእሚኒን እንዲህ ብለዋል፡-

***"ኢብን አቢ ጧሊብ ሆይ! እነሆ የሁሉም ሙእሚኖችና ሙእሚናት መውላ (መሪና አለቃ) ለመሆን በቃህ፡፡"***

*"ፉቱሃት አል-ኢስላሚያ"* የተሰኘውን ኪታብ ለዝርዝሩ ይመልከቱ፡፡

-ፈቱሃት አል-ኢስላሚያ 2/306- የአህመድ ዘይኒ ደህላን አል-መኪ አል-ሻፊኢ- በ1304 የሞቱ- ገዲር ከተሰኘው ምንጭ በመጥቀስ- (ገዲር 1/282፣ 283)፡፡

-አል መናዊ "ፈይድ አል-ቀድር" በተሰኘው ኪታባቸው ላይ ስለ ሐዲስ አል-ገዲር በ 6/218 እ.ግብጽ- ኢብን ሐጀር በሰጡት ጥቆማ መሰረት ሐዲሱ በርካታ መንገዶች እንዳሉትና ከነዚህ ውስጥ በአብዛኛው የሰሂህ ደረጃና የሀሰን

ደረጃ ያለው ዘገባዎች መበርከታቸውን የገለጹበት፤ የሐዲሱ መቼትም በ ገዲር ኩም መሆኑ ጭምር መገለጹን ያነባሉ፡፡

በአል-በዛር ሪዋያ ውስጥ ደግሞ፡-

**"አላሁመ ዋሊ መን ዋለሁ፣ ወዓዲ መን ዓዳሁ ፣ ወ አህብ መን አህበሁ፣ወ አብግድ መን አብገደሁ፣ ወንሱር መን ነስረሁ፣ ወኸዙል መን ኸዘለሁ"**

***(እሱን ለተከተለና ለተወዳጀ አንተም ወዳጅ ሁነው፣ እሱን ጠላት ያደረገን አንተም ጠላቱ ሁነው፣ እሱን የወደደን አንተም ውደደው፣ እሱን ያስቆጣ የአንተም ቁጣ በሱ ላይ ይሁን፣ እሱን የረዳን አንተም ረዳቱ ሁነው፣ እሱን የከዳን አንተም ከዳው"*** የሚል ጭማሪ መኖሩን ተጠቅሷል፡፡

አቡ በክርና ዑመር ይህን በሰሙ ግዜ ፡-

***"የአቡ ጧሊብ ልጅ ሆይ! ይኸው የመላው ሙእሚኖችና ምእምናት መሪና አለቃ (መውላ) ለመሆን በቃህ"*** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡

ዑመር ቢን አል-ኸጣብ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡-

***"ከ አቢ ጧሊብ ልጅ በኋላስ አላህም አያቆየኝ/ አያኑረኝ፡፡"***[233]

በተጨማሪም ዑመር ስለ ዓሊ ከተናገሩት፡-

***"እሱ የኔ መውላ (መሪና አለቃ) ነው፡፡"***

*(ፋይድ አል- ቀዲር አል-መናዊ 6/218 ሊ. ግብጽ)*

---

[233] ሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ (ከ581-645 ሂጅራ የኖረ)- "ተዝከረት አል-ኸዋስ"- ፈስል፡- ፊ ቀውል ዑመር ቢን አል-ኸጧብ- ገጽ 137-138፡፡

እንዲሁም:-*"በኽን በኽን ለከ ያ ኢብን አቢ ጧሊብ አስበህተ መውላየ ወ መውላ ኩሉ ሙስሊም፡፡ "*

***"ጎሽ! ጎሽ! እሰይ! እሰይ! የአቢ ጧሊብ ልጅ ሆይ! የኔ መውላ እና የሁሉም ሙስሊሞች መውላ ለመሆን በቃህ! እንኳን ደስ አለህ፡፡"***

በአቡ ሁሬይራ በተወራ ሐዲስ፡-

*"ከ ዙል ሒጃ ወር አሥራ ስምንተኛውን ቀን የጾመ ሰው ስልሳ ወራትን እንደጾመ ይጻፍለታል፡፡ ይህ ቀንም የገዲር ኹም ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን ነበር ነብዩ (ሰ) የዓሊን (ዐ) እጅ ይዘው ከፍ በማድረግ ፡-*

*"እኔ የሙእሚኖች ዋሊ (መሪና አለቃ) አይደለሁምን ?"ብለው* ሲጠይቁ ታዳሚዎቹም፡-*"አዎን! እንደዛ ነው የአላህ መልእክተኛ ሆይ!"* ብለው ከመሰከሩ በኋላ ነብዩ (ሶ)፡-

*"እኔ መውላ የሆንኩለት ሁሉ ይህ ዓሊ መውላው ነው"* ብለው ነገሯቸው፡፡

በዚህ ጊዜ ዑመር ቢን ኸጧብ፡-*"በኽን በኽን ለከ ያ ኢብን አቢ ጧሊብ፣ አስበህተ መውላየ ወ መውላ ኩሉ ሙስሊም"*

አላህ (ሰ.ወ) በዚህ ጊዜ ነው *"አል-የውም አክመልቱ ለኩም ዲነኩም"* የሚለውን የቁርአን አያህ አወረደ፡፡

**الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ**

**"እነሆ በዛሬው ዕለት ዲናችሁን ሞላሁላችሁ፡፡"[234]**

---

[234] አል-ማኢዳ፡ 3

በሌላ ሪዋያ ደግሞ፡-

*"ሐኒአን ለከ -እንኳን ደስ አለህ! ምንኛ የታደልክ ነሁ እነሆ የኔም ሆነ የመላው ሙእሚኖችና ሙእሚናት መሪና አለቃ ሆነህ አረፍከው ፡፡"[235]*

ዑስማን ቢን ዓፋን ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"ዓሊ ባይኖር ኖሮ ዑስማን በጠፋ ነበር፡፡"[236]***

ዓኢሻ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"የአላህ መልእከተኛ(ሰ) ዘንድ እንደሱ ተወዳጅ የሆነ ሰው አይቼ አላውቅም፡፡"[237]***

ዓብደላህ ቢን ዑመር ለ አንድ ዓሊን እጠላዋለሁ ላለው ሰው እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡-

***"አላህ ይጥላህ! በህወቱ ካሳለፋቸው ነገሮች በሙሉ አንዱ እንኳ ከዱኒያና በውስጧ ከያዘችው ነገር በሙሉ የበለጠና የተሻለ የሆነን ሰው ትጠላለህን?"[238]***

---

[235]ታሪኽ ባግዳድ- 8/279፣ ሐዲስ 4392፣ እ.ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ- ቤይሩት፡፡ ታሪኽ ዲመሽቅ 2/50-ሐዲስ 548፣549 እና 550)፤ የ አል-ኸዋሪዝሚ አል-ሐነፊ- አል-መናቂብ ገጽ 94፤ ሙስነድ አህመድ 4/281 እ.አል-መይመና፤ -------------

-----የኢብን አስ-ሲባግ አል-ማሊኪ---- አል-ፋሱል አል-ሙሂማ ገጽ 24፤ የአል-ሱዩጢ አል-ሐቂ ሊልፈታዋ 1/122፤ ተፍሲር ፊኽር አል-ራዚ 3/63 እ.ዳር አል-ዒሚራ- ግብጽ፡፡

[236] የ አህመድ ቢን መሐመድ አል-ዓሲሚ (378 ሂጅራ)- ዘይነል ፈታ ፊ ሸርህ ሱራህ ሐል አታ -1/318- ሐዲስ 224

[237]አል-ዐቅድ አል-ፈሪድ ዐብድረበህ አል-አንደሉሲ) (328 ሂጅራ) 3/313- *አኽባር አል-ኹለፋእ* የሚለው ክፍል ስር፡፡

[238] አል-መናቂብ 2/3

ሙዓውያ ማንኛውም አስቸጋሪ ጉዳይ ባጋጠመው ጊዜ ጉዳዩን ለዓሊ ደብዳቤ በመጻፍ ይጠይቅ ነበር፡፡ የዓሊን መገደል ዜና በሰማ ጊዜ፡-***"ፊቅህና ዒልም ከዓሊ ሞት ጋር ሄደ/ጠፋ"*** ማለቱ ተዘግቧል፡፡[239]

ሐሰን አል-በስሪ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"በአላህ እምላሁ! እሱ (ዓሊ) ማለት አላህ በጠላቱ ላይ የሚወረውረው አይምሬ ቀስት ነበር፡፡ የዚህ ኡማ አሳዳጊና አናጺ ነበር፡፡"***[240]

## *2. ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ (ዐ)*

አነስ ከተናገሩት፡- ***"ከነሱ ውስጥ እንደ ሐሰን ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ) ጋር የሚመሳሰል የለም፡፡"***[241]

አቡ ሁሬይራ ከተናገረው ደግሞ፡-

***"የአላህ መልእክተኛ (ሰ) ለዚህ ሰው (ማለትም ለ ሐሰን) የሚሆኑትንና የሚያደርጉትን ካየሁ በኋላ እሱን (ሐሰንን) ከመውደድ ወደ ኋላ ብዬ አላውቅም፡፡"***[242]

---

[239] አል-ኢስቲዕያብ /45

[240] አል-አስቲዕያብ/47

[241] አል-ኢሷባ/ 328- ፊደል ተራ "ሀ"- አንቀጽ ቁጥር- 1819

[242] የ ሸብለንጂ (1367 ሂጅራ) -ኑር አል-አብሷር- 131 ኢ.ግብጽ

ዓብደላህ ቢን ዙቤይር ከተናገረው፡-

*"እኔ የምነግራችሁ ከቤተሰባቸው ውስጥ ከሳቸው (ሰ) ጋር የሚመሳልና የበለጠ ተወዳጅ የሆነውን ስለ ሐሰን ቢን ዓሊ ነው፡፡"*[243]

ኢብን ሲሪን ከተናገረው ደግሞ፡- *"ሐሰን ቢን ዓሊ ማለት አንዱን ሰው በመቶ ሺህ የመነዳ ነው ማለት ይቻላል፡፡"*[244]

ዋሲል ቢን ዓጧእ ከተናገረው ደግሞ፡-

*"ሐሰን ቢን ዓሊ የነቢያት መገለጫ እና የነገስታት ግርማ ሞገስ የተላበሰ ሰው ነበር፡፡"*[245]

አቡል ፊዳእ ከተናገሩት፡-

*"ቢያውቁ ኖሩ ለነብዩ (ሰ) የልጅ ልጅ፣ የሙስሊሞች አውራ፣ ከሶሃባ ዑለማዎች ቀዳሚ የሆነ፣ ከሁላቸውም በላይ ቻይና ትግስተኛ ለሆነውና ለ ድንቅ አማካሪያቸው ሙባያዓ በማድረጋቸው አላህ (ሰ.ወ) የዋለላቸው ጸጋ ወደር የለሽ እንደሆነ ተረድተው ጉዳዩን አግዝፈው ባዩ ነበር፡፡"*[246]

### *3. ኢማም ሁሴን ቢን ዓሊ (ዐ)*

ዑመር ቢን አል-ኸጧብ ለ ኢማም ሁሴን ከተናገረው፡-

---

[243] አል-ኢሷባ - ኢብን ሐጀር 2/11- ክፍል 1

[244] ኪታብ ሐሰን ቢን ዓሊ

[245] አል-መናቂብ 4/9

[246] *አል-ቡዲያ ወ አል-ኒሐያ*-የአበል ፊዳእ ኢብን ከሲር አል-ዲመሽቂ (701-774 ሂጅራ) ቅጽ 8/ 14 -የ40ኛው ሂጅራ ክስተቶችና የሐሰን ቢን ዓሊ ኺላፋነት

***"በራሳችን ላይ የምታየውን ነገር ያበቀለው አላህና ከዛ በኋላ ደግሞ እናንተ ናችሁ።"*** *(አል-ኢሷባ የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ)*[247]

አቡ ሑሬይራ ከተናገረው፡-

***"በ አንድ ወቅት ሁሴን ቢን ዓሊ ጥምጣማቸውን ጠምጥመው (ተሸፋፍነው) ሲገቡ ሳይ ሌላ ነብይ የተላከ መስሎ ተሰማኝ።***[248]

ዓብደላህ ቢን ዓምር ቢን ዓስ ከተናገረው ደግሞ፡-

በአንድ ወቅት ኢማም ሁሴን (ዐ) በአጠገቡ ሲያልፉ፡-***"በምድር ሰዎች ዘንድ እና በሰማይ ባሉ ፍጥረታት ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነን ሰው ማየት የፈለገ ሰው ይህንን ወደር የለሽ ሰው ይመልከት።"***[249]

ሙዓውያህ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡-

***"ሁሴንን በነውር (ዐይብ) ማንሳት አስቤም አላውቅም። በአላህ እምላለሁ ነውር የሆነ ነገር በሱ ውስጥ ኖሮት ታይቶኝ አያውቅም።"***[250]

---

[247] *ታሪኽ በግዳድ* -ኸጢብ አል-አል-በግዳዲ 1/141

[248] ቢሓር አል-አንዋር 43/293- ክፍል 12 -ሐዲስ 54

[249] ቢሓር አል-አንዋር- 43/297- ክፍል 12- ሐዲስ 59

[250] አዕያን አል-ሺዓ 1/583

ኢብን ሲሪን ከተናገረው ደግሞ፡-

***"ከያህያ ቢን ዘከሪያ በኋላ በኢማም ሁሴን (ዐ) ላይ እንጂ ሰማይ በማንም ላይ አላለለቀም፡፡ ሁሴን (ዐ) በተገደለ ጊዜ ሰማይ ጠቆረ፤ ከዋክብት በቀን ታዩ፣ አፈር እየቀለጠ ፈሰሰ፡፡"[251]***

የዚድ ቢን መስዑድ ከተናገረው፡-

***"ከእረኞች (ከጠባቂዎች) ሁሉ የላቀ ድንቅ ጠባቂ፣ በሰዎች ላይ ማስረጃ (ሑጃ) ስለመሆኑ ለአላህ (ሱ.ወ) የዋጀበለት፤ የህዝብ ኢማምና የግሳጼው አውራ ከሁሴን (ዐ) ወዲያ ይብቃህ፡፡"[252]***

***4. ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን ዘይን አል- ዓቢዲን (ዐ)***

-አብ ሓዚም እንዲህ ብለዋል፡- ***"ከዓሊ ቢን ሁሴን የበለጠና በዕውቀት የመጠቀ ሐሺማዊ አይቼ አላውቅም፡፡"[253]***

አል-ዙህሪ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"እንደ ዘይን አል-ዓቢዲን በዕውቀት የመጠቀ ሰው አይቼ አላውቅም፡፡"***

*ዓሊ ቢን ሁሴንን ባስታወሱ ጊዜ "ወይ ዘይን አል-ዓቢድን" እያሉ ያለቅሱ ነበር፡፡[254]*

---

[251] ታሪኽ ኢብን ዓሳኪር የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ፡፡

[252] አዕያን አል-ሺዓ 1/59

[253]ተዝኪረት አል-ኸዋስ /299 - እ.1401 ሂጅራ

[254]ተዝኪረት አል-ኸዋስ/297፤ አቡ ኑዔይምም እንዲሁ አል-ዙህሪን ዋቢ በማድረግ መዘገቡንና አቡ-ሐዚምም እንዲሁ ማለታቸውን ጭምር በዚሁ ምንጭ እናገኛለን፡፡

የማሊኪዎች ኢማም- ኢማም ማሊክ ከተናገሩት፡-

***"ዘይን አል-ቢዲን የተባሉበት ምክንያት ከዒባዳቸው ብዛት የተነሳ ነው፡፡"***[255]

በአንድ ወቅት ዓሊ ቢን ሁሴን (ዐ) ከዑመር ቢን ዓብደልዓዚዝ አጠገብ ተነስተው በሄዱ ጊዜ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"ከሰዎች ሁሉ በላጩ ማን ነው?"***ብሎ ሰዎቹን ሲጠይቅ፡-

***"እናንተ ናችሁ"*** ብለው መለሱለት፡፡

እሱም፡- ***"በጭራሽ! በላጩ (ዐሽረፍ) ሰውማ ቀደም ሲል ከዚህ ተነስቶ የሄደው ሰው ነው"*** አላቸው፡፡[256]

ናፊዕ ለኢማም አል-ሰጃድ (ዐ) እንዲህ ማለቱ ተዘግቧል፡፡

***"አንተ የሰው ሁሉ አውራና በላጫቸው ነህ፡፡"***[257]

### *5. ኢማም ሙሀመድ አል-ባቂር (ዐ)*

ኢብን ዑመር ወደ ኢማሙ (ዐ) እያመለከቱ ከተናገሩት፡-

***"እነሱማ ዕውቀት የተቸሩና የሚገለጥላቸው አህለልበይት ናቸው፡፡"***[258]

---

[255] ኑር አል-አብሷር -ሸብለንጂ/153

[256] *አል-አዕያን* የተሰኛውን ኪታብ ይመልከቱ፡፡

[257] ከሽፍ አል-ጉማ/ 78

[258] አል-መናቂብ 4/197

ጃዕፈር አል-ጁዕፊ ከኢማሙ (ዐ) የሰማውን ሲተርክ፦

*"የአውሊያዎች ወልይና የነብያት ዒልም ወራሽ የሆኑት ሙሐመድ ቢን ዓሊ ቢን ሁሴን በነገሩኝ መሰረት... ፡፡"* [259]

ኢብን አቢልሐዲድ ከተናገሩት ደግሞ፦

***"ሙሐመድ ቢን ዓሊ ቢን ሁሴን በሂጃዝ የፉቀሃዎች ዓይነታ ነበሩ፤ ከሳቸውና ከልጃቸው ጃዕፈር ነበር ሰዎች ፊቅህን የተማሩት፡፡"*** [260]

### *6. ኢማም ጃዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ)*

ፉአድ ሰምዓን ከተናገረው፦

***"ኢማም ጃዕፈር  አል-ሷዲቅ ማለት ለ እንደ ማሊክ ቢን አነስ፣ አህመድ ቢን ሐንበል፣ አቡ ሐኒፋ፣ ሻፊዒና ሌሎች የተቀሩት መዝሀቦች መስራቾች መምህር የነበሩ ናቸው፡፡"*** [261]

አቡ ሐነፊ ስለ ኢማ አል ሷዲቅ (ዐ) ከተናገሩት ደግሞ፦

***"እንደ ጃፈር ቢን መሐመድ በዕውቀት የመጠቀ አይቼ አላውቅም፡፡"*** [262]

*(ኑር አል-አብሷርን ይመልከቱ)*

---

[259] ከሽፍ አል-ጉማ 2/125

[260] *አል-መድኸል ኢላ-መውሱዓት አል-ዐተባት* የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም ተዝኪረት አል-ኸዋስ/ 138

[261] *አሸዐህ ሚን ሐያት ኢማም አል-ሷዲቅ* የተሰኘውን መጽሀፍ ይመልከቱ፡፡

[262] ተዘኪረት አል ሁፋዝ አል-ዘሐቢ፤ *መጃሊስ አስ-ሱኒያ* 5/463

ሙሐመድ አቡ ዘህራ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"በሳቸው ዘመን የኖሩ የሱኒ ኢማሞች ከሳቸው ትምህርት ይቀስሙ ነበር፡፡ ሐዲስም ከሳቸው ይወስዱ ነበር፡፡"[263]***

ኢብን ሐጀር ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"በመጓጓዣያዎች እየተጓጓዘ ሐገራትን ማዳረስ የቻለ ዕውቀት ብዙ ሰዎች ከሳቸው (ዐ) ዘግበዋል፡፡"[264]***

ዶ/ር አህመድ አሚን ከተናገሩት፡-

***"ኢማም ጀዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ) ማለት በኖሩበት ዘመንም ሆነ ከዚያ በኋላ ባለው ዘመን ሁሉ ተጽዕኖ አሳዳሪና የዕውቀት ቅርስ የሆኑ ታላቅ የሰው ቁንጮ ነበሩ፡፡"[265]***

### *7.ኢማም ሙሳ አል-ካዚም (ዐ)*

ሐሩን ለልጁ ስለ ኢማም አል-ካዚም ከተናገረው፡-

***"ይህ የሰዎች ኢማም፣ በፍጥረታቱ ላይ የአላህ ማስረጃና በባሮቹ ላይ ኸሊፋው የተደረገ ነው፡፡" - (****አል-አዕያን* የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ::)

---

[263]ሐያት ኢማም አል-ሷዲቅ/66 -የ ሙሐመድ አቢ-ዘሕራ

[264] አል-ሰዋሂቅ አል-ሙህሪቃ/201

[265] ዱሀ አል- ኢስላም 3/265- ክፍል 2

የሐንበሊዎች ሼኽ ኢብን ኺላል ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"የሆነ ጉዳይ አስጨንቆኝ ወደ ሙሳ ቢን ጃዕፈር መቃብር ሄጄ ተወሱል አድርጌ ካሳሰበኝ ነገር ያልተገላገልኩበት አንድም ጊዜ የለም፡፡"[266]*

አል-ሻፈዒ ስለ ኢማሙ (ዐ) ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"የሙሳ አል-ካዚም ቀብር ሙጀረብ የሆነ (የተረጋገጠ) የሐጃ (ጉዳይ) ማስፈጸሚያ በር ነው፡፡"[267]*

***8.ኢማም ዓሊ አል-ሪዷ (ዐ)***

አቡ-ሰልት እንደተናገሩት፡-

*"እንደ ዓሊ ቢን ሙሳ አል-ሪዷ በእውቀት የመጠቀ አንድም ሰው አይቼ አላውቅም፤ እኔ የሰጠሁትን የምስክርነት ቃል የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ዓሊምም አይቼ አላውቅም፡፡"[268]*

አል-ሙእሙን ከተናገረው ደግሞ፡-

*"ይሄ ከሐሺሚዮች ሁሉ በዕውቀት የመጠቀ ሰው ነው፡፡"[269]*

ረጃእ ቢን ዶሓክ ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"በአላህ እምላለሁ! ወላሂ እንደሱ የአላህ ተቅዋ ያለው፣ በሁሉም ወቅት አላህን (ሱ.ወ) እንደሱ የሚያስታውስ (የሚዘክር)፣ ከሁሉ በላይ የሆነውን አምላክ እንደሱ የሚፈራ ሰው በህይወቴ አይቼ አላውቅም፡፡"[270]*

---

[266]ታሪኽ በግዳድ 1/120 -እ.ዳር አል- ኩቱብ -አል-ዒልሚያ

[267] ቱህፈት አል ዓልም ፊ ሸርህ ኹጥበት አል-መዓሊም 2/22 -የ ሰይድ ጃዕፈር ቢን ሙሐመድ ባቂር በህረልዑሉም (1281-1377 ዓመተ ሂጅራ)

[268]አዕያን አል-ሺዓ 1/101

[269]ቢሓር አል-አንዋር 10/337- ክፍል 19- ሐዲስ 2

አል-ሱሊ ከተናገሩት ድግሞ፡-

*"ከ አቢል ሐሰን አል-ሪዷ የሚበልጥ ሰው አይቼም ሰምቼም አላውቅም፡፡ ከማንም ሌላ ሰው ያላየሁትን ነገር ከሳቸው (ዐ) አይቻለሁ፡፡ የሳቸውን ያህል ፊደል ያለው ሰው አይቻለሁ ብሎ የሚናገር ሰው ካጋጠማችሁ ፍጹም አትመኑት፡፡"[271]*

*9. ኢማም ሙሐመድ አል-ጀዋድ (ዐ)*

ሙእሙን እንዲህ ብሏል፡-

*"በዒልሙ (በዕውቀቱ)፣ በፊድሉና በ ወደር የለሽ ተዓምራቱ በእድሜው ትንሽ ከመሆኑ ጋር ከሁሉም አህለልፊደል (ብልጫ ያላቸው ሰዎች) በላይ በብቸኝነት መርጬዋለሁ፡፡ እኔ ከሱ ያወቅኩትን ነገር ለሌሎችም ገሀድ እንዲወጣና እንዲያውቁት እፈልጋለሁ፡፡"[272]*

አል-አስቀፍ ስለ ኢማም አል-ጀዋድ ከተናገረው ደግሞ፡-

*"ይህ ሰው ነብይ ለመሆን የቀረበ ወይም ከነብይ ዝርያ የሆነ ሰው መሆን አለበት፡፡"[273]*

ኢብን አል-ጀውዚ ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"በዒልም፣ በተቅዋ፣ በልግስናና ዙህድ የአባቱን ፋና የተከተለ ታላቅ ሰው ነበር፡፡"[274]*

---

[270]ዑዩን አኽበር አል-ሪዷ (ዐ) 2/180- ክፍል 44- ሐዲስ 5

[271] ከሽፍ አል-ጉማ 2/316

[272]አዕያን አል-ሺዓ 2/33

[273] አል-መናቂብ 4/389

አል-ሶፈዲ ከተናገረው፡-

***"በ ልግስናና ቸርነት ከሚገለጹ እውቅ ሰዎች ቀዳሚው ነበሩ፡፡ ለዚህም ነው "አል-ጀዋድ" በሚል ቅጽል ስም የሚታወቁት፡፡ ከአስራ ሁለቱ ኢማሞች አንዱ ናቸው፡፡"[275]***

***10. ኢማም ዓሊ አል-ሓዲ (ዐ)***

አል-ጁኔይዲ ከተናገሩት፡-

***"በአላህ እምላለሁ! በምድር ላይ ካሉት ሁሉ በላጩና ከአላህ ፍጥረታት በሙሉ የላቀ ሰው ነው እሱ (ዐ)፡፡"*** *(አል-መአሲር የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ)*

የዝዳድ አል-ጠቢብ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"ከፍጥረታት (ሙኽሉቅ) የሩቅ ሚስጥር (ገይብ) የሚያውቅ ካለ ያ ሰው እሱ ነው፡፡"[276]***

አል-ያፊዒ ከተናገሩት፡-

***"ዓቢድ፣ፈቂህና ኢማም ነበር፡፡"*** (´ሚርአት አል-ጂናን´ የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ)

ኢብን ሐጀር አል-ሐይተሚ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"ዒልምና ቸርነትን ከአባቱ የወረሰ የሰው ዓይነታ!!"[277]***

---

[274] ተዝኪረት አል-ኸዋስ/ 321- እ.ቤይሩትመ፣ (1401 ሂጅራ)

[275]አል-ዋፊ ቢልወፊያት- ኸይሊ ቢን አይበክ አል-ሰፈዲ (690-764 ሂጅራ) 4/105- ቁጥር 1587

[276] ቢሓር አል-አንዋር 50/161- ክፍል3- ሐዲስ 50

ኢብን አል-ዒማድ አል ሐንበሊ ከተናገሩትደግሞ፡-

***"ፈቂህ፣ ኢማምና ዓቢድ ነበሩ፡፡"[278]***

አል-ሺብራዊ አል-ሻፊዒ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"ከራማው (ተዓምራቱ) እጅግ በርካታ ነው፡፡"[279]***

### ***11. ኢማም ሐሰን አል-ዓስከሪ (ዐ)***

አል-ወዚር ኢብን ኻቃን ለ ልጃቸው እንዲህ ሲሉ ተሰምቷል፡-

***"ልጄ ሆይ! ኢማም (መሪነት) ከበኒ ዓባስ ኸሊፎቻችን እጅ ቢወጣ ከሱ (ኢማም አል-ዓስካሪ) ሌላ ለ በኒ ሓሺሞች ለማም አይገባም፡፡ ምክንያቱም፣ በፈድል፣ በጨዋነት፣ በቅንነት፣ በሰብዕና፣ በዙህድ፣ በዒባዳ፣ በድንቅ ባህሪና መልካምነት ከሱ የተሸለ የለምና፡፡"[280]***

በኸቲሹዕ አል-ጠቢብ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"በዚህ ዘመናችን ከሰማይ በታች ካሉት ሁሉ በእውቀት የላቀ ሰው ነው፡፡"***[281]

---

[277]አል-ሰዋዕቅ አል-ሙህሪቃ/207

[278] ሸዘራት አል-ዘሐብ 2/128 -የኢብን ዒማድ አል-ሐንበሊ (1089 ሂጅራ)- የ254 ሂጅራ ክስተቶች

[279]አል-ኢትሐፍ ቢሀብ አል-አሸረፍ የሺብራዊ አል-ሻፊዒ የድርሰት ዘመን 1154 ሂጅራ ክፍል 5 ገጽ 176

[280] አል-ኢርሻድ 2/322፣ 323

[281] ቢሓር አል-አንዋር 59/132- ክፍል 54- ሐዲስ 102

የኸሊፋው ጸሐፊ አኑሽ ኢማሙን (ዐ) እንዲህ በማለት ሲያናግር ተሰምቷል፡፡

***"መሲህ ዒሳ የመርየም  የመጀመሪያ ልጅ (ዒሳ ኢብን መሪየም) አላህ ዘንድ እንዳለው ደረጃ አምሳያ ሆናችሁ በዚህ እንጂል  (ወንጌል) ውስጥ አግኝተናቹሃል፡፡"*** *(ሶሒፈት አል-አንዋር* የተሰኘውን ኪታብ ይመልከቱ፡፡)

መነኩሴው ዲር አልዓቁል ስለ አማሙ (ዐ) ከተናገረው፡-

***"ይኼማ አምሳያው ነው (የመሲሁ አምሳያ)፡፡ በተዓምራቱ፣ በመጠቀ ገለጻውና ማስረጃው ልክ እንደ መሲሁ እየሰሱ (ዒሳ) ነው፡፡"***

*(ለምንጩ ሶሒፈት አል-አንዋርን ይመልከቱ፡፡)*

### ***12. ኢማም መህዲ አል-ሙንተዘር (ዐ)***

አል-ሪፋዒ እንዲህ ብለዋል፡-

***"ሐሰን አል-ዓስካሪ ባለ ሲርዳቡን (ዋሻውን)፣ አል-ሑጀት አል-ሙንተዘር (በጉጉት የሚጠበቀውን ማስረጃ) የአላህ ወሊይ የሆነውን ሙሐመድ አል-መህዲን ተተኪ አድርገዋል፡፡"*** *(ሳሂብ አል- አኽባር* የተሰኛውን ኪታብ ይመልከቱ፡፡)

አል-ጃሚ ከተናገሩት ደግሞ፡-

***"መህዲ የመላው ዓለም መሪ ነው፡፡"***[282]

---

[282] ***ከሽፍ አል-አስታር ፊ ወጅህ አል-ጋዒብ ዐንል አብሷር*** የሙሐዲስ አል-ሚርዛ ሁሴን አል-ኑሪ አል-ጠበሪ (1254-1320 ሂጅራ)- ገጽ 65)

ኢብን ሐጀር ከተናገሩት፡-

***"አቡል ቃሲም ሙሐመድ አል-ሑጃ፣ አባቱ ከሞተ በኋላ እድሜው አምስት ዓመት ቢሆንም አላህ (ሱ.ወ) ግን በዚሁ እድሜው ረቂቅ ጥበብ የቸረውና አል-ቃዒም አል-ሙንተዘር በመባል ይታወቃል፡፡"[283]***

ኢብን ከሲር ኢማሙን (ዐ) በተመለከተ ከተናገሩት ሐዲስ፡-

***"እነሆ ዒሳ ከመህዲ ኋላ ሆኖ (ተከትሎ) ይሰግዳል፡፡"[284]***

እንዲሁም ኢብን ከሲር፡-

***" ጥቁር ባንዲራ በመህዲ ዋዜማ ትመጣለች፡፡"[285]***

*አላህ ሆይ! የመገለጫ ግዜውን አፋጥንልን፤ መውጣቱንም ገር አድርግልን!*

---

[283] አል-ሰዋኢቅ ሙህሪቃ) 208)

[284] *ኢርሻድ አል-ሳሪ ሊ ሸርህ ሰሂህ አል-ቡኻሪ* የ አል-ቀስጠላኒ አል-ሻፊዒ (851-923 ሂጅራ)

[285] *ሱነን ኢብን ማጃ- ኪታብ አል-ፊተን ክፍል 34- ሐዲስ 4084:: እዚህ ላይ ከሰውባን በተያዘ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ(ሰ)፡-" ግምጃ ቤታችሁ ጋ ሶስት ይገደላሉ፡፡ሁሉም የኸሊፋ ልጅ ነው፡፤ ከዚያ ብኋላ ወደ አንዳቸውም አይመለስም ፡ከዚያ በኃላ ጥቁር ባንዲራ ከወደ ምስራቅ ትመጣለች የትኛውም ህዝብ ተገድሎ በማያውቅ መልኩ ይገድሏችኋል (ይዋጉዋችኋል) ከዚያም ያልያዝኩት (የረሳሁት) አንድ ጉዳዩ ተናገሩ ፡ባያችሁት ግዜ በረዶ ላይ በመንፏቀቅም ቢሆን ደርሳችሁ ቃል ኪዳን ግቡለት፡፡ እሱ የአላህ ኸሊፋ መህዲ ነውና፡፡"*

## የንጹሃን ኢማሞቹ (ዐ) እና የሺዓዎቻቸው ሚና

ንጹሃኑ የ አህለልበይት ኢማሞች (ዐ) ለኢስላምና ለኢስላሙ ዑማ (ህዝብ) ታላቅ ግልጋለሎት ሰጥተዋል፡፡ እንደዛ ባይሆን ኖሮ ሌሎች ሃይማኖቶችን ያጋጠመው የጥፋት ማዕበል ኢስላምንም ባጋጠመውና ተበክሎ በቀረ ነበር፡፡

ሺዓዎችም እንዲሁ በመላው የኢስላም ታሪክ ዘመን ውስጥ በአላህ መንገድ ላይ በመታገል፣ በርካታ ሀገራትን ድል አድርገው በመክፈት በርካታ ህዝቦችን ወደ አላህ ዲን በማስገባት ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በርካታ አጥፊ ቡድኖችን በመጋፈጥ ተቋቁመው  ድል ባይነሱ ኖሮ ኢስላምና ሙስሊሞች ተዳፍነውና ከስመው በቀሩ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ እራሱን በቻለ የታሪክ ድርሳናት ተዘግቦ ይገኛል፡፡

*"አዕያን አል-ሺዓ"*[286] *እና "አል-ዘሪዐቱ ኢላ ተሷኒፍ አል-ሺዓ"*[287] የተሰኙትን ኢንሳይኮሎፒዲያዎች በጨረፍታ እንኳ ቢሆን ማየት ይህንኑ እውነታ ያረጋግጥልናል፡፡ አሁን የሰው ልጅ ለደረሰበት ስልጣኔ የሺዓዎች ሚና ተጠቃሽ መሆኑን የዱኒያም ሆነ የዲን ዑለማዎች ደርሰውበታል፡፡

ለዚህም ነው ለሺዓዎች የሚገባቸውን ቦታ ለመስጠት የቻሉት፡፡ ከነዚህ ዑለማዎች ውስጥ እንደ ሼክ ሙሐመድ ሸልቱት ያሉ ሌሎች ታላላቅ የግብጽ ምሁራን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ ወደፊት በቦታው ይቀርባል፡፡

---

286 ሰይድ ሙህሲን አል-አሚን አል-ዓሚሊ- ስለ ሺዓ ዑለማዎች እና ሪጃሎች (ሐዲስ አስተላላፊዎችና ዘጋቢዎች) የሚመረምር ሲሆን ከ ሀያ ትላልቅ ሙጀለዶች (ቅጾች) በላይ የተዘጋጀ ነው፡፡

287 ኣጋ ቡዙርግ አል-ጠህራኒ- ከ25 ሙጀለድ በላይ የሆነ ሲሆን የሺዓ ድርሳናትን ይዳስሳል፡፡

# ሺዓ መሆን ለምን አስፈለገ?

## *የሺዓ ማስረጃዎች*

ሺዓዎች ሺዓነትን ለመምረጣቸው በርካታ ማስረጃዎች አሏቸው፡፡ ከታላላቅ እውቅ ዑለማዎች አንዱ የሆኑት አላማ አል-ሒሊ (ረ) *´አልፋይን´* በማለት በሰየሙት መጻሐፋቸው ውስጥ ሁለት ሺህ ያህል ማስረጃዎች ጠቅሰዋል፡፡

ከነዚህ ማስረጃዎች ውስጥ አብዛኛው ከሱኒ ወንድሞቻቸው ኪታቦች ውስጥ የተገኘ ሲሆን የተወሰኑትን ብቻ አጠቃላይ በሆነ መልኩ በመጥቀስ እንብቃቃለን፡፡[288]

### *የአሚረል ሙእሚኒን ዓሊ (ዐ) ኸሊፋነት*

የተከበሩት ነብይ ሙሀመድ ቢን አብደላህ (ሶ) የዓሊ ቢን ዓቢ ጧሊብን (ዐ) ኸሊፋነት በተለያዩ አጋጣሚዎችና ቦታዎች በምልከታ፣ በግልጽና በአጽንኦት ደጋግመው ይናገሩ ነበር፡፡

### *የማስጠንቀቂያው (ኢንዛር)ቀን*

ከነዚህም ውስጥ አንደኛው በ *"ማስጠንቀቂያው ቀን"* ነብዩ (ሶ) የተናገሩት ሲሆን ይህም እንደ ኢብን ኢስሐቅ፣ ኢብን ሐጀር፣ ኢብን አቢ ሓቲም፣ አል በራኒ እና በሌሎች ዕውቅ የአህለሱና ምሁራን የተዘገበ እርግጥ የሆነ ክስተት ነው፡፡[289]

---

[288]ለዝርዝሩ የሰይድ ሸረፈዲን አል-ዓሚሊን *´አል-ሙራጀዓት*እና የ ዓላማ አማኒን *`አል-ገዲር'* ማየት ይቻላል፡፡´

[289]ለዝርዝሩ ሸዋሂድ አል-ተንዚል የ ሐስካኒ አል-ሐነፊ 1/372 ሐዲስ 514 ገጽ 420 ሐዲስ 580፤ ተፍሲር አል-ጦበራኒ 19/74፤ ታሪኽ አል-ጦበሪ 2/319፣ በ ሙሰነድ አህመድ ቢን

ይህ የተከሰተው ኢስላም በመካ ግልጽ ከመውጣቱ በፊት የዳእዋ (ጥሪ) መጀመሪያ አከባቢ ላይ ሲሆን ***"ወ አንዝር ዓሺረተከል አቅረቢን" (የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ)*** የሚለውን የቁርዓን አያህ ከወረደ በኋላ ነበር (አል-ሹዓራእ፡ 218) ፡፡

በነብዩ (ሶ) ጥሪ መሰረት በአጎታቸው በአቡ ጧሊብ ቤት እንዲሰበሰቡ ተደረጉ፡፡ በዕለቱ አርባ ሰዎች ነበሩ የተሰበሰቡት፡፡ እንደ አቡ ጧሊብ፣ ሐምዛ፣ ዓባስና አቡለሀብ ያሉ የነብዩ (ሶ) አጎቶች ይገኙባቸዋል፡፡

በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ ነብዩ (ሶ) እንዲህ አሉ፡-

**"የ ዓብዱልሙጣሊብ ልጆች ሆይ! በአላህ እምላለሁ! እኔ ካመጣሁላችሁ ነገር የተሸለ ለህዝቡ ያመጣ ከዓረብ ውስጥ አንድም ወጣት አላውቅም፡፡ የዱኒያና የአኺራን በላጩን ጉዳይ ነው ይዤላችሁ የመጣሁት ፡፡አላህ (ሰ.ወ) ወደዚህ ጉዳይ እንድጠራችሁ አዞኛል፡፡ ከናንተ ማናችሁ ነው የእኔ እንደራሴ ሆኖ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚረዳኝ? ማነው ከናንተ ወንድሜ፣ ወሲዬና በናንተ ውስጥ ኸሊፋዬ የሚሆን?**

---

ሐንበል 1/111፣ ኪፋየት አል-ጧሊብ -የ ከንጂ አል-ሻፊዒ /204፣ 206፤ ተዝኪረት አል-ኸዋስ የ ስብጥ ኢብን አል ጀውጂ አል-ሐነፊ/38፣ የናቢዕ አል-መወዳ/105፤ አል-ካሚል የኢብን አሲር /2162፤ አል-ዱር አል-መንሱር የ ሱዩጢ 5/97፤ ታሪክ ዲመሽቅ የ ኢብን ዓሳኪር 1/85- ሐዲስ 138፣140፤ ከንዝ አል-ዑማል 15/113- ሐዲስ 323፣ 334፤ አል-ሲራህ አል-ሐለቢያ 1/286፤ ታሪክ አቢል ፊዳእ 1/119፤ ሸርህ ነህጀልበላጋ -የኢብን አቢልሐዲድ 13/210 ፤ ታሪክ አል-ጦበሪ 2/319-321፤ አል-ተፍሲር አል-ሙኒር ሊመዓሊም አል-ተንዚል 2/118. . .

ከዓሊ (ዐ) በስተቀር የተቀሩት ታዳሚዎች ዝም አሉ፡፡ በዚህ ወቅት ዓሊ (ዐ) ከሁሉም በእድሜ ታናሽ ነበር፡፡ የነብዩን (ሶ) ጥያቄ በማጤን ቆም አለና እንዲህ አለ፡-

**"የአላህ ነብይ ሆይ! እኔ በጉዳዩ ላይ እንደራሴህ ለመሆን ዝግጁና ፈቃደኛ ነኝ፡፡"**

በዚህ ግዜ ነብዩ (ሶ) የዓሊን (ዐ) ጫንቃ ያዝ አደረጉና፡-

**"ይህ ሰው ወንድሜ፣ የኔ ወሲይና በናንተ ውስጥ ኸሊፋዬ ነው፡፡ እሱን ስሙት ታዘዙትም"** አሏቸው፡፡

## *የገዲር ቀን*

ከማስረጃዎቹ አንዱ *የገዲር ቀን*[290] ክስተት ሲሆን የገዲር ሐዲስ በአንድ መቶ ሃያ የነብዩ (ሶ) ሰሃቦችና ሰማንያ አራት ታቢኢዎች የተወራ ሐዲስ ነው፡፡

---

[290]የገዲርን ታሪክና በእለቱ ነብዩ (ሶ) ያስተላለፉትን ወሳኝ መልዕክት ዝርዝር ለማግኘት ቀጥሎ ያሉትን መሷዲሮች ማየት ይመከራል፡፡ ይኸውም ነብዩ (ሶ) ከሳቸው በኋላ ኸሊፋቸው ሆኖ በወህይ የተመረጠው ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ) ስለመሆኑ የተገለጸበት፣ በተለያየ አባባሎች (አልፋዝ) ሙተዋትር በሆኑ ሐዲሶች የተነገረ እውነታ ሲሆን ይህንኑ አል-አሚኒ ´አል-ገዲር´ በተሰኘው መጽሀፋቸው ውስጥ ተጠናቅሮ እናገኛለን፡፡
-ሰሂህ ኢብን ሒባን 15/176- ሙአሰሰት አል-ሪሳላ -ቤይሩት፤
-አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሂሀይን 3/118፣ 126፣ 613 -ዳር አል-ኩትብ አል-ዕልሚያ፣
-ሙስነድ አህመድ 1/84፣ 88፣118፣ 119፣ 152፣ 4/368፣ 370- ሙአሰሰት ቁርጡባ- ግብጽ፣
-ሙስነድ አቢ ያዕላ 1/249- ዳረል መእሙን ሊልቱራስ- ደማስቆ፣
-ፈዳኢል አል-ሶሓባ- አህመድ ቢን ሐንበል 2/572፣ 585፣ 586፣ 613፣682፣705 ሙአሰሰት አል-ሪሳላ- ቤይሩት፣ -ፈዳኢል አል-ሶሓባ- አል-ነሳኢ 1/15- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዕልሚያ ቤይሩት፣--------
------ሙዐጀም መስተዕጃም 1/368- ዓለም አል-ኪታብ -ቤይሩት፣
-ተፍሲር ኢብን ከሲር 2/15- ዳር አል-ፊክር፣

የሀዲሱ አስተላላፊ ሰዎች ቁጥር ከሶስት መቶ ስድሳ በለይ መሆናቸው በ ሐዲስ አኢማዎች የተረጋገጠ ሲሆን ከሺዓና ሱኒ ጸሐፊዎች በዚህ ሐዲስ ላይ መጽሀፍት የጻፉት ከሃያ ስድስት በላይ ናቸው፡፡ *(አል-ሰዋሂቅ አል-ሙህሪቃ/ 25- ኢ.ካይሮ-1332 ሂጅራ)*

---

-አል አሓዲስ አል-ሙኽታራ 2/80፣ 87፣105፣ 106፣ 173፣ 174፣ 274፣3/213 -መከተበት አል-ነህዷህ አል-ሐዲሳህ-መከተል ሙከረማ፣
-መዋሪድ አል-ዘምአን/544 -ዳር አል-ኩትብ አል-ዕልሚያ- ቤይሩት፣
-መጅመዕ አል-ዘዋኢድ 5/14፤ 9/104፣ 105፣ 106፣ 107፣ 164፣ ዳር አል- ረያን ሊል ቱራስ-ካይሮ፣
-ሱነን አል-ኩብራ- አል-ነሳኢ 5/45፣ 130፣ 132፣ 134፣ 135፣ 136፣ 154- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዕልሚያ- ቤይሩት፣
-ሙዕተሰር አል-ሙኽተሰር 2/301 -ዓለም አል-ኩቱብ- ቤይሩት፣
-ሙሰነድ አል-ሻሲ 1/127፣ 166 -መዲና አል-ሙነወራ፣
-ሙዕጀም አል-አውሰጥ 2/257፣ 369 - ዳር አል-ሐረመይን- ካይሮ፣
-ሙስነድ አል-በዛር 2/133፣ 235፤ 3/35- ሙአሰሰት ዑሉም አል-ቁርአን- ቤይሩት፣
-ሙዕጀም አል-ሰጊር 1/119፣ አል-መከተበት አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፣
-አል-ሙዐጀም አል-ከቢር 2/357፤ 4/16፤ 5/166፣ 170፣ 171፣ 191፣192፣ 195፣ 204- አል-ሞሱል፣
-አመሊ አል- ሙሓሚሊ/162 -ዮርዳኖስ፣
-አል-ሱና -ኢብን አቢ ዓሲም 2/607- አል-መከተብ አል-ኢስላሚ-ቤይሩት፣
-ፈይዱል ቀድር 6/218 ግብጽ፣
ታሪኽ አል-ተህዚብ 7/296፣ 8/106- ዳር አል-ፊከር- ቤይሩት፣
-ተህዚብ አል-ከማል 11/99፤ 20/484፤ 22/398፤ 33/283- ሙአሰሰት አል-ሪሳላ ቤይሩት፣
-ታሪኽ በግዳድ 8/289- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዕልሚያ ቤይሩት፣
-ሙዐጀም አል-ሶሓባ 1/199 -መዲና አል-ሙነወራ፣
-ሰፍወት አል-ሶፍወህ 1/313- ዳር አል-መዕሪፍ- ቤይሩት፣
-አል-ኢስቲዕያብ 3/1099- ዳር አል-ጀይል- ቤይሩት፣
-አል-ኢሷባ 3/592፣ 597፤ 4/328፤ 7/330- ዳር አል-ጀይል፣
-ነዝሐት አል-ሑፋዝ/102- ሙአሰሰት አል-ኩቱብ አል- ሰቃፊያህ- ቤይሩት፣
-ታሊ ተሽኪስ አል-ሙተሻቢህ- ኸጢብ አል-በግዳዲ 1/130- ሪያድ፣
-አል-ደሊል አል-ሙተናሂያ 1/226- ዳር አል-ኩትብ አል-ዕልሚያ- ቤይሩት፣
-ተዝኪረት አል-ሑፋዝ 2/713- ሪያድ፣
-ሲያር አዕላም አል-ኑበላእ 14/207፣ 274፣ 277 -ሙአሰሰት አል-ሪሳላ ቤይሩት. . . ሌሎች በርካታ ምንጮች፡፡)

እላይ ስለ ገዲር ከተጠቀሱት ምንጮች በተለያዩ አባባሎች (አልፋዝ) የተገለጹትን ማየት የሚቻል ሲሆን፣ አጠቃላይ ታሪኩ እንዲህ ነው፡-

የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ከመሰናበቻው ሀጅ በተመለሱ ጊዜ ***ገዲር ኹም*** ተብሎ የሚጠራ ቦታ ደረሱ፡፡ ተጓዦች በሙሉ ጎዞዞአቸውን እንዲገቱ በማድረግ እንዲሰበሰቡ አዘዙ፡፡ በእኩለ ቀን የሀሩር ቃጠሎ መድረክ ላይ ወጥተው ከመቶ ሺህ ሰዎች[291] በላይ ባሉበት ረዥም ንግግር (ኹጥባ) አደረጉ፡፡ በዚህ ንግግራቸው (ኹጥባቸው) ውስጥ የዓሊን (ዐ) እጅ ከፍ አድርገው በመያዝ እንዲህ አሉ፡-

**"እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ የኔ መውላ ነው፤ እኔ ደግሞ የሙእሚኖች መውላ ነኝ፡፡ እኔ ደግሞ ሙእሚኖች ከነፍሶቻቸው ላይ ካላቸው መብት በላይ መብትና ቅድሚያ አለኝ *(አነ አውላ ቢሂም ምን አንፉሰህም)*፡፡ እነሆ እንግዲህ እኔ መውላው የሆንኩት ሰው ሁሉ ይህ ሰው (ዓሊ ማለት ነው) መውላው ነው፡፡ አላህ ሆይ! እሱን (ዓሊን) መውላው ያደረገን ሰው አንተ መውላው ሁነው፡፡ እሱን ጠላት አድርጎ የያዘን አንተ ጠላት ሁነው፡፡ እነሆ ወደ እኔ በምትመላለሱበት ጊዜ የሰቀሌንን ጉዳይ (የሁለቱን ከባድና ክቡር ነገሮች**

---

[291](በእለቱ የነበሩትን ሰዎች ብዛት በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ዘጠና ሺህ ናቸው ሲሉ ሌሎች ደግሞ አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ይሆናሉ ብለዋል፡፡አንድ መቶ ሃያ ሺህ ያሉም አሉ፡፡ አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ መባሉም ይጠቀሳል:: ከዚህ በላይ እንደሆኑም ይነገራል፡፡ በወቅቱ ከረሱል (ሶ) ጋር ሐጅ ያደረጉት ግን ከዚህም በላይ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ *ተዝኪረት አል-ኸዋስ* ገጽ 30፣ *አል-ሲራ አል-ሐለቢያ* 3/257፣ የዘይኒ ደህላን *አል-ሲራህ አል-ነበዊያ* በ አል-ሲራ አል-ሐለቢያ የግርጌ ማጣቀሻ፣ አል-ገዲር 1/9. . . ይመልከቱ)

**ጉዳይ) እንዴት አድርጋችሁ በነሱ ውስጥ እንደምትተኩኝ (ከይፈ ተኽሉፊኒ ፊሂማ) የምጠይቃችሁ ይሆናል፡፡ ታላቁ ሲቅል (ከሁለቱ ከባድና ክቡር ነገሮች ታላቁ) የአላህ ኪታብ ነው፤ የአንደኛው ጫፍ ሰበብ በአላህ እጅ ነው፡፡ አንዱ ጫፍ በእጃችሁ ነው፡፡ ከጥመትና ከመቀልበስ (ከመቀየር) ትድኑ ዘንድ አጥብቃችሁ ያዙት፡፡ ሌላኛው ደግሞ ዒትራዬ (ዘረ-ሰቤ) አህለበይቴ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሐውድ (የከውሰር ምንጭ) ላይ ወደኔ እስኪመለሱ ድረስ ፍጹም እንደማይነጣጠሉ እነሆ አዛኙ፣ መሐሪና ሁሉን ውስጠ አዋቂ የሆነው ጌታ ነግሮኛል፡፡"** (አል-ሰዋኢቅ አል-ሙህሪቃ- ኢብን ሐጀር/25- ካይሮ- 1332 ዓ.ሂጅራ)

አህመድ ቢን ሐንበል በሙስነዳቸው ውስጥ በዘገቡት መሰረት ደግሞ፡-

***ነብዩ (ሰ) የዓሊን (0) እጅ በመያዝ እንዲህ ብለዋል፡-"እኔ ሙእሚኖች ላይ ከነፍሳቸው በላይ አውላ እንደሆንኩ (መብትና ቅድሚያ እንዳለኝ) ታውቁ የለም?"***

***እነሱም ፡-"አዎ! እናውቃለን"አሉ፡፡***

***ነብዩም (ሰ)፡-"እኔ መውላ በሆንኩለት ሰው ዓሊም መውላው ነው፡፡ አላህ ሆይ የሱን መውላነት ለተቀበሉት አንተ መውላቸው ሁንላቸው፡፡ ለሱ ጠላት የሆኑትን አንተ ጠላት ሁናቸው"አሉ፡፡***

ከዚያም በኋላ ዑመር (ዓሊን) አገኘውና እንዲህ አለ፡-

***"የአቢ ጧሊብ ልጆ ሆይ! እንኳን ደስ አለህ! እነሆ የሁሉም ሙእሚኖችና ምእመናት መውላ ለመሆን በቃህ፡፡"***

እንዲሁም ኢማም አል-ጠበሪ `አል-ዊሊያ` በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ በዘገቡት መሰረት ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ሶሃቦቻቸው ዓሊን (ዐ) ***"አሚር አልሙእሚኒን"*** በሚለው ማዕረግ ስም እንዲጠሩትና ሰላምታ እንዲያቀርቡለት ማዘዛቸውን እናነባለን፡፡ በመሆኑም ሰሃቦች በየተራ ወደ ዓሊ (ዐ) እየመጡ ***"አሰላሙ ዓለይከ ያ አሚር አልሙእሚኒን"*** በማለት ትእዛዙን ፈጸሙ፡፡

ታዲያ ከዚህ ሁሉ በኋላ ከማንም በላይ አዋቂና ከሁሉም በላይ ጥበበኛ የሆኑት የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ከህዝባቸው በቅርቡ እንደሚለዩ እያወቁ ያለምንም ኸሊፋ (ተተኪ) ህዝቡን እንዲሁ ትተው ያልፋሉ ብሎ ከቶ ማሰብ ይቻላል ወይ? ለጥቂት ቀናት እንኳ ከመዲና ለመውጣት ሲያስቡ ተተኪ ሳያስቀምጡ እንደማይንቀሳቀሱ ታሪክ እየመሰከረ ከቶውንስ እንዲህ ይታሰባልን?
ነብዩ (ሶ) ለ ጠቂት ቀናት እንኳን ከ መዲና ሲወጡ ዓሊን (ዐ) ተክተው ይወጡ እንደነበረ በርካታ የታሪክ ምንጮች ያወሳሉ፡፡[292]

[292]በአንድ ወቅት ነቢዩ (ሶ) ወደ ተቡክ ሲወጡ ዓሊን (ዐ) መዲና ላይ እንደወከሉና ***"ዓሊ ሆይ! አንተ እኔ ዘንድ ያለህ ቦታ ሓሩን ለ ሙሳ ያለው ቦታ ነው..."*** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ (ሰሂህ አል ቡኻሪ 5/129 ኪታብ አል-መግዞ የተቡክ ዘመቻ ዳረል ፊክር፤ሰሂህ ሙስሊም 3/360 ኪታብ አል-ፈዳኢል የዓሊ ኢብን አቢጧሊብ ፈዲላዎች በሚያትተው ክፍል፣ሱነን ኢብን ማጃህ 1/42 ሐዲስ 115 እና 121፤ታሪኸ ጠበሪ3/104 ፤ታሪክ ዲመሽቅ 1 ሐዲስ 30 ፣ 125፣148፣150፣251)

***ሐዲስ አል-መንዚላ (የደረጃ/ቦታ ሐዲስ)***

ሐዲስ አል-መንዚላን ኢማም አህመድና ኢማም አል-ነሳኢ እንዲሁም ሌሎች የሐዲስ ሊቃውንት የጠቀሱት የተረጋገጠ ሐዲስ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ለዓሊ (ዐ) እንዲህ ማለታቸውን እናገኛለን፡-

***"ከኔ በኋላ ነብይ ያለመኖሩ በስተቀር  አንተ እኔ ዘንድ ያለህ ቦታ ሐሩን ለሙሳ ያለው ቦታ  ያህል መሆኑ አያስደስትህም?"***

***(ለዝርዝሩ ቀደም ሲል ለዚህ ሐዲስ የተሰጠውን ምንጮች የመልከቱ፡፡)***

እንዲሁም ነቢዩ (ሶ) ለዓሊ (ዐ) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

***"አንተን ኸሊፋዬ ሳላደርግ መሄድ አይገባኝም"***[293]

## *ከ ነብዩ (ሶ) ዒትራ የሆኑ የተቀሩት ኢማሞች ኸሊፋነት*

ከዚያም ነብዩ (ሶ) ከአላህ በመጣላቸው መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) መሰረት እሳቸውን (ሶ) ተከተው ኸሊፋቸው የሚሆኑትን ንጹሀን ኢማሞች አስተዋወቁ፡፡ በአቡዳውድ፣ በሙስሊም በአህመድና በሌሎችም በተጠቀሰው

---

[293]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሀይን 3/143 -ዳረል ኩቱብ አል-ዕልሚያ- ቤይሩት፡፡ መጅምዕ አል-ዘዋኢድ 9/120- ዳረል ረያን ሊልቱራስ- ካይሮ፡፡ ሙስነድ አህመድ 1/330- ሙአሰሰት ቁርጡባ- ግብጽ፡፡ አል-ሙዕጀም አል-ከቢር 12/98- አል-ሞሱል፡፡ አል-ሱና -ኢብን አቢ ዓሲም 2/565፣ 566- አል-መክተብ አል-ኢስላሚ- ቤይሩት፡፡ ሌሎች በርካታ ምንጮችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡

መሰረት ከሳቸው (ሶ) በኋላ አስራ ሁለት ኸሊፋዎች እንደሚተኳቸው እንዲህ በማለት አሳወቁ፡፡

***"ከኔ በኋላ የሚተኩኝ ኸሊፋዎች አስራ ሁለት ናቸው፡፡"***[294]

*የናበዕ አል-መወዳ*[95] በተሰኘው መጽሃፍ ላይ እንደተጠቀሰው ነብዩ (ሶ) በተለያዩ ቦታዎች የኸሊፋዎቹን ስም ለይተው እንደጠቀሱ ማየት ይቻላል፡፡ ከሳቸው (ሶ) በኋላ ስለሚኖሩ ወሊዮች (ኸሊፋዎች) አንድ ሰው በጠየቃቸው ጊዜ ዘርዝረው መናገራቸው ተጠቅሷል፡፡

አንድ ሰው፡- ***"እስቲ ወሲይህ ማን እንደሆነ ንገረኝ?"*** ብሎ ሲጠይቃቸው፣

ነብዩ፡- ***"እነሆ የኔ ወሲይ (ኸሊፋ) ዓሊ ቢን አቢጧሊብ ነው፡፡ ከሱ በኋላ ደግሞ ሲብጦቼ ሐሰንና ሁሴን ናቸው፡፡ ከዚያም ከሁሴን ተወላጅ የሚሆኑ ዘጠኝ ኢማሞች ይካታተላሉ፡፡"***

ሰውየውም፡-***"ሙሐመድ ሆይ! ስማቸውን ጥቀስልኝ?"*** አላቸው፡፡

ነብዩም (ሶ)፡-***"ሁሴን ሲያልፍ ልጁ ዓሊ፣ ዓሊ ሲያልፍ ልጁ መሐመድ፣ ሙሀመድ ሲያልፍ ልጁ ጃዕፈር፣ ጀዕፈር ሲያልፍ ልጁ ሙሳ፣ ሙሳ ሲያልፍ ልጁ ዓሊ፣ ዓሊ ሲያልፍ ልጁ ሐሰን፣ ሐሰን ሲያል ደግሞ ልጁ አል-ሑጃ መሐመድ አል-መህዲ ይሆናሉ"*** አሉ፡፡

---

[294] ቀደም ሲል ለዚህ የተሰጠውን ምንጭ ይመልከቱ፡፡

[295]የናቢዕ አል-መወዳ- አል-ቁንዱዚ አል-ሐነፊ- ገጽ 569- ክፍል 73- *የአስራ ሁለቱን ኸሊፋዎች ስም ዝርዝር መግለጽ፡፡* -ፈራኢድ አል-ሲምጠይን 2/132- ሐዲስ 431፡፡ *ጋየት* አል-*መራም*- ገጽ 843- ሐዲስ 57፡፡

## *የ ሰቀለይን ሐዲስ*

በሁለቱ ታላላቅ ቡድኖች (ሺዓና ሲና) በተዘገበ ሙተዋትር በሆነ ሐዲስ ነብዩ (ሰ) ሁለት ከባድና ክቡር የሆኑ መርጅኦችን (ሰቀለይን) ለህዝበ ሙስሊሙ እንደተናዘዙና ህዝቡ እነዚህ ሁለቱን የሙጥኝ ብሎ እንዲይዝ በተለያየ አባባሎች (አልፋዝ) አበክረው መናገራቸውን ከበርካታ ምንጮች ማግኘት ይቻላል፡፡

ነብዩ (ሰ)፡-

***"እነሆ ሁለት ከባባድና ክቡር ነገሮች በመካከላችሁ እተዋለሁ፡፡ እነሱም የአላህ ኪታብና የኔ ዒትራ -አህሉልቤይቴ ናቸው፡፡ ሁለቱን አጥብቃችሁ ከያዛችሁ ከኔ በኋላ ፍጹም ጥመት ውስጥ አትወድቁም፡፡"***

*(ቀደም ሲል ለዚህ የተሰጠውን ምንጭ ይመልከቱ፡፡)*

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ነብዩ(ሰ):-

***"እነሆ ሁለት ኸሊፋዎችን በመካከላችሁ እተዋለሁ፤ ከሰማይ እስከ ምድር የተዘረጋው የአላህ ኪታብና የኔ ዒትራ– አህለልቤይቴ ናቸው፡፡ እነሆ እነዚህ ሁለቱ የሐውድ መልካ ላይ ወደኔ እስኪመለሱ ድረስ በፍጹም አይለያዩም (አይነጣጠሉም)፡፡"[296]***

[296]ሙሰነድ አህመድ ቢን ሐንበል 5/181 -ሐዲስ 21618- ሙአሰሰት ቁርጡባ-ግብጽ:: መጅምዕ አል-ዘዋዒድ- አቢበክር አል-ሐይሰሚ 9/162 -ዳር አል- ረያን ሊልቱራስ -ካይሮ፡፡ ፈዳኢል አል-ሶሐባ ኢብን ሐንበል 2/603-ሙአሰሰት አል-ሪሳላ -ቤይሩት፡፡

እንዲሁም በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሰ)፡-

*"እነሆ ሁለት ኸሊፋዎችን (ምትኮችን) በውስጣችሁ እተዋለሁ፡፡ የአላህ ኪታብና አህለልቤይቴ፡፡ የሐውድ መልካ ላይ አንድ ላይ ወደኔ እስኪመለሱ ድረስ ሁለቱ ፍጹም አይለያዩም፡፡"*[297]

እንዲሁ በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሰ)፡

*"ሁለት ነገሮችን በውስጣችሁ ተክቻለሁ፡፡ ከሁለቱ በኋላ ፍጽም ጥመት ውስጥ አትወድቁም /አትጠሙም፡፡ የአላህ ኪታብና ቤተዘሬ፡፡ የሀውድ መልካ ላይ ወደኔ እስኪመለሱ ፍጹም አይለያዩም፡፡"*[298]

እንዲሁ በሌላ ሐዲስ ነብዩ (ሰ):-

*"እነሆ እኔ መጠራቴ ነው (በሞት ልለያችሁ ነው):: በእርግጥ በመካከላችሁ (በውስጣችሁ) ሁለቱን ሰቀሎች (ከባድና ክቡር ነገሮች) ትቼአለሁ፤ ማለትም የአላህ ኪታብና አህለልቤይቴን፣ ከሁለቱ ወዲያ በፍጹም ለጥመት አትዳረጉም፡፡"*[299]

---

[297]ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል- 5/189 -ሐዲስ 21697 -ሙአሰሰት ቁርጡባ -ግብጽ::

[298]መጅመዕ አል-ዘዋኢድ -አቢበክር አል-ሐይሰሚ 9/162- ዳር አል- ረያን ሊልቱራስ-ካይሮ፡፡

[299]መጅመዕ አል-ዘዋኢድ -አቢ በክር አል-ሐይሰሚ 9/162 -ዳር አል- ረያን ሊልቱራስ -ካይሮ፡፡

***ሐዲስ አል-ሰፊና (የመርከቡ ሐዲስ)***

የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ንጹህን አህለልቤይቱን በነቢ ኑህ (ዐ.ሰ) መርከብ መሰሏቸው፡፡ እንዲህም አሉ (ሶ)፡-

***"እነሆ በእናንተ ውስጥ የኔ አህለልቤይት ምሳሌ እንደ ኑህ መርከብ ነው፤ በመርከቧ የተሳፈረ ነጃ ይወጣል (ይድናል)፡፡ ከመርከቧ ወደ ኋላ የቀረ (ያልተሳፈረ) ደግሞ ሰጥሞ ይጠፋል፡፡"[300]***

እንዲሁም ነቢዩ (ሶ)፡-

***"በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሰምጠው እንዳይጠፉ ከዋክብት የደህንነት ዋስትና እንደሆኑ ሁሉ፣ የኔ ኡማ (ህዝብ) ለልዩነትና መከፋፈል እንዳይዳረጉ ደግሞ የኔ አህለልበይት ዋስትናቸው ነቸው፡፡ ከዓረብ የሆነ አንድ ጎሳ ከነሱ ባፈነገጡ ጊዜ ለክፍፍልና ልዩነት ይዳረጉና የኢብሊስ ጭፍራ ይሆናሉ፡፡"[301]***

---

[300]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሀይን 2/373፣ 3/163- ዳር አል-ኩቱብ አል-ዒልሚያ- ቤይሩት፡፡ መጅምዕ አል-ዘዋኢድ -9/168፡፡ ኪፋየት አል-ጣሊብ 378 -አል-ሐይደሪያ፡፡ አል-ሙዕጀም አል-ሰጊር 2/22፡፡ ኑሽፈት አል-ሷዲ- ገጽ 79፡፡ ሂልየት አል-አውሊያእ 4/306፡፡ አል-ጃሚዕ አል-ሰጊር 2/132፡፡ ኑር አል-አብሷር 104 አል-የመኒያ፡፡ አል መናቂብ ያአል-መጋዚሊ- 132- ሐዲስ 174-177፡፡ ዑዩን አል-አኽባር- ኢብን ቁተይባ 1/211:: አል- ፈትህ አል-ከቢር 1/414፣2/113:: ሸርህ ነህጅ አል-በላጋ- ኢብን አብልሐዲድ 1/73- ግብጽ፡፡

[301]አል-ሙስተድረክ ዓላ አል-ሰሒሐይን 3/149:: አል-ሰዋሂቅ አል-ሙህሪቃ 91፣ 140- አል-የመኒያ፡፡ ኢህያእ አል-መይት-ሱዩጢ በአል-ኢትሓፍ የግርጌ ማጣቀሻ-114፡፡ ሙንተኸብ ከንዝ አል-ዑማል በሙስነድ አህመድ የግርጌ ማጠቃሻ 5/93:: የናቢዕ አል-መወዳ- 298- እስላምቡል፡፡ ጀዋሂር አል-ቢሓር -አል-ነብሓኒ 1/361 -ግብጽ፡፡

# ሺዓነት በሱኒ ዑለማዎች እይታ

## *ሺዓነት እና የሱኒ ዑለማዎች*

ኢስላም የሙስሊሞች አንድነት ዋጂብ (ግዴታ) መሆኑን አበክሮ ያስተምራል፡፡ ይህንኑ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**إِنَّ هَٰذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاعْبُدُونِ**

**"ይህች ህዝባችሁ አንዲት ህዝብ ነች፤ እኔ ደግሞ ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ፡፡"**[302]

የሙስሊሞች መከፋፈልና መራራቅ የኢስላምን አስተምህሮ የሚጻረር ነው፡፡ ቀደምት የሱና ዑለማዎችም ሆኑ በዘመኑ ያሉትም ታላላቅ ዑለሞች በግልጽ ያስቀመጡትን አቋም የሚቃረን ነው፡፡

የአንዳንዶቹን አስተያየት ለመጥቀስ ያህል፡-

### *ዓላማህ አል-ዘሐቢ*

ከታላላቅ ዑለሞች ጎራ ውስጥ የሚውሉት ዓላማህ አል-ዘሐቢ *"ሚዛን አል-ኢዕቲዳል"* በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ለመጥቀስ ያህል፡-

"ይህ ጉዳይ- ማለትም ሺዓነት- በታቢዒኖችና ተከታዮቻቸው ውስጥ በብዛት የሚገኝ ነገር ነው፡፡ በዲን፣ በወረዕ (የአላህ ፍራቻና ጽድቅ)፣ በሀቀኝነትና በመልካም ስብዕና የተካኑ ተከታዮች ያሉበት ነው፡፡ የነዚህን (ሺዓዎች) ሐዲስ

[302] አል -አንቢያእ፡ 92

ወደኋላ ብንተው (ባንቀበል) በርካታ ነብዩ (ሶ) ሐዲስና ታሪክ ጠፍቶ ይቀር ነበር፡፡" *(ሚዛን አል-እዕቲዳል 1/5)*

ታላቁ ዓላማህ ሸረፈዲን አል-ሙሰዊ *"አል-ሙራጀዓት"* በተሰኘው እውቅ መጽሐፋቸው ላይ በሐዲስና በሌሎች መዛግብት ውስጥ የተለያዩ ዑለሞች የዘገቡላቸውን የአንድ መቶ ሺዓ ሪጃሎች (ሐዲስ ተራኪዎች) ስም ዝርዝር ጠቅሰዋል፡፡ *(አል-ሙራጀዓት/54- አል-ሙራጀዓት ቁጥር 16- ዳር አል-ዑሉም - ቤይሩት፡፡)*

### *ሼኽ ሙሐመድ ሸልቱት*

*ቀደምት ዑለማዎችም ሆነ በዘመናችን ያሉት ዕውቅ ምሁራን ይህንን ጉዳይ* በተመለከተ በርካታ ቅርሶችን ትተውልናል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የቀድሞው የአዝሐር ሼክና ዕውቅ ምሑር ሼክ ሙሐመድ ሸልቱት የሰጡት ፈትዋ ተጠቃሽ ነው፡፡ የሼክ ሸልቱትን ፈትዋ ለመጥቀስ ያህል፡-

*"ሺዓ ኢማሚያ ኢስኑዐሸሪያ በመባል በሚታወቀው የጀዕፈር መዝሐብ ተዐቡድ ማድረግና እንደ ሌሎች መዝሐቦች ተቀብሎ በዒባዳቸው አላህን መገዛት በሸሪዓው የተፈቀደ ነው፡፡ ሙስሊሞች ይህንን አስረግጠው ማወቅና የአንድን የተለየ መዝሐብ ምንነት ሳያውቁ በጭፍን ከመዳኘት መቆጠብ እንዳለባቸው ማወቅ ይገባቸዋል፡፡"*

(የሼክ ሸልቱት ፈትዋ ተከትሎ በርካታ ሌሎች የሱኒ ዑለማዎች ሓሳቡን በመደገፍ ብዙ ማለታቸውን መርዋን ኸሊፋት *"አክረመትኒ አል-ሰማእ"* በተሰኘው መጽሓፍ ላይ ዘርዝሯል ፡፡ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

*ሼክ አል-አዝሐር ዶክተር ሙሐመድ ሙሐመድ አል-ፈሓም፡-*

*"በሼክ መሐመድ ሸልቱት መልካም ስብዕና፣ ዕውቀት፣ ብዙ አንባቢነትና ምርምር፣ የመጠቀ የዓረብኛ ቋንቋ ክህሎት፣ የቁርአን ተፍሲርና በፊቂህ መሰረታውያን ላይ በሚሰጡት ትምህርት ከሚደመሙ ሰዎች አንዱ ነኝ፡፡ በሺዓ መዝሐብ ተዐቡድ ማድረግ የሚበቃ (የሚቻል) ስለመሆኑ ያደረጉት ፈትዋ የዲን መሰረት ላይ የተገነባ ትክክለኛ ፈትዋ መሆኑን በግሌ አምንበታለሁ፡፡"* (ፊ ሰቢል- አል-ወህደት አል-ኢስላሚያ -አል-ረዷዊ -ገጽ 7)

***ሼክ መሐመድ አል- ገዛሊ ፡-***

*"ታላቁ ኡስታዝ ሼክ ሙሐመድ ሸልቱት ያደረጉት ይህ ፈትዋ በዚህ ጉዳይ ላይ የተጋረጡትን መሰሪ እንቅፋቶች የነቀለና እውነታን ለመቀበል ዝግጁ ለሆኑ ባለስልጣናትና ዑለሞች አዲስ ምዕራፍ የከፈተ፣ ጭፍንነትንና እርስ በርስ መነቋቆር ነው ይህ ህዝብ የሚያጠፋው ብለው የሚጠባበቁትን የኦረየንቲያልስቶች ህልሞ የሚያጨልም እንደሆነና በአንድነት ባንዲራ ስር በማሰለፍ የጠላቶችን በር እንደዘጋ አምናለሁ፡፡ በእኔ እምነት ይህ ፈትዋ የአዲስ ምዕራፍ መጀመሪያና ቀዳሚ የተባረከ ስራ ነው፡፡"*

*"ሺዓዎች በነብዩ (ሶ)ሪሳላ ያምናሉ፣ ለነብዩ በነበረው ታማኝነትና ቅርበት የተነሳ ለዓሊ የተለየ ክብር አላቸው፡፡ ከቀደምት ሰዎችም ሆነ ከተቀሩት የሰው ልጅ ትውልዶች ከሷዲቀል አሚን (ነብዩ ሙሐመድ (ሶ) አስበልጠው የሚያዩት አንዳችም ሰው የለም፡፡"* (ዲፋዕ ዐን አል-ዓቂዳ ወ-ሸሪዓ-257)

የቀድሞው የካይሮ መስጂዶች አስተዳደሪ ዓብዱረህማን አል-ነጃር ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"የሼክ ሸልቱት ፈትዋ መሰረት በማድረግ እኛም ስንጠይቅ በአራት መዝሀቦች ሳንገደብ ፈትዋን ማስተላለፍ እንችላለን፡፡ ሼክ ሸልቱት ሙጅተሒድ የሆኑ ኢማም ናቸው፡፡ አስተያየታቸው ትክክለኛና ፍርዳቸው ሀቅ ነው፡፡ ሁላቸውም ሙጅተሂዶች ሆነው ሳሉ አስተሳሰባችንንና ፈትዋችንን በተወሰኑ መዝሀቦች ላይ ብቻ ገድበን የምናየው ለምንድን ነው?"*

(ፊ ሰቢል አል-ወህደት አል-ኢስላሚያ- አል-ረዷዊ -66)

***ዶክተር ሙስጠፋ አል-ሪፋዒ ከተናገሩት ደግሞ፡-***

*"ሁለቱ መዝሀቦች (ኢማሚያና ዘይዲያ) ከአህለሱና መዝሀብ ጋር የሚገናኙ ብቸኞቹ መዝሀቦች ናቸው፡፡ የነዚህ ሁለት መዝሀቦችን አህካሞች መሰረት ለማድረግ ተዐቡድ ማድረግ ትክክለኛ አቋም ነው፡፡"*

*"የጃዕፈሪን መዝሀብ ከአራቱ መዝሀቦች ጋር በማድረግ አምነት ከመቀበል የሚከለክል ነገር አለ ብዬ አላምንም፡፡" (ኢሰላሙና- ገጽ 32፣ 59)*

ሐሰን አል-በና ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"አህለሱና እና ሺዓ ሙስሊሞች መሆናቸውን እወቁ፡፡ ላ ኢላ ሀኢለላህ እና ሙሐመድ ረሱሉላህ የሚለው ቃል አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የዓቂዳ (እምነት) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ደግሞ ሱናም ሆነ ሺዓ እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸው ያሉት ኺላፎች (ልዩነቶች) ደግሞ ለመቀራረብ የሚያስችሉና*

*ሊወገዱ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡"*(ዚክሪያት ላሙዘከራት -ዑመር አል-ቲልሚሳኒ-ገጽ 249፡፡ አል-ዓለም መጽሄት ቁጥር 519 ገጽ 40)

ኡስታዝ አህመድ ቤክ አል-መስሪ- የሼክ ሸልቱትና የአቢ ዘህራ ኡስታዝ ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"ሺዓ ኢማሚያ ሙስሊሞች ናቸው፣ በአላህና በመልእክተኛው ያምናሉ፣ በቁርአንና ነብዩ ሙሐመድ (ሰ) ባመጡት ሁሉ ያምናሉ፡፡ በሺዓ ኢማሚያ ውስጥ ጥንትም ሆነ አሁን እጅግ ታላላቅ የሆኑ ፉቀሃዎችና በሁሉም የእውቀት አውታሮች የተካኑ ዑለሞች አሉ፡፡ በጥናትና ምርምር የመጠቁና የጥልቅና ሰፊ ዕውቀት ባለቤቶች ናቸው፡፡ መጽሀፍትና ድርሳናቸው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በርካታ መጽሐፋቸውን አንብቢያለሁ፡፡"*

ሼክ አል-አዝሐር ሰይድ ሙሐመድ ጠንጣዊ ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"ሙስሊሞች ሱኒም ሆኑ ሺዓ በአላህ እና በነብዩ (ሰ) ያምናሉ፡፡ የሐሳብ ልዩነቶች የአንድን ሰው የኢማን ደረጃ ሊቀንስ አይችልም፡፡" (ታሪኽ አል-ተሸሪዕ አል-ኢስላሚ)*

ኡስታዝ ሙሐመድ አል-ሰርጣዊ በኦርዶን (ዮርዳኖስ) ዩኒቨርስቲ የሸሪዓ ኮሌጅ ዲንና ከታላላቅ ሙፍቲዎች አንዱ የሆኑት ከተናገሩት ደግሞ፡-

*"እኔ የምለው ደግሞ ሰለፎቻችን ያሉትን ነው፡፡ ይኸውም የኢማሚያ ሺዓዎች የዲን ወንድሞቻችን ናቸው፡፡ የወንድማማችነት ሐቅ (መብት) በኛ ላይ*

*አላቸው፡፡ እነሱ በኛ ላይ ያላቸውን ሀቅ ያህል እኛም በነሱ ላይ አለን፡፡ በኛና በነሱ መካካል ኢኽትላፍና የርዕዮት ልዩነት የለም፡፡ ያለን ልዩነት በቅርንጫፍ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡"* (ታሪኽ አል-ተሽሪዕ አል-ኢስላሚ ገጽ 90)

ኡስታዝ ዓብደልፈታህ አብደልመቅሱድ በተናገሩት ደግሞ፡-

*"በእኔ እምነት ሺዓዎች የትክክለኛው ኢስላም መገለጫዎች ናቸው፡፡ ትክክለኛውን ኢስላም የምናይበት የጠራ መስታወት ናቸው፡፡ ኢስላምን ማየት የፈለገ ሰው በዓቂዳቸውና ተግባሮቻቸው ውስጥ ይመልከት፡፡ ኢስላማዊ ዐቂዳን በመጠበቅና ከጥቃት በመከላከል ረገድ ሺዓዎች ያበረከቱትን ታላቅ ግሊጋሎት በሚመለከት ታሪክ ታላቅ ምስክር ነው፡፡*

*ታላላቅ የሺዓ ዑለማዎች ሌሎች መጫወት ያልቻሉትን ሚና በተለያዩ አውታሮች በሚገባ መጫወት የቻሉ የኢስላም ባለውለታዎች ናቸው፡፡ ኢስላምን የበላይ ለማድረግ አስተምህሮዎቹን ለማሰራጨትና ሰዎችን ወደ ቁርአን ለማምጣት ብዙ ያለፉ አይበገሬነታቸውን ያሳዩ በርካታ ተግዳሮቶችን የተወጡና ብዙ መስዋዕት የከፈሉ ናቸው፡፡" (ፊ ሰቢል አል-ወህደት አል-ኢስላሚያ)*

## ሺዓን ለመተዋወቅ የሚረዱ መሷድሮች (ምንጮች)

ሺዓን ለማወቅ የፈለገና ኡሱል (መሰረታዊ) እና ፉሩዕ (ቅርንጫፍ) የሆኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ማስረጃ ለማወቅ የፈለገ ሰው በገበያ ላይ በቀላሉ የሚገኙ በርካታ መጽሐፍትና ሌሎች ምንጮች የሚገኙ ሲሆን ቀጥሎ የተጠቀሱትን መጽሐፍት ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው፡-

**አል-ሙራጇዓት**[303]

**አል-ፉሱል አል-ሙሂማ**[304]

**አል-ገዲር**[305]

**አል-ዘሪዓ**[306]

***ሸርህ አል-ተጅሪድ*** [307]

**ሐቅ አል-የቂን**[308]-

**ወሳኢል አል-ሺዓ**[309]

**ጀዋሒር አል-ከላም**[310]

---

[303] ሰይድ ዓብደልሁሴን ሸረፈዲን (1290-1377 ዓ.ሂጅራ)

[304] ሰይድ ዓብደልሁሴን ሸረፈዲን (1290-1377 ዓ.ሂጅራ)

[305] ዓላማ ሼክ አል-አሚኒ 1390 ዓ.ሂጅራ) - ከሃያ ሙጀለዶች በላይ ሲሆን በደራሲው የህይወት ዘመን በአስራ አንድ ሙጀለዶች ለመታተም በቅቷል፡፡

[306] አል-ዘሪዓ ኢላ ተሷኒፍ አል-ሺዓ- (ሼክ አጋ ቡዘርግ አል-ጠህራኒ- 1389 ዓ.ሂጅራ) በሃያ አምስት ሙጀለዶች ታትሞ ይገኛል፡፡

[307] ዓላማህ አል-ሒላሊ (ሸርህ ኢስቲድላሊ ሊኪታብ፡ተጅሪድ አል-ኢስቲቃድ- ሊልፈይለሱፍ ወል ሐኪም አል-ኢላሂ ኸዋጃ ነሲር አል-ዲን አል-ጡሲ)

[308] ሰይድ ዓብደላህ ሹበር (ዲራሰት ኢስቲድላሊያ ሙስሂበ ፊ ኡሱል አል-ዲን ዐቅለን ወነቅለን አን አል-ኪታብ ወአል-ሱና)

[309] ሼክ አል-ሁር አል-ዓሚሊ- በሃያ ሙጀለዶች የሚገኝ የሐዲስ መጽሐፍ፡፡

[310] ሙሐመድ ሐሰን አል-ነጃፊ -በአርባ አምስት ሙጀለዶች የሚገኝ የፊቂህ ኢስትድላሊ መጽሐፍ፡፡

**አስል አል-ሺዓ ወ ኡሱልሃ**[311]-

**አል-ዓቃኢድ አል-ኢስላሚያ**[312]

**አል-ሙትዓ**[313]

**ዓሊ ምን አል-ለህድ ኢላ አል-መህድ**[314]

**አዕያን አል-ሺዓ**[315]

**ዐቃኢድ አል-ኢማምያ**[316]

እንዲሁም ሌሎች በርካታ መጽሀፍት፡፡[317]

---

[311] ሼክ ሙሀመድ ሁሴን ካሽፍ አል-ጊጣእ (የሺዓን መዝሐብ ምንነት ከነቅል፣ ዐቅልና ታሪክ አንጻር የዳሰሰ መጽሐፍ)

[312] ኢማም ሰይድ ሙሐመድ አል-ሺራዚ) በዓቂዳ ላይ ሰፊ ምርምር ያካተቱና ብዙ ጊዜ የታተመ

[313] ተውፊቅ አል-ፉኪኪ (1321 ዓ.ሂጅራ (በጊዜ የተገደበ ጋብቻ ሸሪዓዊ መሆኑ ላይ የተደረገ ምርምር)

[314] ሰይድ ሙሐመድ ከዚም አል-ቀዝዊኒ) -የኢማም ዓሊ (ዐ) ታሪክ

[315] ዓላማህ ሰይድ ሙሕሲን አል-አሚን አል-ዓሚሊ) ከሃያ ሙጀለዶች በላይ የሆነ በሺዓ ዑለሞችና ሪጃሎች ላይ የሚያተኩር

[316] ሼክ ሙሀመድ ሪዷ አል-ሙዘፈር) -የሺዓ መሰረታዊ ዐቂዳዎች ላይ የሚያተኩር

[317] የ አል-ፈቂህ ኢማም አል-ሺራዚ አል-መውሱዓህ (ኢንሳይክሎፒዲያ) መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ በአንድ መቶ ሃምሳ ሙጀለዶች በላይ የሚገኝ ሲሆን የሺዓዎችን ፊቂህ በሰፊው የሚዳስስና የዑለሞቻቸውን አባባሎች (ሐሳብ) የሚቃኝ ነው፡፡

## *ሺዓና ሺዓነት ዙሪያ -ጥያቄና መልስ*

ይህ ክፍል *"ሓከዛ አል-ሺዓ"* (ሺዓ እንዲህ ነው) ከተሰኘው የኢማም አል-ሺራዚ (ዳመ ዚሉሁ) ኪታም ጠቋሚነት ታስቦ የተወሰደ ነው፡፡

***ጥያቄና መልስ***

ጥ. *"ሺዓ"* የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

መ. "*ሺዓ"* ማለት *`ሙሻየዓ'* ከሚለው ስርወ ቃል ሲሆን *ተከታይ/ወገን* ማለት ነው፡፡

ጥ. ለምንድን ነው ሺዓዎች በዚህ ስያሜ የሚታወቁት?

መ. ዓሊን (ዐ) እና የመልእክተኛውን (ሰ) አህለልቤይት ስለሚከተሉ ነው፡፡

ጥ. "ሺዓ"ብሎ የሰየማቸው ማነው?

መ. በሱናም ሆነ በሺዓ መጽሐፍት ላይ ተጠቅሶ እንደምናገኘው በዚህ ስም የሰየሟቸው ታላቁ መልእክተኛ ሙሐመድ (ሰ) ናቸው፡፡ (ሺዓዎች ማናቸው በሚለው ርዕስ ማስረጃዎቹን ያገኛሉ፡፡)

ጥ. የሺዓዎች ብዛት ስንት ይሆናል?

መ. ከአምስት መቶ ሚሊዮን በላይ ነው፡፡

ጥ. በየትኛው የዓለማችን ክፍል ይገኛሉ?

መ. በመላው ኢስላማዊ ሀገራትና ኢስላማዊ ባልሆኑ ሀገራት ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡

አብዛኛዎቹ ግን በኢራቅ፣ በኢራን፣ በሊባኖስ፣ በሂንድ፣ በኢንዶኒዝያ፣ አፍጋኒስታን፣ በቱርክ እና በባህረሰላጤ ሀገሮች ደግሞ በኩዌት፣ መስቀጥ፣ ባህሬንና ሌሎች በርካታ ሀገራት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ጥ. በስማቸው የሆነ መንግስት አላቸው?

መ. እንደ ኢራን መንግስትና ሌሎች. . .

ጥ. በቀደምት ታሪክ ውስጥ መንግስታት ኖሮአቸው ያውቃል?

መ. በርካታ መንግስታት ነበሯቸው፡- ሰፈዊኖች፣ በውዮች፣ ሐማዳኖች፣ ኢድሪሲዮች፣ ቃጃሮች፣ ፋጢሚዮችና ሌሎችም፡፡[318]

---

[318]ሰፈዊዮች (ሰፋቪድስ)፡- ፋርሳዊ የሆኑ ከሺዓ ኢስላም ቤተሰብ የተገኙ ኢራንን (1501-1736 ዓ.ልደት) የገዙ፡፡ መስራቹ ሼክ ኢስማኢል ቀዳማዊ (1501-1524 ዓ.ልደት) ሲሆን ከታላላቅ ንጉሶች አንዱ ሻህ ዓባስ ቀዳማዊ (1588-1629 ዓ.ል) ነው፡፡ በዚህ ዘመን ነበር ኢራን በንግድና በተለያዩ ፈኖች (ስነ-ጥበባት) የተንሰራፋውና ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው፡፡
*(ሙአሰሰት አል-መዋሪድ-አል-መውሱዐ ቁ.7776)*

***ቡሄዉዮች፡-*** ፈርሳዊ የሆኑ የሺዓ ቤተሰቦች ሲሆኑ ከ (932-1055ዓ.ል) በምእራባዊ የኢራን ክፍል እና በኢራቅ ላይ የነገሱ ነበሩ፡፡ በአቡ ሹጃእ ቡዌህ እንደተመሰረተ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ትክክለኛ መስራቾች ሶስቱ ልጆች ነበሩ፡፡ እነሱም፡-

1. ዓሊ (ዒማድ አል-ደውላህ/የሀገሩ ምሰሶ በመባል ለቀብ የሚታወቅ)
2. ሐሰን (አል-ሩክን አል-ደውላህ/የሐገሩ ማእዘን በሚል ለቀብ የሚታወቅና
3. አህመድ (አል-ሙዕዝ አል-ደውላ/ ለሐገሩ ህዳሴና ሉዓላዊነት የቆመ በሚል ለቀብ የሚታወቅ *(ሙአሰሰት አል-መውረድ- መውሱዐ ቁ.3038)*

***ሐመዳንዮች፡-*** በአስረኛው ምዕተ ዓመት አከባቢ (905-1004) ዓ.ል) ስልጣን ለመቆናጠጥ የበቁ ከዓረብ ቤተሰብ የሆኑ ዓለዊዎች ሲሆኑ ሙሲል፣ ሐለብና አዋሳኝ ሐገራትን ያስተዳድሩ የነበሩ ናቸው፡፡ መስራቻቸው አቡል ሒጃእ ቢን ሐመዳን ቢን ሐመዱን ሲሆን በብዛት የሚታወቁት ሰይፍ አል-ደውላ-አሚር ሐለብ በሚል ስያሜ ነበር፡፡ *(ሙአሰሰት አል-መውርድ-መውሱዐ ቁ.4823)*

***ቃጃሮች፡-*** ከማሊካህ ቤተሰብ የሆኑ ከ(1794-1925 ዓ.ል) ኢራንን የገዙ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው ንጉሳቸው አጋ ሙሐመድ ኻን ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ አህመድ ሻህ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ነበር ኢራን ወደ አውሮፓ የፖለቲካ አውድማ የገባችውና ባኩንና ጆርጂያንን

ጥ. ሺዓዎች ዑለማዎች (ምሁራን) አሏቸው?

መ. አዎ! በቀደምት ዘመናትም ሆነ ዛሬ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዙ ዑለማዎች አላቸው፡፡ *(ጠበቃት አዕላም አል-ሺዓ የሼክ ጠበራኒ እና የሺዓን ሪጃልና ታዋቂ ሰዎቻቸው ላይ የተጻፈ በርካታ መጽሐፍት ማየት ይቻላል፡፡)*

ጥ. ሺዓዎች ለህትመት የበቃ መጽሀፍት አሏቸውንአል-ነጀፍ አል -አሽረፍ

መ. አዎ! እንደ ምድር አሸዋ፣ ጠጠርና አፈር የበዛ፡፡ (አል-ዘሪዓህ ኢላ ተሷኒፍ አል-ሺዓ- የሼክ አጋ ቡዙርግ አል-ጠህራኒ እና ሌሎች... )

ጥ. ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር በወንድማማችነት፣ በፍቅርና መተሳሰብ መንፈስ መኖር የሚችሉ ናቸው?

መ. በሚገባ! ለዚህ በርካታ ምስክሮችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ በባግዳድ፣ በካይሮ፣ በደማስቆ፣ በቤይሩትና በሌሎች በርካታ ሀገራት በርካታ ሺዓዎችና ሱኒዎች በወንድማማችነት አብረው እየኖሩ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡

ጥ. ሺዓዎች ት/ቤቶችና የዕውቀት መገብያ ማዕከላት አላቸው?

መ. አዎ! ለቁጥር ያታከቱና የበረከቱ ት/ቤቶች በነጀፍ፣ በከርበላእ፣ በካዚሚያ፣ በሳመራእ፣ በቁም፣ በኹራሳን፣ በቴህራን፣ በአስፈሃን፣ በቤይሩት፣ በሺራዝ፣ በደማስቆና በሌሎች በርካታ ቦታዎች. . .

---

አብዛኛውን ኢራናዊ አርማንያን ያጣችው፡፡ ይህም የኖነው በሩሺያ የነበረው ቄሳራዊ ኃይል--------በአከባቢው ላይ ስልጣን ለመቆናጠጥ በሙብቃቱ ነበር፡፡(ሙአሰሰት አል-መውርድ መወድዕ ቁ.996)

***ፋጢሚዮች፡-*** ከኢስላማዊ ሺዓ ቤተሰብ የሆኑ ከ(909-1171 ዓ.ል) ሰሜን አፍሪካንና ግብጽን ያስተዳድሩ የነበሩ፡፡ በዑቤይድላህ አል-መህዲ የተመሰረተ ሲሆን በቱኒዚያ የምትገኘው አል-መህዲያ የፋጢሚዮች ዋና ከተማ የነበረችና በኋላ ላይ ወደ ካይሮ የተቀየረ ነበር፡፡ (መወሱዐት አል-መውርድ አል-መውዱዕ ቁ.8918

ጥ. ሺዓዎች ሙስሊሞችን ያከፍራሉ?

መ. በጭራሽ! ይህ የ ሙደሊሶች ውሸትና ቅጥፋት ነው፡፡

ጥ. ሰሃቦችን ያከፍራሉ፣ ይራገማሉ የሚባለውስ እውነት ነው?

መ. ይህም ውሸት፣ ቅጥፈትና ስም ማትፋት ነው፡፡ የመለያየት መሰሪ ዓላማ ያለው ሰው ካልሆን በስተቀር ማንም ይህን አያደርግም፡፡

ጥ. ጣዖት ላይ ነው ሱጁድ የሚያደርጉት የሚባለው ነገርስ?

መ. ይህኛውም ሌላ ስም ማጥፋትና ቅጥፈት ነው፡፡ መሬት (አፈር) ላይና መሬት ላይ የሚበቅል ነገር (የማይበላና የማይለበስ የሆነ) ላይ ሱጁድ ማድረግን ስለሚደግፉ ብቻ ነው እንደዛ የተባሉት፡፡

ጥ. የ ሺዓ ት/ቤቶችና የዕልም ማዕከላት ዬት ዬት ሀገር ነው የሚገኙት? የዑለማዎቻቸው መገናኛስ ዬት ነው?

መ. በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ታዋቂ ከሆኑት ውስጥ *አል-ነጀፍ አል-አሽረፍ፣ ከርበላእ፣ ቁም እና ኹራሳን* ይገኑበታል፡፡[319]

---

[319] ***አል-ነጀፍ አል-አሽረፍ፡-*** መሐል ኢራቅ ላይ በምእራብ ፉራት (ኢፍራጢስ) ወንዝ የሚገኝ የኢማም ዓሊ (ዐ) ዶሪህ የሚገኝበት ታሪካዊ ከተማ ሲሆን በኢራቅ የመጀመሪያው ቅዱስ ዶሪህ መሰረት የተጣለበት ክቡር ቦታ ነው፡፡

***የተቀደሰው ከርበላእ፡-*** መሐል ኢራቅ ላይ ከባግዳድ ከተማ ምእራባዊ ሰሜን ሰማንያ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ፤ የሸሂዶች ሁሉ አውራ- ሁሴን ቢን ዓሊ (ዐ) በአስረኛው ሙሐረም 61 ዓ.ሂጅራ (በኦክቶበር አስር 680 ዓ.ል) የተሰውበትና አሁን ዶሪሃቸው ያረፈበት ታሪካዊ ከተማ፡፡

***የተቀደሰችው ቁም፡-*** በሰሜናዊ ምዕራብ ክፍል መሐል ኢራን ላይ የምትገኝ በውስጧና አከባቢዋ የአራት መቶ አውሊያዎች ዶሪሆች የሚገኙባት ከተማ ስትሆን ከዶሪሆቹ አውራ የሆነው የሰይዳ ፋጡማ መዕሱማ ቢንት ኢማም ሙሳ ቢን ጀዕፈር (ዐ) ያረፈበት ቅድስት ከተማ ነች፡፡

***ኹራሳን፡-*** በትንሽዋ ኣሲያ ውስጥ የሚገኝ በርካታ ክፍለ ሀገራትን ያካተተና በዘመኑ ካርታ መሰረት ሶስት ሀገራት ላይ የተከፋፈለችና ከማዕከሎቹ ውስጥ የጡስ ከተማና---------

ጥ. መረጃዎችን ለማግኘት ከሺዓዎች ጋር እንዴት ነው መገናኘት የሚቻለው?

መ. ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሀገራትንና ሌሎች በርካታ ሀገራትን በመጎብኘትና በማጥናት፡፡[320]

---

----የኢማም አል-ሪዷ (ዐ) መርቀድ ያለበት የመሽሐድ ከተማ የሚያካትት ሲሆን ለተወሰነ ክፍል በተሰጠ አጠቃላይ ስያሜ ዘይቤ ´ኹራሳን´ በመባልም ይታወቃል፡፡

***የተቀደሰችው የመሽሐድ ከተማ ፡-*** ይህች ከተማ የኢማም አል-ሪዷን (ዐ) ዶሪህ የያዘች ስትሆን (148-203 ዓ.ሂጅራ) ከቀደምት ዘመን ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ የኢስላማዊ አስተምህሮ፣ ባህልና ስልጣኔ ማዕከል ለመሆን የበቃች፣ በርካታ ዑለማዎችና መርጅኦች የሚገኙባት፣ ብዙ ት/ቤቶች፣ የትምህርት ማዕከላት፣ ቤተ መጽሀፍትና የዲን ሀውዛዎች በብዛት የሚገኙበትና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሺዓዎችና ሱኒዎች ከተለያዩ ዓለማት የኢማም አል-ሪዷን (ዐ) ዶሪህና የበርካታ ዑለማዎች የዲን መራጅኦችን መካነ-መቃብራት ለመጎብኘት የሚጎረፍባት ታላቅ ከተማ ነች፡፡

እነዚህ አራት ከተሞች በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ጀምሮ በርካታና ከፍተኛውን የዲን ማዕከላት (ሐውዛዎች) የያዙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከፊሉ ከአንድ ሺህ ዓመት እድሜ በላይ ያስቆጠሩ ናቸው፡፡

[320]ቀጥሎ የተጠቀሱት አድራሻዎች የቆዩ በመሆናቸው ተቀይረው ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዳለ ሆኖ በአሁኑ ዘመን ደግሞ በሺዎች እንዲያውም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ማዕከላትን መገናኘትና መተዋወቅ እንደሚቻል በማስገንዘብ -ከብዙ በጥቂቱ ለማጣቃስ ያህል፡-
-መክተበት ኢማም አል-ሪዷ (ዐ)- መሽሐድ -ኢራን
-መክተበት አል-መርዐሽ አል-ነጀፊ -ቁም -ኢራን
-ሐውዛ ዕልሚያ- መሽሐድ -ኢራን
-ሐውዛ ዕልሚያ -ቁም -ኢራን
-ሐውዛ ዕልሚያ -አስፈሃን -ኢራን
-ሐውዛ ዕልሚያ -ነጀፍ አል-አሽረፍ -ኢራቅ
-ሐውዛ ዕልሚያ -ከርበላእ -ኢራቅ
-መክተብ አል-ዑለማእ ወ መራጅዕ አል-ተቅሊድ -ቁም -ኢራን
-መክተብ አል-ዑለማዕ ወ መራጂዕ አል-ተቅሊድ መሽሐድ - ኢራን
-መክተብ አል-ዑለማዕ ወ መራጂዕ አል-ተቅሊድ ሊባኖስ/ሉብናን-------
----- -መክተብ አል-ዑለማዕ ወ መራጂዕ አል-ተቅሊድ ሱሪያ /ሰይዳ ዘይነባ (ዐ)
-ሐውዛ ዕልሚያ አል-ዘይነቢያህ -ደማስቆ /ዲመሽቅ
-መክተብ አል-ዑለማእ ወ መራጂዕ አል-ተቅሊድ -ለንደን

-መክተብ አል-ዑለማዕ ወ መራጂዕ አል-ተቅሊድ -ኩዌት
-በመላው ዓለማት የሚገኙ መስጂዶች፣ ሁሴኒያዎችና የሺዓ ማዕከላት . .

እነዚህ አድራሻዎች በኢንተርኔትና በተመሳሳይ መንገዶች ማግኘት የሚቻል ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የሺዓ ዑለማዎችንም ማግኘት የሚቻል መሆኑን እየገለጽን፤ ኢማም አል-ሺራዚ ከጠቀሷቸው ማዕከላት ለመጥቀስ ያህል ፡-

ኢራቅ፡-
-አል-ነጀፍ አል-አሽረፍ -መክተበት ኢማም አል-ሐኪም
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት ኢማም አል-ሻሐሩዲ
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት -ኢማም አል-ኹኢ
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት ኢማም አል-ሺራዚ
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት ኩሊየት አል-ፊቂህ
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት ኢማም አሚረል ሙእሚኒን (ዐ)
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት ጀሚዐት አል-ነጀፍ
-አል-ነጀፍ አል -አሽረፍ -መክተበት መድረሰህ ኢማም ቡሩጀርዲ
-ከርበላ አል-ሙቀደሳ  - ራቢጠት አል-ነስር አል-ኢስላሚ
-ከርበላ አል-ሙቀደሳ  -መክተብ መናቢዕ አል-ሰቃፊት ኢስላሚያ
-ከርበላ አል-ሙቀደሳ  -ለጀነት አል-ሰቃፋት አል-ዲኒያ
-ከርበላ አል-ሙቀደሳ  -መድረሰት አል-ሑፋዝ አል-ቁርአን አል-ሐኪም
-ከርበላ አል-ሙቀደሳ -ሙአሰሰት አል-አዕለሚ ሊል-መጥበዓት አል-ኢስላሚያ
-ባግዳድ-መክተበት አል ኹላኒ አል-ዓማህ
-አል-ካዚሚያ -መክተበት አል-ጀዋዱይን
-ሰመራእ -መድረሰት ኢማም አል-ሺራዚ

ኢራን:-
-ቁም - መክተብ ኢስላም
-ቁም - መክተብ ኢማም አል-ሽሪዓትመዳሪ
-ቁም - መክተብ ኢማም ጉልባየጋኒ
-ቁም - መክተበት ኢማም አል-ነጀፊ
-ኹራሳን -መክተብ ኢማም አል-ሚላኒ
-ኹራሳን-መክተብ ኢማም አል-ቁሚ
-ቴህራን -መክተበት ኢማም አል -ኹንሳሪ-----

----ሉብናን
-ቤይሩት -መክተበት አል-ሑጃ ሼኽ መሐመድ ጀዋድ ሙግኒዬ

ጥ. ሺዓዎች ጃፈሪያ ተብለው የሚጠሩት ለምንድን ነው ?

መ. ከ አህለልቤይት ኢማሞች ስድስተኛው የሆኑት ኢማም ጃዕፈር መሐመድ አል-ሷዲቅ (ዐ) የቁርአንን እና የመልዕክተኛውን ትምህርትና አስተምህሮ በሰፊው ስላስፋፉና ሺዓዎች ዘንድ ያሉ አብዛኛው ሐዲሶች፣ በተለያዩ የፊቂህ፣ የተፍሲርና ሌሎች ሳይንሶች ከዚሁ ኢማም (ዐ) የተገኙና የተሰራጩ ስለሆነ ነው፡፡

(እንዲሁም የሌሎች ኢስላማዊ መዝሃቦች መሪዎች በኢማም ጃዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ) ላይ የቀሩና የተማሩ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አቡ-ሐኒፋ ኢማም ሷዲቅ (ዐ) ዘንድ መማራቸውን አስመልክተው ከተናገሩት፡-

***"እነዚያ ሁለቱ ዓመታት ባይኖሩ ኖሮ ኑዕማን ጠፍቶ ነበር"*** ማለታቸው ይነገራል፡፡ እንዲሁም ማሊክ ቢን አነስ ከተናገሩት፡-

***"በፈድል፣ በዒልም (ዕውቀት)፣ በዒባዳ፣ በተቅዋ (ወረዕ) በስኑ-ምግባርና ሁሉም ቱርፋቶች ከ ጀዕፈር ቢን መሐመድ የተሻለ ዓይን አላየም፣ ጆሮ አልሰማም፣ በሰው ልጅ ምናብ (አዕምሮ) ላይ አልተከሰተም፡፡ የኢጅግ በርካታ***

---

-ሱር- መክተብ አል-ሁጃ ሰይድ ሙሳ አል-ሰድር
-በዕለበክ -መክተበት አል-ሑጃ ሼክ ኢብራሂም

እንዲሁም፡-
-ደማስቆ -ሶሪያ -መድረሰት አል-ሙህሲኒያ
-ሉክኖው -ህንድ -መድረሰት አል-ዋኢዚን
-ካራቺ -ፓኪስታን-መክተበት አል-ሑጃ ሼክ መሐመድ ሸሪዐት
-ካይሮ -ግብጽ -ዳረል ተቅሪብ በይነል መዛሂብ ኢስላሚያ እና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ማዕከላት . . .

***ሐዲስ ባለቤት፣ የድንቅ መጅሊስ አውራ፣ በቁጥር የማይዘለቅ ፋኢዳ (ጥቅም) ምንጭ ነበሩ፡፡"***

*(አል-መጅሊስ አል-ሰኒያ- 5/462 እና 463 የኢማም አል-ሷዲቅ የህይወት ታሪክ ገጽ 93 የተወሰደ፡፡)*

ጥ. የሺዓዎች ዐቂዳ (ኢዕቲቃዳት) ምንድን ናቸው?

መ. ሺዓዎች በሦስት መሰረቶች (ኡሱል አል-ሰላሳ ) ያምናሉ፡፡

ጥ. ሶስስቱ መሰረቶች ምን ምን ናቸው?

መ. 1.መብደእ (ተውሂድ/ስነ-ፍጥረትና ተዛማች ጉዳዮች

2. መልእክት (ሪሳላና ተዛማች ጉዳዮቹ)

3. ትንሳዔ (መዓድ) እና ተያያዥ ሁኔታዎቹ ናቸው፡፡

ጥ. በመብደእ ዙሪያ ያሉ እምነታቸው (ኢዕቲቃዳቸው) ዝርዝር ምንድን ነው?

መ. ለፍጥረታት ሁሉ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ለጋስ (ረዛቅ)፣ ህያው አድራጊ (ሕይወት ሰጭ)፣ ህይወት ነሺ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ ህያው የሆነ፣ የተብቃቃ፣ ሁሉን ደራሽና አዳራሽ የሆነ፣ ጥንታዊ፣ ዘለዓለማዊ፣ ተናጋሪ፣ እውነተኛ፣ ያልተዋቀረ፣ በአካልና ገላ የማይገለጽ፣ የማይታይ፣ በቦታ የማይገደብ፣ በክሰትና ግኝት የማይታሰብ፣ አቻና ሽሪክ የሌለው፡፡ በተግባራቱ፣ በትዕዛዛቱ እና በፍጥረቱ ፍትህ የሆነ አምላክ መኖሩን ያምናሉ፡፡

***وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّامٍ لِلْعَبِيدِ***

**"ጌታህ ባሮችን የሚበድል አይደለም፡፡"[321]**

[321] ፉሲለት፡ 46

ጥ. ሪሳላን በተመለከተ ሺዓዎች ያላቸው እምነት ዝርዝሩ ምንድን ነው?

መ. ሪሳላን በተመለከተ የሺዓዎች እምነት የሰው ልጆችን ከጥመት ለመታደግና ወደ ቀናው መንገድ ለማቃናት፣ ከመኃይምነት ጨለማ ለማላቀቅና ወደ ሐቅና ቀጥተኛው ጎዳና ለመምራት አላህ (ሱ.ወ) ነብያትን ለመላው የሰው ዘር መላኩን ያምናሉ፡፡ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ ነው፤ የመጀመሪያው የሰው ልጆች አባት የሆኑት ኣደም (0) ሲሆኑ የመጨረሻው ደግሞ የኢስላም ነብይ የሆኑት ሙሐመድ ቢን ዓብደላህ (ሶ) ናቸው፡፡ ሙሳ፣ ኢሳ፣ ኑህ፣ ኢብራሂምና ሌሎች በቁርአን አል-ከሪም ውስጥ ወይም በቅዱስ ሱና ውስጥ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ሁሉም ከአላህ (ሱ.ወ) የተላኩ ናቸው፡፡ እነሱም ሙዐሱሞች (እንከን የለሾች ናቸው፡፡ የጌታቸውን መልእክት (ሪሳላ) ያለ ማጓደል ሙሉ በሙሉ ያደረሱና የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚገባ የተወጡ ናቸው፡፡

ጥ. ኢማማን በተመለከተ ሺዓዎች ያላቸው ኢዕቲቃድ (እምነት) እንዴት ነው?

መ. ነብዩ (ሶ) በአላህ ትዕዛዝ መሰረት ከሳቸው በኋላ የሚተኳቸው አስራ ሁለት ኸሊፋዎች መሰየማቸውን ያምናሉ፡፡ በስማቸው ጠርተው ዝርዝሩን ማሳወቃቸውን ያምናሉ፡፡ እንደ ነብዩ (ሶ) ከማንኛውም ስህተትና ጎደሎ የጠሩና የተጠበቁ እንከንየለሾች (ሙዐሱሚን) መሆናቸውን ያምናሉ፡፡ ይኸውም ነብዩን (ሶ) አስመልክቶ አላህ(ሶ) እንደተናገረው፡-

***وَمَا يَنْطِقُ عَنِ الْهَوَىٰ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَى***

**"ከስሜት ያመነጨ አንዳችም ነገር አይልም፤ ከሚታወጅ ወህይ (መለኮታዊ ራዕይ) እንጅ ሌላ አይደለም ፡፡"[322]**

---

[322] አል-ነጀም፡ 3 እና 4

ጥ. የነብዩ (ሰ) ተተኪ ኢማሞች እነማን ናቸው?

መ. 1. ዓሊ አሚረልሙእሚኒን (ዐ)

2. ሐሰን (ዐ)

3. ሁሴን (ዐ)

4. ዓሊ ቢን ሁሴን (ዐ)

5. መሐመድ አል-ባቂር (ዐ)

6. ጃዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ)

7. ሙሳ አል-ካዚም (ዐ)

8. አሊ አል-ሪዷ (ዐ)

9. ሙሐመድ አል-ጀዋድ (ዐ)

10. ዓሊ አል-ሓዲ (ዐ)

11. ሐሰን አል-አስከሪ (ዐ)

12. ሙሐመድ አል-መህዲ (ዐ) ፡፡

እነዚህ ስሞችና የመልእክተኛው (ሶ) ኸሊፋዎች ስለመሆናቸው በአህለሱና ኪታቦችም ሆነ በሺዓ መሷድሮች የተገለጸ እውነታ ነው፡፡

*(ለምሳሌ ያህል፦በሓር አል-አንዋር 36/283 ክፍል 41- ሐዲስ 106፤ ሲራጥ አል-ሙስተቂም 2/144. . .* ከነዚህም የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ከተናገሩት፡-

"የኔ ወስይ (እንደራሴ ዓሊ ቢን ዓቢ ጧሊብ ነው፡፡ ከሱ በኋላ ደግሞ ሲብጦቼ ሀሰንና ሁሴን ሲሆኑ ከሁሴን አብራክ የሚገኙ ዘጠኝ ንጹሀን ኢማሞች ተከታትለው ይከተላሉ፡፡ ከሁሴን በኋላ ልጁ ዓሊ ይከተላል፣እሱ ሲሄድ ልጁ

ሙሐመድ ይከተላል፣ እሱ ሲሄድ ልጁ ጃዕፈር ይከተላል፣ እሱ ሲሄድ ልጁ ሙሳ፣ እሱ ሲሄድ ልጁ ዓሊ፣ እሱ ሲሄድ ልጁ ሙሐመድ፣ እሱ ሲያልፍ ልጁ ዓሊ፣ እሱ ሲሄድ ልጁ ሐሰን፣ እሱ ሲሄድ አል-ሑጀት ቢን ሐሰን ይተካል፡፡")

ከአህለሱና ኪታብ ደግሞ፡-(ከመጽሐፉ ገጽ 22 እዚህ ይገባል)

ጥ. የነዚህ ኢማሞች መቃነ መቃብር ዬት ነው ያለው?

መ. ኢማም ዓሊ (ዐ) -ነጀፍ-ኢራቅ

-ኢማም ሐሰን፣ ኢማም ዓሊ ቢን ሁሴን፣ ኢማም ሙሐመድ አል-ባቂር እና -ኢማም ጃዕፈር አል-ሷዲቅ (ዐ)- መዲና አል ሙነወራ -ሂጃዝ

-ኢማም ሁሴን- ከርበላ-ኢራቅ

-ኢማም ሙሳ አል-ካዚም እና ኢማም ሙሐመድ አል-ጀዋድ (ዐ) አል-ከዚሚያ- ኢራቅ

-ኢማም አሊ አል-ሪዷ -ኹራሳን- ኢራን

-ኢማም ዓሊ አል-ሐዲ እና ኢማም ሐሰን አል-ዓስከሪ (ዐ) ሳመራእ-ኢራቅ

ጥ. እነዚህ ኢማሞች የሚጎበኝ (የሚዘየር) መርቀድ ወይም ዶሪህ አላቸው?

መ. አዎ! ሙስሊሞች ለነዚህ ኢማሞች ታላላቅ ቁባዎችን ገንብተዋል፡፡ በቀብሮቻቸው ዙሪያ ታላላቅ ህንጻዎችን ሰርተዋል፡፡ በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች እነዚህን ቦታዎች ይጎበኛሉ (ይዘይራሉ)፡፡

ጥ. ኢማም መህዲን (ዐ) አስመልክቶ ያላቸው እምነት (ዐቂዳ) ምንድን ነው?

መ. ኢማም መህዲ (ዐ) የመገለጫው ዘመን እስኪደርስ ድረስ ህያው ሆኖ እንደሚቆይ የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ነግረውናል፡፡ ከረዥም ጊዜ የመሰወር ዘመን በኋላ የማታ ማታ እንደሚገለጥና ይህች ዓለም በጭቆናና በደል እንደተሞላች ሁሉ ሁሉም አልፎ ምድሪቱን በፍትህና ነጻነት እንደሚሞላት ረሱል (ሶ) አብክረው ተናግረዋል፡፡ ይህ ጉዳይ በሱኒም ሆነ በሺዓ መጽሐፍት በግልጽ ተጠቅሶ እናያለን፡፡ *(ቀደም ሲል ኢማም መህዲን በተመለከተ የተሰጠውን ምንጭ መመልከት ይችላሉ፡፡)*

ጥ. እነዚህን ኢማሞች በተመለከተ ሺዓዎች ድንበር ያልፋሉ (ጉሉው ውስጥ ናቸው) የሚባለው እውነት ነው? መሆን ካለባቸው በላይ አድርገው ያስቧቸዋል የሚባለው ትክክል ነው?

መ. በጭራሽ! በሺዓዎች እምነት መሠረት እነዚህ ኢማሞች የአላህ ባሮችና የመልእክተኛው (ሶ) ኸሊፋዎች ናቸው ፡፡

ጥ. የአላህ መልእክተኛ (ሶ) ሴት ልጅ የሆነችዋን ፋጢማ አል-ዘህራን በተመለከተ የሺዓዎች እምነት (ዐቂዳ) ምንድን ነው?

መ. በዚህ ላይ ያላቸው እምነት ፋጢማ ዘህራ ከማናቸውም እንከን የጠራች (ጧሂራ) እና እውነተኛና ሐቀኛ (ሲዲቃ) እንደሆነችና እሷን፣ አባቷን፣ ባለቤቷንና ሁለቱ ልጆቹዋን አስመልክቶ የፍጹምነት ንጽህና አንቀጽ (አያት አል-ተጥሂር) መውረዱን ነው፡፡